የኑሮ መድኀን

በ ዲያቆን አሸናፊ መኰንን

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::

የመጀመሪያ እትም መጋቢት 2000 ዓ.ም.
ሁለተኛ እትም የካቲት 2001 ዓ.ም
ሦስተኛ እትም ሃሐሴ 2001 ዓ.ም

አድራሻ:- መ.ሳ.ቁ. 1591 ኮድ 1110 አ.አ.

መጽሐፉን ለማከፋፈል ለምትፈልጉ:-

0911-393521

እመኒ ትሁቦ ሀብተ መከራ ወሀብተ ፍስሐ ትሁቦ፤
እምርእስየ ለርእስየ አንተ ትቀርቦ፤

ትርጓሜ:-

ደስታንም ብትሰጠው ሀዘንንም ብትሰጠው፤
ከእኔ ይልቅ ለእኔ አንተ ነህ የምትቀርበው::

ስጦታ

ለ _____

ከ _____

በአክብሮት አበረክታለሁ::

ምስጋና

ብቻህን የረዳኸኝ፣ የቀትር ጥላ፣ የምሽት መጠጊያ፣ የበረሃ ጓደኛ፣ የጥማቴ እርካታ፣ የሞት መድኃኒት የሆንክኝን፣ ለመንፈስ ቁስለኞች ፈውስ እንዲሆን ይህን መጽሐፍ የሰጠኸኝን ጌታ አመሰግንሃለሁ::

ያሳደገችኝን ቤተ ክርስቲያኔን፣ ለወንጌልህ ክብር አንተን ከሚወዱ አገልጋዮችህ ጋር ብዙ ዋጋ የከፈሉትን ወ/ሮ ሙሉዓለም ታምሬን፣ ለእኔ ያቆምካቸውን የአለቃ ያሬድ ፈንታ ቤተሰቦችን፣ በወንጌል ጉዞዬ እንዳገለግላቸው የሰጠኸኝን ወንዶችና ሴቶች ልጆችህን፣ ወንድምም ወዳጅም አድርገህ የሰጠኸኝን ኃይሉ ኪዳኔን፣ እንደ ደወል ለመጻፍ የሚያተጋኝንና በፍቅር ስስት አገልግሎቴን ያከበረልኝን ወዳጄን ብሥራት ያሬድንና ባለቤቱን ሃና ዘኪሮስን፣ በቀጣዩ ዘመን የምኖረው በቃል ሳይሆን በመጽሐፍ መሆኑን ሳይታክቱ የሚነግሩኝንና አባታዊ ፍቅራቸውን የለገሱኝን ሻለቃ ካሣዬ አራጋውን፣ በእርግዝና ድካሟ ሳትታክት ይህን መጽሐፍ ደጋግማ የጻፈችውን ገነት ታደሠን እባክህ ባርክልኝ:: በረከት የአንተ ነውና!

መታሰቢያነቱ

የለው ሀዘን ለሚያሳዝናቸው፣ ለራሳቸው የመደቡትን
የፀጥታ ጊዜ ለታወኩት ወገኖቻቸው ለሚያውሉ
እውነተኛ ክርስቲያኖች ይሁን!

ና

በቃልህ ስትጠራኝ ጆሮዬ እንዲነቃ
ስምህ ጣዕም ሆኖኝ ውስጤ እንዲነቃቃ
አንተን አስቀድሜ ሁሉ እንዲከተለኝ
ጸጋህ ሞገስ ሆኖ በክብር እንዲያቆመኝ
መከራን ታግሼ ማለፍ እንዲቻለኝ
ጥበቃህ በዝቶልኝ በቤትህ እንዲያኖረኝ
በልቅሶ እልልታዬ ቁስልህ እንዲታየኝ
የኑሮ መድኅኔ ጌታዬ ኢየሱስ
ፍቅርህ አይለየኝ መጠሪያዬ እስኪደርስ

ማውጫ

ገጽ

መቅድም 8

መግቢያ 11

ምዕራፍ አንድ
ኑሮና ሕይወት 15

ምዕራፍ ሁለት
የፀሐይ ዕድሜ 21

ምዕራፍ ሦስት
ቁጥር አንድ 27

ምዕራፍ አራት
የሚበልጠውን ይዘናል 32

ምዕራፍ አምስት
አርካታ ማጣት 39

ምዕራፍ ስድስት
የበረሃ መና 46

ምዕራፍ ሰባት
መኖሪያህ ማን ነው? 54

ምዕራፍ ስምንት
ፈቃዱ ይሁን 60

ምዕራፍ ዘጠኝ
የነበር ዓለም 70

ምዕራፍ ዐሥር
አትጨነቁ 78

ምዕራፍ ዐሥራ አንድ
የወዳጅ ዋስትና 90

ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት
ከጠላት ዋስትና 101

ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት
የመሪ ዋስትና 110

ምዕራፍ ዐሥራ አራት
የእንጀራ ዋስትና 121

ማጠቃለያ 129

መቅድም

የምትበላው መኖር ስላለብህ፣ የምትሰብሰው አበደ እንዳይሉህ፣ የምታፈቅረው ስለሚያሳዝኑህ፣ የምትረዳው ሕሊና ፀጥ እንዲልልህ ሊሆን ይችላል። እንደ ማሽላ እያረሩ መሳቅ ውስጥህን ጎድቶት ይሆናል። ምስጥ እንደ በላው እንጨት ላይህ ገዝፍ ትንሽ ሲነኩህ የምትወድቅ ሆነህ ይሆናል። ስለገባው ገቢ እንጂ ስለወጣው የማያወቁ ምቀኛ ጎረቤቶች ያበሳጩህ፣ ሁሉም ነገር አልጥም ብሎህ በግድ የምትኖር ሰው ሆነህ ይሆናል። እንዲህ የምሆነው የመረጥኩትና የስለጠንኩበት ትምህርቴ አሊያም በቀደመ አስተሳሰቤ ያገባኋት ሚስቴ ትክክለኛ ምርጫዬ ስላልሆኑ ነው እያልክ ትታመስ ይሆናል። ዛሬ ስታገኝ የድህነት ሚስትህና ጓደኞችህ ያን ክፉ ቀን መስለውህ ይሆናል። በምትኩ ደግሞ በሽንገላ ፍቅር አብደህ ይሆናል። ሊገባ ስፉ ሲወጣ ጠባብ በሆነው፣ ማላመጥ እንጂ መዋጥ በሌለበት ፖለቲካ ውስጥ ገብተህ በሩ ጠፍቶህ እየተቅለጨለጭክ ይሆናል።

አርፍበታለሁ ብለህ የገነባኸው ቤትህ ነገር የተጣደበት ምድጃ ሆኖብህ አሊያም የምትወደው ልጅህ በሕመም የሚንገላታበት ሆኖ ወደ ቤትህ የሚወስደውን ጎዳና ስትጀምር እግርህ እያጠረብህ ተቸግረህ ይሆናል። የሞቀው ትዳርህን ስታስብ ከመሐል አንዳችን ብንቀነስ ልጆቹ ምን ይሆናሉ? የሚል ፍርሃት እየወዘወዘህ ሊሆን ይችላል። ብር ካለ በለማይ መንገድ አለ በሚል ፈሊጥ ተይዘህ ገንዘብ የሁሉም ነገር መልስ መስሎህ ፍቅርን እየገፋህ ገንዘብ ታከማች ይሆናል። የአገሬ ለው የሚያከብረው ሲወፍሩ ነው ብለህ ጭንቀትህን በምግብ እየተወጣኸው ይሆናል። ገንዘብ ሲመጣ ስላሜ በየትኛው በር እንደ ወጣ አላውቅም እያልክ ይሆናል።

ብዙ ሕዝብ እየወደደህ ይህ ሁሉ ተከታይ ቢከዳኝስ እያልክ ተጨንቀህ ይሆን? ወይስ አመስግና በምትራገመው ዓለም ተራው ደርሶህ ያመሰገነህ ሁሉ ስድቦ እስኪጨርስ ወረፋው ረዝሞብህ ይሆን? ክክብርህና ከሥልጣንህ የተነሣ እንኳን ጠላቶችህን ወዳጆችህን ማመን ተስኖህ ጥላህን እየፈራህ የምትኖር ሆነሃል?

በማያስተማምን ፖለቲካ ቤት ሠርቶ ክባድ ማሽን ተክሎ መኖር እያስጨነቀህ ያላረፈ ልብ ይዘህ ሊሆን ይችላል። ወይም መብራት ጠፍቶ፣ ጉንዳን ገብቶ፣ እርሱ ታሞ፣ ሚስቱ ምጥ እንደ መጣባት ለው ሆነሃል? ለነገ የሚሆን በጎተራህ ስለ ሌለ ዕረፍት አጥተህ ይሆን? ብቻህን ስምታወራው፣ ጭር ባሉ መንገዶች ለምታለቅስ፣ በለው ልቅሶ ለራስህ ኑሮ ስምታላዝን፣ በወዳጅና

በትዳር መካከል ብቸኝነት ስለጀህ፣ ቋንቋህ ስሚ ላጣው፣ ከዚህ ሁሉ በላይ በነገ ፍርሃት ለተያዝከው ወገን የኑሮ መድኅንህ ማን ነው?

በለለጠነው ምድር ኢንሹራንስ ያልተገባለት ማንኛውም ተንቀሳቃሽ ንብረት መንቀሳቀስ አይችልም። የጤናና የሕይወት ዋስትና ያልገቡ ስምችን መቅጠርም ባለ ሀብቶች ይፈራሉ። በከፍተኛ በጀት የሚንቀሳቀሱ የዋስትና ተቋማትም መኪና ስወደመበት ያንኑ የሚያህል መኪና፣ ቤት ለተቃጠለበት ተካካይ ቤት ይሰጣሉ። ምንም እንኳ የሕይወት ኢንሹራንስ ቢያስገቡም ሕይወት ላጣ ሕይወትን ሰጥተው አያውቁም። በለማ ክተማ ፍርሃት ለሚንጠው፣ የውስጥ ጥያቄ ስወጠረው፣ ጣራ ሊቆጥር ለሚያድረው እንቅልፍ ብርቁ፣ ትዳሩ እክሲዮን ለሆነበት፣ ሀብቱ እርካታ ለነሣው፣ በጦርነት ቀጠና ለሚኖረው፣ የፍቅር ረሀብ ላጠወለገው፣ ወዳጅ ሁሉ የተልባ ስፍር ለሆነበት፣ ነገ ጨለማ ሆኖ ለሚታየው ዋስትና የሚሰጥ የኢንሹራንስ ተቋም የለም። እንዲህ ያለውን ዋስትና ሰጪ ቢያገኙ የኢንሹራንስ ተቋማት ራሳቸውም ይፈልጉት ነበር። ታዲያ የኑሮ መድኅን ማን ነው?

ይህን ሁሉ ሕመማችሁን የነካካሁት እየቆነጠጡ ማስለቀስ እንደሚወዱ ሰዎች ሆኜ አይደለም። ስለ ኑሮ ሳነሣም ጆሮን ለመማረክ ብዬም አይደለም። ለእናንተ እንደምናገር ባሰብ ኖሮ ብዕሬን አስቀምጥ ነበር። ከድካሜና ከሩጫዬ በኋላ እፎይ የምልበት ቃል ለራሴ እያዘጋጀሁ እንደ ሆነ ግን አውቃለሁ። ይህን የምጽፈው ቃለ መጠይቅ አድርጌ ሳይሆን ራሴን አይቼ ነው።

እኔም ለእኔ ያለሁት እኔ ብቻ እየመሰለኝ የባዘንኩበትን ዘመን አውቃለሁ። ለዎች በሕይወቴ ወሳኝ የሆኑ እየመሰለኝ ሲወዱኝ የምኖር፣ ሲጠሉኝ የምጠፋ ይመስለኝ ነበር። የትልልቅ ስዎችን ስልክ መያዝ እንደ ቡዳና መጋኛ መድኃኒት የኪሴ መሣሪያ ይመስለኝ ነበር። የእግዚአብሔርን ሳይሆን የሰውን ፊት እያየሁ ያገለገልኩበት ዘመን ብዙ ነው። ጊዜዬን እንጂ ሕይወቴንና ክብሬን አስቀምጬ ማገልገል ባለ መቻሌ ሩጫዬ ሁሉ የብቻ ሩጫ እንደ ነበር ተገንዝቤአለሁ። ስህተትን በስህተት ለማጥራት በመሞከር አእምሮዬን ለብዙ ዘመን እንዳቆሰልኩ እግዚአብሔር በሰጠኝ የፀጥታ ጊዜዎች አውቄአለሁ።

ምድር ለተሸከመችኝ እነርሱ ክብዷቸው ብዙ ያሉኝ ወገኖች አሉ። ለመወደድም ለመጠላትም ጊዜ አለውና ሁሉቱንም አይቼ ሕይወት እንዲህ ነው? ያልኩበት ጊዜ ብዙ ነው። መርዝ የተቀላቀለበት ሰላምታ ብዙ ጊዜ ተቀብዬአለሁ። እየወጉ «ይማርህ»

የሚሉ የከበቡኝ ጊዜ ጥቂት አይደለም። ስለ ከዱኝ ባልንጀሮቼ ሰምች ሲጠይቁኝ ውስጤ እያረረ ደህና ናቸው ስል መልሰው «አቤት የእናንተ ፍቅር» ሊሉኝ ደግሞ ራሴን ጠይቄአለሁ። በዚህ ሁሉ ወጀብ ውስጥ ግን የተረዳኹት እግዚአብሔር ቁም ሳይል ሕይወትን የሚያቆማት እንደ ሌለ ነው። በርግጥም የኑሮ መድኅን እግዚአብሔር ነው።

መግቢያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰቡ ቃሎች ብቻ ሳይሆኑ የሚሰብ ፍቅርም ነበረው። በረሃው ዓለም ላቃጠለው ቃሎቹ ጥም ቆራጭ ውኃ፣ ፍቅሩም ማረፊያ ጥላ ነበር። የተናገራቸው ቃሎች ፈደል ሳይሆኑ ሕይወት፣ ፍልስፍና ሳይሆኑ መንፈስ ነበሩ (ዮሐ.6÷63)። ከተናገራቸው ሕይወት አድን ቃሎች በማቴዎስ 11÷28 ያለው ቃል ልብን የሚገዛ ቃል ነው፦ *«እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፣ ወደ እኔ ኑ፣ እኔም አሳርፋችኋለሁ።»*

ሁላችንም ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት እንፈልጋለን። ነገር ግን ይህን ሱስ፣ ይህን ኃጢአት ስተው፣ ንጹሕ ስሆን ነው የምመጣው እንላለን። ነገር ግን ራሳችንን አጽድተን መምጣት ብንችል ኖሮ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት ባላስፈለገው ነበር። እርሱ የሞተው ሰው ራሱን ከኃጢአት ማዳን ስላልቻለ ነው። በምድር ላይ የሚገኙት ሃይማኖቶች ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት ያለበት ታጥቦና ታጥኖ፣ ፀድቶና ተሰውጦ ነው ይላሉ። ክርስትናው ግን የምንፀዳውና የምንለወጠው ወደ ክርስቶስ ስንመጣ እንደሆነ ይነግረናል። ሰው ራሱን ለማዳን አምላክነት ያስፈልገዋል።

ንስሐን በሚመለከት በሃይማኖቶች ሁሉ ያልተቋጨ ክርክር አለ። አንደኛው ወገን ሰው ወደ ክርስቶስ መምጣት ያለበት አስቀድሞ ንስሐ ገብቶ ነው ሲል ሌላው ወገን ደግሞ ንስሐ የሚገባው ወደ ክርስቶስ ሲመጣ ነው ይላል። ኃጢአተኛው ንስሐ ለመግባት ኃጢአቱን በንጹሕ መስታወት ማየት፣ ተጸጽቶ ለመወሰን እርሱን አፍቅሮ የሞተለትን ጌታ መመልከት ያስፈልገዋል። በክርስቶስ የቅድስና ብርሃን ፊት ካልቆመ ኃጢአቱ ሊታየው፣ በቀራንዮ ፍቅር ፊት ካልቆመ የበደሉ ክብደት ሊታየው በፍጹም አይችልም። ስለዚህ ኃጢአተኛው አስቀድሞ ወደ ክርስቶስ ይመጣል። ከዚያም ልቡ ለንስሐ ይዘጋጃል። ለኃጢአተኞች የበደልን ፍርድ ከመንገራችን በፊት የበደላቸው ስርየት የሆነውን ታላቁን ፍቅር ልንነግራቸው ይገባል። ለዚህ ነው *«እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፣ ወደ እኔ ኑ፣ እኔም አሳርፋችኋለሁ»* ያለው።

ብዙ ክርስቲያኖች የበደል ሸክም ተጭኗቸው ቀድሞ ወደ ክርስትና ሲመጡ የነበራቸው ደስታ ርቋቸዋል። ሌሎችም «እግዚአብሔርን እየበደልኩት እንዴት በቤቱ እኖራለሁ?» በማለት በአጉል ትሕትና ተይዘው ወደ ዓለም ኮብልለዋል። እንደ እነርሱ አሳብ ኃጢአትን ለማድረግ በሚቻልበት ቦታ ሆነው ኃጢአታቸውን

ሊፈጽሙት ነው። ኃጢአትን ሳይጨርሱት ንስሐ መግባት ግን ግድ ነው። የተቀሩትም በድፍረት ኃጢአት ተይዘው «ብከፋ ብከፋ ከእነ እገሌ አልከፋም» እያሉ በመሻል መስፈርት ተረጋግተው ተቀምጠዋል። የሚበዙትም «ያሃይማኖት አባቶች ይህን እያደረጉ በእኛማ ምን ይፈረዳል?» እያሉ ከንስሐ ርቀው ይኖራሉ። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች አንድ የሃይማኖት አባት ምን ማድረግ እንዳለበት የሚያውቁ ከሆነ እውቀታቸው ከሃይማኖት አባቶች በላይ በመሆኑ ይበልጥ ይፈረድባቸዋል።

ና

ብቻ ደካማነታችን ከተሰማን ጥሪው ይመለከተናልና ወደ ጌታችን ቀርበን «ጌታ ሆይ፥ በጎ የመሆን ፍላጎት እንጂ አቅም የለኝም። መከራዎቼ ሁሉ ሊለውጡኝ አልቻሉም። አንተ ብቻ ትለውጠኛለህና እንደ ቃልህ አሳርፈኝ» ብለን መጸለይ አለብን።

ከበደል ባሻገር የኑሮ ሸክም የተጫናቸው ብዙ ወገኖች አሉ። እንደ አገልጋይነታችንም ያሳዝኑናል። የሚያሳዝኑን በችግር ውስጥ ስላሉ ብቻ ሳይሆን ሲረዳቸው የተዘረጋውን የእግዚአብሔርን እጅ ማየት ባለመቻላቸውም ነው። እንደ ሳማ በሚለበልብ ትዳር ውስጥ የሚኖሩ፣ ምግባረ ብልሹ ልጆችን የተሸከሙ፣ ጣዕም በሌለው ባለጠግነት የሚዋኙ፣ ሰላም በራቀው ቤተሰብ የሚኖሩ፣ ጉድለት በሚፈራረቅበት ኑሮ የሚንገላቱ፣ ሥር በሰደደ በሽታ የተያዙ፣ የስህተታቸውን ዋጋ ከፍለው መጨረስ ያቃታቸው፣ ዝም ብለው በአሳብና በጭንቀት ማዕበል የሚንገላቱ፣ በፍቅር እጦት ምክንያት የብቸኝነት ብርድ የሚያንዘፈዝፋቸው ... ሰዎች በዙሪያችን አሉ። ይህን ጽሑፍ ለመጻፍ በተነሣሁ በመጀመሪያው ቀን እንኳ በስልኬ አለቃቂ የሆኑ ልቅሶዎችን ሰምቻለሁ። እነዚህ አልቃሾች ይህን ጽሑፍ እንድገፋበት ረድተውኛል።

በዚህ ሁሉ የለቀቀን ድምፅ ውስጥ *«እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፣ እኔም አሳርፋችኋለሁ»* የሚለው ድምጽ የኑሮ መድኅን ነው።

የተሸከምነውን ሸክም እንደ ተሸከምን ለመጓዝ ካልቻልን ታክሲ እንጠብቃለን። ታክሲው ሲመጣ ሸክማችንን ለታክሲው አሸክመን በታክሲው ምቾት ተዝናንተን እንጓዛለን። የመንገዱንም ጉዳይ ለሾፌሩ ስለጣልነው ዓይናችንን ጨፍነን እናዜማለን። እንዲሁም በእምነት ወደ ክርስቶስ ስንመጣ የሚከብደንን ሸክም ሁሉ ለእርሱ ትተን በዕረፍቱ አርፈን መጓዝ ይገባናል። ሸክም ያለ ቦታው አያርፍም። የሚያንገደግድ ሸክም ተሸክሞ ላቡ እንደ ውኃ እየጎረፈ የሚጓዘው ሰው ለምን አይጥለውም? ብንል ሸክም ያለ ቦታው

ስለማያርፍ ነው። እንዲሁም የሕይወትና የኑሮ ሸክማችንን ከክርስቶስ በቀር የሚያሳርፍልን ማንም የለም።

በዛሬው ዘመን ሰዎች ሁሉ ሊገናኙ የሚሰዋወጡት የእግዚአብሔርን ሰላም ሳይሆን ፍርሃታቸውን ነው። የአንዱ ፍርሃት ከሌላው ይለያል። የተቃጠለ አየር ስለሚሰዋወጡ ጥቂት እንደ ቆዩ ነፍሳቸው በፍርሃት ትታፈናለች። ይልቁንም በአንደበታችን የሸንፈት ቃሎች ስንናገር የእግዚአብሔር ኃይል እየራቀን ይመጣል። እንደ ዋዛ የምንናገራቸው «እግዚአብሔር ቢኖርማ እንዲህ ይሆን ነበር? የእኔ ዕድል ጠማማ ነው። አልፎ አወራው ይሆን? . . .» የሚሉት ንግግሮች የተለመዱ ስለሆኑ ምንም አይመስሉንም እንጂ የጭንቀትን ዘመን የሚያራዝሙብን ናቸው። ሰይጣን መረጃ የሚያገኘው ከአንደበታችን በመሆኑ የሸንፈት ቃሎች ስንናገር አሁንስ ደክሞታል ብሎ ጦር ያስከትትብናል። ይህን ስንል ልባችን ወድቆ በአንደበታችን እናስመስል ማለት አይደለም። ከእግዚአብሔር አቅም በላይ የሆነ ፈተና አልገጠመንምና ልባችንም አንደበታችንም ሊፀና ይገባዋል። ድካማችንንም በጸሎት ለእግዚአብሔር መንገር ያስፈልገናል።

በሰለጠነው ዘመንና ዓለም ሁሉም ነገር ዋስትና ይፈልጋል። ስለዚህ ሰዉ፣ መኪናው፣ ቤቱ... ዋስትና አለው። የዋስትና ተቋማትም በታማኝነት መኪና ሲጠፋ መኪና ይተካሉ። ዋስትናችንን አሳድገናል በማለትም ሰዎች የሕይወት ዋስትና እንዲገቡ ያባብላሉ። ነገር ግን ለጠፋ ሕይወት ገንዘብ እንጂ ራሱን ሕይወት ሊተኩ ታይተው አያውቁም። ስለዚህ ዋስትናቸው ከቁሳቁስ አያልፍም። ላዘመሙ ትዳሮች፣ መረን ለሆኑ ልጆች፣ ለታወከች ነፍስ መፍትሔ የላቸውም።

የምንኖርበት ዓለም ጥፋትና ክስረት የሚፈራረቅበት በመሆኑና ዘወትርም በልዩ ልዩ አደጋዎች ውስጥ ስለምናልፍ ዋስትና እንፈልጋለን። እኛ የምንፈልገውን ዋስትና የታወቁ የኢንሹራንስ ድርጅቶች ሊያሟሉት አይችሉም። እኛ ራሳችንን አልተቀበልነውም፣ ሰላማችን እንደ ባሕር የሚነዋወጽ ነው፣ በትዳር ምርጫችን ደስተኞች አይደለንም ...። ታዲያ የኑሮ መድኅናችን ማን ነው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። የዚህ መጽሐፍ ዓላማ በማዕበልና በፍርሃት ለሚንገላቱ ወገኖቻችን የነፍሳቸውን መልሕቅ ለመወርወር ነው። መጽሐፉ ያሳያል እንጂ አንባቢውን ተክቶ አይደርስም። እውነቱን ይናገራል እንጂ ለአንባቢው አያምንለትም።

የመጽሐፉ ፍለት ከብሉይ ኪዳን እስከ አዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ለእኛ ሕይወት ያለውን ዕቅድ ያሳያል። የዓለምን ከንቱነትና የእግዚአብሔርን ቋሚነት ለማሳየት ይጨነቃል።

እያንዳንዱን ምዕራፍ አንባቢው ሲጨርስ የጽሞና ጊዜ በመጠየቅ ከአንባቢው ጋር ይደራደራል። የአንባቢው እሺታ በራሱ ኃይል የለውምና ወደ ጸሎት ያልፋል። መጽሐፉ አንባቢው ከአምላኩ ጋር እየተገናኘ በጸሎት መንፈስ ሆኖ እንዲያነበው የተዘጋጀ ነው። ብዙ ሀዘንተኞች የጽሑፉን ጅምር አይተው እንድፈጽመው ከዓመት በላይ ወትውተውኛል። እናንተም እንደምትበረቱበት ጸሎቴም እምነቴም ነው።

ምዕራፍ አንድ
ኑሮና ሕይወት

አንድ ወጣት ለትምህርት ከአፍሪካ ምድር ወደ ጣልያን አገር ይሄዳል። አንድ ቀንም ትምህርቱን አጥንቶ ፀሐይዋ ዘቅዘቅ ስትል አየር ለመቀበል በጎዳና ላይ ሲጓዝ አንድ በዕድሜ የገፉ አረጋዊ አገኘ። አረጋዊውም መልኩን በማየት ከሌላ አገር እንደ መጣ ተረድተው፦ «ልጄ ወደዚህ አገር ለምን መጣህ?» በማለት ይጠይቁታል። ወጣቱም «ለትምህርት» አላቸው። እርሳቸውም በሦስት እግር እየተጓዙ «ከተማርክ በኋላ ምን ትሆናለህ?» በማለት በዝግታ ይጠይቁታል። ወጣቱም ሽምግልናቸውን በማየት ቢደሰቱ ብሎ «ጳጳስ እሆናለሁ» አላቸው። እርሳቸውም ሳይደነቁ «ጳጳስ ከሆንክስ በኋላ ምን ትሆናለህ?» አሉት። እርሱም «ካርዲናል እሆናለሁ» አላቸው። እርሳቸውም «ካርዲናል ከሆንክስ በኋላ?» አሉት። ወጣቱም በደስታ ዓይኑን ጨፍኖ «አ አይገኝም እንጂ ፖፕ እሆናለሁ» አላቸው። አረጋዊውም «ፖፕ ከሆንክስ በኋላ?» ቢሉት «ከዚያ በኋላማ በመልካም አስተዳደሬ እሞታለሁ» አላቸው። አረጋዊውም ታላቁን ምክራቸውን ሲለግሱት «እየህ ልጄ፦ ጳጳስ፣ ካርዲናል፣ ፖፕ ልትሆንም ላትሆንም ትችላለህ። መሞትህ ግን አይቀርም። መጀመሪያ ለማይቀረው አስብ፣ ከዚያ ቀጥሎ ግን ሊሆንም ላይሆንም ስለሚችለው ነገር አስብ» አሉት ይባላል።

የሰው ልጆች ስለ ትምህርት፣ ስለ ሥራ፣ ስለ ትዳር፣ ስለ ልጅና ስለ ክብር ብዙ ያስባሉ። እነዚህን ነገሮች በቀጥታም ሆነ በአቋራጭ ቢያገኙ ዋናው ማግኘታቸው እንደሆነ ይለማቸዋል። ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ ሲባሉም ከእነዚህ ነገሮች በኋላ እንደሚመለሱ ይናገራሉ። የጉብዝናቸውን ዘመን ለዓለም፣ የድካማቸውን ዘመን ለእግዚአብሔር፤ የሚፈለጉበትን ዘመን ለሥጋ፣ መፈለጋቸው የሚቀንስበትን ዘመን ለእግዚአብሔር ቤት ለማድረግ የወሰኑ ይመስላሉ። ተምረን ሥራ እንይዛለን፣ ሥራ ከያዝን በኋላ ትዳር እንመሠርታለን፣ ከዚያም ዓይናችንን በዓይናችን በልጆቻችን በማየት የከበሬታ ሥፍራን በማጎበረስቡ ዘንድ በመጨበጥ ደስ ይለናል ይላሉ። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ግን ሊሆኑም ላይሆኑም ይችላሉ። በሰዎች ላይ ግን ለማንም የማይቀር አንድ ዕጣ አለ። እርሱም ሞት ነው። ያስቀመጠውን የማይረሳ ጌታ በጫካ ቢሆን በከተማ በፈለገው ሰዓት ፍጡሩን አያጣውም። የቤተ መንግሥት ዘቦች፣ ከባቢሎን ግንብ የሚበልጡ አጥሮች የሞትን መልእክተኛ መመለስ አይችሉም። ሰው ከአፈር መፈጠሩ ምን

ያስተምረናል? ብንል ትሑት እንዲሆንና ሞቱን ማሰብ እንዲገባው ያስተምረናል። ስለዚህ ስለማይቀረው አስቀድሞ ማሰብ ይገባል።

የሰው ልጅ የማይለወጡ ሁለት ቋሚ ባሕርያት አሉት። እነርሱም፦ *ሥጋና መንፈስ* በመባል ይታወቃሉ። *ሥጋው* ግዙፍ ሲሆን *መንፈሱ* ግን ረቂቅ ነው። ለ*ሥጋው* እንጀራ ሲያስፈልገው ለ*መንፈሱ* ደግሞ የእግዚአብሔር *ቃል* ያስፈልገዋል። ጌታችን በገዳመ ቆሮንቶስ ለሰይጣን «*... እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል*» *በማለት ሲፈትነው «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል»* በማለት መልሶለታል (ማቴ.4÷4፤ዘዳ.8÷3)። ሰው ሁለት ባሕርያት እንዳሉት ይገልጻል። እነርሱም፦ *ሥጋና መንፈስ* ይባላሉ። እነዚህ በአንድ አካል የተዋሐዱ ሁለት ባሕርያት ፍላጎታቸው ፍጹም የተለያየ ነው። *ሥጋው* እንጀራ ሲያስፈልገው፣ *መንፈሱ* ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ይፈልጋል። ስለዚህ እንጀራ ብቻውን የሰውን ፍላጎት አያረካም ማለት ነው። የሰው ልጅ ፍላጎት ከመብል፣ ከመጠጥ፣ ከልብስና ከመጠለያ ያለፈ ነውና።

የሰው ልጅ ግን ለሆዱ እንጀራን ለማግኘት የሚደክመውን ያህል ለመንፈሱ ምግብ የሚሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ለማግኘት አለመድከሙ ያሳዝናል። ካልበላን በ*ሥጋ* መኖር እንደማንችል፣ ያለ እግዚአብሔር ቃልም የ*መንፈሳችን* ህልውና ተጠብቆ መቆየት አይችልም። የጥንት ሮማውያን ምርኮኞቻቸውን ራሳ አሸክመው ይነዱአቸው ነበር። ይህ ሸክም ከባድ ሲሆን ምርኮኞቹም መጥፋት አይችሉም ነበር። ቃሉን የማይመገብ *መንፈሰም* የራሳ ሸክም ነው። የበረታ *ሥጋ* የሞተ *መንፈስን* መሸከም አይችልም። ብርቱ *መንፈስ* ግን የደከመውን *ሥጋ* ይሸከማል።

የሰው ልጅ የሚታይና የማይታይ ተፈጥሮ አለው። በማይታየው ባሕርይው እግዚአብሔርን ይመስላል። በሚታየው ተፈጥሮው ደግሞ እንስሳትን ይመስላል። ስለዚህ ለው ምድራዊም ለማያዊም ነው። በ*ሥጋው* እንስሳትን መስሎ ይበላል፣ ይጠጣል፣ ይወልዳል፣ ይዋለዳል። በነፍሱ ደግሞ መላእክትን መስሎ ይዘምራል፣ ይቀድሳል። በ*ሥጋው* ጊዜያዊ ሲሆን በነፍሱ ግን ዘላለማዊ ነው።

በአንድ ሣንቲም ላይ እንዳለ ሁለት ገጽታ የሰው ሁለንተናም ኑሮና ሕይወት በመባል ይጠራል። ኑሮ ያለ ሕይወት ሙት ሲሆን ሕይወት ያለ ኑሮም የማይገለጥ ነው። ሰዎች ሰላምታ ሲለዋወጡ «ኑሮ እንዴት ነው? ሕይወትስ?» በማለት ይጠይቁናል። በርግጥም

የሚጠየቅ ጥያቄ ነው። ነገር ግን ጥያቄውም ሆነ መልሱ የልማድ ንግግር መሆኑ ያሳዝናል። ኑሮ የዚህ ዓለም ቆይታችን ነው። ሕይወት ግን ኢየሱስ ክርስቶስን ካመንበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ዘላለም የሚቀጥል ነገር ነው። ስዎች በትልልቅ ተቋማት ገብተው የሚማሩት የአንጀራ እውቀትን እንጂ የሕይወት እውቀትን አይደለም። ያማ ቢሆን ኖሮ ብዙ ሊቃውንቶች ሕይወታቸው የወደቀ ባልሆነ ነበር። የሕይወት እውቀት የሚገኘው ከሕይወት ባለቤት ከእግዚአብሔር ብቻ ነው።

ኑሮ *መራራም* ጣፋጭም ነው። ቍሳዊ በመሆኑ የውስጥን ጥማት ማርካት አይችልም። ኑሮ ማዘን መደሰት፣ ማግኘት ማጣት፣ መነሣት መውደቅ፣ መወደድ መጠላት፣ መከበር መዋረድ ያለበት በሁለት ተቃራኒና አንጻራዊ ሁኔታዎች የተዋቀረ ነው። ኑሮ በደሳሳውም ጎጆ ሆነ በቤተ መንግሥት ትንሽ ነው። ለው ትንሽነቱን የሚያገኝበትና የሚደብቅበት ቦታ ቢኖር ኑሮ ነው። መሸነፋ፣ ማዘኑ፣ መድከሙ፣ ተስፋ መቍረጡ፣ በስሜት መውደቁ የተሸፈነው በኑሮ ውስጥ ነው። ኑሮ ለባለቤቱ እንደሚመስለው ምሥጢር ነው። ኑሮ በየትኛውም ቦታና ጊዜ ጎዶሎ ነው። ያጎደለው ግን አምላካዊ ጥበብ በመሆኑ የሰው ጥረት ሊሞላው አይችልም። ጎዶሎው የጸሎት ርዕስ ነው። «ጎዶሎ ከሌለ እግዚአብሔር ይረሳል» እንደሚባለው። ኑሮ በክርስቶስ ሕይወትን ካላገኘ የራሳ ሸክም፣ ጨው የሌለው አልጫ፣ የማይደፈር ጨለማ ነው።

ከዘላለም አገር ሆነን ስናየው ግን ኑሮ ቀላልና አስደሳች ነው። ትልልቅ ነገሮች ትልቅ ሆነው የሚታዩት ከምድር ስናያቸው ነው። ከሰማይ ስናየው ግን ትልቁ ተራራ እንኳ ትንሽ ነው። በአጠቃላይ ኑሮ ራሱን የሚተረጉም መዝገበ ቃላት የለውም። የኑሮ ትርጉም ያለው በሕይወት ውስጥ ነው። ያለ ሕይወት ኑሮንም መኖር አይቻልም። ስለዚህ ወደ ቀጣዮቹ ምዕራፎች ከመዝለቃችን በፊት በክርስቶስ ያለውን ሕይወት ወራሽ መሆናችንን ማረጋገጥ አለብን። ምክንያቱም የጸሐፋ ዓላማ ግንዛቤን ማስፋት ሳይሆን በእምነት ማቆም ነውና።

ከመጀመሪያዎቹ ሰዎች እንሥተን ብንመለከት የሰው ዕድሜ እየቀነሰ መጥቷል። የኑሮ ትግል ግን በርትቷል። ዕድሜው ትንሽ ትግሉ ብዙ ሆኗል። በዚህ ዓለም ላይ የምናሳልፈው ዕድሜ በሰማይ ከምናሳልፈው ጋር ሲነጻጸር የዓይን ጥቅሻ ያህል ነው። ከዘላለም አንጻር ስናየው የዚህ ዓለም ቆይታችን እንዲት ሰዓት እንኳ አይሞላም። በዚህ ዓለም ላይ ያሳለፍነው የዕድሜ ልክ መከራችን

በመንግሥተ ሰማያት የአንዲት ሰዓት ደስታ ይካሳል (ሮሜ.8÷18)። የመጽሐፍ መግቢያ የመጽሐፉ ቅምሻ እንጂ ሙሉ መጽሐፉ እንዳልሆነ በትልቁ የሕይወት መጽሐፍም የዚህ ዓለም ኑሮ እንደ መግቢያ ነው።

ቢሆንም ትግል ባይኖር የድል ደስታ፣ በሽታ ባይኖር የጤና ምስጋና አይኖርም ነበር። ጣፋጭን ያጎላው መራራ ነው። አንድን ነገር ሳንፈልገው ከምናገኘው ዋጋ ከፍለን ስናገኘው ያስደስታል። አክብረንም እንይዘዋለን። አዎ ትግሎች ሳይቀር ለደስታችን ተዋቅረዋል። የዚህ ዓለም ቆይታ ጊዜያዊ ቢሆንም ዘላለማዊ ውሳኔ የሚደረግበት በመሆኑ እንደ ቀላል የሚታይ አይደለም። ይህ ዓለም ቆይታው ትንሽ ቢሆንም በጎ ለመሥራትም ሆነ በክፋ ሥራችን ለመፀፀት ዕድል ያለበት ዓለም ነው። የወዲያኛው ዓለም ግን የምርጫችንን ውጤት የምንቀበልበት ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *«ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል»* (ማቴ.6÷33) ብሏል። ቀዳሚዉ መንግሥቱና ጽድቁ ነው። የዚህ ዓለም ኑሮ ግን ተጨማሪ ነው። የሚቀድመውንና የሚከተለውን ማወቅ ትልቅ እውቀት ነው። የብዙዎች ሰዎች ችግር ቀዳሚውንና ተከታዩን አዘባርቆ መኖር ነው። ከምላ ቀጥሎ መክሰስ ወይም የእራት መዳረሻ አለ። የዚህ ዓለም ኑሮም ዋናው ሳይሆን የሰማይ መዳረሻ ነው። በትልልቅ ሆቴሎች ክዋናው ምግብ በፊት የባለጠጎችን አምሮት የሚከፍቱ ቀላል ምግቦች ይከታተላሉ። ዋናው ገና መሆኑን የማያውቅ እስከ መጨረሻው ይመገባቸውና ዋናው ምግብ ሲመጣ ይጠግባል። ይህ ዓለም ዋና የመሰለውም ሰው በቀላል ነገሮች ጠግቦ ዋናውን ሕይወት ይገፋል። በትልልቅ በዓላት የዋዜማ ድግስ አለ። በዋዜማው ጨርሶ የጠገበ ሰው በዋናው በዓል ላይ መቆም ያቅተዋል። ይህ ዓለምም ለሰማዩ ዋዜማ ነው። ነጋዴ ዋና ይዞ ነው የሚነግደው። ትርፍ ዋጥቂ ነው። ዋናውን የማያውቅና የማይጠብቅ ነጋዴ መሆን አይችልም። ከዚህ ሁሉ በላይ ትርፍና ኪሣራውን አጥርቶ አያውቅም። ሕይወትም ብዙ የምናተርፍባት ብዙ የምንከስርባት ንግድ ናት። በሕይወት ውስጥ ዋናው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሌላው ግን ትርፍ ነው። ስለዚህ ዋናውን ላለማስነካት መጠንቀቅ አለብን።

ይህን ዓለም እንደ ዘላለም ቤቱ የሚኖር ሰው ምስኪን ነው። እንደ እውሬ እያጉረመረመ የሚበላ፣ እየነጠቀ የሚያድር ነው። ማጣቱና መውደቁ የጠለቀ ሀዘን ውስጥ የሚከተው ነው። ይህ

ዓለም ጊዜያዊ ቤት ነው። መጽሐፉ እንደሚለው የድንኳን ኑሮ ነው (2ቆሮ.5÷1)። ድንኳን በቶሎ ይፈርሳል፣ ዓለምም ለማለፍ ይቸኩላል። ድንኳን ምንም በጥሩ ካስማ ቢተከል መነዋወጹ አይቀርም። ዓለምም የተረጋጋ ሰላም የለውም።

ታዲያ በዓለም ላይ መኖር እንዴት ይቻላል? እንል ይሆናል። መርከብ በውኃ ውስጥ ሳይሆን በውኃ ላይ መሄድ ይችላል። ከፍተት ከሰጠ ግን ውኃው እየሞላው መስጠም ይጀምራል። ክርስቲያንም በዓለም ላይ መኖር፣ መማር፣ መሥራት ይችላል። ለዓለም ክንቱ አሳብ ግን ትንሽ ክፍተት ከሰጠ መስጠም ይጀምራል። መርከብ በውኃ ላይ እስከሄደ ድረስ ወደ ወደቡ ይደርሳል። ውኃው ከበላዩ ከሆነ ግን እዚያው ይሰጥማል። ክርስቲያንም በዓለም ላይ መኖር ይችላል። ወደ ወደቡ ወደ ሰማይ ለመድረስ ግን ቀዳዳዎችን መድፈን አለበት።

በዛሬው ዘመን የሰው ልጆች የኑሮ ፍርሃት ጨምሯል። የዚህ የመጀመሪያው ምክንያት ያለ ሕይወት ኑሮን መኖር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሚቀድመው ስላልቀደመ የሚከተለው አልገጥም እያላቸው ነው። ክመቼውም ጊዜ ይልቅ የሰው ልጆች በአንድ ዓይነት ትምህርት፣ በአንድ ዓይነት ሥራ አይኖርም ወደሚል እምነት ውስጥ ገብተው ይባክናሉ። ሁለት ዓይነት ሥራ፣ ሁለት ዓይነት ትምህርት ይማራሉ። የእውቀት ስስት ይሏቸው በዚህ ባጣ በዚህ እበላለሁ ብለው ይማራሉ። መማርም መሥራትም ተገቢ ቢሆንም ዋስትና ግን አይሆንም። እኛ ሁሉን ይዘነውስ ሌላው ምን ሆኖ ይኑር?

ሥጋ መፍራት ልማዱ ነው። የታረደውን በሬ ስናይ *ሥጋ* ሞቶ እንኳ እንደሚንቀጠቀጥ እንረዳለን። ባለ ቅኔው፦

«ጥንቱንም ሲፈጥረው ሥጋ ብለውት፣
ሲጨነቅ ይኖራል የለውም ዕረፍት፣» ብሏል።

ሥጋ የሚለው ቃል *ሥጋት* ከሚለው ቃል የወጣ ሲሆን በትእዛዝ አንቀጽ *ሥጋ* ወይም ፍራ ተብሏል። ባለ ቅኔውም *ሥጋ* መፍራት ልማዱ መሆኑን ሲገልጥ ነው። ሰው ልቡን በእምነት ካላሳረፈ በቀር ቢመንንም ቢነግድም ዕረፍት አይኖረውም።

የጽሞና ጊዜ

የሚታይና የማይታይ ተፈጥሮ ስለያዝህ ተፈጥሮህ ራሱ የዚህ ዓለም ሰው ብቻ እንዳልሆንህ ይገልጻል። ሰማያዊ ነህ! ፈላስፋው «ዛሬ ማታ እንደሚሞት ሆነህ ተዘጋጅ፣ ለዘላለም እንደሚኖር ሆነህ ግን ሥራህን ሥራ» ያለውን አስተውል። ከሁሉ በላይ ለአውነት ተፈጥረህ ለውሸት አትኑር። የሚቀድመውን አስቀድም በመጀመሪያ፦

- የማይቀረውን ሞት፣
- መንግሥቱንና ጽድቁን፣
- ዋናውን፣
- ሕይወትን አስብ።

ጸሎት

ለአነሣሥህ ጅማሬ፣ ለዓመታትህ ፍጻሜ፣ ለአሠራርህ ገደብ፣ ለአቅምህ ልክ የለህምና ሕያውነትህ ሕያው ያደረገኝ ልጅህ አመሰግንሃለሁ። ዓለሙን ሳየው አንተ ሳታሳልፈው ቶሎ ለማለፍ እየቸኮለ ነውና በማዕበል፣ በእሳት ውስጥ አባክህ መንገድ ስጠኝ። ጽንሱ ከአናቲቱ ጋር እንደተቆራኘ አኔም ያላንተ አልኖርምና ከፊትህ አትጣለኝ። የማይቀረውን ማለብ ትቼአለሁ፣ ለው አያየኝም ብዬ በምታየኝ በአንተ ፊት ብዙ በድያለሁ፤ ብዙ ሰው አቀስያለሁና አቤቱ ማረኝ። ሥጋዬ የሬሣ ሽክም እንዳይሆንብኝ አንተው ገላግለኝ። ከመልአካዊ ተፈጥሮዬ እንስሳዊ ተፈጥሮዬ አይሎብኝ ተዋርጀአለሁና ዕድሜም አውቀትም ያለወጠኝን ልጅህን በሚለውጥ ፍቅርህ ለውጠኝ። ከሚያልፈው ትግል ውስጥ የማያልፈውን ትምህርት እንዳልጥል አርዳኝ። ቢለምኑህ የማትሰለች፣ ብትሰጥ የማያልቅብህ አንተ ነህና ለዘላለሙ አሜን።

ምዕራፍ ሁለት
የፀሐይ ዕድሜ

አንድ ሰው በጫካ በተከበበና ጭር ባለ መንገድ ብቻውን ሲሄድ ፍርሃት ይይዘውና «ጌታ ሆይ» ብሎ ይጮኻል። «ጌታ ሆይ እንደምታየኝ ጫካ ውስጥ ነኝ። መንገዱም ጭር ያለ ነው። ብቻዬን ነኝና ፈራሁ፣ እባክህ ድረስልኝ» ሲል ይጮኻል። ትንሽ እንደ ቆየ ብቻውን በሚሄድበት መንገድ የሁለት ሰው ጥላ ያያል። ያን ጊዜም ደንግጦ እንደ ገና ወደ እግዚአብሔር «ጌታ ሆይ ፍርሃቴ ጨመረ ብቻዬን እየሄድኩ የሚታየኝ የሁለት ሰው ጥላ ነው። ነገሩ ምንድነው?» ሲል ጮኸ። እግዚአብሔርም፦ «አይዞህ ልጄ ብቻህን አይደለህም፣ የምታየው ሁለተኛ ጥላ የእኔ ነው። እኔ አብሬህ ነኝና አትፍራ» አለው። በዚያን ጊዜ ሰውዬው ደስ ብሎት ያለ አሳብ ጉዞውን ቀጠለ። ተጉዞ ተጉዞ ረግረጋማና ዳገታማ ስፍራ ላይ ሲደርስ ዞር ብሎ ቢያይ ጥላው ከአጠገቡ የለም። ይህን ጊዜ ፍርሃት ያዘውና «ጌታ ሆይ» ይል ጀመረ። «ጌታ ሆይ ቅድም በተደላደለው መንገድ ስሄድ አንተ ከጎን ጎኔ ትሄድ ነበር። አሁን ግን አንዲህ ባለ ሰጉዞ በማይመች የአንተ እርዳታ እጅጉን በሚያስፈልገኝ ረግረጋማና ዳገታማ ቦታ ላይ ስደርስ ግን ጥለኸኝ ሄድክ። ጌታ ሆይ ምን አጥፍቼ ነው ይህ የተደረገብኝ?» ሲል ጮኸ። እግዚአብሔርም በዝግታ «አይዞህ ልጄ የቅድሙ መንገድ የተመቻቸ ስለነበር አብሬህ እንዳለሁ እንዲለማህ ብቻ ጎን ጎንህ እሄድ ነበር። የአሁኑ መንገድ ግን ለጉዞ የማይመች አስቸጋሪ መንገድ ስለሆነ ጥላዬ የጠፋብህ አዝዬህ ነውና አይዞህ። የምታየው የእኔን ጥላ ነውና በርታ» አለው።

እግዚአብሔር አብሮን የሚሆነው እኛ ግድ ስላልነው ሳይሆን ፍቅር ስለሆነ ነው። በአስቸጋሪ ስፍራም አይለየንም። ሲደክመንም ጥሎን አይሄድም፣ ይልቁንም ይሸከመናል እንጂ። የአሕዛብ ጣዖታት ሰዎች የሚሸከሟቸው ናቸው። የሚያምኗቸውን ግን የሚሸከሙ አይደሉም። የእኛ ጌታ እግዚአብሔር ግን የሚሸከመን አምላክ ነው።

የአገራችን መምህራን የሰውን ዕድሜ በፀሐይ ይመስሉታል። ፀሐይ በማለዳ ስትወጣ ድካምና ፍርሃት ተወግዶ ሁሉም ሰው አዲስ በሚላት ቀን ተግባሩን ሊጀምርባት ይነሣል። የጠዋት ፀሐይ ተናፋቂና ተወዳጅ ናት። ሌሊቱን ሲፋንኑ ያደሩ አራዊትና ሌቦች ወደ ጎራአቸው ሲገቡ የብርሃን ልጆች ግን ይወጡባታል። ይህችን የማለዳ ፀሐይ ዱካ ያለው ዱካውን ይዞ የሌለውም በድንጋይ ላይ ተቀምጦ ይሞቃታል። በቤት ውስጥ የሚሸፋፈኑ አራስ ሕፃናትም በእናታቸው ጉልበት ላይ ሆነው ራቁታቸውን ይሞቋታል።

ሰው ሁሉ ተጠራርቶ የሞቃት ያች የጠዋት ፀሐይ ቀትር ላይ ሁሉም ሰው ይሸሻታል፣ ይጠላታል፣ ይመረርባታል፣ በትንሽ ጥላ እንኳን ሲደበቃት ይሞክራል። ተጠራርቶ እንዳልሞቃት ምን ዓይነት ቊጣ ነው? ይላታል። ፀሐዩ እስኪበርድም ከቤት አትውጡ ይባላል። የጠዋቱ አድናቆትና ምስጋና ቀርቶ ምሬት ይተካል።

ቀትር ላይ ሁሉም ሰው የተመረረባት ፀሐይ ሠርክ ላይ ልትጠልቅ ስትል ሁሉም ሰው ይሳሳላታል። ጨርሳ ሳትጠልቅ ይሯሯጥባታል፣ ወደ የቤቱ ይሰበሰብባታል፣ ጥበበኞችም በባሕር ዳርቻ ላይ ከውኃው ጋር የጆት ሰጠውን ውበት ለማስቀረት ፎቶ ግራፋቸውን አስተካክለው ይጠብቋታል። ጠዋት ላይ ጨለማን ወደ ፊት እየገፋች የወጣችው ፀሐይ ሠርክ ላይ ጨለማውን ወደ ኋላዋ አድርጋ ትጠልቃለች። እግዚአብሔር ፀሐይን በውበት አውጥቶ በውበት ያስገባታል።

አንዲ ፀሐይ ጠዋት ላይ ሁሉም ሰው የሚሸማት፣ ቀትር ላይ የሚሸሻት ሠርክ ላይ የሚሳሳላት ናት። ለአንዲቱ ፀሐይ ያለንን ተለዋዋጭ ስሜት ግን አስተውለነው አናውቅም። የሰው ዕድሜም በፀሐይ ይመሰላል። ፀሐይ በቀን ውስጥ ሦስት ዓይነት ስሜት ትፈጥራለች። ሕይወትም እንዲሁ ናት።

ፀሐይ በምሥራቅ ስትወጣ ሁሉም ሰው በናፍቆት እንደሚቀበላት፣ ተጠራርቶ እንደሚሞቃት ሕይወትም ገና በጅምሯ ጣፋጭና የማትጠገብ ናት። ሕጻን ሲወለድ ሁሉም ሰው ተጠራርቶ ይቀበለዋል፣ ሴቶች በእልልታ ወንዶች በጥይት ተኩስ ደስታቸውን ይገልጣሉ። ያ ልጅም ሮጦ አይደክምም፣ ዘሎ አይጠግብም። «ሁሉም ነገር በጠዋቱ ቀዝቃዛ ነው» እንደሚባለው የሕይወት ትግሉም ለእርሱ ቀላል ነው።

አዋቂዎች ስለ ብርቱ ችግር ሲያወሩ ሕጻኑ ግን ስላማረው ምግብና መጫወቻ ያወራል። የእንግሊዝዋ ንግሥት ልጅ ሰው ተራበ የሚል ወሬ ብትሰማ አይስክሬም አይበሉም ወይ? ቢጠፋ ቢጠፋ አይስክሬም ይጠፋል ወይ? አለች እንደሚባለው ሕፃኑም ልክ እንደዚህች ልዕልት ነው። አዋቂዎች ሲያለቅሱ ልጆች ግር ይላቸዋል። ሕይወት ታስለቅሳለች ብለው ማመን በፍጹም አይሆንላቸውም።

ያቺ ተናፋቂ የጠዋት ፀሐይ ቀትር ላይ እንደምታስመርር ሕይወትም ልጅነቱን ለፈጸመውና ለራሱ ማሰብ ለጀመረው ወጣት እንግዳና አስፈሪ ናት። ለራሱ ምንም ባያደርግ እንኳ ለራሱ ማሰብ

ብቻውን ወጣቱን ያደክመዋል። ወጣቱ ሞምብሱን ሲያወልቅ፣ ዓለምን ብቻውን ሲያያት፣ ሁሉም ነገር ሲለዋወጥበት ግር ይለዋል። ሲወለድ ወንድ ተወለደ ተብሎ የተደሰቱ ለምች አሁን እነዚህን ጎረምሶች ይንቀልልን ሲሉ ይደነግጣል። ሲስሙት የኖሩት አሁን ችላ ይሉታል። መንገድ ሲጠፋበት ከመምራት ያዋክቡታል። መንግሥትም ወጣቱ ኃይል ነው ብሎ ስለሚሰጋ ሠራዊት ያደራጅበታል። ሲወድቅ ጎበዝ ይባል የነበረው ሕፃን አሁን ትንሽ ሲሳሳት ፖሲስ ይጠራበታል። እደግ ተብሎ የተመረቀው ሲያድግ ይረገማል። በዚህና በሌሎች የሕይወት ትግል እንዴት እኖራለሁ? የሚለው ጥያቄ ወጣቱን ያስጨንቀዋል።

ቀትሩ ፀሐይ በአናት ላይ የምትወጣበት ለዓት ስለሆነ ክባድ ሰዓት ነው። ሕይወትም በወጣቱ ላይ ብርቱ የምትሆንበት ቀትር አላት። እስከ ዕድሜ ልክ የሚዘልቁ ሱሶችና ስህተቶች የሚጀመሩት በዚህ በወጣትነት ዘመን ነው። በወጣትነት የተፈጸሙ ስህተቶችና የማይገቡ ምርጫዎች እስከ ዕድሜ ልክ የማይስተካከሉበት ጊዜ ብዙ ነውና ወጣቱ ማስተዋል ይገባዋል። ሕይወትን ከትዕግሥት በቊጣ፣ ከትሕትና በትዕቢት ለመምራት መሞከር ለቀጣዩ መንገድ መሰናክል ማስቀመጥ ነው። የአሁን መሳካት የሁልጊዜ መሳካት፣ የአሁን አለመሳካት የሁልጊዜ አለመሳካት አለመሆኑን ወጣቱ ሊያስተውል ይገባዋል። መከራም የጥራት መገኛ መሆኑን ወጣቱ ሊያስተውል ሲገባው፣ መልካም ዕድልም የሚሰጥ ሳይሆን የሚመረጥ መሆኑን መገንዘብ አለበት።

የሌለውን እንዳለው አድርጎ የሚያስብ ጉረኝነት የቀትሩ አጉል አመል ነው። ቀትርን ሁሉም እንደሚሸሸው ወጣቱም ሕይወትን ለመደበቅ ይሞክራል። ሕይወትን ግን ስንጋፈጣት እንጂ ስንሸሻት አትሸነፍም። ቀትሩን በትንሽ ጥላ ለመጋረድ እንደሚሞክር የሕይወት ጥያቄ ሲበዛም በሱስ፣ በቁማርና በኃጢአት ውስጥ ለመደበቅ ቀትር ላይ የደረሰው ሰው ይጥራል። በእርግጥ የወጣትነት ክፉ ባሕርያት ክባልንጀራም እንደሚወረሱ አንዘነጋም። ወጣቱ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ መጀመሪያ የተቀበሉትን ቤተሰቤ ብሎ እንደ ኖረ ከቤቱ ሲወጣም በሰፊው ዓለም መጀመሪያ የተቀበሉትን ቤተሰብ ያደርጋል። ሕይወት ቀትር የሆነችበት ሰው በቶሎ ተስፋ በመቊረጥ ሞቱን ይመኛል። ወላጆቹ የእርሱንና የራሳቸውን ደግሞም የቤተሰቡን ሕይወት ተሸክመው ሳለ መኖር የእርሱን ያህል አልከበዳቸውም። እርሱ ግን በአሳብ ጭነት ለምን እንደሚንገዳገድ አያስተውልም።

ያች ተናፋቂ የጠዋት ፀሐይ ቀትር ላይ እንዳስመረረች ልትጠልቅ ስትል ደግሞ ታሳሳለች። ለዚህ ነው ወጣቱ ሞትን ሲመኝ የታመሙትና ሽማግሌዎች ግን ዕድሜን ይለምናሉ። በሕይወት ሠርክ ላይ ኑሮን ኖርኩበት ወይስ ኖረብኝ ብለን ሂሳብ እንተሳሰባለን። ይህ የፈቃዳችን ጉዳይ ሳይሆን ግድ ነው። ማድረግ በማንችልበት ጊዜ ከማዘን እግዚአብሔር ይጠብቀን! ቢሆንም ለንስሓ እስካለን ጊዜ አያልፍምና ንስሓ መግባት ይገባናል። ንስሓ ከምግባራት ሁሉ ትበልጣለች። ፀሏይ ስትወጣ ጨለማን ወደ ፊት እየገፋች ሲሆን ስትጠልቅ ግን ጨለማን በስተኋላዋ አድርጋ ነው። ይህን ዓለም ለቀን ስንሄድም ከክርስቶስ ጋር ከሆንን ጨለማው ከኋላችን ነው። የዚህ ዓለም መከራና ድካም አይከተለንም። ሕፃኑ ሲወለድ ዙሪያውን የከበቡ ሰዎች እልል ይላሉ። እርሱ ግን በተፈጥሮው ወደዚህች እድካሚ ዓለም መምጣቱን እያወቀ ያለቅሳል። ይህን ዓለም ተሰናብቶ ሲሄድም ዘመድ አዝማዶቹ ያለቅሳሉ። እርሱ ግን ወደ ዕረፍቱ ይሄዳልና ዝም ይላል። የቆሙት ሰዎች ግን አያስተውሉም።

እግዚአብሔር ፀሐይን በውበት አውጥቶ በውበት ያጠልቃታል። ዕድሜም በሕፃንነትና በሽምግልና ውበት ይልቁንም በጨዋነት እንድትፈጸም የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ዘመንህ በውበት እንዲፈጸም በሕፃንነትህ ሽማግሌ አክባሪ፣ በወጣትነትህ ታታሪ ሠራተኛ፣ በሽምግልናህ አስታራቂ ከሁሉ በላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታህና መድኃኒትህ የሆነልህ ሰው ሁን። ምንም ኑሮ ቢከብድብህ ሞትን አትለምን። ወጣቱ ወደ አንድ አባት ዘንድ ሄዶ «አባቴ መሞት እፈልጋሁ» አላቸው። እርሳቸውም ዘና ብለው «ሞትን ባትፈልገውም ወዳንተ ይመጣል፤ ካልፈለግሃቸው ግን ወዳንተ የማይመጡ ብዙ መልካም ነገሮች አሉና ለምን እነርሱን አትፈልግም?» ብለውታል።

ከኮሚኒስት ርእዮተ ዓለም ወዲህ የብዙ የዓለማችን ወጣቶች ሕይወት ተዘርቶ ያልተሰበሰበ ፍሬ ሆኗል። ተስፋ የቆረጠ፣ ሞራሉ የወደቀ፣ በቦምብ ኳስ የሚጫወት ትውልድን ያተረፍነው ዓለም እግዚአብሔር የለም ብላ ካወጀች ጊዜ ጀምሮ ነው። እግዚአብሔር ከሌለ መልካም ሥራ ዋጋ፣ ክፉ ሥራም ቅጣት ሊኖረው እንዴት ይችላል? ስለዚህ ዓለምን ባለቤት የሌላት ቤት ስናደርጋት የዛሬውን የትውልድ መዝረክረክ አተረፍን። ኮሚኒዝም ከአደባባይ ቢወድቅም ገና የአደባባይ ንስሓ ስላልገባንበት ከሰው ልብ አልወደቀም። በአዋጅ ከደን በተናጥል ነው ንስሓ የገባነው። ወጣቱ ትውልድ ወደ እግዚአብሔር ቤት ሲመጣ ብናይም ውስጡ ግን በዚህ ክፉ ሥርዓት

ተገዝቷል። አሁን ያሉት ትልልቅ ሰዎችና የወደፊት ሽማግሌዎችም እግዚአብሔር የለሾች መሆናቸው አይቀርምና ልናስብበት ይገባል።

በአንድ ቀን ውስጥ ሁለት ወጣቶችን ሳማክር በተለያየ ሰዓት ቢመጡም የጠየቁኝ ጥያቄ አንድ ዓይነት ነበር፦ «ይህን ወጣትነቴን ምን ላድርገው? ይህን ዕድሜዬን ምን ላድርገው?» ስሰማቸው ልቤ ቢያዝንላቸውም ነጻ የሚያወጣቸው ክርስቶስ ግን እንደ ተሰቀለ ሆኖ ይታየኝ ስለነበር ደስ አለኝ። አሁን እነዚህ ወጣቶች ወጣት ለዘፈን፣ ወጣት ለዝሙት የሚሰውን መመሪያ ጥለው ወጣት ለክርስቶስ መሆኑ ገብቷቸው ተጽናንተዋል። ለዛሬ ወጣቶች እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን ዓላማ ልንነግራቸው ይገባል። ትዕግሥት የለሾችና በቶሎ ተስፋ የሚቆርጡ ናቸውና ፍቅር የተሞላን ሆነን ልንቀርባቸው ይገባል። በዕድሜ የቀደምን ሰዎች ለእነዚህ ግራና ቀኝ ቸውን ለማያውቁ ወጣቶች ዕዳ አለብን። ቤተ ክርስቲያን መማፀኛ ልትሆናቸው ትምህርት ቤቶችም የግብረ ገብ መማሪያቸው ሊሆኑአቸው ያስፈልጋል። ሕይወት የማይኖር የመሰለህ አንተ ወጣት ወደ ጎዳና ውጣና አረጋውያንን ተመልከት። ለዚህ የደረሱት በአንተ መንገድ አልፈው ነው። ሽበታቸው በአንድ ትልቅ ጦር ሜዳ ላይ አሸንፈው የተቀዳጁት ዘውድ መሆኑን ይመሰክራል። ሽበታቸው ራሱ ደካማነትህን ይነቅፈዋል። ከሁሉ በላይ መጽሐፍ ቅዱስህን ገልጠህ በእምነትና በጸሎት አንብበው። እርሱ የመንገድህ ካርታ /መሪህ/ ነው።

የፀሐይ ዕድሜ አጭር ነው። አንድ ቀን እንኳ አይሞላም። ከመሐልም ጭጋግና ደመና ይጋርዳታል። ነገር ግን ሃያ አራት ሰዓት እንኳ በማይሞላው የፀሐይ ዕድሜ ብዙ ስሜቶች ይፈራረቃሉ። ቢሆንም አጭር ነው። ሰውም በምድራዊ ኑሮው ብዙ ነገሮችን ቢያይም የዚህ ዓለም ቆይታው ግን በጣም ትንሽ ነውና መጨነቅ የለበትም። ሰባና ሰማንያ ዓመት ማለት ትንሽ ቆይታ ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ ሺህ ዓመት እንደ አንድ ቀን ነው ይላል (2ጴጥ.3÷8)። ሺህ ዓመት እንደ አንድ ቀን ከሆነ አምስት መቶ ዓመት እንደ 12 ሰዓት ነው። ሁለት መቶ ሃምሳ ዓመት ደግሞ እንደ 6 ሰዓት ነው። 125 ዓመት ደግሞ እንደ ሦስት ሰዓት ነው። 62 ዓመት ደግሞ እንደ አንድ ሰዓት ተኩል ነው ማለት ነው። ስለዚህ ሰማንያ ዓመት ብንኖር እንኳ በዚህ ዓለም ላይ የምናሳልፈው ዕድሜ በእግዚአብሔር አቆጣጠር ሁለት ሰዓት እንኳ የማይሞላ ነው። ይህ አንድ አውሮፕላን በአንድ አገር ላይ ነዳጅ ለመቅዳት አርፎ ለመነሣት የሚፈጅበት ሰዓት ነው። በጣም አጭር ነው። ሰው በዚህ ዓለም ላይ የሚያሳልፈው ዕድሜ ከዘላለም አንጻር ቢሰላ አንድ ቀን እንኳ አይሞላም። ከዘላለም አንጻር ቆይታችን ንሥር ሥጋ አይቶ

እስኪያነሣ ያለውን ጊዜ የሚያህል ቅጽበታዊ ነው። ስለዚህ በጣም መጨነቅና ማዘን አይገባንም።

የጽሞና ጊዜ

እግዚአብሔር አይተውህም፣ አይጥልህም። እንደማይተውህ ቃል ገብቶልሃል (ዕብ.13÷5፤ኢያ.1÷5)። እግዚአብሔር ቃል የገባልህ ተገዶ ሳይሆን በፈቃዱ ነውና ለመፈጸም አይፈተንም። ስለዚህ አሁን ለራስህ ንገረው፦ ጌታዬ አይጥልኝም፣ ፍጹም አይተወኝም። ደግመህ ለራስህ ንገረው። አሁን የገጠመህ ሰዎች ክዚህ በፊት የገጠማቸው ነው። አሁን የደረሰብህ ብዙ ትውልዶች ያለፉበት ነው። አዲስ ነገር የለም። አዲስ ነገር የገጠመህ መስሎህ አትደነቅ። ጉልበት የሚጨርስ መደነቅ ነው። በእግዚአብሔርና በሥራው ብቻ ተደነቅ። ደግሞም፦

- የሚሸከም አምላክ እንዳለህ፣
- ከቀትሩ በኋላ ሠርክ እንደሚመጣ፣
- ሕይወትህ በውበት ወጥታ በውበት እንድትጠልቅ፣
- ከምንም በላይ የሚያስፈልግህ እግዚአብሔር መሆኑን፣
- ዘመንህ አጭር ቢሆንም ዘላለማዊ ውሳኔ የምትወስንበት መሆኑን አስብ።

ጸሎት

ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ የዘመኔ ጌታ መሆንህን አምናለሁ። የሸረሪት ድር ተደግፌ ብዙ ጊዜ ተበጥሶብኛል። በራሴና በእውቀቴ መመካትም አልጠቀመኝም። ከሞት የማያድነውን እውቀት ጠልቼዋለሁ። ዛሬም ልትሠራኝ እንደቆምክ አይሃለሁ። አንተን መፍራት ስለተሳነኝ ኑሮና ሰዎች ያስፈሩኛል። ያረፍኩበትን ጊዜ አላውቀውም። አንዱ ጭንቀት ለአንደኛው መሬት ላይ ሳላርፍ ይሰጠኛል። ሰላም እንዲህና እንዲያ ሲሆን እንደማይገኝ ገብቶኛልና እንዲሁ አሳርፈኝ። መታገሥ እያቃተኝ ገበታ ስገለብጥ፣ የተሻገርኩበትን ድልድይ ስሰብር ኖሬአለሁና አሁንስ አሰልጥነኝ። ተስፋ መቊረጤን ሳልጨርሰው ቅደመኝ። በሚያስጠልለው ስምህ፣ በፈሰሰው ደምህ ለዘላለሙ አሜን።

ምዕራፍ ሦስት
ቊጥር አንድ

ቤተ ክርስቲያን ቊጥር አንድ ብላ የምትቆጥረው ንዋያተ ቅድሳቷን ነው። ሰው ብላ ብትቆጥር ኖሮ ብዙ ነፍሳት ባልጠፉ ነበር። ለመንግሥት ቊጥር አንድ ምናልባት የክፉ ቀን ደራሹ ሠራዊቱ ይሆናል። አንዲት አገር ቊጥር አንድ ብላ የምትጠራው እርሻ ወይም የነዳጅ ዘይት ይሆናል። በትዳር ውስጥ ቊጥር አንድ ገንዘብ ወይም ልጅ ይሆናል። ለሰዎች ብዙ አንደኛ ነገሮች አሏቸው። እጅግ ዋጋ የሚሰጡት ነገር ማለት ነው። በአያንዳንዳችን ሕይወት ቊጥር አንድ ብለን የምንጠራው ነገር አለ። ለአንዳንዶቻችን ገንዘብ ለሌሎች ክብር ሊሆን ይችላል። የመጀመሪያው ነገር የመጨረሻውን ይወስነዋል። የመጀመሪያ ቀን ግንኙነት ቀጣዩን ይቀርፀዋል። የመጀመሪያው ከተበላሸ ቀጣዩም ብላሽ ነው። ምንጩ ከደፈረሰ ወራጁም ድፍርስ ነው። የመጀመሪያ ልጅ ከተበላሸ ቀጥዮቹም እርሱን ይከተላሉ። ስለዚህ ቊጥር አንድ የምናደርገው ነገር ወሳኝ ነው።

ነገሮችን ሁሉ የምናየው ቊጥር አንድ ካደረግነው ነገር ተነሥተን ነው። ቊጥር አንድ ገንዘብ የሆነባቸው ሰዎች ማንኛ ውንም ግንኙነት የሚመዝኑት ከገንዘብ አንጻር ነው። ቋንቋቸው ሁሉ ገንዘብ ነው። ቊጥር አንድ ፖለቲካ የሆነባቸው ሰዎች የገዛ ትዳራቸውን ሳይቀር የሚመሩት በፖለቲካ አካሄድ ነው። ስለዚህ ሚስታቸውንና ልጆቻቸውን በግምገማ ያጣድፋሉ። ቊጥር አንድ አውቀት የሆነባቸው ሰዎች ለማኅበራዊ ትርፋቸው አይጨነቁም። ቊጥር አንድ ሥልጣን የሆነባቸው ሰዎች አንድ ሰውና አንድ ዛፍ አስኪቀር ይፋለማሉ። ያም አንዱ ሰው እነርሱ ናቸው። ቊጥር አንድ ዝና የሆነባቸው ሰዎች ዝናቸው አንዳይበላሽ እግዚአብሔርን በድብቅ ያመልካሉ። ቊጥር አንድ ያደረግነው እግዚአብሔርን ከሆነ ሁሉንም ነገር የምናየው ከእርሱ አንጻር ነው። ቊጥር አንድ የምናደርገው ነገር ቀጣዩን ተግባር ይወስነዋል።


አንድ ቊጥር መነሻ ነው። የቢሊዮን ቊጥሮች መነሻው አንድ ነው። አንድ ሳይባል ሁለት አይባልም። አንድ ቀዳሚ ነው። መቅደም የሚገባው ካልቀደመ መከተል የሚገባው አይከተልም። ከፈረሱ ጋሪው ክቀደመ ከመጓዝ መገፋፋት ይከስታል። አንድ ቊጥር መነሻ እንጂ መጨረሻ የለውም። የሚቆጥረው ግን ልኩ ጋ ሲደርስ ይቆማል። ፍላጎት አያልቅም። በቃኝ ስንል ግን እንጠግባለን። የዚህ ዓለም ንዋይ የጨው ውኃ እንደጠጡ ባገኙ

ቊጥር መልሶ ያስጠማል። በቃኝ የማይል ሰው ግን መጨረሻው አያምርም።

አንድ ቊጥር ከቊጥር መነሻነት ባሻገር ፊደልን ተክቶ ይሠራል። ስማይናወጥ አሳብ፣ ራእይና መሐላ አንድ የሚለው ቃል ያገለግላል። «ቃሌ አንድ ነው» ይባላል። ማታ የተናገረውን ጠዋት እንደሚሽር ሰካራም ተሰዋዋጭ ቃል መያዝ ክብርን ይነካል። እንደ ለከረ የሚኖር ስሜታዊ በቃሉ አይገኝም። የገዛ ቃሉ የማይዘውን ሰው ፖሊስ አይዘውም። ቃሉን ከማያከብር ሰው ጋር ሕግን ተማምኖ ጉዞ መጀመር ትርፉ ድካም ብቻ ነው።

አንድ ቊጥር ጽኑ ኅብረትን ይገልጻል። ባልና ሚስት አንድ ናቸው። ሁለት አካል መሆናቸው ይቀራል ማለት ሳይሆን በአሳብ አንድ ናቸው። ሁለት ልክ የሆነ ነገር ቢገጥማቸውም አንዱ ልክ ለእንደኛው ልክ እየተሸነፈ በፍቅር ይኖራሉ። አንድ የሚለው ቃል የግለሰቦችንና የአገሮችን ኅብረት ይገልጻል። የጋራ ቃል ኪዳን ያላቸው ሰዎች አንድ ናቸው ይባላል። ቢሆንም አንድነት የሚባለው ሌሎችን ስመጥቀም መስማማት ነው። ሌላውን ስመጉዳት የሆነ ስምምነት አድመኝነት ይባላል። ከዚህ ሁሉ በላይ እግዚአብሔር አንድ ነው። የማንኛውም አይሁዳዊ ዕለታዊ መፈክር «*እስራኤል ሆይ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው*» (ዘዳ.6÷4) የሚል ነው። ክርስቲያንም «በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድ አምላክ አሜን» በማለት የእግዚአብሔርን ኅብረት ይገልጻል። እስላሙም አላህ አንድ ነው ብሎ ይገድላል። ሃይማኖት ግን አስፈላጊ ከሆነ ሙቱ ትላሰች እንጂ ግደሉ አትልም።

አንድ ሁልጊዜ ከፊት ነው። አንድ ቊጥር አዝማች ነው። ቀጥሎ ያለውን ቊጥር ተመልከቱ:- 0000001 ይህ ቊጥር ጥቅም የማይሰጥ ቊጥር ነው። ለምን? ስንል አንድ ቊጥር ያለው መጨረሻ ላይ በመሆኑ ነው። አንድ ቊጥር መጀመሪያ ላይ ቢሆን ኖሮ ግን ዐሥር ሺህ፣ መቶ ሺህ፣ አንድ ሚሊየን መሆን በቻለ ነበር። ነገር ግን አንድ ቊጥር መጨረሻ ላይ በመሆኑ ዜሮዎቹ ጥቅም የማይሰጡ ሆኑ። እስቲ እያንዳንዱ ዜሮዎች ውስጥ ዓለም ትልቅ ግምት የምትሰጣቸውን ነገሮች እንሙላባቸው።



አንዱ ግን እግዚአብሔር ነው። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ቢኖሩንና እግዚአብሔር ግን መጨረሻ ላይ ከሆነ ጥቅም የለውም። የሚጠቅሙ ነገሮች ሁሉ የሚጠቅሙት እግዚአብሔር ሲቀድም ብቻ ነው። እግዚአብሔር ካልቀደመ እውቀቱ ብስጭት ነው። «ለሚ ነው እንጂ ተቸጋሪ፣ ደንቆሮ መልካም ነዋሪ» እንዲሉ። እግዚአብሔር ካልቀደመ ሀብቱ ፍርሃት ነው። «ሰው የሚፈራው ሀብት ካለው ነው» እንደሚባለው። እግዚአብሔር ካልቀደመ ሥልጣኑ የሞት መንገድ ነው። «ጭስ የማይታይበት ቃጠሎ ይሏችኋል የዚህ ዓለም ሥልጣን ነው» በማለት ናፖልዮን እንደ ተናገረ። እግዚአብሔር ካልቀደመ ዝናው እድካሚ ነው። እነልዕልት ዲያናን የገደለ የዝና ማሳደድ ነው። እግዚአብሔር ካልቀደመ ትዳሩ የጉያ እሳት ነው። ብዙ ትዳር ሆድ እንጂ ጎሊና የሚሞላበት አይደለም። እግዚአብሔር ካልቀደመ ልጅ አሳዛኝ ነው። እንደምንፈልገው ሳይሆን እንደሚፈልገው ነው።

በሕይወታችን እግዚአብሔር ቀዳሚውን ሥፍራ መያዝ አለበት። የሕይወታችን ካፒቴን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ጉዞአችን ወደብ ይኖረዋል። በትዳራችን ቅድሚያ ለሴቶች ሳይሆን ለእግዚአብሔር፣ በሥልጣናችን ቅድሚያ ለሕዝብ ሳይሆን ለክርስቶስ ሲሆን ሰላም ይበዛል። አንድ እግዚአብሔር ካልቀደመ የሚጠቅሙት ነገሮች እንኳ አይጠቅሙም። ቢሆንም እግዚአብሔር ጨዋ ነውና ባስቀመጥነው ሥፍራ ብቻ ይቀመጣል። ካስቀመጥነው ስፍራ ውጭ አይቀመጥም። ዋስትናም አይሰጥም። በፈረንጅ አገር እንዲት ሴት እናቷ ጋ እየተጫወተች ባሏን ትጠብቅ ነበር። ባለቤቷ ከጓደኞቹ ጋር ሊመጣ ግን በጣም ሰክሮ ስለነበር እናትዬዋ በጉዞአቸው ደስ አላላትም። ያች ሴትም መኪና ውስጥ ስትገባ የባሏ ጓደኞች በሁካታ ስስተቀበሏት ደስ አላት። እናቲቱ ግን «ብቻ ደስ አላለኝም፣ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን» አለች። ልጂቱ ግን «እግዚአብሔር የቱ ጋ ይሆናል፣ ቦታው ሞልቷል፣ ከፊሰገ ከኋላ ከዕቃዎቹ ጋር ይቀመጥ» አለች። በመኪና ውስጥ የነበሩት ሁሉ ሳቁ። እናቲቱ ግን ተጨንቃ «ብቻ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን» አለች። እነርሱም መኪናውን አሥነስተው ጥቂት እልፍ እንዳሉ በክባድ አደጋ መኪናውና ሰዎቹ እንዳልነበሩ ሆኑ። ነገር ግን ከኋላ የተጫነው ዕቃ ውስጥ አንድ እንቁላል እንኳ አልተሰበረም ነበር። እግዚአብሔር ባስቀመጡት ቦታ ተቀመጠ፣ ስለዚህ እንቁላል እንኳ አልተሰበረም። እኛስ የት ይሆን ያስቀመጥነው?

አንድ የሚለው ቃል ምትክ የለሽነትን ይገልፃል። የአንድያ ልጅ ሀዘን መራራ ነው (ዘካ.12÷10)። የአገራችን ሰው «በአንድ ዓይን አይለቀስም» ይላል። ካለቀሱ እርሱም ይጠፋና የጨለማ

ምርኮኛ መሆን ይመጣል። እግዚአብሔርም በሕይወታችን ሁለተኛ የሌለው እንደኛ፣ ልዋጭ የሌለው ብቸኛ መሆን አለበት። ሁሉንም ነገር ከእግዚአብሔር አንባር መገምገም አለብን። እርሱ ባልወጣበት እንዳንወጣ መጠንቀቅ አለብን። እርሱን ካገኘን ሁሉን አገኘን፣ እርሱን ካጣን ግን ሁሉን አጣን። ዋናውን የከለረ ነጋዴ ለማኝ እንደሚሆን እግዚአብሔርን የጣለም የተጣለ ነው። ሌሎች ነገሮችን ብንከስር በእግዚአብሔር ይካሳል። እግዚአብሔርን ከከሰርን ግን መካሻ በሌለው ጥፋት ውስጥ እንወድቃለን። የሕይወታችን እንዱ ዓለም እግዚአብሔር ነው። ምንምኑ አለኝ ከማለት እግዚአብሔር አለኝ ማለት ይበልጣል። እግዚአብሔር አለኝ ያሉ ብቻ አላፈሩም።

አንድ ምሁር በባሕር ላይ ለመዝናናት ጀልባ ተከራይቶ መጓዝ ይጀምራል። ወደ ለማይ አቅንቶ ከዋከብትን ካየ በኋላ ቀዛፊውን «ሥነ ከዋከብት ተምረሃል?» ይለዋል። ቀዛፊውም እንኳን ለትምህርቱ ለለያሜውም እንግዳ ሆኖ «አልተማርኩም ጌታዬ» ብሎ ይመልሳል። «ይህን ካልተማርክ የሕይወትህን ሩብ እንዳጣህ ቁጠረው» ይለዋል። ጥቂትም እልፍ እንዳሉ በባሕሩ ላይ ያሉትን እጽዋት እያየ «አንተ ልጅ ስለ ሥነ እጽዋት ተምረሃል?» አለው። ልጁም ከቀዘፋ ተግባሩ መለስ ብሎ «የለም ጌታዬ አልተማርኩም» አለ። «ይህን ካልተማርክ ሌላ ሩብ ያህሉን ከሕይወትህ አጥተሃል» አለው። ቀዛፊውም ግማሽ ሕይወቱ በምሁራዊ አስተሳሰብ ተቀንሶበት ጉዞውን ቀጠለ። በባሕር ውስጥ ያለው ጉማሬ ግን አላሳልፍ ብሎ ታንኳይቱን ውኃ እየሞላት ሲመጣ መስጠም ጀመሩ። ያ ምሁርም ውኃ በአፉ እየሞላ ሲተፋ ቀዛፊው ልጅ ዞር ብሎ አይቶ «ጌታዬ ውኃ ዋና ይችላሉ?» ብሎ ጠየቀው። ምሁሩም «አልችልም» አለ። «እንግዲያው እርስዎ ሙሉ ሕይወትዎትን አጥተዋል» ብሎ እየዋኘ ሄደ። ምሁሩም ለጥሞ ቀረ።

ብዙ እውቀን እውቀታችን ግን ከዘላለም ሞት የማያድን ከሆነና አብሮን በመቃብር የሚቀር እውቀት ከሆነ ትርፍ የሌለው እውቀት ነው። ሁሉን ይዘን እግዚአብሔርን ከጣልን፣ በነፍሳችን መግቢያ ከሌለን ሙሉ ሕይወታችንን አጥተናል ማለት ነው። እግዚአብሔርን የማያሳውቅና ከሞት የማያድን እውቀት ከንቱ ነው። መጽሐፍ *«ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?»* (ማቴ.16÷26) ይላል።

የጽሞና ጊዜ

በሕይወትህ ቍጥር አንድ ያደረግኸው ነገር ደስታህን ይወስነዋል። በዚህ ዓለም ላይ አለኝ የሚሉት ነገር ሁሉ ሲደርሱበት የሚርቅ፣ በአሞሌ ጨው እንደተታለለ በሬ በመላስ ወደ ሞት የሚያሯሩጥ ነው። አለኝ የሚሉት ሁሉ ጉም ለፍሮ እንደ መፎከር ነው። አለኝ የሚሉት ሁሉ ሊያሳፍር ይችኩላል። በብዙ ነገር ያፈርህ ወዳጄ አለኝ ብለኸው ያላፈርከው በእግዚአብሔር ነውና አሁንም እግዚአብሔር ብቻ አለኝ በል። ደግሞም፦

- ቍጥር አንድ ያደረግኸው ማንንና ምንን ይሆን?
- በሕይወትህ ከፈረሱ ጋሪው እንዳይቀድምብህ አስብ።
- ልክን ማወቅ ወይም ይበቃኛል ማለት ሲጨነቁ ከማደር እንደሚያሳርፍ አስብ።
- እግዚአብሔርን ቍጥር አንድ ብቻ ሳይሆን ብቸኛ አድርገው።

ጸሎት

የማለፍ ሥርዓት የማይደርስብህ ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ። ስንት ጌታ አይቻለሁ። ራሴም ለራሴ ጌታ ሆኜ አውቃለሁ። እንዳንተ ያለ ትክክለኛ ጌታ አላየሁምና በጽድቅ ግዛኝ። በዓይኔ ፊት ትልቅ የሆነውና የሮጥኩለት ነገር ሁሉ እርካታው አንሶብኛል። እንደ ትንሽ ያየሁትና ትንሽ ጊዜ የሰጠኹት ቃልህ ግን ብዙ አርከቶኛልና የመንፈስ ምግብ ያለህ ጌታዬ ሆይ ተመስገን እልሃለሁ። ከሁሉ በፊት አንተን እንዳስቀድምህ፣ ከስህተት መማር እንዲበቃኝ፣ ሕይወቴን በፍልስፍና ሳይሆን በመለኮታዊ ምሪት እንድመራት እርዳኝ። ለብዙ ነገር ሮጫለሁ። ለኃጢአትና ለውርደትም ሮጫለሁ። አሁን ግን ዘመኔ ለቤትህ ይሁንልኝ። የዘመኔ ባለቤት አንተ ነህና ለዘላለሙ አሜን።

ምዕራፍ አራት
የሚበልጠውን ይዘናል

ዲዮጋን የተባለ የግሪክ ፈላስፋ ኑሮው ጎርፍ በሸረሸረው ፈፋ ውስጥ ነበር። ንብረቱም አንዲት መንቀል /የውኃ መጠጫ ቅል/ ስትሆን አንዲት ውሻም ጓደኛው ነበረች። ታላቁ እስክንድር ዓለምን አስገብሮ ሲመለስ ዲዮጋን የተባለውን ፈላስፋ ማየት አለብህ ስላሉት ሊያየው መጣ። ዲዮጋን ግን ከቤቱ አጠገብ በጀርባው ተኝቶ ፀሐይ ይሞቅ ነበር። ታላቁ እስክንድርም አጠገቡ መጥቶ ቢቆም ማን ነው? ብሎ እንኳ ዲዮጋን ዓይኑን አልገለጠም። እስክንድርም «ዲዮጋን ሆይ ተነሥ እኔ ታላቁ እስክንድር ነኝ። ዓለምን አስገብሬ ተመልሻለሁ፣ የምትሻውን ለምነኝ የመንግሥቴንም አኩሌታ ቢሆን አለጥሃለሁ» አለው። ዲዮጋን ግን ዓይኑን እንደ ከደነ «ይልቁንስ አንተ ልትሰጥ የማትችለውን ፀሐይ አትከልክለኝ» አለው ይባላል። ንጉሥ እንኳ የማይሰጠውን ብዙ ስጦታ ስለተቀበልን እግዚአብሔር ይመስገን!

ሰውዬው «እግር የሌለው አስካይ ድረስ ጫማ የለኝም ብዬ አዝን ነበር» ብሏል። መለስ ብሎ ራሱን ሲመለከት የሚበልጥ ነገር አገኘ። ጫማን ገንዘብ ይገዛዋል፣ እግሩን ግን በገንዘብ አይገዛውም። ጫማም ያማረው እግር ስላለው ነው። ለማማረርም የበቃነው በሕይወት ስላለን ነው። ለማማረር እንኳ ዕድሜ ስላገኘን ልናመሰግን ይገባናል። በሣጥናቸው ብዙ ልብስ አጭቀው ከአልጋዬ ተነሥቼ አንድ ቀን እንኳ በለበስኩት እያሉ የሞቱ ሰዎችን አውቃለሁ። የሚበላው እያለው የሚሞት፣ የሚበላው አጥቶ የሚኖር ብዙ ሰው አለ። ባለጠጎች በገንዘባቸው ለአንድ ቀን ዕድሜአቸውን ማስረዘም አይችሉም። እናት ለምትወደው ልጇ ቀንሳ የማትሰጠው ዕድሜ ስላለንና ሰው የማይሰጠውን ስለተቀበልን እግዚአብሔርን ልናመሰግነው ይገባናል።

በዓለም ላይ የሚገኘው ሀብትና ንብረት በሙሉ የእናንተ ይሆናል። ነገር ግን ሁለት ዓይናችሁን መስጠት አለባችሁ ብትባሉ እሺ ትላላችሁ? አምናለሁ በፍጹም እሺ አትሉም። ግን እኮ የተጠየቃችሁት ሁለት ዓይናችሁን ብቻ ነው። ጆሮአችሁ፣ አንደበታችሁ፣ ልባችሁ፣ እጆቻችሁ፣ እግሮቻችሁ ... አሉ። አሁንም መልሳችሁ «እየዳሰስኩ የእኔ የምለውን ንብረት አልፈልግም» የሚል ነው። ታዲያ በዓለም ላይ ያለው ሀብትና ንብረት በሙሉ ለሁለት ዓይናችሁ እንኳ ዋጋ መሆን ካልቻለ እናንተ ሚሊየነር ሳይሆን ቢሊየነር ኧረ ከዚያም በላይ ናችሁ። ታዲያ ደሃ ነኝ አያላችሁ

ስለምን ትተክዛላችሁ? እግዚአብሔር በዚህ በለውነታችሁ ላይ በዋጋ የማይተመን ውድ ንብረት አፍስሷል።

ሁላችንም እኩል ማልቀሳችን፣ ከእኛ ያነሱትን ሰዎች ማየትና መርዳት አለመቻላችን እግዚአብሔርን ያሳዝነዋል። አዎ ያለንን በትክክል ካላወቅን የጎደለንን በትክክል ማወቅ አይቻለንም። ትልቁ ችግራችን መርሳት ነው። መነጽር አድርገን መነጽር እንፈልጋለን፣ ቁልፍ በእጃችን ይዘን ቁልፉን አምጡ እያልን እንጣላለን። በዕለታዊ ኑሮአችን ያለን ልበ ቢስነት በሕይወት ውስጥ የተጎናፀፍነውንም በጎ በረከት አስረስቶናል። ብዙ የተቀበልን፣ ክብዙ መከራ ወጥተን ለዚህ የደረስን ሰዎች ነን። ግን ስለምንረሳ እንብሳጫለን።

ክፉ ጌትነት የሚበልጠውን ሰጥቶ በትንሹ ይነፍጋል። ክፉ ተቀባይ የሚበልጠውን ተቀብሎ በትንሹ ያማርራል። እግዚአብሔር መልካም ተቀባይ አጥቷል። በሕይወት ላይ ጽንፈኝነት አይጠቅምም። ሚዛናዊነት ያስፈልጋል። ስለዚህ ያለኝ ይህ ነው፣ የጎደለኝ ያ ነው ማለት ያስፈልጋል። በትክክል ካየን ከጎደለን ያለን ይበልጣል።

የምንተነፍሰውን አየር መዋዕለ ንዋያቸውን ያፈሰሱበት ባለጠጎች ቢሆኑ ኖሮ በጉሮሯችን ላይ ቆጣሪ ተክለው ብንክፍል እንኳ እዘጋዋለሁ የሚሰው ማስፈራሪያቸው በገደለን ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ከሕይወት ጋር የተያያዙትን ነገሮች በራሱ እጅ አድርጎታል። ምክንያቱም ለሕይወት የሚጠነቀቅ እርሱ ብቻ ነውና። ደግሞም ውድ ነገሮችን ሁሉ በነጻ ሰጥቶናል። ፀሐይን፣ አየርን፣ ትዳርን፣ ልጅን በነጻ ሰጥቶናል። የሚበልጠውን ይዘናል። ጥቃቅን ጉድለቶች ቢኖሩም ክያዝነው አይበልጡም። የአገራችን ሰው የጤና ቀለቡ ትንሽ ነው፣ የሰላም ቀለቡ ትንሽ ነው ይላል። ጤናንና ሰላምን ግን ማንም አያመሰግንበትም። ግለሰቦችና አገራት የጦርነት ወጪያቸው ምን ያህል እንደሆነ ያውቁታል። ስለ ሰላም ግን አያመሰግኑም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *«ስለዚህ እላችኋለሁ፦ ስለ ነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት፦ ወይም ስለ ሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ አይበልጥምን?»* (ማቴ.6፦25) ብሏል።

እግዚአብሔር ካልሆነ በቀር አትጨነቁ የሚል ማንም የለም። ነገሥታቱ እንኳ ሳይበዛ እንድንጨነቅ በጣቢያቸው

ያዙልናል። «ሁሉም ሰው ራሱንና አካባቢውን በንቃት ይጠብቅ» ይላሉ። አትጨነቁ የሚለው በሰላም አገር የሚኖረው ንጉሠ ሰላም ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልክ ደውለው «ያን ጉዳይህን ለእኔ ተውልኝ፣ አትጨነቅ» ቢሉን ባይፈጽሙት እንኳ የእኛ ጉዳይ አጀንዳቸው በመሆኑ በደስታ አንዘልም? እንደውም ኧረ ብለን እንተኛለን። አትጨነቁ ያሉን ግን የሰማይ የምድር ንጉሥ የሆነውና በቃሉ ሐሰት፣ በተስፋው እብለት የሌለበት እግዚአብሔር ነው። ይህን አምላክ የንጉሥ ያህል እንኳ እንመነው። አንድ ሰው «እግዚአብሔርን የመሬት ያህል ቅንኳ እንመነው» ብሏል። መሬትን ስንረግጣት ትደረመሰለች የሚል ስጋት የለብንም። ስለዚህ ከመራመድ አልፈን እንሮጥባታለን። እግዚአብሔር ታምኖ የማይከዳ፣ ወዶ የማይጠላ ሆኖ ሳለ እኛ ግን የመሬት ያህል እንኳ አምነንበት ይሆን? እግዚአብሔርን የምናገኘው በእውቀታችን ልክ ሳይሆን በእምነታችን ልክ ነው።

ብዙዎች ይጨነቃሉ። ዓለም በቃኝ ያሉ መነኮሳት ሳይቀር ከወለዱት እኩል በፍርሃት ይናጣሉ። የቪዛ ወሬ የብዙ አገልጋዮችን አፍ ሞልቶታል። ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ እጆቻቸውን ወደ እግዚአብሔር ሳይሆን ወደ አሜሪካ ዘርግተዋል። መነኮሳቱ እንኳ የሚመኩበትን ገዳም ትተው አሜሪካ ገዳማቸው ሆኗል። አሜሪካ ግን ከእንድ ሰው ጋር ተጣልታ የምትባረር አገር በመሆኗ ዋስትና ልትሰጥ አትችልም። በአሜሪካ ምድር ከአራት ሰው አንድ ሰው በመንፈስ ጭንቀት በሽታ የተያዘና መድኃኒት ተጠቃሚ ነው። ስለዚህ የምንሸሸባቸው ራሳቸው የሚበላ እንጂ የሚያረካ ነገር የሌላቸው ለምች ናቸው።

ብላቴን ጌታ ጎሩይ ለልጅ ምክር ለአባት መታሰቢያ በተባለው መጽሐፋቸው «ልጄ ሆይ አሳብ አታብዛ ወደ ፊትም ምን ነገር ይመጣ ይሆን ብለህ አትጨነቅ፤ ምንም አሳብና ጭንቀት ብታበዛ የሚሆን ነገር ሳይሆን አይቀርም። ... ልጄ ሆይ፣ ጌታ ለመሆን ትፈልግ እንደ ሆነ ጌትነት ማለት ያለ አሳብና ያለ ጭንቀት መኖር ነው። አሳብህም ሁሉ ከሞትህ በኋላ በወዲያኛው ዓለም ስለሚሆነው ስለነፍስህ ነገር ይሁን እንጂ፣ በዚህ ዓለም በሥጋህ ስለሚሆነው ነገር እጅግ አትጨነቅ» ብለዋል።

በለው ልጅ ኑሮ ውስጥ መሠረታዊ ፍላጎት ተብለው የሚጠሩ ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ናቸው። እነዚህን የሚያሟላ ንጉሥ እግዚአብሔር ነው። ስንጸልይ «የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን» እንላለን። እንጀራ የሚበቅለው ከምድር ሲሆን የምንለምነው ግን ከሰማይ ነው። እግዚአብሔር የበረከት ምንጭ ነውና።

የምንሠራበት መሥሪያ ቤት ደሞዝን እንጂ እንጀራን አይሰጠንም። እንጀራ የተሰናዳ በረከት ሲሆን የምናገኘውም ከጓዳችን ነው። እግዚአብሔር ጓዳችን ነውና እንጀራን ስጠን እንለዋለን። እነዚህን መሠረታዊ ፍላጎቶች የብዙ ሰው ጭንቀት ናቸው። እንድ አባት «መንፈሳዊ ሰው ማለት ምን እበላለሁ? ምን እጠጣለሁ? ምን እለብሳለሁ? ብሎ የማይጨነቅ ነው» ብለዋል።

ስለ ነፍሳችን በምንበላው ስለ ሰውነታችን በምንለብሰው እንዳንጨነቅ ያዘዘን ለምንድነው? ስንል ምክንያቱን ጠቅሷል «ነፍስ ከመብል፣ ሰውነትም ከልብስ አይበልጥምን?» ብሏል። «የቱ ነው የሚከብደው ለነፍስ እንጀራ መስጠት ወይስ ነፍስን ካለመኖር ወደ መኖር ማምጣት? የቱ ነው የሚከብደው ለሥጋ ልብስ መስጠት ወይስ ሥጋን ከአፈር ማነጽ?» ማለቱ ነው። የሚበልጠው ነፍስን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ መፍጠር፣ ሥጋንም ከአፈር ማነጽ ነው። የሚበልጠውን መያዝ ለትንሹ ዋስትና ነው። የሚበልጠውን ይዘን ለትንሹ መጨነቅ አይገባም። ወርቅ የሰጠ ነሐስ ይከለክላል ተብሎ እንደማይገመት እንዲሁም ነፍስንና ሥጋን ፈጥሮ መብልና ልብስ ይነሣል ተብሎ አይጠረጠርም። ሆድን ፈጥኖ እንጀራ፣ ራቁት ፈጥሮ ልብስን፣ ኑሮን ሰጥቶ መኖሪያውን አይከለክልም። በእውነት የምንጨነቀውም ትንሽ ስላለን ነው። ምንም የሌለውማ አይጨነቅም። የምናለቅሰውም ትንሽ ዕንባ ማበሻ መሐረብ ስላለን ነው። የልቅሶን ድንበር የጨረሰማ ሳቅ ነው የሚጀምረው። በጎዳና ላይ ተኝተው የሚያንኮራፉትን ስናይ እኛ በጥሩ ፍራሽ ላይ ለምን እንቅልፍ እምቢ እንዳለን ይገባናል። የምንጨነቀው ያለን ነገር ስላለን ነው። ምንም የሌለው አይጨነቅም። የሚርበው የበላ ነው፤ የበላ አምጣ አምጣ ይለዋል።

የመጀመሪያውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጠል ስንገልጥ በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ ሃያ ስድስት ቊጥሮች እንደተጓዝን የምናገኘው ቃል አለ። ይህ ቃል የሰውን ክብር ከሚገልጡ ቃሎች የመጀመሪያውም የዳርቻውም ነው። ሰውን በሚመለከት የመጀመሪያው መለኮታዊ ቃለ ጉባዔ ሲሆን ይችላል። *«እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር!»* (ዘፍ.1÷26)። ሰውን በሚመለከት የመጀመሪያው የሥላሴ ምክር ነው። ሰው በስህተት ወይም በአጋጣሚ የተፈጠረ ሳይሆን መለኮታዊ አጀንዳ የተያዘበት ፍጡር ነው። እያንዳንዳችን የራሳችንና የወላጆቻችን ዕቅድ ሳንሆን የእግዚአብሔር ዕቅድ ነን። «ሕገ ወጥ ወላጆች ሊኖሩ ቢችሉ እንኳ ሕገ ወጥ ልጆች ግን የሉም።» እስቲ እኔ አጋጣሚ አይደለሁም÷ እኔ የእግዚአብሔር

ዕቅድ ውጤት ነኝ÷ መነሻዬ እግዚአብሔር ነው» ብለን ለራሳችን እንናገር።

የሰው ልጅ የተፈጠረው ለእግዚአብሔር የመፈጠርን ጥያቄ አቅርቦ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ፈቃዱ የእግዚአብሔር በሆነበት ምሥጢር ነው። ሰው በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥሯል። ስለዚህ እግዚአብሔር እኛን ሳይሆን እኛ እግዚአብሔርን እንመስላለን። እኛን የሚመስል አምላክ እኛ የምንፈጥረው ጣኦት ነው። እውነተኛ አምላክ ግን እንድንመስለው የፈጠረን ነው።

የሥነ ፍጥረትን ትምህርት ስንመረምር ሁሉም ነገር ለሰው ተፈጥሯል። በሰማይና በምድር ውስጥ የሚገኙት ነገሮች ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለሰው ጥቅም ተፈጥረዋል። ቍሳቍስ ለእኛ፣ እኛ ለእግዚአብሔር ተፈጥረናል። ቍሳቀስ ለእኛ እንጂ እኛ ለቍሳቍስ አልተፈጠርንም። ዛሬ ግን ሎሌው ጌታ ሆኖ ሰውን ይገዛዋል። ወርቁ በሥላሴ አርአያ በተፈጠረው አካል ላይ በማረፉ ሲኮራ ሲገባው ሰው በወርቅ ይኮራል። በሉቅ ውስጥ የተቀመጡት ዕቃዎች ዋጋቸውን ያውቃሉ። እኔ ይህን ያህል አወጣለው ይላሉ። ሰው ግን ዋጋውን አያውቅም። የሰው ዋጋው እግዚአብሔር ነው። ይህ ዋጋ ደግሞ በየትኛውም ቦታና ዘመን አይዋዥቅም።

እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ ከፈጠረ በኋላ በመጨረሻው ቀን ሰውን ፈጠረው። ሰው ከመፈጠሩ አስቀድሞ ለሰው የሚያስፈልጉ ነገሮች ተፈጥረዋል። ዛሬ የሰው ልጅ የሚጨነቀው ከእርሱ በፊት ለተፈጠሩት ነገሮች ነው። እያንዳንዱ ፍጡር ከነፀጋቱ ወደዚህ ዓለም መጥቷል። እግዚአብሔር ሰውን ወደዚህ ዓለም ሲያመጣው ስፖንሰር (ወኪል) የሆነው ራሱ ነው። ታዲያ ስፖንሰር ያለው አይጨነቅምና ሰው መጨነቅ የለበትም። በየአገራቱ ያለው የስፖንሰር ሕግ ወደዚያ አገር ያመጡትን ሰው የማኖር አቅማቸውን ይለካል። አቅም ከሌላቸው ስፖንሰር መሆን አይችሉም። ያለ መንግሥት ድጋፍ ምን ያህል ጊዜ እንግዳውን ማኖር እንደሚችል ይጠናል። እግዚአብሔር ከዚህ በተሻለ መለኪያ ያለ ማንም ብቻውን በቂና ከበቂ በላይ ሆኖ ሊያኖረን ፈጥሮናል።

መልካም ወላጅ ልጁ ከመወለዱ በፊት ለልጁ የሚያስፈልጉ ነገሮችን እንደሚያዘጋጅ፣ አሳድጎ ርስት ሰጥቶ፣ የጨዋ ልጅ ድሮ ጎጆ እንደሚያወጣው እግዚአብሔርም ለሰው ልጅ መኖሪያውን ዓለም፣ የፍላጎቱን ግብ፣ አጽናኝ ጓደኛ ሰጥቶ ፈጥሮታል። ከዚህ ባሻገር እግዚአብሔር ማንንም ሰው ያለ ወዳጅ አልተወውም። ከፉ

ቢሆን እንኳ የሚወዱትን ሰዎች አዘጋጅቶለታል። ይህም የእግዚአብሔር በጎ ስጦታ ነው።

የሚበልጠውን ይዘናል? ከበረከት ሁሉ የሚበልጠው በረከት የዕድሜ በረከት ነው። ብዙ ጊዜ የምንኖረው መኖር መብታችን ስለሆነ ይመስለናል። መኖር ግን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ወላጆቻችን ረጅም ዘመን ስለኖሩ እኛም እንደ እነርሱ ረጅም ዘመን ኖረን የምናልፍ ይመስለናል። መኖር የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑ የሚገባን ግን መኖርን የሚቋቋሙ ነገሮች ሲገጥሙን ነው። ስንታመም፣ በምርኮ ውስጥ ስንሆን እያንዳንዱን ቀን ዋጋ እንለጠዋለን። እኛ ግን ለመኖር እርግጠኞች ሆነን ለመኖሪያው እንጨነቃለን። እስቲ መጀመሪያ ስለ መኖራችን እናመስግን። ከእኛ የተሻሉ ቆንጆዎች፣ ከእኛ የተሻሉ አዋቂዎች፣ ከእኛ የተሻሉ ኃያላን አልፈዋል። እኛ የቀረነው በብልጠታችን ሳይሆን የእግዚአብሔር ምሕረት ስለበዛልን ነው።

የሚበልጠው አለን ማንም በደግነት ለማንም የማይሰጠው የዘላለም ሕይወት አለን። የልጅነት ጸጋ አለን። መንፈሳዊ ፍቅር፣ የእግዚአብሔር ቤተሰብ የምትሆን መንፈሳዊ ጎብረት አለን። የመረጃ እጥረት ያለብን እንጂ ብዙ ያጣን ሰዎች አይደለንም። ስለ ኑሮ መባነን ከበዛብን ግን የጤናችን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ዶክተር ኢሳይያስን ልክ ከምዕራፍ 49÷14-16 ፍቱን መድኃኒት አዞልናል፦

«ጽዮን ግን÷ እግዚአብሔር ትቶኖል ጌታም ረስቶኖል አለች። በውኑ ሴት ከማኅፀንዋ ለተወለደው ልጅ እስከማትራራ ድረስ ሕፃንዋን ትረሳ ዘንድ ትችላለችን? አዎን÷ እርስዋ ትረሳ ይሆናል÷ እኔ ግን አልረሳሽም። እነሆ÷ እኔ በእጆ መዳፍ ቀርጬሻለሁ÷ ቅጥሮችሽም ሁልጊዜ በፊቴ አሉ።»

<u>የጽሞና ጊዜ</u>

ያለህን በትክክል ካላወቅህ የጎደለህን በትክክል ማወቅ አትችልም። ስለጎደለህ ስታለቅስ አሁን አለኝ የምትለውም ያንተ አለመሆኑን አስብ። ስለጎደለህ ከማዘንህ በፊት ስላለህ ነገር አመስግን። «ውለታው ብዙ የእግዚአብሔር፣ አመስጋኝማ ቢኖር» እንደተባለ ይህች ሰዓት እንኳ የእርሱ ውለታ መሆኗን ተገንዘብ። ከሁሉ በላይ የሚበልጠውን ተቀብለሃል። ስለዚህ፦

- ገንዘብ የማይገዛው ተፈጥሮ እንደተቀበልህ፣

- ውድ ነገሮች በነፃ እንደ ተሰጡህ፣
- እግዚአብሔርን የመሬት ያህል እንኳ ልታምነው እንዳልቻልህ አስብ።

ጸሎት

ያለ መያዣ የወደድኸኝ፣ ለምጻም ሳለሁ ያፈቀርከኝ፣ ሙት ሳለሁ ያልረሳኸኝ ሠሪዬም ሰሚዬም እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ። ዓለም ለዲዮጋን እንዳሰፈች ለእስክንድርም አልፋለችና አሳላፊው ጌታዬ አመሰግንሃለሁ። ያኖረኝ እጅህ እንጂ መልፋት መፍጨርጨሬ አይደለም። ሁሉ ባንተ ዘንድ ከተወሰነ መጨነቄ ከንቱ ነውና እርቅልኝ። ስለጎደለኝ ነገር አንተን ከሰይጣን ጋር ከማማህ፣ ስላለኝ ነገር ከመላእክት ጋር እንዳመሰግንህ አርዳኝ። እንዳትረሳኝ በእጆችህ መዳፍ ስለቀረጽከኝ አመሰግንሃለሁ። ያመኑህን በመንገድ ጥለህ አትገባምና ለዘላለሙ አሜን!

ምዕራፍ አምስት
እርካታ ማጣት

ራሳችን የሺህ ለው ያህል ያሳስበናል። እንኳን በሰባና በሰማንያ ዕድሜ ሚሊዮን ዓመት ብንኖር ስለ ራሳችን እስበን የምንጠግብ አይመስልም። የተፈጠርነው ስለ ሌሎች እንድናስብ ነውና ስለ ራስ ማሰብ ያደክማል። ደግሞም ለራስ ዋስ መሆን አይቻልም። ስለዚህ ለራሳችን ራሳችን ዋስትና መስጠት አይቻለንም። በዚህ ዓለምና በሚመጣው ዓለም ዋላችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዕብ.7÷22)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደ ያዕቆብ ለራስ በማሰብ የደከመና ብዙ አቋራጭ መንገድን የተጠቀመ ለው አናገኝም። ያዕቆብ ግን አቋራጩ ሩቅ ሆኖበት፣ ቍሳዊ ትርፍ እርካታ ቢስ አድርጎት እንደ ነበር እናነባለን። ያዕቆብ ገና በእናቱ ማኅፀን ሳለ ከወንድሙ ከኤሳው ጋር የሚገፋፋ ነበር፣ በተወሰደ ጊዜም ወንድሙ ስለ ቀደመው ተረከዙን ይዞ ወጣ። ይህ መገፋፋትና ተረከዝን መያዝ ገና በጠዋቱ የጀመረው ባሕርይ ነበር።

ዓለማችን መገፋፋትና መጠላለፍ የበዛበት ዓለም ነው። ሕጻን ልጅ በእጹ ባለው ከመደሰት በሰው እጅ ባለው እንደሚያለቅስ እንዲሁም ሁሉን ለእኔ በሚል አመል ራሳቸውን የሚያውኩ ጥቂት አይደሉም። የሌላውን ነገር መመኘት ስንጀምር መገፋፋት ይከሰታል። ሁላችንም እኩል እንውደቅ ካላልን በቀር የሌላው የእኛ ሊሆን አይችልም። መስመር ጠብቀን ከመሮጥ የቀደመንን ጠልፈን መጣል፣ በሐሜትና በነቀፋ ከአገር ማባረር አንዱ የመኖራችን እሴተ ሥርዓት ሆኗል። ስለዚህ የምንጓዘው ጉዞ የመጠባበቅ ጉዞ ነው። ጅብ ፊትና ኋላ ሆኖ አይሄድም ይባላል። ምክንያቱም አንዱ ከፊት ሊሄድ ታፋው ያምረውና የኋለኛው ሊገምጠው ይችላል። ስለዚህ ጅብ በመጠባበቅ ነው የሚሄደው። ዛሬም የለው ጉዞ ሳይሆን የጅብ ጉዞ የምንጓዝ መሆናችን ያሳዝናል። በማንኛውም የሕይወት አንጻር ወረፋ ቆመናል። ለመልካሙም ለክፉም ወረፋ ላይ ነን። ሕይወት በዙር የምትሄድ ጽዋ ናትና። በወረፋ ዓለም ከፊት ያለው ሲጠራ ተረኛ እኛ ነን። ስለዚህ ከፊታችን ያለው መልካም ዕድል ሊያገኝ አንድ ችግረኛ ከመቀነሱም በላይ ቀጥሎ እኛ ነንና ደስ ሊለን ይገባል። እንዲሁም ዓለም ወረፋ ነውና ከፊታችን ያለው በሞት ሲጠራ ቀጥሎ እኛ በመሆናችን መዘጋጀት ይገባናል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ካላላቀቀን በቀር ከወላጆቻችን እየተማርን ያደግነውን ነገር በትምህርትና በብዙ ጥረት እንኳ መላቀቅ አይቻለንም። አልቻልንምም። ወላጆቻችን በእቅፍ ላሰን ምግብ ሲያበሉን ምግብ ጣፋጭ ነው፣ ምግብ ጠቃሚ ነው እያሉ አላሳደጉንም። «እገሌ ሊበላብህ ነው» እያሉ ነው ያሳደጉን። ስለዚህ ከማንኪያ ጋር የጠቀጠቁብንን አመለካከት ዲግሪ እያስያዝነው እንቀጥላለን እንጂ መተው አልቻልንም። የሁልጊዜ ኑሮአችን እገሌ እንዳይበላ ከጥጋብ በላይ መብላት ሆኗል።

ያዕቆብ አድልኦና መከፋፈል በሚታይበት አስተዳደግ ስላደገ ለወንድሙ ፍቅር አልነበረውም። ልጆችን በልዩነት ማሳደግ የማይበርድ ጠብ በትውልድ ውስጥ መዝራት መሆኑን ከያዕቆብና ከኤሳው ዘሮች ማየት ይቻላል። ያዕቆብ የእግዚአብሔር በረከት የሆነውን በኩርና በምስር ወጥ ለመግዛት የሞከረ ሰው ነው። ወንድሙን እስከ አሁን ያስናክለዋል። አባቱ ይስሐቅ ኤሳውን ሊመርቅ ጣፋጭ ምግብ አሰናዳልኝ ሲል ርብቃ ሰምታ ያዕቆብ በረከቱን እንዲወስድ የማታለል ጎዳናን ጠረገች። ያዕቆብ በማታለል የወንድሙን በረከት ቢወስድም ልቡ ግን ሰላም አላገኘም። በመጨረሻም ወንድሙን ፈርቶ ተሰደደ (ዘፍ.27.)።

በዘመናችን ያለው ትልቁ የሕዝባችን ውድቀት ምንድነው? ስንል ውሸት ነው። ውሸት ዘመናዊነትና የኑሮ ስልት ሆኗል። በውሸት በረከት ሊሰበሰብ ይችላል። ነገር ግን ሰላም የለውም። የሰላምን እንጀራ ከመንፈሳዊ ሰው በቀር ማንም የማያገኛት ውድ ናት። ርብቃ ለልጇ ባሳየችው የማታለል ጎዳና የምትወደው ልጇን አጣችው። እስከ ሞት ድረስ ሳይተያዩ ቀሩ። ለሰዎች የምናሳየው የማታለል ጎዳና ለዘላለም አያገናኘንም። የሰው መንገድ አያገናኝምና። ለሰዎቹ አስበንና ተጨንቀን ሊሆን ይችላል። ኃጢአት ግን ይለያያል።

ያዕቆብ በተሰደደበት በሶርያ ምድር በአጎቱ በላባ ቤት ከሃያ ዓመት በላይ አገለገለ። አጎቱ ብዙ ጊዜ አታለለው። እርሱ አባቱን አታሏልና የዘራውን አጨደ። በኋላም የገዛ ልጆቹ አታለውት ዘመኑን በህዘን ፈጀ። ያዕቆብ በመረጠው አቋራጭ መንገድና የራስ ብልሃት ብዙ የደከመ ሰው ነው። ከአጎቱ ቤት ሁለት ሚስቶች፣ አሽከሮች፣ ልጆችና ብዙ ከብቶች ይዞ ተመለሰ። ብቻውን ሄዶ ሠራዊት ሆኖ ተመለሰ። ባዶ እጁን ሄዶ ሀብቱ ምድርን ሞልቶ ተመለሰ። ያዕቆብ ግን በሕይወቱ እርካታ አልነበረውም።

እንድ ቀንም ሚስቶቹንና ከብቶቹን ልጆቹንም የያቦቅን ወንዝ ካሻገረ በኋላ ብቻውን ይተክዝ ጀመረ። እግዚአብሔርም ተገልጦለት ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር አስኪነጋ ታገለ። እግዚአብሔርም «ሊነጋ አቅላልቶአልና ልቀቀኝ» ቢለው ያዕቆብ ግን «ካልባረክኸኝ አልለቅህም» አለው (ዘፍ.32÷26)። እግዚአብሔርም ያዕቆብን ባረከው። ያዕቆብም እግዚአብሔርን አይቷልና ሰውነቱ ድና ቀረች።

ያዕቆብ ሁለት ታማኝ ሚስቶች ነበሩት። ዛሬ እንድ ታማኝ ጠፍቷል። ኋላ የነገድ አባቶች የሆኑ አሥራ እንድ ልጆች ነበሩት። ቍጥር የሌላቸው ከብቶችና ንብረቶች ነበሩት። ታዲያ «ካልባረክኸኝ አልለቅህም» አለ። እነዚህ ሁሉ በረከቶች አይደሉም ወይ? አዎ በረከቶች ቢሆኑም እርካታዎች ግን አይደሉም። ያዕቆብ አንድ ከብት ይኖረኛል ብሎ እንኳ የሚያስብ አልነበረም። ብዙ ሺህ ከብቶች ቢኖሩትም በሕይወቱ ግን እርካታ አልነበረውም። ስለዚህ «ካልባረክኸኝ አልለቅህም» አለ። ያዕቆብ ከንብረት ሌላ መባረክ እንዳለ ተረድቷል። እርሱም ከፍታና ዝቅታ በሌለው በራሱ በእግዚአብሔር መርካት ነው።

አንድ የቀዶ ጥገና ሐኪም የሆነ ወዳጄ «እንደ በሬ መኖር ሰለቸኝ» አለኝ። ንግግሩን ሲቀጥልም «በሬ ጠዋት ተነሥቶ ለመሥራት ይወጣል። ላቡን ጠብ አድርጎ ሲያርስ ይውላል። ማታ ሲመጣ ሣር ይቀርብለታል፣ ይበላል፣ ላም አለችው አጠገቧ ይተኛል። ጥጆች አሉት ይከቡታል። ጠዋት ሲነጋ ደግሞ ወደ ሥራ ይሄዳል። እኔም ጠዋት ሥራ ብዬ እወጣለሁ፣ ቀኑን በሙሉ ላቤን ጠብ አድርጌ እሠራለሁ። ማታ ወደ ቤት ስገባ እንደ ላሚ እኔም ሚስት አለችኝ፣ እንደ ጥጆች ልጆች አሉኝ። ከበውኝ አተኛለሁ። ሲነጋ ደግሞ ወደ ሥራ እሄዳለሁ። እኔና በሬው ልዩነታችን ምንድነው? በእውነት እንደ በሬ መኖር ሰለቸኝ» አለኝ። ለዚህ ወንድም የሚያስፈልገው ከእግዚአብሔር ጋር ተጣብቆ መኖር ነበር።

ትልቁ መባረክ በእግዚአብሔር ማረፍ ነው። ትልቁ መባረክ ኑሮን መቀበል ነው። ትልቁ መባረክ አሁን በሆንነው መደሰት ነው። የኤፌሶን መልእክት ወንበራችን ላይ እንድንቀመጥ ያሳስበናል (ኤፌ.2÷6-7)። የእኛ ወንበራችን ክክርስቶስ ቀኝ በሰማያዊ ስፍራ መቀመጥ ነው። ስፍራችን እዚያ ነው። በምድር ስፍራና አገር የለንም። ሁሉም ነገር ከሰማይ ሊያዩት ትንሽ ነው። በምድር ትልቅ የሆነው እንኳ ከሰማይ ሊያዩት በጣም ትንሽ ነው። ከምንወርሳት አገር ሆነን ስንመለከተው ሀብትና ዝና፣ ክብርና ውበት ትንሽ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተልን ለቀኖሳዊ ትርፍ ሳይሆን ለሰማያዊ በረከት ነው። ለዚህ ነው፡- *«በክርስቶስ በሰማያዊ ሥፍራ*

በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ» (ኤፌ.1÷3) የሚለው::

ህብት ጥያቄ አንጂ በራሱ መልስ አይደለም:: ትዳር ጥያቄ እንጂ በራሱ መልስ አይደለም:: የሕይወት መልስ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: እንጀራ ብቻውን የሰውን ፍላጎት አያረካም:: ምክንያቱም የሰው ፍላጎት ከእንጀራ ስለሚያልፍ ነው:: የሰው እርካታ ከሕይወት ጋር የተያያዘ ነው:: አንድ አውሮፕላን ቢኖረን ሥጋችን ይኮራል:: ሥጋ ግዙፍ ነውና ወገኑን ሲያፍኝ ይኮራል:: መንፈሳችን ግን እርካታ የለውም:: ከዚያ ይልቅ አንዲት አበባ ብንመለከት እንደለታለን:: የሰው እርካታ ከሕይወት ጋር የተያያዘ ነው:: ሕያው ለሆነው ለሰው ነፍስ ጊዜያዊ የሆነው የአበባ ሕይወት በሙሉነት እርካታ ባይሰጥም ሕይወት ሕይወት ይፈልጋልና ከቍሳቍስ በተሻለ የአበባ ሕይወት ያረካናል::

እንስሳትም እንራባለን፣ እንቸገራለን ሳይሉ እኛን አምነው መኖራቸውና ታማኝነታቸው ያረካናል:: ለዚህ ነው በሰለጠነው ዓለም ንብረታቸውን ለውሻ አወረሱ ሲባል የምንሰማው:: እንስሳት ቢያረኩንም ደመ-ነፍስ ለሕያው ነፍስ ካሣ አይሆንምና ሙሉና ጥልቅ የሆነ እርካታ ሊሰጡን አይችሉም:: በወለድናቸው ልጆችና በምንረዳቸው ወገኖቻችን የምንረካው ለምንድነው? ስንል እርካታችን ከቍሳቍስ ይልቅ ከሕይወት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ነው:: ይልቁንም እግዚአብሔር የእኛን እርካታ የደበቀው የት ነው? ስንል በሌሎች ጉድለት ውስጥ ነው:: እውነተኛው ደስታ በመስጠት ውስጥ እንጂ በመቀበል አይደለም:: አበባን ስናጠጣ፣ እንስሳትን ስንቀልብ፣ ለዎችን ስንወድ እንረካለን::

በምድር ላይ ሕይወት ሦስት ደረጃዎች አሏት:: የእጽዋት ሕይወት፣ የእንስሳት ሕይወትና የሰው ሕይወት:: ከእጽዋት ሕይወት የእንስሳት ሕይወት፣ ከእንስሳት ሕይወት የሰው ሕይወት ይበልጣል:: ከእነዚህ ይልቅ የእግዚአብሔር ሕይወትነት ይልቃል:: ስለዚህ የእርካታችን ምንጩ እግዚአብሔር ነው::

ቍሳቍሶች ራሳቸውን ስለማይለውጡ አያረኩንም:: ራሳቸውንም ስለማይጠብቁ ዕረፍት አይሰጡንም:: እንደውም ቍሳቍሶች በበዙ ቍጥር እርካታችን እየቀነሰ ይመጣል:: በእጠቃላይ «አለኝ» በምንላቸው ነገሮች እርካታ የለም:: ምክንያቱም አሉኝ የምንላቸው ነገሮች አንድ ቀን ላይኖሩን ይችላሉና:: «ነኝ» የምንለው ነገር ግን ያረካል:: የማይለወጥ ነውና:: በዓለም ላይ ግን ማንም

«እኔ እንዲህ ነኝ» ብሎ መናገር አልቻለም:: ሰው ተለዋዋጭ ነውና:: ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ «እኔ÷ እኔ ነኝ» ብሎ ተናግሯል::

«የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ» (ዮሐ.6÷35)::
«እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ » (ዮሐ.8÷12)::
«እኔ የበጎች በር ነኝ» (ዮሐ.10÷7)::
«መልካም እረኛ እኔ ነኝ» (ዮሐ.10÷11)::
«ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ» (ዮሐ.11÷25)::
«እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ» (ዮሐ.14÷6)::
«እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ» (ዮሐ.15÷1)::

«አለኝ» የሚሉት ነገር አያረካም:: «ነኝ» የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ያረካል:: የረካን ማርካት እንደማይቻል በኢየሱስ ክርስቶስ የረካ ሰውም ሌሎች ነገሮች ሊያረኩትና ሊመጥኑት አይችሉም::

ብዙ ሰዎች እርካታቸው ያለው በሌላቸው ነገር ውስጥ ይመስላቸዋል:: ስለዚህ ለመርካት ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣሉ:: ያ ቢኖረኝ ይህ ቢሳካልኝ እረካለሁ ብለው ያስባሉ:: ዓለም ትልቅነቷ በምኞት ነው:: ሲጨብጧት ግን አታረካም:: የአረፋ ኪስ ሲያዩት ያምራል፣ ማማር ብቻ ሳይሆን ያሯሩጣል:: ሲጨብጡት ግን ባዶ ነው:: ዓለምም ክብሯ ዝናዋ በምኞት ትልቅ ነው:: ሲይዙት ግን ባዶ ነው:: ትልልቅ ኑሮዎች ትልልቅ ጉድለት እንዳለባቸው እግዚአብሔር ብቻ ያውቃል::

ምንም ይሁን ምን አሁን በሆንነው መርካት ካልቻልን በምንም ነገር መርካት አንችልም:: ከዚህ ሁሉ በላይ ኢየሱስ ክርስቶስ በማንነቱ ሲያረካን ካልቻለ በምንም ነገር መርካት አንችልም:: ባለጠጋው በደሃው እንቅልፍ፣ ደሃው በባለጠጋው ቤት ቢቀናም የሚታዘንለት እንጂ የሚቀናበት ሰው እንደሌለ ተረድቻለሁ:: የሚቀናበት እግዚአብሔርንና ኑሮን የተቀበለ ሰው ብቻ ነው::

እጅግ ባለጠጋ የሆኑ ባልና ሚስቶች ሲዝናኑ ወደ ባሕር ዳርቻ ይሄዳሉ:: በዚያም አንድ ዓሣ አጥማጅ ዓሣ እያጠመደ በመጥበስ ለእንግዶች ያቀርባል:: እነዚህ ባለጠጎችም ይህ ሰው ስላሳዘናቸው ጠርተው «ከዚህ ኑሮ መውጣት አለብህ፣ ተምረህ ራስህን መለወጥ አለብህ» አሉት:: እርሱ ግን «ተምሬ ምን እሆናለሁ?» አላቸው:: «ተምረህ ሥራ ትይዛለህ» አሉት:: እርሱም «ሥራ ከያዝኩ በኋላ ምን እሆናለሁ?» አላቸው:: እነርሱም «ባለጠጋ ትሆናለህ» አሉት:: «ባለጠጋ ከሆንኩኝ በኋላስ» አላቸው:: «ብዙ ሰው ቀጥረህ

ታስተዳድራለህ» አሉት። ጥያቄውን በመቀጠል «ብዙ ሰው ካስተዳደርኩስ በኋላ» አላቸው። «ሚሊየነር ትሆንና ልክ እንደ እኛ አዚህ መጥተህ ትዝናናለህ» አሉት። ዓሣ አጥማጁም «ይህ ከሆነማ ይዤዋለሁ» አለ ይባላል። አዎ በዓለም ላይ ምንም አዲስ ነገር የለም። ሠርክ አዲስ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

ባለጠጎች በባሕላዊ ቤቶች ለመደሰት ጎጆ ቤት ያሠራሉ። ደሃ ገበሬዎች የቆርቆሮ ቤት ሠራን ብለው እልልታ ያሰነግራሉ። ነገር ግን እርካታ ያለው ላይና ታች ቪታ በመለዋወጣቸው አይደለም። እርካታ እግዚአብሔር የሚሰጠን ሀብት ነው። ሥልጣኔው የሰለቸው ፈረንጅ በተፈጥሮና በጥንቱ ነገር ለመርካት ወደ አፍሪካ ምድር ይመጣል። አፍሪካዊው ደግሞ የእርካታዬ መልስ ያለው በሰለጠነው ምድር ነው ብሎ ወደ ፈረንጅ አገር ሲሄድ ሁለቱም ከርታቶች በአየር ማረፊያው ይተላለፋሉ። እርካታችን እግዚአብሔር ብቻ ነው። በእውነት ኑሮአችንን እንቀበለው ደግሞም ሰላም ይሰማን እንጂ በላስኪት ቤት ብንኖርም የትም መኖር ነው። ኑሮ የሚለካው በልብ ሰላም ነው።

<u>የጽሞና ጊዜ</u>

ከቤተሰብህ የተማርከው ትምህርት ዕድሜህን በሙሉ ይይዝሃል። በቆራጥነትና በእግዚአብሔር ጸጋ ዘረኝነትንና ጥላቻን ካልተላቀቅህ ሩጫህ በሙሉ በመረብ ላይ እንደ መሮጥ ነው። ዛሬ የማትደርስበት የመሰለህ ነገር ሁሉ ይደረስበታል። የተደረሰበት ነገር ሁሉ ግን አያረካም። በትልቅ ኑሮ እንጂ በትልቅ እርካታ የሚኖር ከእውነተኛ ክርስቲያን በቀር ማንም የለም። የሕይወት እርካታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ስለዚህ፦

- የኑሮህ መለኪያ እግዚአብሔር ብቻ ይሁን።
- አለኝ የሚሉት ሳይሆን «ነኝ» ያለው ክርስቶስ ብቻ እንደሚያረካህ አስተውል።
- ዓለም የአረፋ ኪስ መሆኗን ተረዳ።
- የምትቀናባቸው ሰዎችን አንተ ትበልጣቸው ይሆናል። የሚያስቀናው ግን የክርስቶስ ሰላም ያለው ሰው ብቻ ነው።

<u>ጸሎት</u>

የደስታ መፍለቂያ፣ የሐሴት ባሕሯ፣ የጥበብ አገሯ፣ የእውነት ድንበሯ ጌታዬ አምላኬ ሆይ አመሰግንሃለሁ።

ከምኖርበት ከበረሃው ዓለም ሆኜ የመምጫህን ቀን እየናፈቅሁ እጅ እነሣሃለሁ። ሁሉን አየሁ፣ ሁሉን መዘንኩ ካንተ በቀር ሁሉም ባዶ ነው። አንተ የሌለህበት ቤት፣ አንተ የሌለህበት አገልግሎት፣ አንተ የሌለህበት ቤተ ክርስቲያን በድን ነውና እባክህ ከእኛ ጋር ሁን። አንተ ደስታን ስትሰጥ እንዲሁ ደስ ታሰኘለህና ምክንያቱ ባልታወቀ ነገር ደስ አሰኘኝ። እንደምትችል አምናለሁ ለዘላለሙ አሜን።

ምዕራፍ ስድስት
የበረሃ መና

የእግዚአብሔር መግቦት በሕጻናት፣ በሰው ልጆችና በእስራኤል ጉዞ ውስጥ ድንቅ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። የእግዚአብሔር መግቦት የምንለው የእግዚአብሔር አስተዳዳሪነት ነው። ይህ ዓለም ፈጣሪ ብቻ ሳይሆን አስተዳዳሪም የሚፈልግ ዓለም ነው። የሉሲትና የቀኑ፣ የክረምትና የበጋው መፈራረቅ ይህ ዓለም አስተዳዳሪ፣ መጋቢና ተቆጣጣሪ እንዳለው ያስረዳል።

እግዚአብሔር ሕጻናትን ያኖራል። የሰው ልጅ ኑሮ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው በተአምራት የተሞላ ነው። ዘመናዊው ሳይንስ እንደሚነግረን ከአንድ ወንድ አምስት መቶ ሚሊዮን ዘሮች ይወጣሉ። ከአምስት መቶ ሚሊዮን ውስጥ አንዱ ብቻ ከሴቷ እንቁላል ጋር ተገናኝቶ ሰው ይገኛል። ይህ ከሰው ጥበብና ቍጥጥር ውጭ የሆነ ነገር ነው። እግዚአብሔር ግን ፈሳሽን በማጎፀን በመቋጠር ሰውን ይፈጥራል። ይህ ዘር በዓይን እንኳ ልናየው የማንችለው በጣም ረቂቅ ነው። ከዚህ በዓይን ከማይታይ ዘር ውስጥ ዓይን አለ፣ አፍንጫ አለ፣ እጅና እግር ሌላም የሰውነት ክፍል አለ። ሁሉም በጊዜያቸው ብቅ ማለት ይጀምራሉ። ይህን የሚያደርግ እግዚአብሔር ነው። ጽንሱንም በማጎፀን ሰውሮ የሚመግበው እግዚአብሔር ነው። እናት ጽንሱን እያየች የመንከባከብ ዕድል የላትም። እግዚአብሔር ግን ለአምሮቷ ከበላችው በርበሬውን ከአልጫው ጋር መጥኖ በቀጭን መስመር ለጽንሱ ይመግበዋል። ጽንሱም በማጎፀን የሚቀመጠው ተዘቅዝቆ ቢሆንም እንደ ማጎፀን ዓለም የሚመች ስፍራ በምድር ላይ ያለ አይመስልም። እግዚአብሔር ካስቀመጠ ተዘቅዝቆም ቢቀመጡ ይመቻል።

ሕጻኑ ሊወለድ ጥቂት ጊዜ ሲቀረው ከሰው ቍጥጥር ውጭ የእናትዬዋ ጡቶች ወተት ማዘጋጀት ይጀምራሉ። የላም ወተት በማይገኝበት በረሃማ ቦታ ብትወልድም ይህ የተፈጥሮ ምግብ ቋሚ ነው። በጠቃሚነቱ ወደር የሌለውን ወተት ያለ ክፍያ የሚያዘጋጅ እግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔር እንክብካቤ ከማጎፀን የሚጀምር ከዚያም ለዘላለም የሚቀጥል ነው። *«እናንተ የያዕቆብ ቤት ሆይ፥ የእስራኤልም ቤት ቅሬታ ሁሉ፥ ከሆድ ያነሣኋችሁ ከማጎፀንም የተሸከምኳችሁ፥ ስሙኝ። እስከ ሸምግልና ድረስ እኔ ነኝ፥ እስከ ሽበትም ድረስ እሸከማችኋለሁ» (ኢሳ.46፥3-4)።*

እግዚአብሔር ለሕጻኑ ያደረገው ቸርነት ይህ ብቻ አይደለም። የሚወዱት ወላጆችን አዘጋጅቶለታል። ወላጆች ከዚህ በፊት የማያውቁትን፣ ቁም ነገር ያላዩበትን፣ ራሱን መርዳት የማይችልን፣ ሲያዩት እንኳ የማያምር እርጥብ ሰውነት ያለውን ሕጻን የሚወዱትና ያልለፋበትን ቤትና ንብረት እንዲወርስ በፈቃድም በሕግም እሺ የሚሉት እግዚአብሔር ፍጥረቱን ያለ ወዳጅ ስላልፈጠረው ነው። የሚወዱን ሰዎች ከራሳቸው የተነሣ አልወደዱንም። ወላጆቻችንም ቢሆኑ በራሳቸው አልወደዱንም። በነጻ ማፍቀር የሰው ባሕርይ አይደለምና። የሚወዱን እግዚአብሔር እኛን መውደድ ስለሰጣቸው ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ሕጻናትን ብቻ አይደለም፣ የሰውን ልጅ የሚያኖርበት ጥበቡም አስደናቂ ነው። ስለ ሆድ ስናስብ «ሆድ ጠላት ነው» ብለን እናስብ ይሆናል። ሆድ ግን ወዳጅ ነው። ሆድ ባይኖር ኖሮ ሰው ሁሉ ተኝቶ ሣር ይበቅልበት ነበር። ምክንያት አጥቶ ከቤት አልወጣም ይል ነበር። አንዱ አንዱን የሚፈልገውና የሚታዘዘው ሆድ ስላለ ነው። እግዚአብሔር ሕይወት የምትናፈቅ እንድትሆን በማያቋርጥ ፍላጎት አዋቅሯታል። ሆድን የፈጠረ እግዚአብሔር ይመስገን!

ታዲያ ስለሆድ የሚዘጋጀው እህል ተራ በሆነ ሂደት የሚዘጋጅ ሳይሆን ተአምራት ያስበት ነው። ተአምራት ለሰው የማይቻል ቢሆንም ለእግዚአብሔር ግን የተለመደ አሠራሩ ነው። እቤት የተቀመጠውና ለዘር የተመረጠው እህል ለሰኔ ጭቃና ዝናብ ይበተናል። ይህ ምኝነት ደግሞም ማባከን ቢመስልም ገበሬው ግን ትክክል ነው። ያ ዘርም ከጭቃ ተለውሶ ፍጹም ይሞታል። ከወራቶች በኋላ ከሞተው የእህል ዘር ሕይወት ብቅ ይላል። ልምላሜ፣ አበባ፣ ከዚያም ፍሬ ይታያል። በአንዱ ዘር ፈንታ 30፣ 60፣ 100 ፍሬ በዘለላው ላይ ይታያል። ዝናቡ የማብቀሉን ሥራ ሲፈጽም ይቆማል፣ ከዚያ ካለፈ እህሉ ይበላሻል። ቀጥሎ በፀሐይ ይበስላል። የነጣው እህልም በታህሣሥና በጥር ይታጨድና ወደ ጎተራ ይገባል። በእግዚአብሔር በረከት ጉድለት ሞልቷልና በጥር ሠርግ መደገስ ይጀመራል። ይህን የሚያደርግ እግዚአብሔር ነው። ዝናቡም፣ ፀሐዩም ቆጣሪ የላቸውም። የእህሉም ዘለላ በኪሎ አይከፈልበትም። እግዚአብሔር ነጻ ስጦታ አድርጎ ሰጥቶናል።

ለሰው ሁሉ የአኗኗሩን ጥበብ ሰጥቶ ያኖረዋል። የሰው አኗኗር ሦስት ዓይነት ነው። በቀን፣ በወርና በዓመት ስፍር ይኖራል። በቀን የሚኖር የቀን ሠራተኛ፣ በወር የሚኖር የወር ደሞዝተኛ፣ በዓመት የሚኖር ደግሞ ገበሬ ነው። እህሉም ወደ ቤት ከገባ በኋላ የሴትና

የሙያ መለኪያ ይሆናል። «እህሉ አንድ ዓይነት፣ ሴቱ አሥራ ሁለት» የተባለው ተረትም ይተረታል። ምግቡም ከበለስ በኋላ ሬሳ ይሆናልና በቶሎ በለው ሆድ መቀበር አለበት። የበለስ ምግብ ተመልሶ ጥሬ እህል መሆን አይችልም። ስለዚህ ለበለስ ምግብ መለስት የለብንም። ደግሞም የምግብ ክብሩ እስከ ጉሮሮ ነው። ከጉሮሮ ካለፈ በኋላ ምግብ ክብር የለውምና እንደ ኤሳው ለምግብ ክብራችንን መጣል አይገባንም (ዕብ.12÷16)።

እግዚአብሔር በመግቡ ሕጻናትንና መላውን የለውን ልጅ እንዴት እንደሚያኖር አይተናል። 40 ዓመት በሙሉ ያለ ዘርና ያለ ጎተራ እስራኤልን እንዴት እንደመገበ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። የእስራኤል ልጆች ልክ እንደ እኛው በልቶ ካጅ ቢሆኑም በበረሃ ማዕድ ማዘጋጀት የምትችለውን የእግዚአብሔርን እጅ ግን አይተዋል። ከለው እንጂ ከእግዚአብሔር አይጎድልበትምና ምንም በሌለበት በረሃ ላይ እግዚአብሔር መናን ከደመና እያወረደ፣ ውኃን ከዓለት ላይ እያፈለቀ ዐርባ ዓመት መገባቸው። መና ከደመና፣ ውኃ ከዓለት ላይ የማይጠበቅ ቢሆንም ከማይጠበቅበት እያስገኘ አኖራቸው። ከጠበቅነው ቀርቶ ካልጠበቅነው፣ ከኖርንላቸው ሰዎች ሳይሆን ምንነታችንን ከማያውቁ መናንና ውኃን እየሰጠን እንዳኖረን እኛም ምስክር ነን። እርሱ በዚህ ጋ ይመጣል ተብሎ አይጠበቅም። በየብስ ሲጠብቁት በባሕር ይመጣል። ሁሉም ለእርሱ መንገዱ ነው። «ለመንገዱም ፍለጋ የለውም» (ሮሜ.11÷33)።

ከግብፅ ምድር የወጡት የእስራኤል ልጆች ቍጥር ከግማሽ ሚሊየን በላይ ነበረ። ይህን ሁሉ ሕዝብ እንደ አንድ ሰው ሲመግብ አልከበደውም። እርሱ እንድ ሰው ለመመገብ የሚያወጣው በረከትና ሚሊየን ሕዝብ ለመመገብ የሚያወጣው በረከት እኩል ነው። በረከቱ ፍጹም ነውና። ይህ ሁሉ ሕዝብ በለው ኩሽናና በለው አሳላፊ ቢመገብ ኖሮ በወረፋና በእድልአ ይሞት ነበር። መናው ግን በየቤታቸው ደጃፍ ይወርድ ነበር።

ሴትዬዋ በእግዚአብሔር ታምነው እግዚአብሔር ይመግበኛል ብለው የሚኖሩ ነበሩ። ለዕለታዊ ጉድለታቸው ሁሉ ተንበርክከው ይጸልዩ ነበር። እግዚአብሔርን ክብሪትና ጨው ሳይቀር ስጠኝ እያሉ የሚለምኑ ሲሆን እግዚአብሔርም ይሰጣቸዋል። በእንደበታቸውም እግዚአብሔር ስጠኝ ከማለት በቀር አገሌ ሰጠኝ አይሉም ነበር። በእግዚአብሔር ታምነው በክርስቶስ እርፈው በመኖራቸው ምክንያት የሚጠሉአቸው ጎረቤቶቻቸው ሁልጊዜ «እዩለት ጌታዬ ሰጠኝ» ትላለች እያሉ ይነቅፏቸዋል። አንድ ቀንም ደህና እቅም የነበረው ባለ ሉቅ «እኔ ከሉቄ ፓስታ፣ መኩረኒ፣ ዘይት፣ ስኳር፣ ጨው፣ ክብሪት

... አድርጌ በትልቅ ላስኪት በጠዋት በሯ ላይ አስቀምጣለሁ። ሁላችንም እንጠብቃታለን። በሩ ሲከፈት ጌታዬ ሰጠኝ ትላለች። ያን ጊዜ ጌታዋ እንዳልሰጣት እንነግራታለን» ይልና የሰፈሩን ሰው በዚህ አሳብ አሳምኖ ቀጠሮ ያዘ። ሴትዬዋም «ጌታዬ ሆይ፣ ለዛሬ የሚያስፈልገኝን ሁሉ አንተ ሙላልኝ» እያሉ ከጸለዩ በኋላ በራቸውን ሲከፍቱ በትልቅ ላስኪት ሙሉ በረከት ተቀምጧል። «ጌታዬ ለድሮ እኔ ሄጀ ነበር የምትለጠኝ፣ ዛሬ ደግሞ ብለህ ብለህ እበሬ ድረስ አመጣህልኝ? ተመስገን» ሲሉ ያ ባለ ሉቅ የሰፈሩን ሰዎች ይዞ «ጌታሽ አይደለም ያመጣልሽ፣ ጉድሽን ለማየት እኔ ነኝ ያስቀመጥኩት። ታዲያ ጌታሽ መቼ አመጣልሽ?» አላቸው። ሴትዬዋ ግን ሳይደነቁ «ጌታዬማ ንጉሥ ነው፣ እዚህ ድረስ አይለፋም፣ አንተን አሽከሩን ይልካል እንጂ» አሉ ይባላል።

ይህ ጌታ ለእስራኤል የደጃፍ በረከት አዘጋጀላቸው። ሙሴ ይህንን ሁሉ ሕዝብ እየመራ ሲወጣ ስለሚበሉት ሳይጨነቅ አልቀረም። በግዞት የነበረ ሕዝብ ሲሆን ስንቅ ቢቋጥር እንኳ ለ40 ዓመት የሚቆይ ስንቅ ሊቋጥር አይችልም። ሙሴ ይህን ሕዝብ ምን አበላዋለሁ? ብሎ የፈጠረው አምላክ ተቀምጦ እርሱ ቢጨነቅ እግዚአብሔር «ሙሴ ሆይ÷ የቆምከበትን ድንጋይ ፈንቅል» አለው። ቢፈነቅለው ትሎች ይርመሰመሳሉ። «እነዚህን ትሎች ማን ይመግባቸዋል?» አለው። ሙሴም «አንተ» አለ። «ታዲያ ድንጋይ የተጫናቸውን ትሎች የምመግብ ጌታ በመልኬና በአምሳሉ የፈጠርኩትን ሰው እረሳለሁን?» አለው እየተባለ በትውፊት ይነገራል።

ሴትዬዋ በጠና ታምመው እቤት ከዋሉ ሰንብተዋል። ከበሽታ ጋር ረዥብ ፀንቶባቸዋል። የተበላበት ቤት ጭር ሲል ሰው ከዚህ በፊት የተንጫጫበት አይመስልም። በአልጋቸው ላይ ሆነው የሚሸጥ ንብረት ሲያስቡ አንድ እሞሌ ጨው ብቻ ትዝ አላቸውና አስታማሚ ልጃቸውን «ያን አሞሌ ጨው ሸጠሽ ጥሩ ምግብ ሥሪልኝና በልቼ ልሙት» ብለው ገበያ ይልኳታል። እርሷም ሸጣ፣ የሸጠ የሚገዛ ያያልና ገበያውን ስትቃኝ ያማሩ የጆሮ ጌጦች አየች። ጆሮዋን ብትዳስሰው ባዶ ነው። በልብዋም «እኔ የበሳኹትን ጆሮ መድፈን የእኔ ግዴታ ነው፣ የበሳውን ጉሮሮ መድፈን ደግሞ የእግዚአብሔር ግዴታ ነው» ብላ የጆሮ ጌጥ ገዝታ እጊጣ ተመለሰች። እቤት ስትገባም እኚህ እናት እጅ እጇን ቢያዩ ምንም አልያዘችም። «ሽጥሽው ወይ ልጄ?» ቢሏት «አዎን» አለች። ታዲያ ምን ገዛሽ ቢሏት «እኔ የበሳኹትን ጆሮ ጉትቻ ደፈንኩበት፣ እግዚአብሔር የበሳውን ጉሮሮ እርሱ ይድፈንበት» አለቻቸው። እናትዬዋም አዘኑ። እንዳይናገሩ አስታማሚ ደግሞ ሊያጡ ነውና ዝም አሉ። ወዲያው

ብዙ እህል የጫኑ ነጋዴዎች አሳድሩን ብሰው መጡ። እህል የሰውም እንጂ ቤቱ ጎተራ ነበረው፤ እህሉን በጎተራ፣ አህያ የሰውም እንጂ ቤቱ ጋጣ ነበረውና አህያውን በጋጣ፣ የሚበላ የሰም እንጂ ሰዎቹን በሳሎን አስቀመጡ። ምሽት ላይም እናቷን ስታጥባቸው አነዚህ ነጋዴዎች አይተው «ምን ሆነው ነው?» ብሰው ይጠይቃሉ። እርሷም «ተስቦ በሽታ ይዟት ነበር አሁን ድናለች» አሰች። አነርሱም ተስቦ የሚሰውን ቃል ሲሰሙ «እንግዲያው እህሉ ተበላሽ» ብሰው ሲነጋ እህሉን በጎተራ እያራገፉ አህዮቻቸውን እየነዱ ወደ አገራቸው ተመለሱ። ልጅቷም ለእናቷ «አዋሽ እናቴ እኔ የበሳኹትን ጆሮ ጉትቻ ደፈንኩበት፣ እግዚአብሔር ያበሳውን ጉሮሮ እርሱ ደፈነበት» አሰች ይባላል።

እግዚአብሔር ሕዝቡን ስሰቃል ኪዳኑ ያኖራል። ፍጠረኝ ሳይል ለፈጠረው ሰው ያስባል። እግዚአብሔር ያኖራል። የእስራኤል ልጆች በበረሃ ላይ የሚሆነውን ሳያዩ አጉረመረሙ። ማጉረምረም አልማዙ እንዳስቀበት ቴፕ መነፋነፍ በመሆኑ ለሰውም ለእግዚአብሔርም የማይጥም ድምጽ ነው። የእስራኤል ልጆች በሚታየው መሪ በሙሴና በማይታየው መሪ በእግዚአብሔር ላይ አጉረመረሙ። የማጉረምረም ምክንያት ያስፈውንና የአሁኑን ማነጻጸር እንደ ነበር እናነባለን፦ *«ይህን ጉባዔ ሁሉ በራብ ልትገድሉ እኛን ወደዚች ምድረ በዳ አውጥታችኋል! በሥጋው ምንቸት አጠገብ ተቀምጠን እንጀራ ስንበላ ስንጠግብ ሳለን በግብፅ በእግዚአብሔር እጅ ምነው በሞትን ኖሉቸው»* (ዘፀ.16÷3)። የእስራኤል ልጆች በግብፅ ምድር የሥጋ ምንቸት አልበሱም። ግብፁውያን ሲበሱ ግን አይተዋል። ምሬት የትላንቱን መከራ አስረሳቸውና «ስንበላ» አሱ። ከግብፅ ምድር አውጣን ብሰው የሰመኑትን ልመና ረሱ። ማጉረምረም ዛሬን ስማጣጣል የማይሻሰውን ትላንትን ይሻላል ይላል። ማጉረምረም ዓይንን ያሳውራል። አጉረምራሚ ራሱን የሚኰንን ነው። ራሱን የሚኰንን ሰው ወደ ፊት መራመድ የማይችል ነው። በትላንት ትዝታ ይኖራል እንጂ የሚታየው ተስፋ የሰም። «ዕድሌ ጠማማ ነው፣ ግንባሬ ደረቅ ነው፣ የተፈጠርኩት በጎዶሎ ቀን ነው፣ ያልታደልኩ ነኝ» እያሰ ራሱን ይረግማል።

የክርስቲያን ዕድሉ እግዚአብሔር ነው (መዝ.15/16/÷5)። ዕድሉ እግዚአብሔር ከሆነ ዕድሉ ሚሲየን ሳይሆን ከዚያ በላይ ነው። ማጉረምረም የሚሆነውን መጠበቅ አለመቻልና አሁን ባለው በቶሎ መፍረድ ሁሉንም ነገር በዜሮ ማባዛት ነው። የእስራኤል ልጆች ያሰቡትን ተናገሩ፣ የታሰበላቸውን ግን መገንዘብ አልቻሉም። አነርሱ በግብፅ ሽንኩርት ትዝታ ያማርራሉ። ቀጥሎ ግን መና ሊወርድ ነው።

እግዚአብሔር ነገ መናን ስማውረድ ዛሬ መመሪያ ሰጣቸው፦ *«እግዚአብሔርም ሙሴን፣ በሕጌ ይሄዱ ወይም አይሄዱ እንደሆነ እኔ እንድፈትናቸው እነሆ ከሰማይ እንጀራን አዘንብላችኋለሁ፣ ሕዝቡም ወጥተው ሰዕለት ሰዕለት የሚበቃቸውን ይልቀሙ»* (ዘፀ.16÷4)። እግዚአብሔር በረሀብ ሳይሆን በሚዘንብ እንጀራ አፈትናችኋለሁ አለ። በእንጀራ መፈተን ከባድ ነው። ብዙዎች በማግኘት ተፈትነው ከእግዚአብሔር ርቀው አገልግሎታቸውን አስቀምጠው ሄደዋል። ስማያጠግበው እንጀራ እግዚአብሔርን መካድ ያሳዝናል!

መናው ቀለል ያለ የማይከብድ፣ በብዙ ንጥረ ነገሮች የዳበረ፣ እስከ ዛሬ በታወቁ ማዕድ ቤቶች ሊሠራ ያልቻለ የማር እንጎቻ የሚመስል ነው። አስራኤል ያሉት በበረሃ በመሆኑ መናው አሸዋ ላይ ከወረደ ይቆሽሻል። ስለዚህ እግዚአብሔር ሌሊቱን ውርጭ አምጥቶ ለፈሩን ያሰብሰዋል። የውርጭ ገበታ ከሠራ በኋላ መናውን ያወርድላቸዋል። ልዩ እንክብካቤ! የመናው የመጀመሪያ ሕግ ሰዕለት ሰዕለት የሚበቃቸውን መልቀም ሲሆን ሁሰተኛው ሕግ ደግሞ በለንበት መና ስስማይወርድና መልቀም ስለማይገባ በስድስተኛው ቀን በእጥፍ መልቀም ነበረባቸው። የእስራኤል ልጆች ግን በሁለቱም ትእዛዛት አልታመኑም። *«አንዱ አብዝቶ አንዱም አሳንሶ ሰቀመ። በጎሞርም በሰፈሩት ጊዜ እጅግ ለሰቀመ አልተረፈውም ጥቂትም ለሰቀመ አልጐደሰበትም፣ ሁሉ እያንዳንዱ የሚበሳውን ያህል ሰቀመ። ሙሴም፦ ማንም ከእርሱ አንዳች ለነገ አያስቀር አላቸውም። ነገር ግን ሙሴን አልሰሙትም፣ አንዳንድ ሰዎችም ከእርሱ ለነገ አስቀሩ፣ እርሱም ተላ ሸተተም፣ ሙሴም ተቆጣቸው»* (ዘፀ.16÷18-20)። *«በሰባተኛውም ቀን እንዲህ ሆነ፣ ከሕዝቡ አንዳንድ ሰዎች ሊለቅሙ ወጡ፣ ምንምን አላገኙም»* (ዘፀ.16÷27)።

እግዚአብሔር ሕይወትን በዕለት በዕለት እንድንኖራት ይፈልጋል። እርሱ የምንኖርበትን ስፍራና ዕድሜ ብቻ ሳይሆን የምንበላውን ልክ ወስኖታል። ከልካችን ማለፍ አንችልም። ብዙ ስላሰን ብዙ አንበላም። ባለጠጎች ከድሆች በላይ አይበሱም። እንደውም አነርሱ በሐኪም ገደብ የማይበሉት ይበዛል። ቅቤና ማሩ ለቤቱ ክብር ይገባል እንጂ እነርሱ አይበሉትም። ቅቤና ማሩ የሚስማማው ለቤት ሠራተኞችና ለዘበኞች ነው። ብዙ ልብስ ስላሰን ሁለት ሱሪ ወይም ሁለት ቀሚስ ሰብሰን መውጣት አንችልም። ከልካችን ውጭ ላሉት ነገሮች ተጠቃሚዎች ሳይሆን ዘበኞች ነን። ያውም በነጻ የምንጠብቅ ዘበኞች!

የአንድ ደሃ የቀን ወጪ ዐሥር ብር ሊሆን ይችላል። የአንድ ንጉሥ የቀን ወጪ ደግሞ አንድ ሚሊየን ብር ሊሆን ይችላል። የሁለቱም የገበታ ስፋት ግን እኩል ነው። ይህን የሚያስናዳ ስውር እጅ አለ። ዐሥር ብር ካጣ የሚራብ ደሃ አለ፣ ዐሥር ሚሊየን ብር ካጣ የሚራብ ባለጠጋ አለ። የሁለቱን ችግር እኩልነት የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። አም ጥቂት የለቀመ አያንሰውም፣ ብዙ የሰቀመም አይተርፈውም።

የእስራኤል ልጆች በሰንበት ኾለ መና ማሰብ አልነበረባቸውም። ምክንያቱም ሰንበት የእግዚአብሔር ነውና። ከእነርሱ ግን አንዳንዶቹ ቢወጡም ምንም አላገኙም። እግዚአብሔር ግን ታዘባቸው። ዛሬም ለእግዚአብሔር የምናወጣው የቀን አሥራት ሰንበት ነው። ሰንበት የእግዚአብሔር ነው። በዚህ ቀን ለመልቀም ብንወጣም ምንም እናገኝም። የስድስቱ ቀን መና ካለረካን የእንዱ ቀን መና እንዴት ያረካናል? ያውም የሌለ መና! እግዚአብሔር ያልከበረበት ሩጫ ድካም እንጂ ትርፍ የለውም።

«ወይ ዓለም መውደድ መሞኘት፣
ጌታን ረስቶ ጌትነት!»

<u>የጽሞና ጊዜ</u>

በእያንዳንዱ ቀን የእግዚአብሔር ተአምራዊ እጅ ከዚህች ዓለም እንዳልተለየች አስብ። ባትገነዘበውም የመጣህበት መንገድ ሁሉ በተአምር የተሞላ ነው። የሚሞተውን ሰው ያህል ይወለዳል። ይህን በበላይ የሚቆጣጠር ያንተ እግዚአብሔር ነው። መፍጠር በሚችል አምላክ ስለምታመልክ ደስ ይበልህ። ከማኅፀን የጀመረው ታሪኬ ሁሉ ተአምር ነው በልና አሁን ተአምረኛውን ጠብቅ። ደግሞም፦

- ኤልያስን ከቁራ አፍ ሥጋ የመገበ ጌታ አንተንም በማይጠበቁ ሰዎች ያገለግልሃል።
- እግዚአብሔር በበረሃ ላይ ሙላት መሆኑን እመን።

<u>ጸሎት</u>

በረሃውን የምታናግረው፣ ምድረ በዳውን የምታረካው ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ። በበረሃ የምትገኝ፣ በበረሃም መርዳት የምትችል አንተ ነህና በሕይወት በረሃ ሳልፍ እርዳኝ። ከምበላው የምስገበገበው እንዳይበዛብኝ በልኬ መኖርን አስተምረኝ። ብሮጥም ለማን እንደምለበስብ

አላውቅምና አንተን ማገልገልን እንዳልረሳ አለምንሃለሁ። ማድረግ በምችለውን በስምህ እንዳደርግ ማድረግ በማልችለው ግን «ድርሻው የጌታዬ ነው» ብዬ እንዳርፍ አርዳኝ። የማትደፈር ምሽግ ነህና ሰዘላለሙ አሜን!

ምዕራፍ ሰባት
መኖሪያህ ማን ነው?

ሙሴ የእስራኤላውያን የነጻነት ታጋይ፣ ታላቅ መሪና የጦር አለቃ ነበር። ቍጥሩ ከግማሽ ሚሊየን በላይ የሆነውን ሕዝብ በረሃና ጠላት ባለበት ስፍራ ያውም በኃያላን መንግሥታት ወደ ተያዘች ወደ ምድረ ከነዓን የመራው በእምነት ነበር። የፈርያን የልጅ ልጅ ወይም ልዑል መባልን ንቆ ከወገኖቹ ጋር የተጨቆነን ኑሮ የመረጠው የማይታየውን በሚያይ በእምነት ኃማካይነት ነበር (ዕብ.11÷24-27)። እውነት የሌለበት ቤተ መንግሥት ያማረ አስር ቤት ሆነበት። ከጎሊናቸው ጋር ሆነው ከሚጠቁት እንደ አንዱ መሆን ክብር ሆኖ ታየው። በአጠቃላይ ሙሴ ጊዜያዊውን ዋጋ ሳይሆን ዘላለማዊውን ዋጋ አለበ። ሙሴ ለምችቱ ያልኖረ፣ የጨቋኞችን ወዳጅነት የጣለ፣ ከሁሉ በላይ በእግዚአብሔር እየተመራ የሚመራ መሪ ስለነበረ በእስራኤላውያን ዘንድ እስከ ዛሬ ተወዳጅ መሪ ነው።

ይህ ሙሴ በመሪባ ውኃ አጠገብ ቆሞ *«ለውኑ ከዚህ ድንጋይ ውኃን እናወጣላችኋለን»* (ዘኁ.20÷10-13) ብሎ በመናገሩ እግዚአብሔር ተቆጣው። ክብርን ለእግዚአብሔር ባለመስጠቱና ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ «እናወጣላችኋለን» በማለቱ አርባ ዓመት የደከመለትን አገልግሎት እንደማይወርስ ተነገረው። በዚህ ጉዳይ ቢለምንም እግዚአብሔር *«ይበቃሃል፤ በዚህ ነገር ደግመህ አትናገረኝ»* (ዘዳ.3÷26) አለው። እግዚአብሔር በክብሩ ከማንም ጋር አይደራደርምና (ኢሳ.42÷8)። ሙሴ የተስፋይቱን ምድር እንደማይወርስ ቢያረጋግጥም አገልግሎቱን ግን እስከ ሞት ድረስ ቀጠለ። እርሱ ያገለግል የነበረው እግዚአብሔርን ስለማፍቀርና እውነቱ እውነት መሆኑ ስለገባው እንጂ ስለ ከነዓን አልነበረም። ልክ እንደ ሙሴ ሁሉ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩት የእምነት አባቶች ከሞት በኋላ ወደ ሲኦል እንደሚወርዱ እያወቁ በዘመናቸው ሁሉ እግዚአብሔርን አገለገሉ። እግዚአብሔርን ስለ ገነት እንኳ አልተከተሉትም። አንድ አባት «እግዚአብሔርን የምከተለው ባምነው መንግሥት ለማያት እገባለሁ፣ ብክደው ገሀነመ እሳት እወርዳለሁ ብዬ ሳይሆን ወዶኛል ሞቶልኛል ብዬ ነው» ብለዋል።

ሙሴም እግዚአብሔርን ስለ በረከቱ ሳይሆን ስለ ራሱ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ይከተለው ነበር። የተስፋይቱን ምድር አትወርስም ተብሎ እንኳ አገልግሎቱን ቀጥሏል። ሙሴ ይህ ብቻ አይደለም፣ እግዚአብሔር ወደሚሞትበት ተራራ በጠራው ጊዜ በፍጹም መታዘዝ የራሱን መቃብር ቆፍሮ ሊሞት ወጣ።

«ወንድምህም አሮን በሖር ተራራ እንደ ሞተ ወደ ወገኖቹም እንደ ተሰማች÷ በወጣህበት ተራራ ሙት÷ ወደ ወገኖችህም ተሰማች፤» (ዘዳ.32÷50)።

እግዚአብሔርን ስለ ራሱ ብቻ ማምለክና በፈቃደኝነት መሞት በዚህ ዘመን የሚቀሩን መንፈሳዊ ብቃቶች ናቸው። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል ብንመለከት አሁን ባዶ ነው። ለምን ባዶ ሆነ? ስንል በእርሱ ያመንን በእምነት ራሳችንን እንድንሰቅልበት ባዶ ሆኗል። የሞተ ሰው ለዚህ ዓለም ክብር እንደማይደነግጥ ሹመት መጥቶልሃል ቢሉት እንደማይነቃ ከክርስቶስ ጋር የሞተው ክርስቲያንም ለዚህ ዓለም ነገር አይደነቅም። ዓለም ለምታቀርብለት የኃጢአት ግብዣ መልሱ፡- «ስለ ሞትኩ አልችልም» የሚል ነው። ሙሴ በፈቃዱ የራሱን ጉድጓድ ቆፈረ። ዛሬ መነኮሳት በቁማቸው ሞቻለሁ ብለው እንደሚያስቡትና የቁም ተዝካራቸውን እንደሚያወጡት ከዚያ በላቀ ትርጉም ለእኔነት መሞት ያስፈልጋል። ለሞተ ሰው የዚህ ዓለም ኑሮ ቀላል ነው። ላልሞተ ሰው ግን የሚያየው፣ የሚሰማው፣ የሚደርስበት ነገር ያውከዋል። መሞትን በሚመለከት በዘመናችን ካሉ ክርስቲያኖች የቀደሙት ፈላስፎች ይበልጣሉ።

ሙሴ እግዚአብሔር ወደሚሞትበት ተራራ በጠራው ጊዜ ለሕዝቡ የመጨረሻ ንግግርና ቡራኬ አደረገ። የእግዚአብሔር ሰዎች የመጨረሻ ንግግራቸው ኑዛዜ ሳይሆን ቡራኬ ነበር። ምክንያቱም በዚህ ምድር ላይ ያፈሩት ሀብት እግዚአብሔር ነውና የሚቀሩትን ወገኖቻቸውን ይባርካሉ። ኑዛዜ ያልቃል፣ በረከት ግን አያልቅም። ኑዛዜ የቤተሰብን ሰላም ያጠፋል፣ በረከት ግን ያስተሳስራል። ለትውልድ እግዚአብሔርን መስጠት የማያልቅ ሀብት መስጠት ነው። ሙሴ እያንዳንዱን ነገድ ከባረከ በኋላ መላውን እስራኤልን በመጨረሻ ሲባርክ እንዲህ አለ፡-

«መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው÷ የዘላለምም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው፤ ጠላትህን ከፊትህ አውጥቶ፡- አጥፋው ይላል። እስራኤልም ተማምኖ÷ የያዕቆብም ምንጭ ብቻውን እህልና የወይን ጠጅ ባለባት ምድር ይኖራል፤ ሰማያቱም ጠልን ያንጠባጥባሉ። እስራኤል ሆይ÷ ምስጉን ነህ፤ በእግዚአብሔር የዳነ ሕዝብ እንደ አንተ ማን ነው? እርሱ የረድኤትህ ጋሻ÷ የክፍተኛነትህም ሰይፍ ነው። ጠላቶችህም ይገዙልሃል፤ አንተም ከፍታቸውን ትረግጣለህ» (ዘዳ.33÷27-29)።

ለእስራኤላውያን መኖሪያቸው እግዚአብሔር መሆኑን መስማት ትንፋሽን የሚቀጥል ነገር ነው። ያሉበት ሁኔታ ዋስትና የሚፈልጉበትና የከበባቸው ነገርም ለመጨነቅ በቂ ምክንያት ይመስል ነበር። ሙሴ ከቀናት በኋላ ሊሞት ነው። እንኳን ደግ መሪ ክፉ መሪም ቢሆን ሞቱ ያሳስባል። በየዕለቱ ላለፉት ዐርባ ዓመት ይወርድላቸው የነበረው መናም ከወር በኋላ ይቆማል። በሚታረስበት አገር መናን ማውረድ ስንፍናን በለማይ ሽንጎ እንደ ማጽደቅ ነውና። የሚወርሷት ምድር ደግሞ በጠላት እጅ ናት። የቀድሞውን ታሪክ የሚያውቁ ከግብፅ ምድር የወጡ ቁዙ ሺህ ሰዎች አልቀዋል። ነገርን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው የሚያወሩት የቆየ ባልንጀራ የለም። ስለዚህ የእስራኤል ልጆች «እንዴት እንኖራለን?» የሚል ጭንቀት ገባቸው። ሙሴም መሪ ነውና የልባቸውን አሳብ አውቆ፦ *«መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው፥ የዘላለምም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው»* አለ።

አም ገንዘብ መኖሪያ አይሆንም፥ ትዳርም መኖሪያ አይሆንም፥ ጤናም መኖሪያ አይሆንም፥ ያከማቸነው ጥሪትም መኖሪያ አይሆንም። እንኳን ትንሹ የእኛ ቤት፣ ትልቁ ዓለምም መኖሪያ አይሆንም። የአሳት ቀጠሮ ተይዞለታል (2ጴጥ.3፥12)። እግዚአብሔር ግን የኑሮ መድኅን ነው። ኅተራም ይጎድላል፣ ለሠርግ ያስቀመጡትም ለሀዘን ይውላል፣ የሰበሰቡትም ላለፉበት ሰው ሊሳይ ይሆናል። እግዚአብሔር ግን የኑሮ መድኅን ነው። በደርጉ ዘመን ያለ ምንም ጥፋት ባለጠጋ መሆን በራሱ ወንጀል ነበር። ጠዋት ባለጠጋ ሆነው ከሰዓት ንብረታቸው ተወርሶ ደሃ ሆነው የለመኑ ሰዎች ብዙ ነበሩ። በስደት ዘመን ብዙ ባለጠጎች በአንድ ላስቲክ መቀየሪያ ልብሳቸውን ብቻ ይዘው ሊወጡ ሽኝተናል። ዛሬ የእነርሱን ቤት የሚያከራዩ፣ ግቡና ውጡ የሚሉት ዘበኞቻቸው የነበሩት ናቸው። ያማሩት የመኳንንትና የመሳፍንት ቤቶች ከዘራቸው ማን ይኖርበታል? ተረኞች ይዛለሉበታል። እነርሱም ካለፉት አይማሩም። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መሳፍንትና መኳንንት ለኑሮአቸው ጨርሰው ለቀብራቸው ተጨንቀው በገዳማትና አድባራት ጌጠኛ መቃብር ቤት አሠርተው ነበር። ሰው ግን የተወለደበትን ቦታ እንጂ የሚሞትበትን ቦታ አያውቀውምና የትም ተጥለው ቀሩ። ለብዙ ቆንጆዎችና ጎበዞች ያለቀስነው ለሞታቸው ሳይሆን ለምኞታቸው ነው። አም ንዋይ መኖሪያ አይሆንም። *«መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው»* (ዘዳ.33÷27)።

ዐፄ ቴዎድሮስ ደጃች ውቤን ይዘው ባሰሩአቸው ለዓት «የሰበሰብከውን ብርና ወርቅ አምጣ» ብለው ጠየቁአቸው። ደጃች ውቤ የወሎና የትግራይ ሕዝብ ብር ከዛፍ ላይ ይለቅማል ወይ?

እስኪባል እያስጨነቁ በዝብዘውታል። ዐፄ ቴዎድሮስም ያን ስለሚያውቁ አምጣ ቢሏቸው ደጃች ውቤ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆኑም። በዚህ ጊዜ ዐፄ ቴዎድሮስ በፈረስ ጭራ አስረው ሲያሰቃዩአቸው አሳያለሁ አሉ። ደጃች ውቤም በአንድ ተራራ ሥር የቀበሩት ብርና ወርቅ ቢወጣ ቢወጣ አላልቅም አለ። ዐፄ ቴዎድሮስም ተደንቀው «ይህን ሁሉ ብርና ወርቅ የሰበሰብክው ለምንድነው? ለሕዝብህ ወይ ለወታደርህ ለምን አልሰጠህም?» ቢሏቸው ደጃች ውቤ «ለክፉ ቀን ብዬ ነው» አሉ። ዐፄ ቴዎድሮስም «በደግ ቀን ያስቀመጡትን በክፉ ቀን መብላት ከተቻለማ ምን ክፉ ቀን አለ» አሉ ይባላል።

በርግጥም በደግ ቀን ያስቀመጡትን በክፉ ቀን መብላት ቢቻል ክፉ ቀን በዓለም ላይ ባልኖረ ነበር። ዛሬ ለደጃች ውቤ ክፉ ቀን ነች። ነገር ግን ያስቀመጡትን አረፍ ብለው ሊበሉ አልቻሉም። ነገሥታት ሕዝባቸውን በድለው በባዕድ አገር ያስቀመጡትን ወርቅና ብር እነርሱም ሆኑ ልጆቻቸው አልበሉትም። ያማሩና ያጌጡ ቤቶቻቸውም ተወላጆቻቸው ሳይሆኑ ሌሎች ይኖሩበታል። *«ለክንቱ ይታወካል እንጂ በአውነት ሰው እንደ ጥላ ይመላለሳል፤ ያከማቻል የሚሰበስበለትንም አያውቅም»* (መዝ.38(39) ÷6)።

«መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው የዘላለም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው፤» (ዘዳ.33÷27)። ብዙ ሰዎች የዕለትና የዓመቱን መሪ ጥቅሶች የማውጣት ልማድ አላቸው። የሕይወት ዘመናችን መሪ ጥቅስ ግን ይህ ነው። «የዘላለም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው» ተኛ ማለት ነው። ክንድ መንተራስ ይመቻል። ያውም የሚወዱት ሰው ክንድ ከሆነ ያሳርፋል። ያ የተሸከመን ክንድ ግን ስለሚዝል መተኛ ታችንን አረጋግጦ ይሰበሰባል። ምቾትም ጠፍቶ መባነን ይመጣል። ምክንያቱም የተንተራስነው ክንድ «ጊዜያዊ» ነውና። በእምነት የምንንተራሰው የአምላካችን ክንድ ግን «የዘላለም ክንዶች» ናቸው። በቅዳሴያችን *«ፍጥረትህንም ሁሉ በቃልህ ፈጠርህ፤ መገዛት ሳይኖርብህ ሁሉን ፈጠርህ። ሳትደክም ሁሉን ትሸክማለህ፤ ሳታጐድል ለሁሉ ትመግባለህ፤ ዝም ሳትል ለሁሉ ታሰባለህ። ሳታጐድል ለሁሉ ትሰጣለህ ሳትነጥፍ ለሁሉ ታረካለህ ሳትዘነጋ ሁሉን ታሰባለህ። ሳትተኛ ሁሉን ትጠብቃለህ ቸል ሳትል ሁሉን ትሰማለህ ሳትቀበል ለሁሉ ትተዋለህ ... የማያዙት ፈጣሪ የማይሸሙት ንጉሥ፤ የማይነቅፉት ጌታ፤ የማያበድሩት አምላክ፤ የማይሰጡት ባለጠጋ፤ ከማያልቀው ገንዘቡ የሚሰጥ»* እያልን እናመሰግነዋለን።

ለብዙዎቻችን ሰላም የሚሰማን ሰላም ካሰ ብቻ ነው። የተመሠረትንበትን የኑሮ አቋም ግዙፍ የጦር መርከቦች ወደ መካከለኛው ምሥራቅ መጠጋት፣ የነዳጅ ዋጋ መናር፣ የኑሮ ውድነት ያናውጠዋል። ደግሞም ያመኑበት የፖለቲካ ፓርቲ ካሰ ብቻ የሚኖሩ የሚመስላቸው፣ የልጆቻቸውን ትንፋሽ በአጻቸው የቋጠሩ የሚመስላቸው፣ ለእኔ ያለሁት እኔ ብቻ ነኝ እያሉ በአሳብ የሚታክቱ ብዙዎች ናቸው። ቃሉ ግን «*መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው የዘላለምም ክንዶች ካንተ በታች ናቸው*» ይለናል። ስለዚህ እረፍ እፎይ በል ማለት ነው። ታዲያ እረፍ የሚል ተገኝቶ ነው?

በነቢዩ ዳዊት፡- «*ዕረፉ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ እወቁ፤ በአሕዛብ ዘንድ ከፍ ከፍ እላለሁ በምድርም ላይ ክፍ ከፍ እላለሁ*» (መዝ.45(46)÷10) ብሏል። እግዚአብሔር የሚሠራው እኛ ስናርፍ ነው። እንቅልፍ ባጣንበትና አቋራጭ መንገዶችን በምንፈልግበት ነገር እርሱ አይሠራም። ሙሉ በሙሉ ገመዱን ለቅቀን ለእርሱ ስንተውለት እግዚአብሔር በታላቅነቱ ይሠራል። የእግዚአብሔርን ሥራ ለማየት አስቀድሞ ማረፍ ያስፈልጋል።

እኛስ የቤታችን ራስ ያልነው ህልውናው አስግቶን ይሆን? ይመሩናል የምንላቸው በሞት አደጋ ውስጥ ገብተው ይሆን? የምንበላው ደሞዝና እርዳታ ሊቀር የወር ዕድሜ ቀርቶት ይሆን? ድሮ የምናውቃቸው ሰዎችን ዓይናችን እስኪፈዝ ፈልገን አጥተን ይሆን? በምድራችን ላይ ያንዣበቡት ጭንቆች እንቅልፍ ነሥተውን ይሆን? የዚህ ሁሉ ጥያቄአችን መልስ «*መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው የዘላለምም ክንዶች ክለንተ በታች ናቸው*» በሚለው ሕያው ቃል ውስጥ ተጠቃሏል። ይህ ቃል በግድግዳችን ላይ ሳይሆን በልባችን ላይ መጻፍ አለበት። በቃል ማጥናት ሳይሆን እንደ ቃሉ የሆነውን እምላክ ማየት ያስፈልጋል።

አዎ እውነተኛውና አስፈላጊው ጥያቄ «እንዴት እኖራለሁ?» የሚለው ሳይሆን «ለምን እኖራለሁ?» የሚለው ነው። ለምን እንደምንኖር ካወቅን እንዴት እንደምንኖር እናውቃለን። ለምን እንደምንኖር ካወቅንም እንዴትም መኖራችን አያሳስበንም። አኗኗር ኑሮን አይለውጠውም። ዓላማ ግን ኑሮን ይለውጣል። በአንድ ታክሲ ውስጥ አንድ ማስጠንቀቂያ ተለጥፎአል፡- «ያለምክንያት መኖር ክልክል ነው።»

የጽሞና ጊዜ

እግዚአብሔርን ስለ ራሱ ብቻ ተከተል። ስለሚሞላና ስለሚጎድል ኑሮ ብለህ አትከተል። ይልቁንም አገልጋይ ከሆንህ በኋላ እንጀራዬ የሚል ቋንቋ አትጠቀም። የምትኖረው ለእንጀራ ሳይሆን ለእግዚአብሔር መሆን አለበት። የምትሻውን ለማግኘት መጀመሪያ ማረፍ አለብህ። ስታርፍ እግዚአብሔር ይሠራል። ሁለት ነገሮች ቢሟሉልህ ኑሮህ ብዙ ጤና ያገኛል። እነርሱም፡-

- እግዚአብሔርን ስለ እግዚአብሔር ብለህ መከተል።
- ለእኔነትህ መሞት።

ጸሎት

የምታድን የምትገድል፣ የምትሰጥ የምትነሣ፣ የቆመውን የምትሰበስብ፣ ሕፃኑን በልደት የምታመጣ አምላክ ሥልጣንህ ፍጹም ነውና አመሰግንሃለሁ። የማየው የምሰማው የማያሳርፍ ቢሆንም ካንተ ኃይል የሚበልጥ ምንም ስለ ሌለ ልቤን አበረታለሁ። ካንተ በቀር በምንም አልታመንም። ገንዘብም አያድንም፣ ወገንም አያድንም አንተ ግን አዳኜ ነህና አመሰግንሃለሁ። መኖሪያዬ ነህና ለዘላለሙ አሜን!

ምዕራፍ ስምንት

ፈቃዱ ይሁን

ሰውዬው በራ ሲገዛ ገንዘብ በኪሱ ይዞ ወደ ገበያ ሲሄድ ጓደኛውን ያገኘዋል። ጓደኛውም «ወዴት እየሄድክ ነው?» ቢለው «በራ ልገዛ ወደ ገበያ እየሄድኩ ነው» አለው። «እግዚአብሔር ቢፈቅድ» አለ ጓደኛው። ሰውዬው ግን «ገንዘብ እኮ በኪሴ ይዣለሁ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን ያደርጋል?» አለውና ጉዞውን ቀጠለ። ትንሽ አልፍ እንዳለ ወንበዴዎች ገጥመውት እርሱን ደብድበው ገንዘቡን ነጥቀው ይሄዳሉ። ሰውዬውም ወደ ቤቱ በባዶ ሲመለስ ጠዋት ያገኘውን ጓደኛውን አገኘው። ጓደኛውም «ወዴት እየሄድክ ነው?» ቢለው «እግዚአብሔር ከፈቀደ ወደ ቤቴ እየገባሁ ነው» አለው ይባላል።

የምንኖርበት ዓለም የትግል ዓለም ነው። ኢዮብ እንደ ገለጠው ሕይወት ብርቱ ስልፍ ናት (ኢዮ.7÷1)። አንድ ሰውም «ሕይወት እያለቀስክ የምትልጣት ሽንኩርት ናት» ብሏል። ብዙ ትግሎች አሉ። ከትግሎች ሁሉ የሚበልጠው ትግል ግን የእግዚአብሔር ፈቃድና የእኛ ፈቃድ በሥጋችን ሜዳ ላይ መታገላቸው ነው። በብዙ ደክመናል፣ በብዙ ዝለናል፣ በብዙ እኛችንን ለምርኮ ዘርግተናል፣ ሕይወትም ትርጉም አጥተንላታል። በራሳችን፣ በሁኔታዎችና በእግዚአብሔር ተቀይመናል። ብዙ የደከመን ሰዎች ብንሆንም የብዙ ድካማችን ምክንያቱ ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን የእኔ ፈቃድ ይሁን የሚል እልኸኛ ተፈጥሮአችን ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ቀርቶ የእኛ ፈቃድ እንዲሆን እኛና እግዚአብሔር ቦታ መለዋወጥ አለብን። እግዚአብሔር አምላክ ከሆነ ግን የእርሱ አሳብ መጽናት አለበት። እኛ ፍጡራን ከሆንን የእርሱን አሳብ መቀበል አለብን። ብዙዎቻችን እግዚአብሔርን የምንፈልገው ፈቃዳችንን እንዲያገለግል እንጂ ፈቃዱን ለማገልገል አይደለም። እግዚአብሔርን የፍላጎታችን አገልጋይ ልናደርገው እንፈልጋለን። እግዚአብሔር ያልኩትን አልፈጸመልኝም በማለት ብዙ ጊዜ እንቀየመዋለን። ያልነውን አልፈጸመም ብለን ስናዝን እርሱ ያለንን ፈጽመናል ወይ? ብለን ራሳችንን መጠየቅ ግን አልቻልንም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣበት ዐቢይ ዓላማ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ፈቃድ ለሰዎች ለመግለጽ ነው። በዚህ ምክንያት ትምህርቱና ሕይወቱ የእግዚአብሔር የፈቃዱ ማብራሪያ ነበር። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ኖረ፣ እንደ ፈቃዱ

አገለገለ፣ እንደ ፈቃዱ ሞተ። ጥጋቡ ፈቃዱን መፈጸም ነበር (ዮሐ.4÷34)። ይህች ዓለም እንደ ክርስቶስ የገፋችው ሰው የለም። ምድር ካልተመቸቻቸው ሰዎች አንዱ ቢሆንም ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ደስተኛ ነበር። ደስታው መሳካቶች ያመጡት ደስታ ሳይሆን የሚኖረው ለማን መሆኑን ማወቁ ነበር። ለማንና ለምን እንደሚኖር የሚያውቅ ብቻ ደስተኛ ነው። ለእግዚአብሔር ፈቃድ የሚኖር የማይጎድል ደግሞም ማንም የማይቀማው ደስታ አለው።

«ለምን?» በሚል ጥያቄ የተሞላን ነን። በሚሆኑትና በሚከሰቱት ነገሮች ለምን? እንላለን። ለምን? የሚለው ቃላችንም መልስ እያጣ እንደ ገደል ማሚቱ መልሰን እንሰማዋለን። እግዚአብሔርንም «ለምን?» እንለዋለን። ዝም ሲለንም እንበሳጫለን። «ለምን?» ማለት ይግባኝ ማለት ነው። የቀበሌውን ሲቀ መንበር ለምን? ስንለው ወደ ወረዳው እሄዳለሁ ማለታችን ነው። የወረዳውን ለምን? ስንለው ወደ ዞን እሄዳለሁ ማለታችን ነው። የዞኑን ለምን? ስንል ወደ ክልል እሄዳለሁ ማለታችን ነው። የክልሉን ለምን? ስንል ወደ ንጉሡ እሄዳለሁ ማለታችን ነው። ንጉሡን ግን ለምን? አንለውም። የመጨረሻው ዳኝነት እርሱ ነውና። ንጉሥ ከእርሱ በላይ ማንም የለምና ይግባኝ አይባልም። እግዚአብሔርም ንጉሥ ነውና ለምን? አይባልም። እርሱ እግዚአብሔር ስለሆነ የወደደውን ያደርጋል። የሚሆኑት ነገሮች መሆን ስላለባቸው ይሆናሉ። እግዚአብሔርም ፈቃዱ እስኪገባን ሥራውን አያቆምም። ፈቃዱ እየተከናወነ ይገባናል። ፈቃዱ ሲገባን በደስታ እንሞላለን። ፈቃዱ አልገባ ካለን ግን በጥያቄ እንሞላለን።

በማዕበል ለምትንገላታ መርከብ መልሕቋን የምትጥልበት ዓለት ማግኘት ዕረፍት ነው። ከዚያ ሁሉ በላይ ወደቧ ላይ መድረስ አስደሳች ነው። የዚህ ዓለም ጉዳይ ለሚያንገላታት መርከብ ሰውነታችን ፈቃዱን መቀበል መልሕቅን በዓለት ላይ እንደ መጣል ሲሆን ከዚህ ሁሉ በላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ወደሚፈጸምባት ወደ ሰማይ መድረስ ትልቅ ዕረፍት ነው። ሰማይን ሰማይ ያስኛት የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሙሉ በሙሉ የሚፈጸምባት አገር መሆኗ ነው። የሰማይን ተድላ የምንኖረው የእግዚአብሔር ፈቃድ በሙሉነት እንዲገዛን ስንፈቅድ ነው። *«ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን»* (ማቴ.6÷10)።

ነቢዩ ዳዊት ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ምንነት በመዝ.22(23). ላይ ገልጧል። «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው» የሚለውን ይህን ዝማሬ ብዙ ክርስቲያኖች የሚያውቁትና የሚወዱት ነው። በብዙ ታክሲዎች ውስጥ ይህ ጥቅስ ተለጥፏል። መኪናው ላይ እንጂ ሾፌሩ ልብ ላይ

መስጠቱ ግን ያጠራጥራል። በየቤቱ ግድግዳ ላይ ይህ ጥቅስ ተሰጥፎአል። ወረቀቱ የተቀበለውን ያህል የሰዎቹ ልብ ግን አልተቀበለውም። የጥቅስ ፍቅር የመታዘዝ ፍቅር ቢሆን ኖሮ ባረፍን ነበር።

«እግዚአብሔር እረኛዬ ነው÷ የሚያሳጣኝም የለም።
በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤
በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።
ነፍሴን መለሰት÷
ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ።
በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ
አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤
በትርህና ምርኵዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል።
በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ
በጠላቶቼ ፊት ለፊት፤
ራሴን በዘይት ቀባሁ÷
ጽዋዬም የተረፈ ነው።
ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል÷
በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ»
(መዝ.22(23).)።

ነቢዩ ዳዊት እረኝነትን በተግባር ያውቀዋል። እግዚአብሔር እረኛዬ ነው ሲል እርሱ ለበጎቹ የነበረውን ፍቅርና እንክብካቤ እያስታወሰ ነው። እረኛ ማን ነው? እረኛ ጠባቂ ነው። እረኛ በጎቹን ከጠላት ብቻ ሳይሆን ከራሳቸው ሞኝነትም የሚጠብቅ ነው። ይጠቅመናል ብሎው ወደ ገደል ሲሄዱ ዝም አይልም። እረኛ መላሽ ነው። እረኛ ተንከባካቢ ነው። በሰመሰም መስክ፣ በጥሩ ውኃ አጠገብ ያሰማራል። በጎች ስለ ራሳቸው አያስቡም፣ እረኛው ያስብላቸዋል። እረኛ ሐኪም ነው፣ በገደል ስትዘል ከአውሬ ስትሸሽ የተሰበረችውን ያክማል፣ ይጠግናል። በግ ከማንከስ በቀር ራሷን ማከም አትችልም። እረኛው ግን ሐኪሟም ነው። እረኛ ተሸካሚ ነው። ግልገሏን፣ አቅመ ደካማዋን፣ ገመምተኛዋን በግ ጥሏት አይገባም፣ ይሸከማታል። እረኛ የበጎቹን ጠባይ ያውቃል። እንደ ጠባያቸው ብዙ ስሚመገቡ ብዙ፣ ጥቂት ስሚመገቡ ጥቂት እያቀረበ ይመግባቸዋል። እረኛ መሥዋዕት ነው። ከአውሬ ጋር ስለ በጎቹ ሕይወት ሲደራደር የራሱን ሕይወት አያስብም። ነቢዩ እግዚአብሔር እረኛዬ ነው ሲል ይህ ሁሉ ተሰምቶት ነው።

- ጠባቂዬ
- አዛኜ

- ሐኪሜ
- ተሸካሚዬ
- ሸፋኜ ማለቱ ነው።

እረኛ በጎች አይጠግብም። ዘጠና ዘጠኝ በጎች አሉኝ ብሎ በአንዲ መጥፋት አይረጋጋም። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡- *«የሰው ልጅ የጠፋውን ለማዳን መጥቶአልና። ምን ይመስላችኋል? ለአንድ ሰው መቶ በጎች ቢኖሩት ከእነርሱም አንዱ ቢባዝን፣ ዘጠና ዘጠኙን በተራራ ትቶ ሄዶም የባዘነውን አይፈልግምን? ቢያገኘውም እውነት እላችኋለሁ ካልባዘኑቱ ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ በእርሱ ደስ ይለዋል። እንደዚሁ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ በሰማያት ያለው አባታችሁ ፈቃድ አይደለም»* (ማቴ.18÷11-14) በማለት እረኝነቱን ገልጧል።

ከእረኛ አንጻር የቆሙ አሉ። እነርሱም፡- ሙያተኞች (ሠራተኞች፣ ቅጥረኞች)፣ የበግ ነጋዴዎች ናቸው። ሙያተኞች ራሳቸውን ለበጎቹ መሥዋዕት የሚያደርጉ አይደሉም። ተበላ ብሰው ለማውራት የሚችኩሉና ራሳቸውን ከተጠያቂነት ነጻ ለማድረግ የሚጥሩ እንጂ ከአራዊት ታግለው የሚታደጉ አይደሉም (ዮሐ.10÷11-13)። የበግ ነጋዴዎችም መንጋውን ቢነዱም የሚነዱት ወደ ሰምሰም ሣር ሳይሆን ወደ እርድ ስፍራ ነው። በዛሬው ዘመን በማንኛውም መንፈሳዊና ሥጋዊ አስተዳደር ያሉት እረኞች ሳይሆኑ የበግ ነጋዴዎች ናቸው። የበጎቹን ሥጋቸውን ለመብል፣ ቆዳቸውን ለክት ልብስ የሚመኙ፣ ለመንጋው የሚኖሩ ሳይሆኑ መንጋው የሚኖርላቸው ሙያተኞች በዝተዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን፡- *«መልካም እረኛ እኔ ነኝ»* (ዮሐ.10÷11) አለ።

እረኛ ለምን አስፈለገ? ስንል፡-

- *መንጋ ራሱን ማስማራት ስለማይችል፣*
- *መንጋው በአንድነት እንዲገዝና እንዲውል፣*
- ከአውሬ ከነጣቂ ለመታደግ እረኛ ያስፈልጋል።

መንጋ ራሱን ማሰማራት አይችልም። እስካሁን ከእረኛ ነጻ ሆኖ ራሱን የሚያሰማራ መንጋ የለም። ራሳቸውን የሚያሰማሩ በጎች ካሉም ይጠፋሉ፣ በአውሬ ይበላሉ፣ የቤታቸው መመለሻ ጠፍቷቸው ይቅበዘበዛሉ። ስለዚህ የሚያሰማራ እረኛ በግድ ያስፈልጋል። እረኛ ያስፈለገበት ሌላው ነገር መንጋው በአንድነት እንዲገዝና እንዲውል ነው። እረኛ የሌለው መንጋ ወደሚግጥበት አቅጣጫ ስለሚገዝ ይበተናል። እረኛው ግን ሲራራቁ ይሰበስባል። እረኛ ከአውሬ ከነጣቂ

ስለሚታደግ አስፈላጊ ነው። ዳዊት ተጠሪነት የሌለው ሕይወት የሚኖር አልነበረም። እግዚአብሔር እረኛው ስለነበር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚመላለስ ሰው ነበር።

ነገ ምን መሆኑን አናውቅም። ዓለሙንም አናውቀውም፣ በመልካም ዕድል ውስጥ የተቀመጠውንም ክፉ ነገር አናውቅም። ስለዚህ እረኛ ያስፈልገናል። ወታደር የጦር መሪ፣ ተማሪ አስተማሪ፣ መንጋ እረኛ፣ ክርስቲያን አምላክ አለው። ራሳችንን ስናሰማራና በፈቃዳችን የኖርን ስለሆንን ትዋቃችንን ጨርሰናል። ጉልበታችን ደክሟል። የሚያሳቅቅ ትዝታ አትርፈናል። የኃጢአት የግፍ ታሪክ ባለቤቶች ሆነናል። የሕይወታችን ካፒቴን ሊሆን የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ነው። በማስተዋላችን ሳይሆን በማስተዋሉ ሊያኖረን ይገባል፣ የእኛ የምርጫ እውቀታችን ዳቦ የመረጠ መስሉት ድንጋይ የሚያነሣ፣ ዓሣ መረጥኩ ብሎ እባብ የሚያጠምድ ነው። ብዙ የማንችላቸው ነገሮች ቢኖሩም ከማንችላቸው ነገሮች አንዱ «መምረጥ» አለመቻላችን ነው። በበሽታ የተሰከፈውን ሰው እስቡት ለደስታው የመጨረሻውን የመረጠ ነው። አስር ቤት የወረደውን ሰው አስቡ። ሰራሱ አስቦ አስቦ የገባ ነው። ብዙ የውድቀት ስፍራዎችን ስናይ ሰው ሰራሱ መምረጥ እንደማይችል ያስረዳሉ። እግዚአብሔር ይምረጥልን። የሚውሉበትን ቦታ የሚወስኑ በጎች የሉም። በእረኛቸው ፈቃድ ይውላሉ፣ ስለዚህ ከስረው አያውቁም። ዛሬ እንኳ መቆም አለብን። ራሳችንን እንዳናሰማራና «ወይኔን» እትርፈን እንዳንገባ መጠንቀቅ አለብን። በእውነት እግዚአብሔርን እየተከተልን ነው ወይስ እንዲከተሰን እየጋበዝነው ነው? ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን።

አዎ እግዚአብሔርን አረኛ ማድረግ ማለት ፈቃዳችንን ለፈቃዱ መተው ማለት ነው። እግዚአብሔርን አዳኜ ማለት አልከበደንም። ጌታዬ ብለንም የሚጎዳንን ነገር ሁሉ እየተውን ነው። እረኛዬ ብለን ደግሞ ፈቃዳችንን ለፈቃዱ መተው ይገባናል። «የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወትህ እንዲከናወን አንተ ፈቃድ አይኑርህ!» የሚባለውን ማስተዋል ይገባናል። ነቢዩ «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው» አለ። ራሴን አላሰማራም ማለቱ ነው። መንጋ ጠዋት ከበረት ሲወጣ የት እንደሚውል አያውቅም። በእረኛው ፈቃድ ለመዋል ይወጣል፣ ረክቶ ይገባል። ያመነውን መንጋ ሰአራዊት የሰጠ እረኛ ሰምተን አናውቅም። ትንሹ እረኛ እንዲህ ከሆነ ትልቁ እረኛማ የሚከተሉትን እንዴት ወደ ገደል ይመራል?

ወዴት እንደምንሄድ የማናውቅ፣ ቀጣዩ የዓለም ገጽታ ምን መሆኑን ማስረዳ የሌለን ልንሆን እንችላለን። ይህን ማወቅ ለእኛ

አስፈላጊያችን አይደለም። የእኛ ድርሻ እግዚአብሔርን መከተል ብቻ ነው። እርሱን ስንከተል የሚሆነው ቢሆን አያሳስበንም። እግዚአብሔርን ተከትለን ብንከሰር እንኳ ዋስትና አለን። የእግዚአብሔር ፈቃድ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም።

1. <u>ፈቃዱ ቅዱስ ነው</u>:- ፈቃዱ ከቅዱስነቱ ውስጥ ይወጣል። እንከን የለውም። ሁልጊዜ ትክክል ነው። የሰው ፈቃድ ግን በኃጢአት ከረከሰው ማንነቱ ይወጣል። ዙሪያ ገባውን ማየት የማይችል ከቆመበት አንጻር ብቻ የሚያይ፣ ሙሉነት የጎደለው፣ በአጋጣሚ እንጂ ሁልጊዜ ትክክል ያልሆነ፣ የሚያፀፅት ነገር የማይታጣበት ነው።

2. <u>ፈቃዱ ነገሮችን ሁሉ የመቆጣጠር አቅም አለው</u>:- ፈቃዱ በእስር፣ በበሽታ፣ በምርኮ፣ በስደት ማሰፍ ቢሆን እንኳ ይህን የመቆጣጠር አቅም አለው። ችግሮችን የእግዚአብሔር ፈቃድ ባይቆጣጠር ኖሮ ማንም አይኖርም ነበር። የሰው ፈቃድ ግን ፈቅዶ አንድ ነገር ማድረግ ቢችልም የነገሩን ሂደት ግን መቆጣጠር አይችልም። ነገሩ ራሱ ሰውዬውን መቆጣጠር ይጀምራል።

3. <u>ፈቃዱ በመጨረሻ ይፀናል</u>:- ጠቢባን በጥበባቸው፣ ኃያላን በኃይላቸው ይጓዛሉ። በመጨረሻ ግን የምታሸንፈው የእግዚአብሔር ፈቃድ ናት። በዚህ ዓለም ላይ የምንኖረው እንደምንፈልገው ሳይሆን እንደ ተፈቀደልን ነው። እንደ ፈቃዳችን እዚህ አገር፣ በዚህ የኑሮ ደረጃ አልነበርንም። የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን ገድባናለች። ይህ መልካም ነው። እግዚአብሔር ከፈቀደው ውስጥ ምንም ክፉ የለም። *«የጌታ ፈቃድ ይሁን ብለን ዝም አልን»* (የሐዋ.ሥራ 21÷14)። ምንም አስተያየት ሳንሰጥ እንዲህና እንዲያ የሚሉ ግምቶችን ሳንሰነዝር በፈቃዱ ተስማምተን ማረፍ ይገባናል። *«ሰው ዝም ብሎ የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ ቢያደርግ መልካም ነው»* (ሰቆ.ኤር 3÷26)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ምንም ነገር ጥያቄ እንዳይሆንብን ነው። ሕመማችን፣ እስራታችን፣ ስደታችን ... ጥያቄ እንዳይሆንብን ወደ ዓለም መጥቷል። የጥያቄዎቻችንም ሙሉ መልስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አዎ የእግዚአብሔር ፈቃድ ፍጻሜው ያማረ ነው። የሰው ፈቃድ ግን ጅምሩ ያምራል፣ በዓለም ላይ ያለው ትልቁ ችግር ያጨራረሰ ችግር ነው። ስለዚህ ነው «መጨረሻዬን

አሳምርልኝ» «የማታ እንጀራ ስጠኝ» እየተባለ የሚጸለየው። ብዙዎች የወጣትነት ዘመናቸውን በሥልጣን፣ በሀብት ያሳልፉና የሽምግልና ዕድሜያቸውን በአስራት በድህነት ያሳልፋሉ። *«የነገር ፍጻሜ ከመጀመሪያው ይሻላል»* (መክ. 7÷8)። የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን ፍጻሜው ያምራል። ስለዚህ ለዚህ ታላቅ ፈቃድ እጅ መስጠት አለብን። አንድ አባት የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድን ነው? ቢሏቸው «የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢጥምም ባይጥምም ነው» ብለዋል። እኛን ደስ ያለን ብቻ ሳይሆን የከፋንም ነገር ፈቃዱ ሊሆን ይችላል።

እም ገዝ ለሆነችው የእግዚአብሔር ፈቃድ መማረክ ያስፈልጋል። ወታደር ጠላት በቁረጣ ገብቶበት ወይም ስንቅና ትጥቅ አልቆበት አሊያም ልቡ ወደ ጠላቱ አዘንብሎበት ይማረካል። ትጥቁን ጨርሶ አንዳንዴ ከነትጥቁ ይማረካል። እኛም ትጥቃችንን ጨርሰን እንደሆነ ትጥቃችንን ካልጨረስንም ለእግዚአብሔር ፈቃድ መማረክ አለብን። «የማይጋፉትን ግንብ ዞረው ያልፉታል» እንዲሉ።

ራሳችንን ስንረሳው፣ የመጨረሻውን ትንሽ ነገር ስንመርጥ እግዚአብሔር ያስታውሰናል። ከፍ ያለውን ይመርጥልናል። «ጌታ ሆይ ሰላም ይስማኝ ደግሞም ካንተ ጋር ይሁን እንጂ በላስቲክ ቤትም ለመኖር ወስኛለሁ» ልንለው ይገባል። ነቢዩ ዳዊት *«እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ፣ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል»* (መዝ.126÷1) ብሏል። እግዚአብሔር ለእኛ ቤት፣ እኛ ለእግዚአብሔር ቤት ልንኖር ይገባል። ኑሮን ካልተሰዋወጥን እየጎደለ መንቦጫቦጩ አይቀርም። ያለ እግዚአብሔር ሁሉም ነገር የአሳብ መስመርና የአየር ላይ ቤት ነው።

ይህን ዓለም እየመራ ያለ የእግዚአብሔር ስውር እጅ ነው። ነገሥታት ቅንጣት ያህል የማያዙባቸውን ፀሐይና አየርን የሚያዝዝ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ፈቃዱ የታሪክንም ጉዞ ይቆጣጠራል።

ፈቃዱን ማወቅና እግዚአብሔርን እረኛ ማድረግ ማለት ሙሉ ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር ማስረከብ፣ እርሱ በወደደው እንዲያውለንና እንዲያኖረን መፍቀድ፣ «አንተ የመረጥኸው አይቆረቁረኝም፣ የወሰንከውን እቀበላለሁ» ማለት፣ የሕይወታችንን ሙሉ ክፍል ለኢየሱስ ክርስቶስ ማስረከብ ነው።

ስውየው ዐሥር ክፍል ቤት ሠርቶ ብቻውን ሲኖር አንድ ቀን በር ተንኳኳ ሲከፍት ጌታ ነው። «ውይ ጌታዬ አንተ እኔ ቤት መጣህ?» ብሎ በደስታ ተቀብሎት አንድ ክፍል ቤት ሰጥቶት መኖር ጀመሩ። በሌላ ጊዜ በሩ ተንኳኳ፣ ሲከፍት ሰይጣን ነው። ተበሳጭቶ

ይዘጋና «ጌታዬ ሆይ አንተ እኔ ቤት እያለህ ሰይጣን የእኔን ቤት እንዴት ያንኳኳል?» አለው። ጌታም «ቤቱ የአንተ እንጂ የእኔ አይደለም» አለው። ስውየውም ተስምቶት ሁለት ክፍል ቤት ለጌታ ጨምሮለት እርሱ ሰባት ክፍል ይዞ መኖር ቀጠሉ። በሩ ግን ተንኳኳ ሲከፈት ሰይጣን ነው። ተበሳጭቶ ይዘጋና «ጌታዬ ሆይ አንተ እኔ ቤት እያለህ ሰይጣን የእኔን ቤት እንዴት ያንኳኳል?» አለው። ጌታም «ቤቱ የአንተ እንጂ የእኔ አይደለም» አለው። ስውየውም ተስምቶት ከጌታ ጋር እኩል ለእኩል ተካፈሉ። ነገር ግን ቤቱ ከቀድሞ ይልቅ ተንኳኳ። አዝኖም ይዘጋና ጌታ ሆይ አለው። ጌታም የቀድሞውን መልስ ሰጠው። በዚህ ጊዜ ስውየው ለራሱ አንድ ክፍል ቤት ይዞ ዘጠኙን ክፍል ቤት ለጌታ ሰጠው። ነገር ግን ከቀድሞው ይልቅ በጣም ተንኳኳ። ቢከፈት ሰይጣን ነው። በሩን ይዘጋና ወደ ጌታ ሄዶ «ጌታ ሆይ ምሥጢሩ ምንድን ነው?» አለው። «ጌታ ግን ቤቱ የአንተ እንጂ የእኔ አይደለም» አለው። በዚህ ጊዜ ዐሥሩንም ክፍል ለጌታ አስረከበ። ጌታም አንድ ክፍል ቤት ለስውየው ሰጠው። በሩም ተንኳኳ። ጌታም ሊከፍት ተነሣ። ሲከፍት ሰይጣን ነው። ሰይጣንም «ይቅርታ የአንተ ቤት መሆኑን አላወቅሁም» ብሎ ሄደ። ከዚያን ቀን ጀምሮ መንኳኳት ቆመ።

ሁሉንም የሕይወታችንን ክፍል ለጌታ ካላስረከብነው መንኳኳት አይቆምም። 10% ስንሰጥ ይንኳኳል። 30% ስንሰጥ ይንኳኳል። 50% ስንሰጥ ይንኳኳል። 99% ስንሰጥ ይበልጥ ይንኳኳል። 100% ስንሰጥ መንኳኳት ይቆማል። እኛ ከከፈትን ለይጣን ይገዳደረናል። ጌታን ክፈት ካልነው ግን ጌታ ሲከፍት ሰይጣን «ይቅርታ የአንተ ቤት መሆኑን አላወቅሁም» ብሎ ይሄዳል።

ነቢዩ ራሴን ፈርሜ አስረክቤሃለሁ፣ በምትሄድበት እከተልሃለሁ ሲል «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው» አለ። በመቀጠልም «የሚያሳጣኝም የለም» አለ። እግዚአብሔርን በእውነት ስንከተል የምናጣው ነገር የለም። በሌላ ስፍራ «ልባቸው ለቀና ለእስራኤል እግዚአብሔር እንዴት ቸር ነው» (መዝ.72(73)÷1) ይላል።

«በለመለመ መስክ ያሰማራኛል፣ በዕረፍት ውሃ ዘንድ ይመራኛል» (መዝ.22÷2)። እረኛ በጎቹን የሚያሰማራው በእንዲህ ያለ ጥጋብና እርካታ ስፍራ ነው። ሰምለም መስክ ለዓይንም ለሆድም ጥጋብ ነው። እግዚአብሔርን ስንከተል የሚሰጠን መልካም ነገር በሥጋም በነፍስም የሚያስደስት ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን «ይበቃኛል» አስኝቶን የሚያረካን ነው።

«ነፍሴን መለሳት፣ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ» (መዝ.22÷3)። እረኛ በጎቹ ሲባዝኑ በድምፅ አልያም በበትሩ

ይመልሳል። እግዚአብሔርም ከመንገዱ ስንወጣ በቃሉ፣ እምቢ ስንልም በቅጣት ይመልሰናል። ሁለቱንም ሥልጣን የሚጠቀም እግዚአብሔር ነው።

«በምት ጥላ መካከል እንኳን ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል» (መዝ.22÷4)። እረኛ ከበጎቹ ጋር ካለ በጎቹ በነጻነት ሣር ይግጣሉ። በመንገድም ሲሄዱ አይገለማመጡት። እነ ሚዳቋና ዋልያ ግን ውኃን ለመጎንጨት ግራና ቀኝ ይገለማመጣሉ። ራሳቸውን ስለሚጠብቁ ዕረፍት የላቸውም። እግዚአብሔርን የሚከተል በመተማመን ይኖራል። ሞትና ክፉ ነገር እንኳን አያስፈራውም። በእረኛው እጅ ያለው በትር በእግዚአብሔር እጅ ያለው ቃሉን የሚያሳይ ነው። በትርና ምርኩዝ አጠቃቀም ሲሆን በትሩ ምርኩዝ፣ ምርኩዙ በትር ይሆናል። ጠላት ሲመጣ በትር፣ ድካም ሲመጣ መደገፊያ /ምርኩዝ/ ይሆናል። እንዲሁም ቃሉ የሰይጣንን ድምፆችና ውጊያዎች የምናባርርበት በትር፣ የምንጽናናበትም ምርኩዝ ነው።

«በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት፣ ራሴን በዘይት ቀባህ፣ ጽዋዬም የተረፈ ነው» (መዝ.22÷5)። እግዚአብሔር ፈቃዳቸውን በፈቃዱ ለለወጡ ሰዎች ገበታን ያዘጋጃል። እንደ ዛሬው ቍርጥ እንደሚባለውና እንደሚያቆራርጠው (እንደሚለያየው) ያለ ማዕድ ሳይሆን እንደ ጥንቱ የሚሰበሰብ፣ አንድ የሚያደርግ፣ የተትረፈረፈ ገበታን እግዚአብሔር ያዘጋጃል። እግዚአብሔር ገበታን የሚያዘጋጀው ጠላት ዓይኑ እያየ ነው። የገበታውን መዘጋጀት ከእኛ በፊት የሚያየው ሰይጣን ስለሆነ ከዚያ ገበታ እንዳንቋደስ ብዙ ፈተናና መከራ ያመጣብናል። ገበታችን ሲሰናዳ ፈተና ይበዛብናልና አዋቂ መሆን ይገባናል። ነቢዩ «ራሴን በዘይት ቀባህ፣ ጽዋዬም የተረፈ ነው» አለ። ዘይት ሹመት፣ ክብረት ነው። እንደ ፈቃዱ ለሚጓዙት እግዚአብሔር ለትልቅ ኃላፊነት ያጫቸዋል። ጽዋ (በረከቱም) የተትረፈረፈ ነው።

«ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፣ በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ» (መዝ.22÷6)። ነቢዩ ክፍሉን ሲጀምር «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው» አለ። እኔ እርሱን እከተላለሁ ማለቱ ነው። አሁን ደግሞ ቸርነትና ምሕረት እኔን ይከተሉኛል አለ። ተራው እንዲህ ነው፣ እኛ እግዚአብሔርን ስንከተል ፍላጎታችን እኛን ይከተለናል። እግዚአብሔርን መከተል ትተን ከኋላችን የሚከተለንን በረከት ብንከተል ግን እንሽከረከራለን እንጂ አናገኘውም። የሚከተለንን መከተል መሽከርከር ነው። በአገልግሎት ሕይወትም ነፍሳትን መከተል የለብንም። የእኛ ድርሻ እግዚአብሔርን በትክክል መከተል ነው። እርሱን ስንከተል

የሚከተለው ይከተለናል። ነፍሳትም በመዓዛችን ይከተሉናል። *«ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል»* (ማር. 16÷17) ይላል። ተአምራትና ምልክትንም መከተል የለብንም። እኛ በእምነት ጌታን ስንከተል እነርሱ ይከተሉናል።

ነቢዩ «በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ» አለ። የቸርነትና የበረከት ዓላማው በእግዚአብሔር ቤት እንድንኖር እንጂ ነጥቀን እንድንሮጥ አይደለም። የእግዚአብሔርን በረከት በእግዚአብሔር ቤት መመገብ ተገቢ ነው።

<u>የጽሞና ጊዜ</u>

ለብዙ ዘመን የራስህ ምርጫ ሲያፀፅትህ ኖሯል። ስለዚህ ያልኩት ይሁን ብለህ ብዙም አትበሳጭ። እግዚአብሔር ያለው ሲሆን ይሻላል። በራስህ ፈቃድ ወደዚህ ዓለም እንዳልመጣህ በራስህ ፈቃድም አትኖርም። አንድ ቀንም ያለፈቃድህ ከዚህ ዓለም ትሄዳለህና «ፈቃድህ ይሁን» በል። ሰማይን የደስታ አገር ያደረጋት ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ የጸናባት በመሆኗ ነው። ባንተም ሕይወት የሰማይ ደስታ የሚመጣው የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወትህ ሙሉ በሙሉ ሲፈጸም ነው። ስለዚህ፦

- እግዚአብሔርን እረኛ አድርገው።
- በፍጹም ልብህ ተከተለው።
- የሚያስፈልጉህ ነገሮችም አንተን ይከተሉሃል።

<u>ጸሎት</u>

ምክር የማይሰጠህ ጥበበኛ፣ ፍርድ የማያስተምሩህ እውነተኛ፣ የራስህ ፈቃድ ያለህ ትክክለኛ፣ ሁልጊዜ ያልከው ትክክል የሚሆንልህ ቀጥተኛ አቤቱ ጌታዬ አመሰግንሃለሁ። የእኔን ፈቃድ ታውቀዋለህ። የመረጥኳቸውን ሰዎች ታውቃለህ። ዓላ ያዝኩ ብዬ እባብ ስጨብጥ ኖሬአለሁ። በማላውቀው ዓለም ላይ እንደ አዋቂ መራጭ መሆኔ ደክሞኛል። የመረጥከውን አንተ ስጠኝ። የእኔ ፈቃድ መጀመሪያው ያምራል፣ ፍጻሜው ግን መራራ ነው። የእንተ ፈቃድ ግን ከፊት ይመራል። ኋላ ግን ይጣፍጣል። ፍጻሜና ተስፋ ያለው የአንተ አሳብ ይሻለኛልና በአሳብህ አኑረኝ። በዘላለማዊ ክብርህ አሜን።

ምዕራፍ ዘጠኝ
የነበር ዓለም

እቴጌ ጣይቱ ከሚኒልክ ጋር ሆነው ፈላጭ ቆራጭ የነበሩ ተፈርተውና ተከብረው የኖሩ ሴት ናቸው። ይህ መፈራትና ክብር ግን እስከ መጨረሻው አልዘለቀም። ሚኒልክ ታምመው አልጋ ላይ በቀሩ ጊዜ ንግሥቲቱ ዐርፈው ሲቀመጡ ስላልቻሉ መኳንንቱ መክረው ከቤተ መንግሥት እንዲወጡና ለመታሰቢያ በተሠራላቸው በመንበረ ፀሐይ እንጦጦ ማርያም እንዲቀመጡ ወሰኑባቸው። እቴጌ ጣይቱም ከአምስት ደንገጡሮች ጋር ሆነው የመከራና የሀዘን ኑሮአቸውን ሲኖሩ፦

«ተወድዶ ከመኖር ተጠልቶ መውለድ፣
ማን ያይብኝ ነበር ይህን ሁሉ ጉድ፤»

በማለት ገጥመው እንደነበር ይነገራል። አንድ ቀንም የመስቀል ዋዜማ የደመራ ዕለት አዲስ አበባን ቁልቁል እያዩ የአሁኑንና ያለፈውን ኑሮ ሲያነጻጽሩ በትዝታ ጠፉ። «ይህን ጊዜ ሚኒልክ እዚህ ጋ ተቀምጠው፣ እኔ በቀኛቸው ተቀምጬ፣ ፊታውራሪ እገሌ በዚህ ጋ ደጃች እገሌ እዚህ ጋ ተቀምጠው፣ ሠራዊቱ እኔና ሚኒልክን እጅ እየነሣን ሲያልፍ ጳጳሱ ተነሥተው ደመራውን ሲባርኩ . . .» እሱና «ወይ ጉድ ነበር ለካ እንዲህ ቅርብ ነው ወይ?» እሱ ይባላል። እም ነበር ቅርብ ነው። ትላንትም ነበር ነው።

ሐዋርያው ጴጥሮስ *«ሥጋ ሁሉ እንደ ሣር ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ነውና፣ ሣሩ ይጠወልጋል፣ አበባውም ይረግፋል፣ የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል»* (1ጴጥ.1÷24) ብሏል። ሣር አረንጓዴ ነው። አበባውም ልዩ ልዩ ሕብረ ቀለም ያለው ነው። ቅጠሉ ለምለም፣ አበባውም ማራኪ ነው። ቅጠሉ ይቀድማል፣ አበባው ይከተላል። ነገር ግን ከቀደመው ቅጠል የኋላው አበባ ለመርገፍ ይቸኩላል። በዕድሜ ቢለያዩም ሁለቱም ይጠወልጋሉ፣ ይረግፋሉ። ቅጠሉ የሥጋ፣ አበባው የክብር ምሳሌ ነው። ቅጠሉ ተመሳሳይ እንደ ሆነ ሰውም በአፈጣጠሩ ተመሳሳይ ነው። ልዩነቱ በአኗኗሩ ነው። ቅጠሉ ስላለ አበባው ይመጣል። ሰውነት ስላለ ክብር ይመጣል። ቅጠሉ እንደሚጠወልግ ሰውም ይጠወልጋል። ክብሩም ይረግፋል። እንደውም አበባ ሲረግፍ ሲል ያምራል። ሰውም መውደቂያው ሲደርስ ያሳሳል። የእግዚአብሔር ቃል ግን የማለፍን ሥርዓት ተቋቁሞ ለዘላለም ይኖራል።

ሀብት እንደ ሕልም ነው፣ ይጠፋል፤ ክብርም እንደ ጉም ነው፣ ይበናል፤ ወዳጅ የጢስ ምሰሶ ነው፣ ቢያምርም ድጋፍ አይሆንም፤ ትዳርም ይፈርሳል፣ የሚወዱን ይጠሉናል፣ የሚጠሉንም ይወዱናል፣ የቆመ ይወድቃል፣ የወደቀም ይነሣል፣ ጓደኛ ጉደኛ ይሆናል፣ ሥልጣን ይሻራል፣ ዝና ይቀራል፣ ውበት ይረግፋል፣ ተወዳጅነት ያበቃል፣ ጀግንነት ይረሳል፣ ውለታ አመድ ይደፋበታል፣ ወጣትነት ያልፋል፣ የሚያረዳ ይሞታል፣ ሳቅ ይለወጣል፣ ሀዘን ይረሳል፣ ጉስቍልና ይራገፋል፣ ሰ፪ነት ይቀራል፣ መቀበልም ያክትማል፣ ገዢ ያልፍበታል፣ ሀብታም ያልቅበታል፣ ጀግና ይሸነፋል፣ ብልሀ ይሳሳታል፣ ቆንጆ ይበላሻል፣ ጠበቃ ይረታል፣ ዳኛ ይፈረድበታል፣ ጤናማን ያመዋል፣ ሐኪምም ይሞታል። እም በዓለም ላይ ሁሉም ያልፋል። እግዚአብሔር ግን በዙፋኑ ሆኖ ሁሉን ያሳልፋል።

ዓለም የነበር ዓለም ነው። ሁሉም ነገር ነበር ለመባል ይቸኩላል። ሁሉ ማለፉ፣ ሁሉም መለወጡ፣ የፀሐይን ትኩሳት እንደማይቋቋም እንደ ጠዋት ጤዛ ሁሉም ነገር ቶሎ መርገፉ፣ የዓለም ከንቱነት የሰማዩ ክብረት፣ የማንነቱ ከንቱነት የእግዚአብሔር ብርቱነት ለማን ተገልጸአል? ሁሉም ነገር ከንቱነት እዝሎ እንደሚዞር ከትውልዱ ማን አስተውሏል? እም ዛሬ ላይ የሌሉ፣ በአንድ ዘመን የገዘፉ፣ አሁን ግን መንፈስ የሆኑ፣ ተጨባጭነት የሌላቸው፣ እሱ ብለን የማንደራደርባቸው፣ ይመጣሉ ብለን ተስፋ የማናደርጋቸው፣ ከዚህ በፊት የነበሩ የማይመስሉ፣ የትዝታ እሹሩሩዎች፣ የታሪክ መማሪያዎች «ነበር» በሚለው ቃል ይጠቃለላሉ።

አንቺ ዓለም አንቺ ዓለም፣
የጀመረሽ እንጂ የጨረስሽ የለም፤

ታሪክና ትውልድ ተጓዥ መንገደኛ ነው። ታሪክ ያልፋል፣ ታሪክ ይተካል፣ ትውልድ ያልፋል ትውልድ ይመጣል። ዘመን ከሸማኔ መወርወሪያ ይልቅ ይፈጥናል። እግዚአብሔር የሌለበት ሁሉ የእንባይ ካብ ነውና ሲናድ ይቸኩላል። በንጉሡ ፊት ስላምታ እየሰጡ እንደሚያልፉ ሠራዊቶች ታሪክና ትውልድ በእግዚአብሔር ፊት እንዲህ ያልፋሉ። እም ዓለሙ የነበር ዓለም ነው። ከነፋስ ይልቅ የሚፈጥን ዓለም ነው። የነበረው እንዳልነበር ለመሆን ይቸኩላል። ያለፈው የነበረ አይመስልም። ያለውም አምሮና ተውቦ፣ ገዝፎና ተንጣሎ ሲታይ የሚያልፍ አይመስልም። ትላንት ለዛሬ ነበር እንደሆነች ዛሬም ለነገ ነበር ናት። ዛሬ ተረት የሆኑት የትላንት ብርቱዎች ናቸው። ዛሬ ለሕጻናት የሚተረኩት ትላንት ስማቸውን

ለመጥራት እጅ መንሣት የሚጠይቁ ነበሩ። «ነበር» የሚባለው በእውነት የነበረ ነገር ነው። የዛሬውም ነገ ላይ ነበር ይባላል። በዚህ ዓለም እንደ ነበረ የኖረ ማንም የለም። እንዳለ ያለ እግዚአብሔር ብቻ ነው። *«ለቤቱ፥ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥ ለማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው። እነርሱ ይጠፋሉ፥ አንተ ግን ትኖራለህ፤ ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፥ እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፥ ይለወጡማል። አንተ ግን ያው አንተ ነህ። ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም»* (መዝ.101/102/÷25-27)።

በዚህ በገሀዱ ዓለም ላይ የሚገዛ አንድ ገዥ አለ። ይህ ገዥ ወኪል ሲሆን የወከለውም እግዚአብሔር ነው። ይህ ገዥ አሳላፊ ይባላል። አሳላፊ ነውና ጽዋ ይለጣል፣ ጽዋ ይነጥቃል። አሳላፊ ከእግዚአብሔር የተሾመ ትልቅ ባለሥልጣን ነው። አሳላፊ በሚገዛበት ዓለም አበባ የተለጣቸው አፈር ተበትኖባቸዋል። የተሳሙ ለዎች ተነክለዋል። የተከበሩ ተዋርደዋል። የተዘፈነላቸው ሹሞች ሌባ ሌባ ተብለዋል። በወረተኛዋ ዓለም ያመኑ ዓለሚን የማያውቁ ብዙዎች በብስጭት ሞተዋል። የለው ጎበዝ፣ የለው ብርቱ፣ የለው ጀግና የለውም። ቀን ነው ጎበዝ! ዘመን ግን መንገደኛ ነውና ያልፋል። ዘመን ሲያልፍ የተወደደው ይጠላል፣ የቆመው ዛፍ ማንም ሳይነካው ይወድቃል።

ሀብት ንብረት ይጠፋል፣ ውበትም ብላሽ ነው ይረግፋል። ጊዜና ዘመን ሲለዋወጥ በመለኮታዊ ድምቀቱ የሚኖር እግዚአብሔር ብቻ ነው። ባለጠጎች ባዶ እጃቸውን ቀርተዋል፣ ጌቶች ከርታታ ሆነዋል፣ የተከበሩት ተዋርደዋል፣ ብዙ ምሁራን በጎዳና ወድቀዋል። «መልክ ምስክር ያሻዋል» ይባላል። ሲበላሽ ቅሬታ እንኳን የለውም። «ለው ማንን ይመስላል?» ተብሎ ቢጠየቅ «ኑሮውን» ተብሏል። የብዙ ቆንጆዎች መልክ ጠፍቶናል። ዛሬ የሚለምኑት የትላንት ባለጠጎች ነበሩ። ስንቱን ግብር ያበሉ ዛሬ ይለምናሉ። ጠዋት ሚሊየነር ከሰዓት በኋላ ለማኝ የሆኑ ለዎችን እናውቃለን።

ባለፈው ዘመን ቋሚ ሥራ ማግኘት ያኮራል፣ ዋስ መሆን ያስችላል። ስለዚህ ቋሚ ሥራ አለኝ በማለት በኮንትራቱ መኩራት የተለመደ ነበር። ቋሚ አንድ አምላክ ብቻ መሆኑን ግን በዓይናችን አይተናል። እንኳን ሠራተኛው ፋብሪካውም ሲዘጋ አስተውለናል። ዛሬ ደግሞ የራስ ቤት ቋሚ ነው እንላለን። ግን እንኳን ቤቱ እኛም ቋሚ አይደለንም።

የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት እንደ ተካሄደ መደገም እንደ ሌለበት ሁሉም አምኗል። ሠላሳ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ግን ሁለተኛው

የዓለም ጦርነት ተደገመ። የአንደኛውን የዓለም ጦርነት ያካሄደ ትውልድ ነው ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት የደገመው። የለው ልጅ እግዚአብሔር ካልመከረው ከታሪክ አይማርም።

ጠቢቡ ለሎሞን *«ከንቱ÷ ከንቱ÷ የከንቱ ከንቱ፤ ሁሉ ከንቱ ነው ይላል። ከፀሐይ በታች በሚደክምበት ድካም ሁሉ የለው ትርፉ ምንድር ነው? ትውልድ ይሄዳል፥ ትውልድ ይመጣል ምድር ግን ለዘላለም ነው። ፀሐይ ትወጣለች፥ ፀሐይም ትገባለች፥ ወደምትወጣበትም ስፍራ ትቸኩላለች። ነፋስ ወደ ደቡብ ይሄዳል፥ ወደ ሰሜንም ይዞራል። ዘወትር በዙሪቱ ይዞራል። ነፋሱም በዙሪቱ ደግሞ ይመለሳል። ፈሳሾች ሁሉ ወደ ባሕር ይሄዳሉ፥ ባሕሩ ግን አይሞላም። ፈሳሾች ወደሚሄዱበት ስፍራ እንደ ገና ወደዚያ ይመለሳሉ። ነገር ሁሉ ያደክማል፤ ለው ይናገረው ዘንድ አይችልም፤ ዓይን ከማየት አይጠግብም፥ ጆሮም ከመስማት አይሞላም»* (መክ.1÷2-8) ብሏል።

ለሎሞን ሁሉም ከንቱ ነው አለ። ከንቱ ማለት ባዶ ማለት ነው። ሥልጣን በሩቁ ትልቅ ይመስላል፣ ሲይዙት ግን ባዶ ነው። ሀብት በሩቁ ትልቅ ይመስላል፣ የጥያቄ መልስ ሳይሆን በራሱ ጥያቄ ነው። እውቀት ትልቅ ይመስላል፣ ይደረስበታል ግን ባዶ ነው። ታዲያ ባዶ ከሆነ ማወቅ ለምን ያስፈልጋል? ቢባል ባዶውንም ባዶ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። ዓለም ከንቱ ነው የሚሉ ድሆችና ምንም የሌላቸው ምስኪኖች አይደሉም። ጠቢቡ፣ ንጉሡና ባለጠጋው ለሎሞን ነው፡- «ከንቱ÷ ከንቱ ÷የከንቱ ከንቱ፤ ሁሉ ከንቱ ነው» ያለው። እንደውም ድሆች በባለጠጎች ይቀናሉ። እንደ እነርሱ እስኪሆኑ እንቅልፍ ያጣሉ። ዓለም ከንቱ ነው የሚሉ ያዩትና ሳያዩም በእምነት ሁሉን የናቁ ለዎች ብቻ ናቸው።

ታላቁ እስክንድር የዓለምን ከንቱነት፣ የንብረትን ጠፊነት፣ የለውን ኃላፊነት መርምሮ ሲሞት «እጄን ወደ ደጅ አውጥታችሁ ቅበሩኝ» በማለት ተናዘዘ። እንዴት ያለ ኑሣዜ ነው? ቢሉት «ከዚህ ዓለም ምንም ይዤ አለመሄዴን ለዎች ሁሉ እንዲያውቁልኝ ነው» አለ ይባላል። ዓለም ከንቱ መሆኑን ብርቱና ኃያላኖች የመለከሩት ነው።

ብዙ ፈላስፎች ዓለም ከንቱ መሆኑን ተናግረዋል። ኃላፊነቱን ተረድተውም እንደ መናኝ ኖረዋል። እነርሱ ዓለም ከንቱ ነው ያሉት ተስፋ ቆርጠው፣ አዝነውና ተበሳጭተው፣ የሚያዩትንና የሚለሙትን መቋቋም አቅቷቸው ነው። እኛ ግን ዓለም ከንቱ ነው የምንለው ዓለምን በዓለም፣ ንጉሥን በንጉሥ ንቀን ነው። ዓለም

ኃላፊ መሆኑን እንጠራጠርም። ለብዙዎች ሲያልፍባቸው አይተናል። እነ እስክንድር፣ እነ ቄሣር፣ እነ ናፖልዮን፣ እነ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሕያው ምስክሮቻችን ናቸው። ለእነርሱ ያለፈ ዓለም ለእኛማ በደንብ ያልፍብናል። ሁሉም ነገር ለመለወጥ ተሸናፊ ነው።

ዓለም ኃላፊ ነው ብለን ስንናገር ብዙዎች ስቀዋል። ምንም እንበለው ሉናሚም እንበለው ዓለም እያለፈ ነው ያለው። ዛሬ በዓለማችን ላይ ያሉት የጦር መሣሪያዎች ዓለምን አንድ ጊዜ አይደለም እየደጋገሙ ከ50 ሺህ ጊዜ በላይ ሊያጠፏት እንደሚችሉ ተረጋግጧል። ታዲያ ለአንዱው ማለፍ ምን ይደንቀናል?

ሰሎሞን ከንቱ ነው አለ። በዓለም ላይ ሥልጣን፣ እውቀትና ገንዘብ ትልቅ ስፍራ ይሰጣቸዋል። ሰዎች የአንዱ ባለቤት እንኳ መሆንን ይመኛሉ። ሰሎሞን ግን ንጉሥ፣ ጠቢብና ባለጠጋ ነበር። በዘመኑ እስራኤልን በታላቅ ሰላምና ዕረፍት የመራ ንጉሥ ነው። የስሙ ትርጓሜ እንኳ ሰላማዊ ማለት ነው። ሰሎሞን ከእርሱ በፊትም ሆነ ከእርሱ በኋላ የሚተካከለው ያልተገኘ ጥበበኛ ነበር። በዚያ ዘመን የግል መርከቦች የነበሩት፣ ቤቱን ባማረ ወርቅና በዝሆን ጥርስ ያስጌጠ ባለጠጋ ነበር። ካማረው ነገር ያስቀረው ምንም ነገር የለም። ነገር ግን አልረካም። እንደውም ሁሉም ነገር ግብ የሌለው ሳይክል (ዙረት) ሆነበት። ከእግዚአብሔር ውጭ ወይም ያለ እግዚአብሔር ሕይወትን ብቻዋን ስናስባት እንደዚህ ድግግሞሽ ናት። እግዚአብሔር ሕይወትን ሊመራ ግን ሕይወት መጨረሻ (ግብ) አላት።

እውቀት ለሕይወት ጥያቄ መልስ አይደለም። ጠቢቡ ስለ ዓለም እውቀት ሊናገር ህዘን መሆኑን ተናግሯል (መክ.1÷18)። ብዙ የሚያውቁ ከማያውቁት ይልቅ ህዘንተኞች ናቸው። በዚህ በመረጃ ዘመን ዓለምን የአንድ መንደር ያህል አውቃታለሁ ብንልም እርካታ ግን የለም። እኛ ስለ አሜሪካ፣ ስለ እንግሊዝና ስለ ቡድን ስምንት አገሮች እንበላጫለን። ሠላሳ ኪሎ ሜትር ሳንርቅ የምናገኘው ገበሬ ግን የሚኖረው ኑሮ ብቻ ያስጨንቀዋል። ለእርሱ ትልቅ ነገር የሰኔ ዝናብ ነው። ለእርሱ ሁሉም ነገር የገበሬ ማኅበሩ ሊቀ መንበር ነው። ከዚያ ውጭ ንጉሥ ያለው እንኳን አይመስለውም። «ሰሚ ነው እንጂ ተቸጋሪ፣ ደንቆሮ መልካም ነዋሪ» የሚባለው ለዚህ ነው።

ሥልጣን የሕይወት ጥያቄ መልስ አይደለም። ጭስ የማይታይበት ቃጠሎ ቢኖር የሥልጣን ዓለም ነው። በሥልጣን ላይ ያለ እንኳን ጠላቱን ወዳጁን ተጠራጥሮ የሚያጠፋ ነው። እንደ

ባለሥልጣን ነጻነቱ የተገፈፈ ፍጡር የለም። ባለሥልጣን ማለት የደለበ ባሪያ ማለት ነው። በሥልጣን ላይ ያለ ሁሉን ደስ ማሰኘት አይችልም። ሌባው ሲወደው ደህነኛው ይጠላዋል፣ ደህነኛው ሲወደው ሌባው ይረግመዋል። እንኳን በለው አገዛዝ በእግዚአብሔር አገዛዝ ያልረካን የለው ልጅ መምራት ከባድ ነው። ባለሥልጣናት በወጣትነት ዘመናቸው በምኞት ኖረው በእርጅና ዘመናቸው በእስርና በስደት ይንገላታሉ። ለብዙዎች ጡረታ ይፈቅዳሉ፣ እነርሱ ግን ጡረታን ያጣሉ። እንኳን እነርሱ ልጆቻቸው እንኳን አገር የለሽ ይሆናሉ። ለዚህ ነው ሰሎሞን መካከለኛን ኑሮ የለመነው (ምሳ.30÷7-9)።

ሀብት የሕይወት ጥያቄ መልስ አይደለም። ከምድር ከፍ ባልን ቁጥር አየር እንደሚሳሳ እንዲሁም በሀብት ከፍ ባልን ቁጥር እርካታ እየቀነሰ ይመጣል። ብዙ ትልልቅ ቤቶች ትልልቅ ጥያቄ አለባቸው። ባለጠጎች ባለጠጋ በመሆናቸው ብቻ ይጠላሉ። ያለ ጥፋታቸው ይገደላሉ። በደርግ ዘመን ብዙ ባለጠጎች ታስረዋል፣ ተገርፈዋል፣ ድህነትም ተመርጧል። ደርግ ወደ ሥልጣን ወጥቶ የከተማ ትርፍ ቤቶችን፣ የገጠር መሬቶችን ሲወርስ፣ ባለጠጎች ሊታሰሩ መምሬ በለጠ የሚባሉ ቁስ ሴት ልጅ ቢወልዱ «ደሃ ለው በለጠ» ብለው ለየሚት ይባላል። ጣሊያን ወደ ኢትዮጵያ እንደ ገባም ባንዳና ሽፍታ ባለጠጎችን መግደልና መዝረፍ ጀመረ። ህብት ያለውም መኝታ እጣ። ሁለት ባለጠጎችም ተጨንቀው እያወሩ በመንገድ ሲሄዱ ጎዳና የሚያድር አንድ ቡቱቷም ደሃ ሰማቸውና «አዳሜ ተርበድበሺ እኔ እንደ ሆነ ድህነቴን በሺህ ብርም አልሸጣት» አሰ ይባላል። ባለጠግነት እረፍት አይሆንም። ሰሎሞን እነዚህ ሁሉ ትልቅነቶች ያደከሙት ሰው ነበረ። ስለዚህ ከንቱ (ባዶ) ነው አለ።

ታዲያ የዚህ ዓለም ማረፊያ ምንድን ነው? ሰው ሠርቶ ሠርቶ የሚያርፍበት ዱካ፣ ሄዶ ሄዶ የሚያርፍበት ድንጋይ፣ እንብቦ እንብቦ የሚያርፍበት ምዕራፍ አለው። ኖሮ ኖሮም ማረፊያው በሞት ወደዚያኛው ዓለም ማለፍ ነው። የዚህ ዓለም ትግል ምዕራፍ ሞት ነው። <u>እግዚአብሔር በዕለቱ ሲጠራንና ሥራችንን ፈጽመን ስንሄድ ሞት የሠርግ ያህል ነው።</u> ነቢዩ ዳዊት «*ምሕረትህ ከሕይወት ይሻላልና*» (መዝ.62(63)÷3) ብሏል። ዳዊት ምሕረት ያለው ሞትን ነው። ሁላችንም እንደሚገባን እዳም በበደለ ጊዜ ወደዚህ ዓለም ለማዘት ነው የተላከው። ስለዚህ ዓለሙ በራሱ ትልቅ እስር ቤት ነው። ሰው በሞት ሲጠራ ምሕረት ተደረገለት ማለት ነው። ለዚህ ነው ነቢዩ «ምሕረትህ ከሕይወት ይሻላልና» ያለው።

በሉቃስ 16. ላይ የተጠቀሱትን የባለጠጋው የነዌና የደሃው የአልዓዛርን ታሪክ ለዚህ ምዕራፍ መደምደሚያ እናደርገዋለን። ነዌ እጅግ ባለጠጋ ነበር፣ አልዓዛር ደግሞ እጅግ ደሃ ነበር። የባለጠጋው ብልጥግና የደሃው ድህነት መጠን አልነበረውም። ሁለቱም ግን ሞቱ። እግዚአብሔር እውነተኛውን የፍትሕ ሚዛን ለሞት አስጨብጦታልና። እንደ ድሆች ባለጠጎችም ይሞታሉ። የባለጠጋውም ብልጥግና የደሃውም ድህነት አለፈ። ወደ ነፍስ ዓለም ሲሄዱ አድራሻቸው ተለያየ። ይህ ዓለም የነዌ ነበር፣ የወዲያኛው ዓለም ግን የአልዓዛር ሆነ። የዌዌ ባለጠግነት ጊዜያዊ ነበር። የአልዓዛር ሕይወት ግን ዘላለማዊ ሆነ። የባለጠጋው ብልጥግና «ነበር» ይባላል። የአልዓዛር ዕድል ግን አያረጅም። በዚህ ዓለም ባለጠጋ ተብሎ በወዲያኛው ዓለም የውሃ ጠብታ መለመን ያሳዝናል። በዚህ ዓለም ትልቅ ሰው ተብሎ በሰማይ መለቃየት በጣም ያሳቅቃል። የመጨረሻው ምስኪን በነፍሱ መግቢያ የሌለው ነው። የዚህ ዓለም መክራማ እንደ ምንም ያልፋል። የወዲያኛው ዓለም ግን ደስታውም ሆነ መክራው ዘላለማዊ ነው። አንድ አባት «ወደ መንግሥተ ሰማያት የማያስገባ ሀብትን ሀብት ብላችሁ አትጥሩት» ብለዋል።

ይህ ዓለም ጥሩ በልቶም ያልፋል፣ ክገንዳ ላይ በልቶም ያልፋል። ምጽዋት የማያድነው ደሃ ግን በነፍሱ የክሰረ ነው። ነዌና አልዓዛር ሁለቱም አንድ ነገር አልተከተላቸውም። የነዌ ባለጠግነቱ፣ የአልዓዛር ድህነቱ። አም የዚህ ዓለም ሀብትና ዝና ለነፍስ ምንም አይጠቅምም። በወዲያኛው ዓለም የሚታሰበው እንደ ሕልም ነው። የነበረም አይመስልም። የሞትን ድልድይ የሚሻገር ሀብት በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ ነው።

ንብ ዓመቱን በሙሉ ትደክማለች፣ ትሮጣለች። የታታሪነት ምሳሌ ናት። ትጉህ ድርጅቶች ንብ ይባላሉ። ንብ ግን ማር የምትሠራው ለሰው ብላ አይደለም። ለመብላት ስትዘጋጅ ያልደከሙበት ሰዎች ቆርጠው ይወስዱታል። እኛም እንሮጣለን፣ እንሰበሰባለን። ለማን እንደምንሰበስብ ግን አናውቀውም። እግዚአብሔር ግን ሰውየውን ያውቀዋል።

ይህ ዓለም ሞተንም የሚያልፍ፣ ቆመንም የሚያልፍ የነበር ዓለም ነው። እንደሚኖር እየሠራን እንደሚሞት መዘጋጀት አለብን። ዓለምን በዓለም፣ ንጉሥን በንጉሥ መለወጥ ይገባናል። የመንግሥተ ሰማያት ውበት፣ የንጉሥ ክርስቶስ ደግነት የዓለምን ጎስቋላነት ሊያስረሳን ይገባል። ዓለም ከንቱ ኃላፊና ጠፊ ነውና በጣም መጨነቅ አይገባንም።

የጽሞና ጊዜ

አንድ ሰው «ይህ ዓለም፣ የምሥራች ቃልና የመርዶ ቃል የያዘ መልእክተኛ ነው። ዛሬ ጠዋት ሹመትህን ካበሰረህ ነገ ማለዳ ሞትህን ያረዳሃል» ብለዋል። አንድ የማክብራቸው መንፈሳዊ አባትም በልዑል ቃል «ነገሡም ጳጳሱም ዓለም ከንቱ ነው» ያሉኝን አስታውሳለሁ። ወገኔ! ልብ ብለህ አስተውል። እነ አስክንድር፣ እነ ቂሣር፣ እነ ናፖልዮን፣ እነ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያልኖሩበትን ዓለም አንተ ምስኪኑ የምትኖርበት ይመስልሃልን? ዓለሙ ሲያዩት ውበቱ በየዕለቱ እየጨመረ የሚያሳሳ ይመስላል። ነገር ግን አበባ ሲረግፍ ሲል ያምራል የሚባለው ለሁሉም ይሠራል። የበረዶ መቅለጥም እንበለው፣ ሱናሚም እንበለው፣ ኒውክለርም እንበለው ዓለም እንደምታልፍ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ አሁን እየጎላ ነው። ስለዚህ፡-

- በሚያልፍ ዓለም የማያልፍ በጎ ሥራ ሥራበት።
- በሚያልፍ ዓለም የማያልፍ የነፍስ ውሳኔ ወስንበት።
- በሚያልፍ ገንዘብ የማያልፍ ዘመድ አፍራበት። ማለት ድሆችን ጎብኝበት፣ የእግዚአብሔርን ሥራ ሥራበት።
- በሚያልፍ ዓለም ለሚተካው ትውልድ መሠረት ጣልበት።

ጸሎት

አምላኬ ወዴት ነህ? አገርህ ወዴት ነው? መገኛህስ? በፀባያት ስፈልግህ በልቤ ውስጥ ትላወላለህ። ክትምህርትህ ሁሉ ዓለም ከንቱ መሆኗን ስማር እያየሁት ስለሆነ ልቤን ነካው። ውበትም ሐሰት፣ ጎበዝ ነኝ ማለትም ቅዠት ነው። ስንቱ በቁመቱ ልክ ሲወድቅ አየሁት። ጌታዬ ሆይ ከንቱ በሆነው ዓለም ላይ ክንቱ ያልሆነውን እርሱን ለይቼ እንዳከናውነው እርዳኝ። መኖሬን ላይሆን አኗኗሬን ከንቱ እንድል እርዳኝ። ለስንቱ ስክንፍ፣ ለሽንገላ ፍቅር አንኳ ሳብድ ኖሬአለሁ። አሁን ግን ተራው ያንተ ይሁን። በፍጹም ልቤ፣ በፍጹም አሳቤ እንድወድህ እርዳኝ። ማለፍ መለወጥ በሌለበት ክብርህ ለዘላለሙ አሜን!

ምዕራፍ ዐሥር
አትጨነቁ

«አትጨነቁ» የሚለውን ዋስትና ደራሲው በደግነት ሊሰጥ አይችልም። ነገሥታትም በሥልጣናቸው ተማምነው አትጨነቁ ማለት አይችሉም። እንደውም ነገሥታት እንኳን አትጨነቁ ሊሉን ሳይበዛ እንድንጨነቅ ይነግሩናል። «ሁሉም ሰው አካባቢውን በዓይነ ቍራኛ መመልከት አለበት» በማለት ከላይ ወደ ታች ጭንቀትን ያዙልናል። «አትጨነቁ» ያለን ግን ያ የሞት መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ጌታችን በተራራው ስብከቱ የጭንቀትን ትርጉም፣ መንስኤውንና መፍትሔውን አስቀምጦልናል (ማቴ.6÷25-34)። ጭንቀት ማለት አለማመን ማለት ነው። ሕይወትን እንደ ዛሬ ገጠመኙ የሚፈርድና ራሱን በጣም በማየት አቅም የለኝም የሚል ሰው ለጭንቀት ይዳረጋል። ያለማመን መፍትሔው ማመን ብቻ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጭንቀትን መንስኤዎች አስቀምጦልናል።

ያለንን አለማወቅ

«ስለዚህ አላችኋለሁ÷ ስለ ነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት÷ ወይም ስለ ሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ አይበልጥምን?» (ማቴ.6÷25)። የአግዚአብሔርን ተአምራት፣ ቸርነትና ከለላ ለማወቅ መጻሕፍት ማንበብ፣ ሊቃውንትን መጠየቅ አያስፈልግም። በራሳችን ላይ የተከናወነውን ተፈጥሮ ማየት ብቻ ይበቃል። ሰው መሆን ትልቅ ዋጋ አለው። ሰው ሆነን መፈጠራችን በልመና ወይም በምርጫችን ያገኘነው ሳይሆን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።

አንድ ዕቃ የራሱን ዋጋ አያውቅም። ዋጋው ያለው በሠሪው ልብ ውስጥ ነው። የሰውንም ትክክለኛ ዋጋ ራሱ ሰውዬው አንኳ አያውቀውም። የሠራው እግዚአብሔር ግን ያውቀዋል። አንድን ዕቃ ውድ የሚያደርገው የተለጠፈበት ዋጋ ነው። ሰውም የእግዚአብሔር ምሳሌ ታትሞበታል። ቀራጭን ስንመለከት ደግሞ የሰው ዋጋው ጎልቶ ይታየናል። እርሱም አምላካዊ ደም ነው።

ተፈጥሮአችንን ማለትም ነፍስና ሥጋችንን ስንመለከት ውድ ዋጋ ፈሶብናል። ዛሬ ቢደረግልን እንኳ ከተደረገልን አይበልጥም።

የሚበልጠውን የተቀበልን በሚያንሰው መጠራጠር አይገባንም። ማንኛችንም ብንሆን የማንፈልገውን ነገር አንደክምበትም። የምንደክመው ስምንፈልገው ነገር ነው። እግዚአብሔር ከአፈርና ከሕያዊት ነፍስ ሲፈጥረን ደክሞብናል። ይህን ድካሙን አስቦ ነው እንደ ገና በቀራንዮ የደከመው። ነቢዩ ለጌታው አዝኖ *«እናንተ የዳዊት ቤት ሆይ÷ ስሙ! በውኑ ሰውን ማድከማችሁ ቀላል ነውን? አምላኬን ደግሞ የምታደክሙ!»* (ኢሳ.7÷13) ማለቱ ለዚህ ነው።

ከማኅፀን ጀምሮ እስከዚህ ዕድሜያችን በችግር፣ በድካማችን፣ በታሪካችን ሁሉ አብሮን ተራራ ወጥቷል፣ ሸለቆ ወርዷል። ታዲያ ይህን ሁሉ ዋጋ የከፈለብን ሊተወን ነውን? በፍጹም አይደለም።

ጭንቀት ሲገጥመን፣ አሳብም ሲወጥረን የምንለው ችግር በትክክል የሆነ ነው? ወይስ ይሆናል የምንለው ፍርሃት ነው? ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን። አብዛኛው ጭንቀታችን ባልተጨበጡ ነገሮች ላይ ነው። ጭንቀት ያለንን ነገር አንዳናይ ይጋርደናል። ስለዚህ ያለንን ማየት ያስፈልጋል። ሥራ ስናጣ ቢያንስ ሥራ ያማረን ጤና ስላለን መሆኑን ማሰብ ይገባናል። ለመጨነቅም አንድ ነገር ሲኖረን ያስፈልጋል። ምንም የሌለው አይጨነቅምና። መጨነቃችን በራሱ ባዶ እንዳልሆንን ይመሰክርብናል።

ሕጻን ልጅ ጤንነቱ ካልታወከ በቀር ምን እበላለሁ? ምን አጠጣለሁ? ምን አስብሳለሁ? ብሎ አይጨነቅም። ምክንያቱም ስለ እርሱ የሚያስቡ ወላጆች አሉትና። እኛም ለእግዚአብሔር እስከ ሽበት ሕጻናቶች ነን። የፍቅር ጥገኞች ነን። ወላጆች በልጆቻቸው፣ መምህራን በደቀ መዛሙርቶቻቸው፣ ንጉሥ በሠራዊቱ ደስ እንደሚላቸው እግዚአብሔር በእኛ ደስ ይለዋል። ስለምንበላውና ስለምንጠጣው ደግሞም ስለምንለብሰው እርሱ ያስብልናል። እርሱ የፈጠረውን የማይጥል፣ ያስቀመጠውን የማይረሳ ነው። መብልና መጠጣችንን ደግሞም ልብሳችንን የሚያዘጋጅልን ክርስቲያን ስለሆንን አይደለም፤ ስለፈጠረን ነው። «ፍጠረኝ ሳይሉኝ ፈጥሬአቸዋለሁ» ብሎ ያስብልናል። እግዚአብሔር ስለ ፈጠራቸው ብቻ የሚያኖራቸው ብዙ ሕዝቦች አሉ።

አንድ ሕጻን አድጎ ለአካለ መጠን ሲደርስ ከወላጆቹ ጥገኝነት ይወጣል። ያለ ወላጆቹ መኖር የማይችለው ሕፃን ብቻውን መኖር ይችላል። አሁንም ግን ያለ እግዚአብሔር ጥገኝነት መኖር አይችልም። የእግዚአብሔር መጠጊያ የማያሳቅቅ፣ ራስን ለመቻል የማያሳስብ ነው!

በሕይወት በተሞላው ዓለማችን ሦስት ዓይነት ሕይወቶች አሉ። የእጽዋት ሕይወት፣ የእንስሳት ሕይወት፣ የሰው ሕይወት። የእጽዋት ሕይወት ልምላሜያቸው ሲሆን በመጠውለግ ይሞታል። የእንስሳት ሕይወት ደመ ነፍስ ሲሆን እስካሉ ድረስ ብቻ ይኖሩና ሲሞቱ ያበቃል። የሰው ሕይወት ግን ሰባዊነት /አሳቢነት/፣ ነባቢነት /አሳብን መግለጥ/፣ ሕያውነት /ዘላለማዊነት/ ያለው ነው። ስለዚህ የሰው ሕይወት በመጠውለግና በመሞት ብቻ አያበቃም። ዘላለማዊ ነው። ሰውን ከቡር ከሚያሰኙት ነገሮች አንዱ በውስጡ የተቀመጠው ይህ ዘላለማዊነት ነው።

ጌታችን ወቅታዊ ስለ ሆነው ስለ እጽዋት ሕይወት በመናገር የእኛ ሕይወት የላቀ መሆኑን ይገልጣል፦ *«ስለ ልብስስ ስለምን ትጨነቃላችሁ? የሜዳ አበቦች እንዴት እንዲያድጉ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ አይደክሙም አይፈትሉምም ነገር ግን እላችኋለሁ፦ ሰሎሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከነዚህ እንደ አንዱ አልለበሰም። እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን የሜዳን ሣር እንዲህ የሚያለብስ ከሆነ፦ አናንተ አምነት የጐደላችሁ አናንተንማ ይልቁን እንዴት?»* (ማቴ.6÷28-30)።

ዳግመኛም ከእንስሳትና ከእጽዋት ሕይወት የሰው ሕይወት እንደሚበልጥ ተናግሯል፦ *«ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ አይዘሩም አያጭዱምም በጎተራም አይከቱም፦ የሰማዩ አባታችሁ ይመግባቸዋል። አናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡምን?»* (ማቴ.6÷26)።

አንድ የኢራን ንጉሥ በሥልጣን ዘመናቸው ከ35 ሺህ ሕዝብ በላይ ፈጅተዋል። የእኚህ ሰው የሚገርመው ጠባያቸው ግን አንዲት የጽጌረዳ አበባ ስትቀጠፍ ስቅስቅ ብለው ያለቅሱ ነበር። ለእርሳቸው ትልቅ የሰው ሕይወት ሳይሆን የጽጌረዳ አበባ ነበር። የአገራችንም ሰው «የሰው ልጅ ከማሳደግ የውሻ ልጅ ማሳደግ ይሻላል» ይላል። ከሰው ሕይወት ለእንስሳ ሕይወት ዋጋ ይሰጣል። የሕይወት ምንጭ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሰው እንደሚበልጥ ተናግሯል።

እኛ ለአበቦች አልተፈጠርንም፣ አበቦች ግን ለእኛ ተፈጥረዋል። እኛ ለእጽዋት አልተፈጠርንም፣ እጽዋት ግን ለእኛ ተፈጥረዋል። እግዚአብሔር ለራሳቸው ማሰብ ለማይችሉት እጽዋት ያስባል። የተራቆቱ መስኮችንም በአበባ ያለብሳል። ከእኛ አልፎ ለእኛ ስለ ተፈጠሩት የሚያስብ ከሆነ እኛማ የታየንና ዘወትር የምንታይ ሕዝቦቹ ነን። ሰሎሞን በባለጠግነቱና በክብሩ ብዛት ሁሉን አድርጓል። ቤቱን በወርቅ ጭፍልቅ፣ በሐር ቍጥቍጥ አስጊጧል። የተዋቡ ልብሶችን ለብሷል። እርሱ በንጉሣዊ፣ በጥበባዊና

በባለጠግነት ክብሩ የሰበሰው ልብስ እግዚአብሔር አንዲት አበባን ካሰበላት ልብስ ጋር አይወዳደርም። ሰሎሞን በንጉሥነቱ ሰራሱ ተጨንቆ ያደረገው እግዚአብሔር ለአበባ ካደረገው ጋር ቢመዛዘን አይጠጋጋም።

የሰሎሞን ልብስ ከተፈጥሮው ጋር የተከናወነ አይደለም። ከሰውነቱ በላይ የሚውል ነው። የአበቦች ልብስ ግን ከተፈጥሮአቸው ጋር የተሠራ ነው። ልብሳቸውም የሚያድግ የሚፈካ፣ ራሱን የሚያድስ የክረምትና የበጋ የሆነ ሁሉም ልብስ ግን ውብና የታወቁ ዲዛይነሮች እንኳ የማይሠሩት /የማይጠልፉት/ ነው። ሸማኔዎች አበቦችን አይተው ይሠራሉ። አበቦች ግን የራሳቸው ልብስ አላቸው። እኛ በንጉሣዊ ክብር እንኳ ሰራሳችን ብንጨነቅ እግዚአብሔር ለአበባ የተጨነቀውን ያህል አይሆንም። እኛ ስራሳችን ከምናስብ እግዚአብሔር ለአበባ ያሰበውን ቢያስብልን ይሻላል። እግዚአብሔር ለአበባ ያሰበው እንዲህ ከሆነ ለእኛ ያሰበውማ እንዴት ይልቅ!

ሁላችንም ብንሆን በአእዋፋት ላይ ጥናት ልናደርግና ልንደነቅባቸው እንችላለን። ነገር ግን አንድ ኪሎ ሰንዴ እንኳ ሰፍረንላቸው አናውቅም። እግዚአብሔር ግን ያኖራቸዋል። እነዚህ ፍጥረታት አይዘሩም፣ አያጭዱም፣ የማብሰያ ማዕድ ቤት፣ የማከማቻ ጎተራ የላቸውም። የሰማይ አምላክ ግን ያኖራቸዋል። በእርግጥ የሰማይ ወፎች አይዘሩም እንጂ አይሠሩም አልተባሰም። ባይዘሩም ምግባቸውን ለመልቀም ይሯሯጣሉ። እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እንደ ሰማይ አእዋፋት እርባ ዓመት በበረሃ መግቧቸዋል። እግዚአብሔር ለመሰከ አበቦችና ለሰማይ አእዋፋት እንዲህ ካሰበ ለእኛማ እንዴት ያስብልን ይሆን?

በማቴ.6÷25-28 «ተመልከቱ» የሚል ቃል ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል። ማየት ብቻ አይበቃም፣ መመልከት ማስተዋል ይገባል። ተመልከቱ የተባለው ፍጥረታትን ነው። አእዋፋት የሚያዜሙት በሰው ጎጆ አጠገብ ነው። እእዋፋት በእኛ ደስ ብሏቸው የሚዘምሩትን ያህል እኛ ደስተኞች አይደለንም። ዛፎች ቀጥ ብሰው ቆመዋል። እኛ ግን ኑሮን፣ ሰዎችን፣ ጠላትን እየፈራን አንገታችንን ደፍተናል። እነርሱ ለእኛ በመፈጠራቸው ኮርተው ከቆሙ እኛማ እንዴት ልንፀና ይገባል! ሰማዩን ተመልከቱ፣ ጥቁር ወይም ነጭ አይደለም፣ ሰማያዊ ነው። ጥቁር ቢሆን የሚያስፈራ ነጭ ቢሆን አዙሮ የሚጥል በሆነ ነበር። እግዚአብሔር ግን ውብ ጣራ አድርጎልናል። ሰማዩ ቅርጹ እንደ ድባብ (ጥላ) ነው። ድባብ የሚዘረጋው ለትልቅ ሰው ነው። እግዚአብሔር ስላከበረን በሰማይ ድባብ ወጥተን እንድንገባ አድርጎናል። ሰፊው ዓለም

የእግዚአብሔርን ቸርነት የሚያብራራ ትምህርት ቤት ነው። በትንሽ ክፍል ውስጥ ተቀምጣችሁ ብቻ አትማሩ። በእያንዳንዱ ፍጥረት ውስጥ የተጻፈውን ምስክርነት አጥኑ። ማንበብ ለሚችል ፍጥረታት ፊደል ናቸው። ይህን ዝናብ የሰጠን ማን ነው? እግዚአብሔር ነው። የሚሰጠንም በጊዜው ነው። ይህ ዝናብ በስው አስተዳደር ሥር ቢሆን የቢሮ ሠራተኞች እስኪፈራረሙ ክረምቱ የሚገባው ጥቅምት ላይ በሆነ ነበር። እግዚአብሔር ግን ከሕይወት ጋር የተያያዙ ነገሮችን በእጁ እድርጎታል። ለሕይወት የሚጠነቀቅ እርሱ ብቻ ነውና።

ይህ ሁሉ እንክብካቤ ይህ ሁሉ ፍቅር ለእኛ ነው። እንደዚህ ተወድደን ለምን እንጨነቃለን? እንዲህ ተደርጎልን ለምን እንደነግጣለን? እም የጭንቀታችን መንስኤ ያለንን አለማወቅ ነው።

አቅማችንን አለማወቅ ነው

የጭንቀታችን ሁለተኛው መንስኤ አቅማችንን አለማወቅ ነው። ተፈጥሮአችንን ብናየው በዓይን እንኳ ሊታዩ የማይችሉ ባክቴሪያዎች ሊያጠቁት የሚችል እጅግ ደካማ ተፈጥሮ ነው። የዓለምን ሕዝብ በአንደኛ ደረጃ እየፈጀ ያለው የወባ ትንኝ በዓይን እንኳ ሞልታ የምትታይ እይደለችም። በጣም አቅመ ደካሞች ነን። አቅም የሌለው ሰው ይገዛል። እኛም አቅመ ቢሶች ስለሆንን ኃይለኛ ውን ጌታ መጠጋትና ለእርሱ መገዛት ያስፈልገናል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *«ለእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው?»* (ማቴ.6÷27) ብሏል። በገዛ ቁመታችን ላይ እንኳ ማዘዝ አንችልም። ረዘምኩ ብለን ማጠር፣ አጠርኩ ብለን መርዘም አይቻለንም። በራሳችን ላይ አቅም ከሌለን በሁኔታዎች ላይ እንዴት አቅም ይኖረናል? የገዛ ጭንቀታችን የያዝነውን ነገር ካላስተካከለ የሌለንን ነገር ማምጣት እንዴት ይችላል? ብዙ ከንቱ ነገሮች ቢኖሩም መጨነቃችንም ትልቁ ከንቱ ነው።

ለብዙ ዘመናት ለራሳችን ተጨንቀናል። ከእግዚአብሔር በላይ ግን ለራሳችን ደግ አልሆንም። ለብዙ ዘመናት በፍርሃት እምጠናል። የሚጎድለው ከመጉደል፣ የሚሆነውም ከመሆን አልቀረም። ራሳችንን መርሳትና እግዚአብሔርን ማሰብ ያስፈልገናል። አሊያ ራሳችንን ከመጠን በላይ ካየነው እንጨነቃለን፣ እንችልምና። እግዚአብሔርን ስናይ ግን እንበረታለን። ጭንቀት ለመጣው ችግር ወለድ መክፈል እንጂ መፍትሔ አይደለም። እንደውም ስንጨነቅ ነገሮች መወሳሰብ

ይጀምራሉ። የውሉ ጫፍ እየጠፋ ቀጣዩ ቀንም አልታይ እያለን ይመጣል። ስንጨነቅ የመለኮት ብርታት ይርቀናል። እግዚአብሔር ቢያስብልን ይሻላል!

በሕይወታችን ውስጥ ያገኘናቸው ትልልቅ ትርፎች ተጨንቀን ያገኘናቸው አይደሉም። መልካችን፣ ቤተሰባችን፣ እገራችን፣ ትዳራችን እግዚአብሔር ያስበልን ናቸው። በሕይወት ላይ የእኛ ድርሻ ትንሽ ሊሆን እርሱም መቀበል ነው። በሕይወት ላይ አብዛኛው ድርሻ የእግዚአብሔር ነው። ለምሳሌ፦ አገራችንን እንወዳለን። ባንዲራዋንም ስናይ ዕንባችን ይመጣል። ቤተ ክርስቲያንና ቤተ መንግሥት በዚህ ባንዲራ ያጌጣሉ። በየቲሸርታችን ላይ ባንዲራውን አስቀርፀናል። አገራችንን ግን የሰጠን ማን ነው? ስንል እግዚአብሔር ነው። ቤተሰባችንን በጣም እንወዳለን። ያውም ሳይታወቅብን። የሌላውን ሰው ችግር ስንሰማ ተራራ ቢያክልም ቀላል ነው እንላለን። የቤተሰባችን ግን የስናፍጭ ቅንጣት የምታህል ችግር ዕረፍት ትነሣናለች። ይህን ቤተሰብ የመረጠልን ማን ነው? እግዚአብሔር ነው። ራሳችንን በጣም እንወዳለን። ሰፊ ቤት ቢኖረን የቁም መስታወት ተክለን ራሳችንን ለማየት እንመኛለን። ራሳችንን የሰጠን ማን ነው? እግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔር አሳብ ይበልጣል። እርሱ ያስበውም ይስማማናል። አገራችን፣ ቤተሰባችንና ራሳችን ተስማምቶን ወደነዋልና። እግዚአብሔር የመረጠው የምንወደው ነው። አሁንም እየሆነ ያለው የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ደስ ሊለን ይገባል።

እያንዳንዱ ጉዞአችን የእሾህ ጉዝጓዝ ያለበት፣ የማይረገጥ ጎዳና ሆኖብን ይሆናል። ክርስቲያን ከሆንን በኋላ የምንኖርበት ስፍራ የፈንጂ ወረዳ ሆኖብን ይሆናል። ባላጋሮቻችን ስለበላን፣ ስለጠጣን፣ ስለለበስን ሳይሆን ምድር ለተሸከመችን ይከብዳቸው ይሆናል። ግን ስለለበስን ሳይሆን ምድር ለተሸከመችን ይከብዳቸው ይሆናል። ግን በሕይወት አለን። አውጥቶ የሚያገባን ደግሞም የሚያኖረን ማን ነው? እግዚአብሔር ነው። ተጠልተንም፣ ተሰደንም፣ ሰዎች ሳይቀበሉንም ያኖረናል። ሕይወትን የኃያላን ጉልበት፣ የነገሥታት ሥልጣን አያቆማትም። የሕይወት ባለቤት እግዚአብሔር ነው። ከራስ ፀጉር የሚበዙ ጠላቶቻችንን ለማስተናገድ አቅም የለንም። ነገር ግን አቅም ካላቸው በላይ እየኖርን ነው። የማይታየው እግዚአብሔር የሚታየውንና የማይታየውን ጠላታችንን ይመልስልናል።

በማቴዎስ 10÷29-31 *«ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም። የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቈጥሮአል። እንግዲህ እትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች እናንተ*

ትበልጣላችሁ» ይላል:: አስደናቂ ዋስትና፣ የማይደፈር ከለላ ነው:: ድንቢጦች ትንንሽ ቢሆኑም በገበያ ስፍራ ሁለቱ በአምስት ሳንቲም ይሸጣሉ:: ዋጋው ምንም ትንሽ ቢሆን ዋጋ አላቸው:: እኛ ከድንቢጦች ይልቅ ዋጋ አለን:: ራሳችንን ብናውቀውም የራስ ጠጉራችን ቍጥሩ ምን ያህል መሆኑን ግን አናውቅም:: የሰማዩ አባት ግን የራሳችንን ጠጉር ቆጥሮታል:: እኛ አንዲቱ ጠጉር ሳይሆን ዐሥሩ ቢነቀል አይጨንቀንም:: ያለ ሰማዩ አባታችን ፈቃድ ግን አንዲቱ ጠጉራችን አትነቀልም::

ኖ

አንድ አባት ጣልያን አገር ሄደው በድንገት ትርፍ አንጀት ታመው ቀዶ ጥገና ያደርጋሉ:: ነገር ግን ቀዶ ጥገናው እየተደረገ ሳለ ነቁ:: እርሳቸውም ሲናገሩ:- «ስነቃም ፈረንጆቹ ተደንቀው የጥቁርም ደም ቀይ ነው? ሲሉ ሰማሁ:: እኔም አዎ ቀይ ነው» ስላቸው በጣም ደነገጡ አሉና «ከሁላችሁም እበልጣለሁ አንጀቴን አይቼዋለሁ» አሉ:: የሰውነት ክፍሎቻችንን ካየናቸው ያላየናቸው ይበዛሉ:: እነርሱን የሚያይና ትክክለኛ ሥራቸውን እንዲሠሩ የሚያደርጋቸው እግዚአብሔር ነው:: በእውነት የጭንቀታችን መንስኤ አቅማችንን አለማወቅ ነው:: ልብና ኩላሊታችንን ያላየን እነርሱን የማዘዝ አቅም የሌለን ሰዎች ነን:: ሁሉ ስሚገዛለት ጌታ ጭንቀታችን እንዲገዛ እኛ አስቀድመን ለእግዚአብሔር እንገዛ::

<u>የሚበልጠውን ክብር አለማሰብ</u>

ጌታችን ሲናገር *«ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል»* (ማቴ.6÷33) ብሏል::

ዋነኛውና ቀዳሚው ነገር መንግሥቱና ጽድቁ ወይም የዘላለም ሕይወት ነው:: የዚህ ዓለም ነገር ግን ተጨማሪ ነው:: የሰው የጸጋ ደሞዝ የዘላለም ሕይወት ነው፣ የዚህ ዓለም ትርፍ ግን ቦነስ ነው:: ዋስትና የሚጻፈው በደሞዝ እንጂ በቦነስ አይደለም:: የወዲያኛው ዓለም እንጂ ይህ ዓለም ዋስትና የለውም:: የሚቀድመው ካልቀደመ የሚከተለው ስፍራውን አይዝም:: አንደኛን ሁለተኛ ላይ ወስደን ከኖርን፣ ሁለተኛውን አንደኛ ላይ አምጥተን ከኖርን መልካም አይደለም::

በአገራችን «አንቺ ምን አለብሽ ሁለት አባት አለሽ፣ አንዱ ቢሞትብሽ በአንዱ ትምያለሽ፤» ይባላል:: በእውነት ሁለት አባት፣ ሁለት አገር ያለው ክርስቲያን ነው:: የምድሩ ባይሳካለት የሰማዩን ማን ይነካበታል? ሁለት ቤት ያለው አንዱ ቢፈርስበት ሀዘኑ አንድ

ቤት ብቻ እንዳለው ሰው ሳይሆን ከፊል ነው:: ክርስቲያንም የምድሩ ጎጆ ቢፈርስበት በሰማይ የማይፈርስ አገር አለው:: የሚኖረው እስከ ጊዜው ነው:: የቀጠረው ወዳጅ አለ:: የሚቸገረው እርሱ እስኪመጣ ነው::

ጳውሎስ ስለማይፈርሰው ማደሪያ ከተረከ በኋላ የክርስቶስ መልእክተኞች እንደሆንን ይናገራል (2ቆሮ.5÷20):: በጥንት ትርጉም መልእክተኞች የሚሰው እንደራሴዎች ተብሎ ተተርጉሟል:: በአሁኑ ዘመን የቋንቋ አጠቃቀም ደግሞ አምባሳደር ተብሏል:: ክርስቲያን የክርስቶስ አምባሳደር ነው:: አምባሳደር ከአገሩ ርቆ የሚኖር ነው:: ክርስቲያንም አምባሳደር ከሆነ የሚኖረው ከአገሩ ርቆ ነው ማለት ነው:: አምባሳደር ወደ መንግሥቱና ወደ አገሩ የሚጠራበት ጊዜ አለ:: ክርስቲያንም ወደ መንግሥቱና ወደ ወገኖቹ ወደ ጻድቃን የሚጠራበት ጊዜ አለ:: እስከዛው ድረስ የአምባሳደርነት ሥራውን እየሠራ ጥሪውን ይጠባበቃል:: በእውነት የጭንቀታችን አንዱ መንስኤ የሚመጣውን ክብር አለማሰብ ነው:: ፍርድ የሚታወቅባት፣ እውነት የበላይ የሆነባት አገር አለችን:: ይህችን አገር የሥጋ መጋረጃ ሲገለጥ እናያታለን::

<u>ነገ</u>

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *«ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል»* (ማቴ.6÷34) ብሏል:: በሰው ሕይወት ውስጥ ነገ ሰላም ሳይሆን ረባሽ ቃል ነው:: ሰው ሁሉ ስለ ነገ በማሰብ ደክሟል:: የማያውቃት ነገ ሰውን በጣም ታስጨንቀዋለች:: ነገ ክፉ ሊመጣ ይችላል፣ ነገ ደግ ሊመጣ ይችላል፤ ግን እርግጠኛ አይደለንም:: ስለማናውቀው ነገር መጨነቅ ነገ ይባላል:: የሰው ልጅ በነገ ፍርሃት ተይዟል:: የሰው ዕድሜ የሚያልቀው ያሰፈውን በማመስገን፣ ያለውን በማማረር የሚመጣውን ምን ይሆን? ብሎ በመጠራጠር መሆኑ ያሳዝናል:: ገጣሚው:-

ትላንትን አታስብ ሞቶ ቀርቷልና፣
ነገንም አታስብ ያንተ አይደለምና፤
ዛሬን ግን ሥራበት ገንዘብህ ነውና» ብሰዋል::

የሰው ልጅ የሚኖረው በትላንትና በነገ መካከል ታፍኖ ነው:: ሁሉም ሰው በጣም የሚጨንቀው ዛሬ አይደለም፣ ነገ ነው:: ነገ ግን የእግዚአብሔር ምሥጢር ናትና ማንም አያውቃትም:: ነገ ዘላለም ናትና ላይደረስባት ይችላል:: የሚገርመው የሰው ልጅ ነገን

ለመኖር እርግጠኛ ሆኖ የሚጨነቀው ለአኗኗሩ ነው። እስከ ነገ ግን ብዙ ተአምሮች አሉ። ነገ ክፉ ይመጣል ብሎ መጨነቅም ሆነ ነገ አገኛለሁ በምንለው ነገር መመካት ተገቢ አይደለም። *«ቀን የሚያመጣው ምን እንደሆነ አታውቅምና ነገ በሚሆነው አትመካ»* (ምሳ.27÷1)።

ዛሬ ከተቀደስን ግን ነገ ድንቅ ናት። ትላንት ዘር ነው፣ ዛሬ ቅጠል ነገ ፍሬ ነው። አንድ ታዋቂ ሰው «ስለ ነገ ይጨነቃሉ ወይ?» ቢባሉ «ዛሬን በትክክል ከኖርኩ ለነገ ስለሚተርፈኝ ለነገ አልጨነቅም» ብለዋል። ዋናው ነገርም ዛሬን በትክክል መኖር ነው። ጌታችን *«ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል»* ብሏል (ማቴ.6÷34)። የቀኑ ክፋት የተባለው የቀኑ ግዳጅ ነው። እያንዳንዱ ቀን የራሱ የሆነ የቤት ሥራ አለው። የዛሬን የቤት ሥራ ዛሬ ሥሩ ማለቱ ነው። ስለ ነገ ብንጨነቅም ጭንቀቱ እንጂ የነገ ትክክለኛ የቤት ሥራ ምን መሆኑን አናውቅም። ስለ ነገ ያለን ግንዛቤ ከግምት አያልፍም። የዛሬን ጉዳይ መወጣት መቼ አነሰንና ነው ስለ ነገ የምንጨነቀው? በእውነትም ሁሉም ነገር እንደ ስጋታችን አይደለም። ትላንትና ላይ ዛሬ ነገ ነበረች። ነገር ግን ዛሬ እንደ ፈራናት ሳይሆን መልካም ቀን ነች።

በዘመነ ለማዕታት አንድ ሰው ነገ በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት ተፈረደበት። እርሱ ግን ማታ ላይ ሻማ ለኩሶ መለማመድ ጀመረ። ጣቱን ወደ ሻማው ሲሰድ አቃጠለውና ቶሎ መለሰ። በዚህ ጊዜ «ወይኔ ጌታዬን ላሳፍረው ነው» ብሎ ሲጨነቅ አደረ። በማግሥቱ ግን ሲጠራ እየዘመረ ወደ እሳት ገባ። ከሰዓቱ በፊት ሁሉም ነገር ከባድ ነው። ኃይል ግን በጊዜው ይመጣል።

ስለ ዛሬ ስናስብ የማይጨንቀን ስለ ነገ ስናስብ ግን የሚጨንቀን ለምንድነው? ስንል ዛሬ ላይ ስንደርስ ዛሬን የሚያኖር ኃይል ከሰማይ ተልኮልናል። ነገ ላይ ግን አልደረስንም። ስለዚህ ነገን የሚያውል ኃይል አልመጣም። ስለ ነገ ያለን አሳብ በራሳችን ጫንቃ ላይ ብቻ ስለሚያርፍ ያስጨንቀናል። ሁሉም ነገር ግን በሰዓቱ ቀላል ነው።

ስለ ነገ ማሰብ ካስፈለገን ግን ዛሬ ክፉ ብሠራ ነገ መከራ እቀበላለሁ፣ ዛሬ በወንጌል ካላመንኩ ነገ ገሀነም እወርዳለሁ ብሎ ማሰብ ተገቢ ነው። ሰው ግን ስለ ነገ የሚያሳስበው ያው ሆዱ ነው። ሆዱ እንዳይጎድል ጎሊናውን ያጎላል። ሌባ ነፍሰ ገዳይ የሚሆነው ስለ ነገ በመጨነቅ ነው። ትልልቅ ሌቦች የአገር ንብረት የሚያሸሹት

ነገ ተረጋግተው ለመኖር ነው። ጠብ ለማይል ኑሮ ሰረቅን ቀማን። ኑሮም መጉደሉን አላቋረጠም።

የጭንቀት መፍትሔ

1. እግዚአብሔር እንደሚያስብልን ማመን፦ እግዚአብሔር የፈጠረውን የማይረሳ አምላክ ነው። እርሱ ያስብልናል። *«እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት»* (1ጴጥ.5÷7)።

2. የሚያስጨንቀንን ለእግዚአብሔር መጣል። እርሱ ስለእኛ ያስባል። እርሱ ስለ እኛ የሚያስብ ከሆነ መጨነቅ አይገባንም። አንድ ሰው የሚይዘውን ዕቃ ሁለት ሰው ከያዘው ይበልጥ ይከብዳል። እንዲሁም ጉዳያችንን እኛና እግዚአብሔር ስንይዘው ይበልጥ ይከብዳል። ስለዚህ ለእግዚአብሔር በጸሎትና በምስጋና መተው ያስፈልገናል። *«በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ። አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል»* (ፊልጵ.4÷6-7)።

3. ለእግዚአብሔር የሰጠነውን ዳግም አለማንሣት፦ ጭንቀታችንን እንለቀዋለን እንጂ አንጥለውም። ፍጹም መተው አንችልም። ለእርሱ ስንተው ጫፉን ይዘን ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ለቀን ሲሆን ይገባል። *«የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት»* (1ጴጥ.5÷7)።

4. እምነት ያስፈልገናል፦ ፈጥሮ አይጥለኝም፣ ስለ እኔ ነፍሱን ለጥቶ ሌላውን አይነሣኝም። ቢከለክሰኝ እንኳ ነፍሳኝ ጠልቶኝ ሳይሆን ለዓላማ ነው ብለን ማመን ይገባናል።

አንድ የታወቀ ሰባኪ በጣም አዝኖ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ማመን ተስኖት ባየችው ጊዜ ሚስቱ የሀዘን ልብስ ለበሰችና «ዛሬ የሀዘን ልብስ ለብሻለሁ፣ ምክንያቱም ልክ አምላክህ እንደ ሞተ ያህል በጣም ተጨንቀሃልና» አለችው ይባላል። እኛም ልክ እንደዚህ ሰባኪ የምንሸነፍበት ቀን ጥቂት አይደለም። መጨነቅ የእግዚአብሔርን ፍቅሩን፣ ተስፋውን፣ ኃይሉን መጠራጠር መሆኑ አይገባንም። መጨነቅ ኃጢአት በመሆኑ ንስሐ መግባት ያስፈልገናል።

ወገኖቼ! ኑሮን የጀመርነው እኛ አይደለንም። ብዙ ትውልድ አልፏል። የተሄደበት መንገድ ደግሞ አያስጨንቅም። በችግር የሞተ ሰው ቢኖርም ጭንቀት ግን ከችግሩ በፊት ይገድላል። በፍርሃት ዘጠኝ ጊዜ ከመሞት አንዱን ሞት አንድ ጊዜ መቀበል የእምነት ጀግንነት ነው። አትጨነቁ ያለ አምላክ በዙፋኑ አለ። አትጨነቁ ብቻ አይደለም ያለው እርሱ በዙፋኑ አለ። አለ ብቻ ሳይሆን አለ ብለን እናምናለን። ውሸቻችን በእኛ አምነው ለኛ ታምነው የሚኖሩትን ያህል በእግዚአብሔር አለማመናችንም ሆነ አለመተማመናችን ያሳዝናል።

ና

የጽሞና ጊዜ

ዋጋህ ያለው በሠራህ ጌታ እጅ ነውና ዋጋህ ስንት እንደ ሆነ እርሱን ጠይቀው። አንተ የምትጥለውን ነገር ትደክምበታለህን? እርሱም የሚደክምብህ ሊጥልህ ሳይሆን ሊከብርብህ ነውና ደስ ይበልህ። ልብህ ታንቡር የመታበት ቀናቶች፣ እንቅልፍ ያጣህበት ሌሊቶች ብዙ ናቸው። እንደዚያ በመሆንህ ግን ምን አመጣህ? ዛሬም ነገርህን ለእግዚአብሔር አስረክብ እንጂ ራስህን አታድክም። ጭንቀት የቀረበውን ከማራቅ በስተቀር ምንም ዓይነት መፍትሔ የለውም። «ጭንቀት ለመጣው ችግር ወለድ መክፈል እንጂ መፍትሔ አይደለም።» በጭንቀት ውስጥ ስትሆን ቀጣዩ ቀን አይታይህም። ስለዚህ፦

- የሚበልጠውን ተቀብለሃልና ለትንሹ ዋስትና አለህ።
- ለራስህ በመጨነቅ ከእግዚአብሔር በላይ ደግ አትሆንለትም።
- ስለ ትርፉ በጣም የሚጨንቅህ ዋናውን ስላልያዝህ ነው።
- ያንተ ቀን ዛሬ እንጂ ነገ አይደለችምና ስለ ነገ አትጨነቅ።

ጸሎት

አምላኬ ሕያው መንገዴ አንተ ነህ። ላንተም የማይፈጸም ምስጋና እስከ አርያም ይሁን። ጌታዬ ሆይ በእኔ ጭንቀት ሳይሆን በአንተ ረዳትነት ለዚህ በቅቻለሁና አመሰግንሃለሁ። በመጨነቅ ራሴን እደክምኩት። የምበላው ምግብ ጣዕሙ ጠፋኝ። የሚሆነው መሆኑ ላይቀር በከንቱ ፈራሁ። አምላኬ እኔ በትምህርት

አልለወጥምና እንዳምንህ እባክህ አርዳኝ። ሰይጣን የእምነት ወገቤን ብዙ ጊዜ ደበደበኝ አንተ በጽኑ ፍቅርህ እንደ ገና አስታጥቀኝ። ለሥጋ ፍርሃት እጅን የማልሰጥ እንድሆን ይልቁንም በእምነት የማስከብርህ ልጅህ እንድሆን እመኛለሁ። እሹ ያልህ ጌታ መስጠት ልማድህ ነውና ለዘላለሙ አሜን።

ምዕራፍ ዐሥራ አንድ
የወዳጅ ዋስትና

የምንኖርበት ዓለም በድምፅ የተሞላ ዓለም ነው። የነፋስ ሽውታ፣ የወንዝ ፈሳሽ፣ የውሃ ጠብታ፣ የአእዋፋት ዝማሬ፣ የዶሮ ጩኸት፣ የሰዎች ጨዋታ፣ የመኪና ድምጽ፣ . . . ይሰማል። እነዚህ ድምፆች ባይኖሩና ሕይወት የሌለበት ፍጹም ፀጥ ረጭ ያለ ቢሆን ኖሮ ምድር አስፈሪ ቦታ ትሆን ነበር። ብዙ ድምፆች ባሉበት ዓለም ላይ ግን አንድ ትልቅ ድምፅ አለ። እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። እውነትን የማይወዱ ሰዎች ይህን ድምፅ ላለመስማት በብርቱ ይጠነቀቃሉ። ሊያመልጡ በማይችሉበት ጠባብ ሰዓት ይህ ድምፅ ቢመጣባቸው በልዩ ልዩ ጨዋታ ለማሰለወጥ፣ ቸኩያለው የሚል ሰበብ ለማቅረብ ይሞክራሉ። በማያውቋቸውና በፍርድ ቀን በማይከሰሱባቸው ሰዎች ወሬ ለመጠመድ ይጣደፋሉ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እያስተማረ ሳለ እውነትን መስማት የሚረብሸው አንድ ሰው «እነሆ÷ እናትህና ወንድሞችህ ሊነጋገሩህ ፈልገው በውጭ ቆመዋል» አለው። በአይሁድ ባሕል የቃሉ ገበታ ተዘርግቶ ማቋረጥ ፍጹም ክልክል መሆኑን ቢያውቅም የትምህርቱን ሂደት ለማደናቀፍ ይህን አለ። ነገር ግን አንድ እውነት ላለመስማት የሚፈልጉ ሰዎች የበለጠ እውነት እንደሚሰሙ የዚህ ሰው ታሪክ ያስረዳናል። የሰማርያይቱ ሴት የንስሓን ድምፅ ላለመስማት ያነሳችው የአምልኮ ጥያቄ ለቤተ ክርስቲያን ትልቅ መልስ አስገኝቷል (ዮሐ.4÷16-24)።

ጌታችንም፡- *«እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው? አለው። እጁንም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘርግቶ፡- እነሆ እናቴና ወንድሞቼ፤ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ÷ እርሱ ወንድሜ እኅቴም እናቴም ነውና»* አለ (ማቴ.12÷46-50)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋዊውን ዝምድና ማቃለሉ፣ እናቱንም መናቁ በፍጹም አልነበረም። ያማ ቢሆን ኖሮ ለእርሱ በሚታሰብለት ሰዓት በመስቀል ጭንቅ ላይ ሆኖ ለእናቱ ባላሰበ ነበር (ዮሐ.19÷26)። ነገር ግን ከሥጋ ዝምድና የዓለማ ዝምድና እንደሚበልጥ መናገሩ ነው።

ወዳጅ ማለት ምን ማለት ነው? ብንል የዓለማ ዘመድ ማለት ነው። በዚህ ዓለም ላይ ሦስት ዓይነት ዝምድናዎች አሉ፡-

1. ወንድም
2. ጓደኛ
3. ወዳጅ

በሥጋና በደም የተሳሰርነው ወንድም ይባላል። የቅርብ ዘመድ የአገር ልጅም ወንድም በመባል ይጠራል። ወንድማችን ወንድማችን የሚሆነው በእኛ ፈቃድ ሳይሆን በተፈጥሮ ስንሰሰት ነው። ይህ የሥጋ ማሰሪያ ክሞት በቀር ምንም አይበጥሰውም። የልብ ውህደት ግን ብዙ ጊዜ የለውም። ከወንድም ቀጥሎ የምናየው የዝምድና ደረጃ ጓደኛ ነው። የልጅነት፣ የትምህርት ቤት፣ የሥራ ጓደኞች ቢኖሩም ለአካለ መጠን ከደረስን በኋላ ግን የሕይወትን ምሥጢር የምናካፍለው ጓደኛ እንፈልጋለን። ለብዙዎች ቀለብ ከቤታቸው ሲሆን ምክር ግን ከደጅ (ክጓደኛ) ነው። አርስጣጣሊስ የተባለው የግሪክ ፈላስፋ፡- «ጓደኛ ማለት በሁለት አካል ውስጥ የምትገኝ እንዲት ነፍስ ማለት ነው» ይለዋል። ወንድም ያለ ፈቃዳችን የእግዚአብሔር ተፈጥሮ ያስተሳሰረን ሲሆን ጓደኛ ግን ምርጫችን ነው። ለዚህ ነው ስለ ወንድማችን የሚጠይቀን የለም፣ ስለ ጓደኞችን ግን እንጠየቃለን። ምርጫችን ነውና (1ቆሮ.15÷33)።

ጓደኛ እየጠለቀ ሲመጣ ወዳጅ ይሆናል። ወዳጅ የጓደኛ ጓደኛ፣ ጥልቅ ምሥጢራችንን የምናጫውተው፣ በትልልቅ ውሳኔዎቻችን ላይ የምንጋብዘው፣ የምንወደውና የሚወደን፣ ራሳችንን የሰጠነው ነው። ወዳጅ የምንታዘዘው ጌታ፣ የምናዝዘው ሎሌ ነው። ወዳጃችንን ብዙ ጊዜ አናውቀውም። ወዳጅ የሚባለው፡-

- ተገቢ ነጻነታችንን የምንገልጥበት፣
- እንዲያበረታታን የምንፈልገው፣
- የምሥጢራችን መቃብር፣
- ስናጠፋ በፍቅር ፍርሃት የምንፈራው፣
- ክማይገቡ ባልንጀሮች ጋር እፍ ስንል የሚጠብቀን፣
- የመልካችን ወይም የሀብታችን ጠባቂ ሳይሆን በዋናነት የመልካምነታችን ጠባቂ፣
- ብስለት ያለው የተፈተነና ያለፈ ነው።

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ፍቅርን ፈላጊ ነው። ሴሎችን መውደድና በሌሎች መወደድ ይፈልጋል። በዚህ ዓለም ላይ ለመውደድና ለመወደድ ካልሆነ በቀር የምንኖርበት ሌላ ምክንያት የለንም። ትልቁ ትርፋችን ወዳጅ እንጂ ቍሳቍስ አይደለም። ለራሳችን መኖርን ብንጠላ እንኳ ስለምንወዳቸው መኖርን እንፈልጋለን። እንኳን የሰው ፍቅር የውሻ ፍቅርም ዕድሜ

እንደሚቀጥል ታውቋል። የምንኖርለት ነገር ከሌለ መኖር ያን ያህል አይጣፍጥም። ለራሳችን አንድ ልብስ ስንገዛ አንድ የምንገዛለት ወዳጅ ከሌለን እርካታችን ጎዶሎ ነው። ሕይወት ለእኔ ለእኔ ሲሉት አይጣፍጥምና።

ፍቅር ማለት እኛ ሰዎቹን ስንወዳቸው እንጂ ሰዎቹ እኛን ሲወዱን አይደለም። የፍቅር ደስታ ያለውም ከመስጠት ውስጥ እንጂ ከመቀበል ውስጥ አይደለም። ሌሎች ሲያፈቅሩን አፍቃሪ የሆንን የሚመስለን ጊዜ ብዙ ቢዥንም ፍቅር ግን መስጠት ነው። ብዙ ጊዜም ጠላቶቻችንን ለመውደድ እንታገላለን። ወዳጃችንን ሳንወድ ጠላታችንን መውደድ እንደማንችል ግን አይገባንም። ወዳጁን መውደድ ያልቻለ ጠላቱን መውደድ እንዴት ይችላል?

ለስማያዊ አባት ያለንን ፍቅር የምንገልጠው እርሱ የወደዳቸውን የሰው ልጆች በመውደድ ነው። የእግዚአብሔር ውለታ ብርቱ ነው። የት አግኝተን እንመልሰለታለን? ብንል እግዚአብሔር ከምናያቸው ፍጥረቶቹ ጋር ነውና ለእነርሱ መልካም ስንሆን ለእርሱ ማድረጋችን ነው። በዓለም ላይ ብዙ ኃይሎች ቢኖሩም ፍቅር ግን ከማንኛውም ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ኃይል ይበልጣል። ፍቅር ያሸንፋል! በሰለጠነው ዘመን ሰዎች መኪናዬን እወዳለሁ፣ ውሻዬን እወዳለሁ ብለው ይናገራሉ። ሰውን እወዳለሁ ብለው ግን አይናገሩም። ትልቅ ምስኪንነት ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን ሰዎችን እንድንወድ ነው።

ፍቅርን የምናውቀው እግዚአብሔርን ስናውቅ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና (1ዮሐ.4÷8)። በርግጥ ፍቅር የሚባለው ሁሉ እግዚአብሔር ነው ማለት አይደለም። ዓለም ስለ ፍቅር ትናገራለች። ነገር ግን እግዚአብሔርን አታውቅም ለማወቅም ፈቃደኛ አይደለችም። እግዚአብሔር በማይታወቅበትና በማይከብርበት ስፍራ ፍቅር ሊኖር በፍጹም አይችልም። በትእዛዝ ማፍቀር አንችልም። እግዚአብሔር እንዴት እንደወደደን ስናውቅ እንወደዋለን፣ ከዚያም ሰዎችን መውደድ እንጀምራለን። ምንጊዜም የፍቅር መነሻው እግዚአብሔር ነው። ፍቅር ከሁሉም በላይ እውነት ይፈልጋል። እውነትና ፍቅር አይነጣጠሉም። እውነት በሌለበት ግንኙነት እውነተኛ ፍቅር ሊኖር አይችልም።

ፍቅር ብዙ ምሳሌዎች አሉት። ለዚህ ምዕራፍ ግን ፍቅርን በወንዝ መስለነዋል። ወንዝ የመንፈስ ቅዱስ፣ የማያቋርጥ የእግዚአብሔር ሰላም ምሳሌ ሆኖ ተጠቅሷል (ዮሐ.7÷38)። መንፈስ ቅዱስ በፍቅር የሚሠራ መንፈስ ስለሆነና የእውነተኛ ሰላም ምንጩ

ግብዝነት የሌለበት ፍቅር በመሆኑ ፍቅርን በወንዝ መመሰላችን እውነት ነው። ወንዝ ዐሥር ዓይነት ጠባያት አሉት።

1. <u>ወንዝ አይቋረጥም</u>:- ወንዝ ደራሽ ውኃ አይደለም። ደራሽ ውሃ በክረምት እንጂ በበጋ አይፈስም። ወንዝ ግን በክረምትም በበጋም ይፈሳል። ምንጭ ስላለው አይቋረጥም። እውነተኛ ፍቅር በየትኛውም ዘመን ይኖራል። ምንጩ እግዚአብሔር ነውና አይቋረጥም። ምላሽ ቢያገኝም ባያገኝም ብድርን ሳይጠብቅ ይወድዳል። በችግርም ሆነ በምቾት ዘመን፣ በማግኘትም ሆነ በማጣት ዘመን፣ በሕመምም ሆነ በጤንነት ዘመን ፍቅር ሕያው ሆኖ ይኖራል።

በዓለም ላይ ስለፍቅር ብዙ ትርጉሞች ተሰጥተዋል። ፍቅር በሌላት ዓለም የሚሰጠው የፍቅር ትርጉም ሁሉ ባዶ ነው። ዓለም ፍቅር የምትለው ከፍትወት ጋር የተያያዘውን እንስሳዊ ግብር ነው። እውነተኛውን የፍቅር ትርጉም የሚሰጠን ግን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የፍቅር መዝገበ ቃላት ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ሲገልጽ «እግዚአብሔር ፍቅር ነው» (1ዮሐ.4÷8) ይላል። ፍቅር እግዚአብሔር ከሆነ ፍቅር ሁልጊዜ ቅዱስና በቅድስናም የሚገለጥ ነው። ፍቅር ዕውር አይደለም፣ ስለ ፍቅር በስመ አብ ይቅርም አይባልም። በስመ አብ የሌለበት ፍቅር እውነተኛ ፍቅር አይደለምና።

ወንዝ አይቋረጥም። እውነተኛ ፍቅርም አይቋረጥም። የብዙዎች ፍቅር መከራን፣ ፈተናንና ችግርን አይሻገርም። መከራን አብረው ያሳለፉ ወዳጆችና ባለ ትዳሮች ማግኘት ሲመጣ ይጠላላሉ። ፍቅር ግን ሁኔታዎችን የሚለውጥ እንጂ በሁኔታዎች የሚለወጥ አይደለም። ብዙ ሰዎች በስሜት ያፈቅራሉ፣ በደህና ቀን የማያፈቅሩም ሲሰክሩ ሰው የሚወዱ ብዙ ሰዎች አሉ። እውነተኛ ፍቅር ግን ከእግዚአብሔር ዙፋን ሥር የሚፈልቅ በመሆኑ አይቋረጥም።

እውነተኛ ፍቅር የሚወደው የሰውዬውን ቁመና፣ መልክ፣ አለባበስ፣ ሥልጣን፣ ገንዘብ ሳይሆን ራሱን ሰውዬውን ነው። ቁመናውና መልኩ፣ ሥልጣንና ገንዘቡ ቋሚ አድራሻዎች አይደሉም። የሰው ቋሚ አድራሻው እርሱነቱ ነው። እርሱነቱ መቼም አለ።

2. <u>ወንዝ ወደ ራሱ አይመለስም</u>:- ማንኛውም ወንዝ ተመልሶ ወደ ራሱ አይገባም። ወደ ውጭ ይፈስሳል፣ ስለዚህ

አይቋረጥም። እውነተኛ ፍቅርም ራሱን አያይም፣ ምቾቱን አያዳምጥም፣ ጥቅሙንም ለሌሎች ጥቅም ይተዋል። አስፈላጊ ከሆነ መብቱንም ይተዋል። ለወደዳቸው ሰዎች ይኖርላቸዋል። አፍቃሪነት ሲያከላ ቢችልም ነገር ግን አይገድልም። ዓለም ዋጋ ባትሰጠውም እግዚአብሔር ግን ያከብረዋል።

3. <u>ወንዝ ርቆ ይሄዳል</u>፦ የዓባይ ወንዝ ከኢትዮጵያ ተነሥቶ ሱዳንን፣ ግብፅን አጠጥቶ ወደ ውቅያኖስ ይቀላቀላል። ወንዝ ርቆ ይሄዳል። ፍቅርም ከሚገባው ክፍ ገደብ፣ ከባሕል ገደብ አልፎ ይሄዳል። የእኔ ድርሻ ይህ ብቻ ነው አይልም። የራሱን ድርሻ ከተወጣ በኋላ የሌሎችንም ያልተከናወነ ድርሻ ይፈጽምላቸዋል። ተበድሎ ይቅርታ ሲጠይቅ ይችላል፣ ያበደረው ሳይመለስለት በድጋሚ ሲያበድር ይችላል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ርቆ በመሄድ ትልቁ ምሳሌአችን ነው። እርሱ እኛን በመልካም ካለበን እንኳ ይበቃ ነበር። ነገር ግን በጲላጦስ ፊት ቆሞ ተከሰሰ፣ የግፍ ግፍ ተገርፎ ተሰቀለ። ፍቅር ርቆ ይሄዳል። ክብሬ ስሜ አይልም።

4. <u>ወንዝ ያገኘውን አያልፍም</u>፦ ሰዎች ወንዝ ሲመጣ ቆሻሻ ይጥሉበታል፣ ሳይደፈርስ ተሸክሞ ይሄዳል። ግንድ ቢገጥመው ይሸከማል፣ ቋጥኝ ያንከባልላል። አፍቃሪ ስንሆን ሰዎች ሊያደፈርሱን ይፈልጋሉ። ሞኝ እንመስላቸዋለን። እንደሚያመን እንኳ ማሰብ እያቃታቸው ጦር ይወረውሩብናል። ፍቅር ግን ግንድም ድንጋይም ተሸክሞ የሚሄድ አስቸጋሪ ሰዎችን ሳይቀር የሚታገሥ ነው።

5. <u>ወንዝ ይሸነፋል</u>፦ ወንዝ ኃይለኛ ነው። ግን ይሸነፋል። በቀኝ በኩል ያለው ገበሬ ለመስኖ ሲጠልፈው ወደ እርሱ ጎራ ይላል። ትንሽ ራቅ እንዳለ በግራ በኩል ያለው ገበሬ ሲሰበው ወደ እርሱም ይሸነፋል። ግን አይቆምም። መንገዴን ልሂድበትም አይልም። አሸናፊ ሳለ ይሸነፋል። ፍቅርም ይሸነፋል። ለራሱ የመደበውን የፀጥታ ሰዓት ለታወኩት ያውላል። በሚያስፈልግበት ቦታ ሁሉ ይገኛል። ማንም ይሁን የእርሱ እርዳታ የሚያስፈልገው ከሆነ ባልንጀራ ይሆንለታል።

6. <u>ወንዝ ኪራይ አያስከፍልም</u>፦ ወንዝ ገበሬ ይጠልፈዋል፣ ያለማበታል፣ ለብሉ ሲደርስ ሸጦ ይጠቀምበታል፣ ታታሪ ገበሬ ተብሎ በመንግሥት ይሸለምበታል። ይህ ሁሉ የሆነው በወንዝ ነው። ወንዝ ግን ይህ ሁሉ የሆነው በእኔ ነው ደግሞም ኪራይ ይከፈለኝ አይልም። ፍቅርም ኪራይ አያስከፍልም።

እኛ ያስተዋወቅናቸው ሰዎች ሲጋቡ፣ እኛ የረዳናቸው ሰዎች ባለጠጋና ባለሥልጣን ሲሆኑ ይችላሉ። ፍቅር ግን ሁሉን ያደረገ እግዚአብሔር እንደሆነ ያምናል እንጂ እኔ ነኝ አይልም። በጎ ነገርን ለማየት እግዚአብሔር የጠራኝ ተጋባዥ ነኝ ብሎ ይቆጥራል እንጂ ፍቅር በምንም አይመካም። ለሰዎች መልካም ነገር አድርጎ ምስጋና እንኳ አይጠብቅም። ድርሻውን መወጣቱ ብቻ ያረካዋል።

7. <u>ወንዝ ያረካል</u>፦ ወንዝ አሸንዳን ያጥበዋል እንጂ አያረካውም። የአፈር ቦኖችን ግን እያረካ ያልፋል። ፍቅርም ደንዳኖችን እያጠባቸው ሲያልፍ የተጠሙትን ግን ያረካል። ቢሆንም ፍቅር ደንዳኖችን ሳይቀር ያንቀጠቅጣቸዋል።

8. <u>ድንበር የለውም</u>፦ የዋቢ ሸበሌን ወንዝ ብናይ ከኢትዮጵያ እስከ ሱማሌ ይፈስሳል፣ የመረብ ወንዝ በኤርትራ፣ በኢትዮጵያና በሱዳን ይፈስሳል። በጦርነት በተፋጠጡ አገሮች እንኳ ያለማቋረጥ ይፈስሳል።

ፍቅርም በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጎሣ ሳይገደብ ይፈስሳል። ሑቱ ቢሆን ቱትሲ፣ ቡዲስት ቢሆን ኤቲስት (እግዚአብሔር የለሽ) ፍቅር ያለ ልዩነት ይወድዳል። በምጽዋትም ፍቅር በፍጹም አያዳላም።

9. <u>የኋላውን አያስብም</u>፦ ወንዝ ወደ ፊት ይገሰግሳል እንጂ የኋላውን አያስብም። የገጠመውን ቋጥኝ፣ የተደፋበትን ቆሻሻ ሳያስብ በመንገዝ ራሱን እያጠራ ይገሰግሳል። ፍቅርም ክፉ ትዝታን እያስታወሰ የዛሬውን ኑሮ አያመርም። ዛሬ አዲስ ቀን ነው ብሎ ያምናል። እውነትም ዛሬ አዲስ ቀን ነው። ቀኑን ወሩን ዓመተ ምሕረቱን ጻፉት። ይህችን ቀን ከዚህ በፊት አይታችኋታል? በፍጹም አዲስ ቀን ናት። ትላንት የከዱን ይኖራሉ። ፍቅር ግን ዛሬ ያፈቅራል እንጂ ትላንት ላይ አይቆምም። የትዝታ እስረኛ አይደለም። ብዙ ዓይነት የፍቅር ታሪክ ቢኖረንም መውደድ ግን ድርሻችን ነው። *«ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ»* (ዘሌዋ.19÷18) እንጂ ይውደዱህ አልተባለምና።

10. <u>ወንዝ ግብ አለው</u>፦ ወንዝ ተንከራታች አይደለም። በጠባብና ከመሬት በታች በተሸረሸሩ ፈፋዎች የሚጓዘው ከእርሱ ወደሚበልጠው ውቅያኖስ ውስጥ ለመግባት ነው። ፍቅር ሞኝነት አይደለም። ዓላማ፣ ግብና መጨረሻ አለው። የምናፈቅረው የሰውን ልብ ለጌታ ለማንበርከክና ነጻነትን ለመጎናፀፍ ነው። ፍቅር በዚህ ዓለም ላይ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ አልፎ ከታላቁ የፍቅር

ውቅያኖስ በአጋፔ ውስጥ ለዘላለም ያርፋል። ታዲያ እኛ ወንዝ ነን ወይስ ደራሽ ውሃ?

ሁላችንም ወዳጅ ወይም ጓደኛ ፈላጊዎች ነን። የወዳጅ መስፈርትም እናወጣለን። የማይዋሽ፣ ምሥጢረኛ የሆነ፣ ብበድለውም ይቅር የሚለኝ ... እንላለን። እኛ ባለቤቶቹ ግን ይህን መስፈርት የምናሟላ ነን ወይ? ብለን ራሳችንን እንጠይቅም። በእኛ የሌለውን በሰው መፈለግ ድካም ነው።

ፍ

ወዳጅ የማትረፊያው ብቸኛ መንገድ ወዳጅ መሆን ነው። የምንኖርበት ዓለም የዘራነውን የምናጭድበት ዓለም ነው። ስለዚህ ፍቅርን ስንዘራ ፍቅርን እናጭዳለን። በዘር ሕግ የምናጭደው የዘራነውን ያህል ሳይሆን ከዘራነው በላይ ነው። አንድ ቀን በጎ የዋልንለት ብዙ ቀን በፈቃዱ ያገለግለናል። የወደድነው ሰው ባሪያ ይሆንልናል። ገና ያልተሞከረ መሣሪያ ቢኖር ፍቅር ነው።

የወዳጅ ዋስትና ብዙ ጊዜ አይለማንም። ብዙዎች አውላላ ሜዳ ላይ ጥለውን የሄዱ፣ ወርቅ አበድረን ድንጋይ የተቀበልን ሰዎች ነን። በዕድሜያችን ያሳለፍናቸው ከአሸዋ የሚበዙ ባልንጀሮች ናቸው። ከሁሉም በላይ አብሮ የመኖር ፈተና ያስፈራናል። ነገር ግን አብሮ የመኖር ፈተና ሲያስፈራን ዋስትናችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ወዳጅ ለማትረፍና ወዳጅን ለማቆየት አራት ነገሮች ያስፈልጉናል።

1. <u>ማዳን አለብን</u>:- የወዳጅነት ዋነኛ ዓላማ አንዳችን አንዳችንን ለመታደግ ነው። የዳነ ባልንጀርነት ከዳነ ሕይወት የሚገኝ ነው። ሰራሱ የጠፋ ሰው ለእኛ ሊገኝልን አይችልምና ወዳጃችንን ማዳን ቀዳሚው ተግባር ነው።

2. <u>መምከር</u>:- ወዳጅ ራስን የሚያሳይ መስታወት ነው። በፊታችን ላይ ቆሻሻ እንዳለብን ካወቅን ሳያስችለን በቶሎ እናስወግደዋለን። ወዳጃችን ማለት ሌላኛው ፊታችን ማለት ነው። ስለዚህ ራሱን ልናሳየው ልንመክረው ይገባል። ይህ ሲሆን ብቻ ወዳጃችንን እናተርፋለን፣ እናቆያለን።

3. <u>ከልብ ማፍቀር</u>:- ከልብ ስናፈቅር ሰውዬው ያለ ንግግር አንድ መንፈሳዊ ኃይል ሲያናውጠው ያውቀዋል። ይልቁንም ፍቅር ቃል ሳይሆን ተግባር ነውና በተግባር ማፍቀር አለብን። ፍቅራችንም ይቅር የሚል ፍቅር ሲሆን ወዳጅ ይቀርበናል አብሮን ይኖራል።

4. <u>በፈገግታ መቀበልና መሸኘት አለብን</u>:- አብዛኛው ሰው የፊት ረሀብተኛ ነው። ለወዳጅ ለምለም እንጀራ ከማቅረባችን በፊት ለምለም ፊት ማሳየት አለብን። ይህን ሁሉ አሟልተን ቢሄድስ ብንል ይሂድ። ፍቅር ብድር ሳይሆን ፍቅር ትእዛዝ ነው። የምናፈቅረው ለራሳችን ብለን እንጂ ሰውዬው ስለሚገባው አይደለም። ገበሬ ብዙ ከዘራ አንበጣና ተምች ቢመጣ እንኳን ጥቂት ያተርፋል። እኛም ብዙ ፍቅር ከዘራን ብዙ እናጭዳለን። ባይሆን እንኳ ጥቂት እናጭዳለን። የጠበቅናቸው ቢከዱን ያልጠበቅናቸውን እግዚአብሔር ወዳጅ ያደርግልናል።

ሸምበቆ ሲደገፉት ይሰበራል። ተሰብሮም አይቀርም ተሰንጥሮ ይወጋል። ሰውም የሸምበቆ ምርኩዝ ነው። ከታመነው ይሰበራል፣ ተሰብሮ ቢቀር ደግሞ መልካም ነበር ነገር ግን ተሰንጥሮ ይወጋል። መልሶ ያሳድደናል። አም አፈር ለሆነው ሰው ፍቅር በቂው ሲሆን ማመናችን ግን በእግዚአብሔር ላይ ሊሆን ይገባዋል።

ለላሣ ስምንት ዓመት እንደ ትኋን በአልጋ ላይ ተጣብቆ የኖረው መፃጉዕ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀርቦ «ልትድን ትወዳለህን?» (ዮሐ.5÷2-9) ቢለው «ሰው የለኝም» የሚለውን ብሶቱን አሰማ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሊረዳው መምጣቱን አላወቀም ነበርና «ሰው የለኝም» አለ። ዛሬም ሰው የለኝም የሚሉ ወገኖች በዝተዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሊረዳቸው ሰው ሆኖ መጥቷልና ይህ ቃል ከእንግዲህ ወዲህ ከንቱ ቃል ነው። ወዳጅ ከዳኝ ለምንል ከዛሬ 2ሺህ ዓመት በፊት በጦር ሳይሆን በፍቅር ተገዶ ክርስቶስ ሞቶልናል። በብዕር እንባ የተጻፉ የፍቅር ደብዳቤዎችን ደጋግመን እናነባቸዋለን። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ፍቅሩን የጻፈልን በገዛ ደሙ ነው። እንወዳችኋለን ያሉን ለዎች ዛሬ አይወዱንም። የክርስቶስ ፍቅር ግን የማይለወጥ ነው። ብዙዎች በወዳጅ ፍቅር እንዳበዱ ይነገርላቸዋል። አያሳብድም እንጂ ማበድ ቢገባ ተሳሳች ለሆነው ለሰው ፍቅር ሳይሆን ለክርስቶስ ፍቅር ነበር።

በዓለም ላይ ስንኖር ለዎች የመልካችን፣ የቁመናችን፣ የቁንጣችን፣ የአለባበሳችን፣ የዝናችን፣ የሀብታችን፣ ሌሎችም የዓይናችን፣ የፀጉራችን ወዳጆች ናቸው። ይህ ሁሉ ያለቀ ቀን ግን ወዳጅም አብሮ ያልቃል። ለዎች እኛን የሚያፈቅሩበት ፍቅር ምክንያቱ ደካማና ምድራዊ ነው። እኛነታችንን በለማያዊ ፍቅር የወደደ ክርስቶስ ብቻ ነው። እስረኞችን በወጎኒ፣ ምርኮኞችን በአምባ ማስጠበቅ ብንችል እንኳ ወዳጆቻችንን ግን ቆልፈን መያዝ አንችልም። ወዳጅነት ፈቃድን እያከበርን የምንይዘው ነው።

ብዙ ወዳጆች አሳልፈናል። ሰዎች ምንም ሳያዩብን እንኳ ተለይተውናል። እየተጠነቀቅንላቸው፣ እየከነፍንላቸው ሸሽተውናል። ብዙ ጉዳችንን እያወቀ ግን እግዚአብሔር ዛሬም ከእኛ ጋር በመሆኑ ደስ ሊሰን ይገባል። የወዳጅ መለየት ያሳዝናል። ከማን ጋር ነበርኩ? ያለኛል። ግን እስከ መጨረሻው ሊያሳዝነን አይገባም። ሌሎችን ማየት እስኪያቅተን ሁሉንም ሰው በዜሮ ማባዛት አይገባም። ትዝታችንም የወደፊቱን ኑሮ እንዳንናር እንቅፋት ሊሆንብን አይገባም። ሴት የከዳችው ወንድ፣ ሁሉንም ሴት እንደ ሰይጣን መመልከት፤ ወንድ የከዳት ሴት፣ ሁሉንም ወንድ እንደ አውሬ መመልከት ተገቢ አይደለም። ከዚህ ሁሉ በላይ አበበች ስለከዳችው አልማዝን መበቀል፣ ከበደ ልለሰዳት ወጋየሁን መበቀል እብደት ነው።

በእውነት ስናየው ለሰዎች ያለን ፍቅር ፍቅር ሳይሆን አምልኮት ነው። ወዳጆቻችን ጣኦት ይሆኑብናል። ለእግዚአብሔር ብቻ የሚለጠውን እምነት ተስፋ ፍቅር እንጥልባቸዋለን። እግዚአብሔር ግን ከእርሱ በቀር ማንም እንዲመለክ አይፈልግምና ጣኦት የሆኑብንን ነገሮች ይሰብራቸዋል። ከዓይናችን ፊት ገለል ያደርጋቸዋል። ምክንያቱም በእርሱ ላይ ያለንን መታመን እንዳይወስዱብን ነው። ይልቁንም በሰው የሚታመን ርጉም ነው ተብሎ ተጽፏልና እንዳንረገም እግዚአብሔር ያነሳቸዋል (ኤር.17÷5-8)። «ያለ እገሌ አልኖርም» ስንል እገሌን ወስዶ በደንብ ያኖረናል። «ያለ እገሌ አብዳለሁ» ስንል እገሌን ወስዶ እንደውም የአብድ አማካሪ ያደርገናል። ሽምበቆ ምርኩዝ አይሆንም። ለውም መታመኛ አይሆንም። ይህን ስንል ስውን እየተጠራጠርነው እናፍቅረው ማለት ነው? አይደለም። መታመናችንን ግን በእግዚአብሔር ላይ ብቻ እናድርግ ማለት ነው።

ጌታችንን ያስያዘው ይሁዳ ያለበትን አድራሻ የሚያውቅ ነበር። ዛሬም የሚያሳድዱን አድራሻችንንና ስሜታችንን የሚያውቁ ናቸው። ስለዚህ ልባችንን ይጎዱታል። ጌታ ግን ይሁዳ በመሳም አሳልፎ ሊሰጠው ሲል «ወዳጄ ሆይ» አለው። ጠላቱ ሊሆን ወዳጄ ሆይ አለው። እርሱ ፍቅር ደግሞም ይቅር ባይ ነውና። ወዳጆቻችን ቢጎዱንም ያን ያህል ግን አልጎዱንም። እንድንበሰል እድርገውናል። ተምረንባቸዋል። ማንኛውም ትምህርት ሕመም አለው። ተማሪው ሊማር ሩቅ መንገድ መንዝ፣ የአስተማሪውን ቁጣና ዱላ መቻል፣ እንቅልፍ አጥቶ ማጥናት... አስበት። ትምህርት ሁሉ ሕመም አለው። መደበኛው ትምህርት እንኳ ሕመም ካለው የሕይወት ትምህርትማ በደንብ ሕመም አለው።

ሰዎችን እንወዳቸዋለን። ነገር ግን አይከዱኝም፣ አይተውኝም አይረሱኝም አንልም። ይተዉናል፣ ይከዱናል፣ ይረሱናል። ፍቅራችን ግን ሲጥሉ ብቻ የምንጥለው ዕቁብ መሆን የለበትም። ይህ ሲቆም ይቆማልና። ይልቁንም ደጉን ጊዜ እያሰብን መደለት አለብን። ጥሩ ወዳጅ እንጂ ዘላለማዊ ወዳጅ የለምና።

ሰዎች የከዱን ብቻ አይደለም፣ እኛም ሰዎች ነንና ብዙዎችን ከድተናል። ብዙ ዕድሜያችን ያስቀው የሚወዱንን እየሸሸን፣ የጠሉን የሚመስለንን ስናሳድድ ከሁለት ያጣ ሆነን ነው። ብዙ ፍቅር ስስ ገፋን ብዙ ፍቅሮች ተሰብረውብናል።

እግዚአብሔር ግን የወዳጅ ዋስትና ነው። እኛ ወዳጆች እንዳይከዱን የማድረግ ሥልጣን የለንም። ነገር ግን ወዳጆቻችን ቢከዱን እንኳ እግዚአብሔር ወዳጃችን ነው። ምሥጢራችንን የሚያውቅልን፣ ገበናችንን የሚሸፍንልን እውነተኛ ወዳጅ አለን። እግዚአብሔር በፈረሰው ቅጥር በኩል ሙሉ ሆኖ ይቆምልናል። የወዳጅ ቅጥር ቢፈርስ ወዳጅ ሆኖ፣ የዘመድ ቅጥር ቢፈርስ ዘመድ ሆኖ ይቆምልናል። ወዳጅ፣ ገንዘብ፣ ትዳር፣ ልጅ ለመኖር ድጋፍ ሰጪ ሊሆኑ ይችላሉ። ሕይወት ግን አይደሉም። ሕይወት ክርስቶስ ነው።

የጽሞና ጊዜ

በድምፅ በተሞላው ዓለም ውስጥ የእግዚአብሔር ድምፅ አለ። ከእውነት አትሽሽ፣ ከእውነት መሸሽ ከነጻነት መሸሽ ነውና። ብድር የማይጠብቅ ነጻ ፍቅር እንዲሰጥህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ። ፍቅር የሚያረካህ ሰዎቹ ሊወዱህ ሳይሆን ሰዎቹን እንተ ስትወዳቸው ነው። ፍቅርን ብቻ ሳይሆን ባሕርያቱን በመመርመር ፍቅር አለኝ ወይ? በል። በዚህ ፍቅር ዋጋ ባጣበት ዘመን እንተ ለፍቅር ዋጋ እንድትሠጥ አምልሃለሁ። ከወዳጅ ጋር ለመኖር ፍርሃት አለብህ። ነገር ግን ወዳጅህ፦

- ሊጠፋብህ ፈልገው።
- ሊተውህ እትተወው።
- ሊያስቀይምህ ይቅር በለው።
- እንደ ገና ዕድል ስጠው።

ጸሎት

ከወዳጅ በላይ ወዳጅ፣ ከአባት ይልቅ አባት የምትሆን እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ። የአንተን ወዳጅነት እስካውቅ የፍጡር ወዳጅነት በጣም ያስጨንቀኝ ነበር። እንዳይተውኝ፣ እንዳይረሱኝ እደክም ነበር። ወዳጅነትህ ግን ሁሉን አስረስቶኛልና ተመሰገን። ሁሉን ያየሁብህ የነሮ ሠገነቴ ጌታዬ ምርኩዜ ሆይ አንተ ካልተውከኝ ከሰው መሚገት ከንቱ ነውና ዓይኔን ከሰው ላይ አንሣልኝ። ለዎችን በፍጹም ልቤ እንድወዳቸው እንጂ እንዳልቀየ ማቸው አርዳኝ። በታላቁ ምሕረትህ አሜን።

ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት
ከጠላት ዋስትና

በዓለም ላይ የሚኖሩ ሰዎች በሦስት ምድብ የሚከፈል የተለያየ አመለካከት እንዳላቸው ይነገራል። የመጀመሪያዎቹ ምድቦች፡- በዓለም ላይ ያለነው እኔና የእኔ ወገን ብቻ ነው። ከእኔና ከእኔ ወገን በቀር የተሻለ ማንም የለም። ስለዚህ ከእኔና ከእኔ ወገን ውጭ ያለው መጥፋት አለበት ብለው የሚያስቡ ናቸው። ሁለተኛ ዎቹ ምድቦች፡- በዓለም ላይ የእኔና የእኔ ወገኖች አስተሳሰብ የተሻለ ነው። ሌሎች የራሳቸው የሆነ አስተሳሰብ ቢኖራቸውም እኔ ግን ከማንም ምንም አልፈልግም ብለው የሚያስቡ ናቸው። ሦስተኛዎቹ ምድቦች ደግሞ እኔና የእኔ ወገን የተሻለ ነገር ቢኖረንም ሌሎችም ከእኔ የተለየ የተሻለ ነገር አላቸውና አስፈልጋቸዋለሁ፣ ያስፈልጉኛል ብለው የሚያስቡ ናቸው።

በጀርመን ስድስት ሚሊየን አይሁዶች በታላቅ ጭካኔ እንዲጨፈጨፉ ያደረገ፣ በሩዋንዳ ሁቱና ቱትሲዎችን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አንድ ሚሊየን ሰዎችን ለእልቂት የዳረገ፣ በናይጄሪያ ፕሮቴስታንትንና እስላሞችን፣ በአየርላንድ ፕሮቴስታንቶችንና ካቶሊኮችን ያለ ርኅራኄ ያገዳደለ፣ ዛሬም ጅሃድን በዓለም ላይ ያወጀ ይህ የመጀመሪያው አመለካከት ነው። የራሳችንን እናት ለመውደድ የሌላውን እናት መጥላት አስፈላጊ እንዳልሆነ ሁሉ አገራችንን ለመውደድ የሌላውን አገር መጥላት አስፈላጊ አይደለም። አመለካከታችንንም ለማክበር የሌሎችን አመለካከት መዋጋት አያስፈልገንም። በጥላቻ ላይ የተመሠረተ ፍቅር እውነተኛ አይደለምና። የዓለምን ጨለማ ገፍፈው ያለፉ ጥቂት ሰዎች ሦስተኛ ው ምድብ ላይ የሚገኙ ቅን ሰዎች ናቸው። የመጀመሪያዎቹና ሁለተኛዎቹ ምድቦች ግን ዓለምን በስቃይ ጦር ወግተዋት ያለፉና አሁንም እየወጓት ያሉ ናቸው። በዓለም ላይ ጠላትነትን የሚወልደው ቀዳሚው ነገር የመጀመሪያው አስተሳሰብ ነው። ከእኔና ከእኔ ወገን ውጭ ያለው ማንኛውም ነገር መጥፋት አለበት የሚል ደካማ አስተሳሰብ የጠላትነት መነሻ ነው።

በአንድ ወቅት የዱር አራዊትና የቤት እንስሳትን በአንድ ትልቅ ሙዚየም ውስጥ ስንበኝ ባለሙያው የዱር አራዊት ሥጋቸው ቀይ እንደ ሆነና እንደማይሰባም ነገረኝ። ለምን? ስለው ዘወትር በፍርሃትና በሽሽት ስለሚኖሩ አይሰቡም በማለት መለሰልኝ። በለው ኃጢአት ምክንያት ይህች ምድር ለእንስሳትና ለአራዊት እንኳ ምቹ መኖሪያ መሆን አልቻለችም። አራዊት የሚጠላሉ ለሞት የሚፈላለጉ

የሆኑት ከሰው ውድቀት በኋላ ነው። አራዊት ባላቸው የደመ-ነፍስ እውቀት የፊቱና የአፍንጫው አቀማመጥ እነርሱን የማይመስለውን እንደ ጠላት ያዩታል። ደግሞም ሰዎችን የሚገድሉት የሚገድሏቸው ስለሚመስላቸው ለመቅደም ነው። ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ለልጅ ምክር ለአባት መታሰቢያ በተባለው መጽሐፋቸው «ልጄ ሆይ! የአንበሳና የነብር የሴሎቹንም አራዊት ግርማ ከመፍራት ይልቅ እግዚአብሔርን የማይፈሩ የክፉ ሰዎችን ፊት ፍራ። የዱር አራዊት ለመግደል ካልፈለጓቸው እነርሱ ፈልገው አይመጡም። ክፉ ሰዎች ግን ሰውን ፈልገው ካላጠፉ እንቅልፍ አይወስዳቸውም። ከተሳለ ጦር ይልቅ የክፉዎች ሰዎች መላስ ጠልቆ ይወጋል» ብለዋል።

የሰው ልጆች በየዘመናቱ እግዚአብሔርን አስወጥተው እርስ በርሳቸው በሰላም ለመኖር አስበዋል። ነገር ግን ሰው ከእግዚአብሔር ተለይቶ በራሱ ዕቅድና መንገድ ሰላምና ፍቅር ሲያገኝ አልቻለም። በእውነትም አይችልም። ከእግዚአብሔር ሲጣላ ሁሉም ነገር እንደተጣላው ከአዳም ማየት እንችላለን፦

- የሕሊና ሰላም አጣ፣
- ትዳሩ ከሰ በዛበት፣
- ልጆቹ የሚጋደሉ ሆኑ፣
- ተፈጥሮ በሰው ላይ ዐመፀ። ከእግዚአብሔር ስንጣላ ሁሉም ነገር የገዛ ተፈጥሮአችን ላይቀር ይጣላናል። ጎሲናም ያሳድደናል።

ሰላም ሦስት ዓይነት ቅርጽ አለው። ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም፣ ከራስ ጋር ሰላም፣ ከጎረቤት ጋር ሰላም። ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ስንሆን ብቻ ከራሳችንና ከሌሎች ጋር በሰላም መኖር እንችላለን። አሲያ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ጦርነት እስከ ገጠምን ድረስ ከራሳችንና ከሌሎች ጋር በሰላም መኖር አንችልም። ሰዎች በዛሬው ዘመን ሰላም ላይሆኑ ሰላም ነው እያሉ ይዋሻሉ። የሰላሙን ጌታ አስወጥተው እንዴት ሰላም ይሆናሉ?

ጠላትነት በምድር ላይ አለ። ስለዚህ እግዚአብሔር ለፍጥረታት መከላከያ ሰጥቷቸዋል። ለአንዳንዶች ቀንድ፣ ለሌሎች ሩጫ፣ ለቀሩት ዛፍ፣ ለተወሰኑት ጉድጓድ ደግሞም ባሕር መከላከያ ሆኖ ሲሰጣቸው ለሰው ግን የተሰጠው መከላከያ ጸሎት ነው። ገና ያልተጠቀምንበት ትልቅ የጦር መሣሪያ ቢኖር ጸሎት መሆኑን ብዙ ጡረታ የወጡ የጦር መኮንኖች ሲናገሩ ሰምቻለሁ፣ አንብቤአለሁ። በአንድ ገዳም ውስጥም «ጸሎት ከጠበቀ ከአጥር ይበልጣል» የሚል ጥቅስ ከዓመታት በፊት ማንበቤን አስታውሳለሁ። ምድራዊው አጥር የሚመልሰው የሚታየውን ጠላት ነው። የጸሎት አጥር ግን የሚታየውንም የማይታየውንም ጠላት ይመልሳል።

በግብጽ አገር አንድ መነኩሴ ካለበት ገዳም ተነሥቶ ወደ ሴላ ገዳም ሲጓዝ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ውስጥ መሸበት። ጨለማውም ወደ ፊት አንድ እርምጃ አላራምድ አለው። በዚህ ጊዜ ባለበት ቆመ። በትረ መስቀሉንም አንሥቶ ዙሪያውን በክብ አሰመረ። ይህ አጥር እንደ መሥራት ነው። በአራት ማዕዘንም ስመ እግዚአብሔርን ጠርቶ ክፉውን ሁሉ አሠረ። በመካከሉም ተኛ። ጠዋት ሲነጋም አንበሳው በዚህ፣ ነብሩ በዚህ፣ የጫካው አራዊት ሁሉ ከበውት ነበር። ነገር ግን የተሠመረውን መስመር ማለፍ አልቻሉም ነበር። ተነሥቶም ስመ እግዚአብሔር ሲጠራ ወደ ጫካቸው እየተሯሯጡ ገቡ። የእምነት ነገር ቀላልና የሞኝነት ተግባር ይመስላል። ነገር ግን ብርቱና ጥበበኛ የሚመስለውን የፍጡር አሳብ ሁሉ ያሸንፋል። አራዊት ሁሉ የጸሎትን መስመር ማለፍ አይችሉም።

ፈረንጆች «ከጠላቴ ራሴን እጠብቃለሁ፣ ከወዳጄ ግን አንተ ጠብቀኝ» ይላሉ። ጠላት የሚጠብቁት ሲሆን የወዳጅ ባላጋራ ግን የማይጠነቀቁት ሰባሪ ነው። የወዳጅ ጠላት እንደ ይሁዳ ያለ ነው። ይሁዳ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለበትን ስፍራ የሚያውቅ፣ ደግሞም የሚስም ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ ከወዳጅ ፍቅር የገንዘብ ፍቅር የበለጠበት ነው። የወዳጅ ባላጋራም ጣዕሙ አልቆ እሬቱ የጀመረ ሲሆን ስሜታችንንና ስስ ብልታችንን የሚያውቅ ነው። ስለሚስመንም ማወቅ ይሳነናል። መሳም ጠብም መሆኑን የምናውቀው ቆይተን ነው። የማይሰድበን ነገር ግን እየሳመ ለከፍተኛ መከራ የሚያዘጋጀን፣ ከፊታችን እያወደሰን ከጀርባችን የሚሸጠን ይሁዳ እርሱ ነው። ይሁዳ እኛ ነን። በሩቅ የሚጮኸውን አንበሳ ሁሉም ይፈራዋል፣ ይጠላዋል። ነገር ግን ሲጮኽ መዘጋጀት ይቻላል። መፍራት ግን በእግራችን ሥር የሚሸሎከለከውን፣ ከልስላሴው የተነሣ ባዕድ የማይመስለውን እባብ ነው። የራስ ገላ እስኪመስል የሚያሳስት እርሱ ነው። መፍራት እያሰከሩን ወደ ዝሙት የሚነዱንን፣ እያባበሉ ሱስ የሚያስለምዱንን፣ በቁማር ቤታችንን የሚያፈርሱትን ... ነው። ለዚህ ነው ፈረንጆቹ «ከጠላቴ ራሴን እጠብቃለሁ፣ ከወዳጄ ግን አንተ ጠብቀኝ» ያሉት።

በአንድ ድራማ ላይ ጅልና ሽማግሌ ሆነው ይታያሉ። ቀጥሎ ያለውን ምልልስ ይመላለሳሉ፦ ጅሉ፦ «አብዬ እገሌ» ሲል ሽማግሌውም «አቤት» ይላሉ። ጅሉም «እኔን ሰው ሁሉ ይወደኛል» ሲላቸው ሽማግሌውም፦ «አይ ልጄ ጅልን ማን ይጠላዋል ብለህ ነው?» ሲሉት ይሰማል። ሰው ሁሉ ይወደኛል ብሎ ማሰብ ጅልነት ነው። በርግጥም አይጎዳምና ጅልን የሚንቀው እንጂ የሚጠላው የለም። እውነተኛው ፍቅር ግን አከባሪ ነው። በአንድ ወቅት አንድ ሰው «አንተ ታድለሃል ምን ጠላት አለብህ?» አለኝ። እኔም «እንኳን

እኔ የዋሁዋ ርግብ እንኳ ጠላት አለባት» በማለት መለሰኩለት። አሁንም የሚጠሉን ቢኖሩ እንኳ ተጠልተንም መኖራችን ክጥላቻቸው በላይ ሊደንቀን ይገባል።

ያደግንበት ጎብረተሰብ ጠላት፣ ምቀኛ፣ ሸረኛ አለብኝ የሚል በመሆኑ ሁሉም ለው ጠላት አለብኝ እያለ ያስባል። ብዙ ጠላቶች ቢኖሩብን እንኳ እንደ ራስ ወዳድነታችንንና እንደ ስንፍናችን ያለ ጠላት ግን የለብንም። ራስ ወዳድነታችን ገነትን ያጣንበት ሊሆን ስንፍናችን ደግሞ ባለመጸለይ ወደ ፈተና የሚከተን ነው። የትኛውም ጠላት ገንዘባችንን እንጂ መንግሥተ ሰማያትን ሊነጥቀን አይችልም።

ጠላት አስፈላጊ ነው። ጠላት የሌለበት ዝርክርክ ነው። ጠላት ያለበት ግን ለቅድስናው ይጠነቀቃል። ጠላት የመኖር ምልክት ነው። ነቃፊ፣ ተቃዋሚ፣ አሳዳጅ ካለብን በሕይወት አለን ወይም ተፈርተናል ማለት ነው። ለእኛ ያልታወቀን ጥሩ እንቅስቃሴ ላይ ነን ማለት ነው። የሞተ ለው ጠላት የለበትምና። ለዎች የሞተን ለማማት እንኳ ተፀይፈው «ቱ ቱ ሙት ወቃሽ አያድርገን» ይላሉ። ከዚህ በኋላ አያስፈራቸውምና አያነሡትም። በሕይወት ያለ ለው ግን ጠላት አለበትና ደስ ሊለን ይገባል። ለውን የሚጠላ መጀመሪያ ራሱን የጠላ ለው ነው። ለለዚህ ለዎች ከጠሉን ራሳቸውን ጠልተዋል ማለት ነው። ታዲያ ራሳቸውን ጠልተው እኛን ሊወዱን እንዴት ይችላሉ?

የነቢዩ የዳዊት የእምነት ንግግር እጅግ ይማርካል፡- *«በእግዚአብሔር ታመንሁ፥ ለልፈራም፤ ሰው ምን ያደርገኛል? ...»* (መዝ.55(56)÷4)። የዳዊት ጠላቶች፡-

- ባዩት ቊጥር ደማቸው የሚፈላ፣
- ቃሎቹን የሚያጣጥሉበት፣
- በክፉ የሚመክሩበት፣
- ለባራ ቀንና ትንሽ ስህተት የሚፈልጉበት፣
- የሚጠቋቀሙበትና ወድቆ ያሳየን የሚሉ፣
- በምን እናለናክለው የሚሉ፣
- ወጥመድን ያለ ዕረፍት የሚያጠምዱበት ነበሩ። ነገር ግን ዳዊት ክእነርሱ ተንኮል የእግዚአብሔር ማዳን እንደሚበልጥ ለለ ተረዳ «በእግዚአብሔር ታመንሁ፥ ለልፈራም፤ ሰው ምን ያደርገኛ ል?» አለ። የመጠላትን ጽዋ በደለታ የምንቀበለው በእምነት ነው። በእምነት ለው ፊትም ጠላቶች ጥርስ እንደ ሌላቸው እንበሶች ናቸው።

ሐማ ለመርዶክዮስ በጠረበው እንጨት እንደ ተሰቀለ፣ በዳንኤል ጉድጓድ ቆፋሪዎቹ እንደ ገቡ ዛሬም እግዚአብሔር እንዲሁ ይሠራል። እግዚአብሔር ያነሣውን ላይጥሉት ክፋዎች እንቅልፍ ያጣሉ። ገማልያል የተባለው የብሉይ ኪዳን ሊቅ በሐዋርያት ላይ በሚመክረው የክፉዎች ሽንገ ታሪክን ጠቅሶ ከተናገረ በኋላ *«ለሁንም እላችኋለሁ፥ ለእነዚህ ለዎች ተለዩ ተዉለቸውም፤ ይህ አሳብ ወይም ይህ ሥራ ከለው እንደ ሆነ ይጠፋልና፤ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ግን ታጠፉለቸው ዘንድ ለይቻላችሁም፥ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ጋር ለትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ»* (ሐዋ.ሥራ 5÷38-39) ብሏል። ቢሆንም የሚጠሉን ለዎች ይታዘንላቸዋል እንጂ አይታዘንባቸውም።

አሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድን ለናነብ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ ሊፈጥር በመጨረሻ ላይ *«እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ»* (ቊ.5፤12፤18፤21፤25) ይላል። ከእርሱ በላይ ጥበበኛ የለምና ራሱ እድናቆትና ማረጋገጫ ይለጥ ነበር። በመጨረሻው ቀን ለውን ከፈጠረ በኋላ ግን *«እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ ለየ÷ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ»* (ቊ.31) ይላል። ሁሉንም ፍጥረታት መልካም አለ። ለውን ግን «እጅግ መልካም ነው» አለ። በትምህርት ቤት የሚለጠው የመምህሩ ዋጋ ጥሩ እና እጅግ በጣም ጥሩ የሚል ነው። መምህሩ ለረኩበት ተማሪ እጅግ በጣም ጥሩ ይሉታል። እግዚአብሔርም ለው እጅግ መልካም ነው አለ።

በዓለም ላይ ለው ክፉ ነው በሚል መመሪያ የሚመሩ ለዎች አሉ። ለው መልካም ነው በሚል መመሪያ የሚመሩ ለዎችም አሉ። ይህ መመሪያ የማይቀር ነው። ለው ክፉ ነው ብለን ለናለብ ሁሉንም ለው እንጠላለን፣ ደግነቱን እንኳ በዓይነ ቊራኛ እንመለከተዋለን፣ የማናውቀውን ለው በጎዳና ላይ የሚሄደውን እንኳ «ለታስጠላ፣ ሊያስጠላ» እያልን አየር እየጎለምን እንጣላለን። በዚህ ምክንያት ለላም ይሸሸናል፣ ለጥቅማችን ወይም ግድ ሆኖብን ብቻ ከለዎች ጋር ለለምንገናኝ ሥቃይ ይገጥመናል። እንደ እግዚአብሔር ቃል ለው እጅግ መልካም ነው ለንል ብቻ ለላም እናገኛለን። ክፋው ለው? ተንኰለኛው ለው? አዎ ለው እጅግ መልካም ነው። እግዚአብሔር ያለው ይፀናል።

የአገራችን ለው «ለው ከነ ክፉቱ ጥሩ ነው» ይላል። ለው ሁሉ እቤቱ ተከቶ ባልወጣበት የግርግር ለሞን ጭር ባለው ጎዳና ላይ መውጣት በጣም ያለፈራ፣ አንድ ኪሎ ሜትር መጓዝ በጣም ያስጨንቅ እንደ ነበር አይተናል። ለካ በጎዳና ላይ የሚፈለለው፣ የሚተራመለውና የማናውቀው ለው ለእኛ መኖርና በድፍረት

መውጣት አስተዋጽአ አለው? አዎ እንኳን ሰው እንዲት ቅጠል ያለ ጥቅም አልተፈጠረችም። የአጠቃቀም ጉድለት እንጂ።

ከተማውና በከተማው ላይ ያለው ሀብት ንብረት ሁሉ የእናንተ ቢሆን ነገር ግን በከተማው ላይ ከእናንተ በቀር አንድ ሰው ባይኖር ደስተኛ ናችሁ? አንዱን መኪና አስነሥታችሁ አንድ ኪሎ ሜትር እንደ ተጓዛችሁ ሌላውን ትቀይራላችሁ። ከአንዱ ቡቲክ ገብታችሁ የለበሳችሁትን ለአንድ ሰዓት አድርጋችሁ ትለውጣላችሁ ... ግን ማንም ሰው የለም። ደስ ይሟችኋል? በፍጹም! ንግሥናም አያምራችሁም። ያለ ሰው አይነገሥምና። ያለ ሰው ሰው አልሆናችሁምና ለው አትጥሉ። «ሸገሌ ጎዳኝ፣ አባዘነኝ» ብላችሁ የምታወሩለት ሰው አለ። የምታወሩለትም እኮ ሰው ነው። በአንዱ ብታዝኑ በአንዱ ተጽናንታችኋልና ሰው ጨርሶ ክፉ አይደለም። ጉዳታችሁ ሳይሰማኝ ቀርቶ አይደለም። ምናልባት እንደ እኔ አልቆሰላችሁ ይሆናል። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን ሳይ ቁስሌን ሁሉ ረስቼዋለሁ። ፍቅሩ ሕመሜን ሁሉ ወስዶልኛል። ከሚጠሉአችሁ ሰዎች በሚወዳችሁ አምላክ ለምን አትደነቁም? ሰው ወዶ የሚሰጣችሁ፣ ጠልቶ የሚያሳጣችሁ ምንም ነገር የለም። መስጠት መንሣት የአንድ አምላክ ሥልጣን ነው። በሚሰጥ በሚነሣ፣ በሚገድል በሚያድን አምላክ እመኑ።

በአንድ ወቅት ለተቸገሩ አረጋውያን እንድሰጥ አንድ ሰው ገንዘብ በእደራ ላክ። እኔም እውነተኛ ችግረኞችን የሚያሳየኝ አንድ ሰው ይገኜ በየመንደሩ እዞር ነበር። አሁን ከዚህ መንደር ይበቃል ብዬ ልሄድ ስል አንድ ወጣት «አንድ ደሃ እዚያ ጋ አለ፣ እንድትሰጣቸው ሳይሆን ዝም ብለህ እያቸው» አለኝ። በቃ ልሂድ ስለው ግድ ስላለኝ ገባሁ። በወንዝ ዳር በፈረሰ ቤት የሚኖሩ፣ ጅብ ብዙ ጊዜ ሲገባ ቤታቸውን የሚቆፍርባቸው፣ ዕድሜያቸው ከዘጠና ዓመት በላይ የሆነ፣ ዓይነ ስውር፣ የወላድ መሐን ሴት ነበሩ። ከዚህ በፊት ካየኋቸው ሰዎች ይልቅ መረዳት የሚገባቸው ሰው ነበሩ። በርግጥ ሌሎቹም ካልተደረሰላቸው እንደ እርሳቸው መሆናቸው አይቀርም። ሰባት መንግሥት አይቻለሁ የሚሉት እኚህ አረጋዊ እናት «ለእኔ የሰጠውን ሰማን ሰጠ? እግዚአብሔር ይመስገን» ብለው ነው ለላምታችንን የተቀበሉት። መስጠት የሚያውቁ የአንድ ዘመን እመቤት ነበሩና «ልጆቼ ምን ላቅርብላችሁ?» ብለው መሬቱን ዳሰሱ። ጉልበታቸውን ከእገጫቸው ጋር ገጥመው ብርዱን ለመከላከል የጎንጥላ ልብስ ውጥር አድርገው የሰበሱት አሁንም ድረስ ይታየኛል። እእምሮአቸው ብሩህ፣ በእግዚአብሔር ቃል እውቀት የተሞሉ፣ ታሪክን በጥሩ መስፈሪያ እየሰፈሩ የሚያቀርቡ ናቸው። እኔም ተነሥቼ ያንን ገንዘብ ስለጣቸው ከመሬት ላይ

ለመነሣት በእንድ እጃቸው መሬቱን ጨበጡ፣ ተቀመጡ ብላቸው ተነሡ። እኛን ሲያመሰግኑ መስሎኝ መንፈሴ ሲጨነቅ ሁለት እጆቻቸውን ወደ ላይ ዘረጉ፣ ወደ ሰማይ ወደ ታላቁ ንጉሥ ከተማ አንጋጠጡ። እንደ ጓደኛ አጫወቱት። «ጌታዬ ሆይ፣ አብላኝ ወይም ግደለኝ ብዬህ ነበር። የዘላለሙ ሥላሴ ጠዋት የነገርኩህን ቊርጥ ልመናዬን ስለመለስክልኝ አመሰግንሃለሁ ...» አሉና መሬት ላይ ወድቀው ሰገዱ። ከተነሡም በኋላ «ልጆቼ» አሉ። «ልጆቼ እናንተ በፍጹም አልሰጣችሁኝም የሰጠኝ ጌታዬ ነው። ሰጪ አንድ አምላክ ነው፣ ሰው ግን አቀባባይ ነው። ሰው ይመረቃል፣ እግዚአብሔር ይመሰገናል። ክፈሰጋችሁ ስማችሁን ተውልኝና እጸልይላችኋለሁ። እንደ ሰርዶ ለምልሙ፣ እንደ ከዋክብት ድመቁ፣ እንደ ፀሐይ ለልጥኑ ...» ብለው ምርቃቱን ከምግብ በላይ አጠገቡን። እኔም በጣም ተነካሁ። የለጣቸው ጌታ ብቻ ነበር። ምክንያቱም በግድ እንደ ገባሁ አውቃለሁና። ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ የተናገሩት ንግግር ወዲያው ትዝ አለኝ «እግዚአብሔር ካልላክ በቀር እንኳን ሰው መልአክ አይሰጥም።»

እዎ ሰጪ እንድ እምላክ ነው። እግዚአብሔር ሲያስብ ንጉሡን ስለ ደሃው እንቅልፍ ይነሣዋል። እርሱ ሰጥቶን የሚያስቀርብን፣ እርሱ ነሥቶን የሚሰጠን ማንም የሰምና በሰው መቀየም ከንቱ ነው።

ይህን ጽሑፍ እየጻፍኩ ሳለ ትዳሯ የፈረሰባት፣ ብዙ የሆነችለት ባሏ ሌላ ወድዶ የከዳት ሴት ደውዬላት ነበር። ባለፉት ቀናት እጽናንቻታለሁ። የዛሬው መደወሌ እንዴት ነሽ? ልላት ነበር። «እግዚአብሔር ይመስገን፣ በጣም ደህና ነኝ። እግዚአብሔር ሲሰብር ይጠግናል። እግዚአብሔር ሰምን? አይባልም። ወደፊት ያለውን ለሳየ ይህን አደረገ። ትልቅ ስጦታን ያለ አድልኦ ሰጥቶናል። አንድ ልጁን። ለሰዚህ ደስ ይለኛል። ዕድሜን የሚሰጠኝ እንድኖርባት ብቻ ሳይሆን ክእርሱ ጋር እንድጣበቅባትም ነው። ትላንትና እስቲ ዝም ልበል ብዬ በዝምታ ውስጥ እግዚአብሔርን አዳመጥኩኝ። በዝምታ ውስጥ አገኘሁት። ... ብዙ ፈተናዎችን አይቻለሁ። ጠላት ለይጣን ካልገደለህ አያርፍም» በማለት መልሳ እኔን እጽናናችኝ።

እኔም ትምህርት ሁሉ ዋጋ እንደሚያስከፍል ትምህርት በነጻ እንዳልሆነ ነገርኪት። እንድ የማውቀው ታሪክም ትዝ አለኝ። ወጣቱ እስረኛ ነው። በጣም የሚወደው አብሮት ያደገ፣ ዘመዱና አብሮት ታስሮ የነበረ ሰው ቀድሞት ሲፈታ ብዙ ሺህ ብሮች በአደራ ሰጠው። ያ ሰው ግን ወዳጅነቱን፣ ዝምድናውን፣ አብረው ያሳለፉትን ጊዜ ረስቶ ገንዘቡን ይዞ ጠፋ። ይህ ወጣትም ከእስር ጋር በጣም

የሚወጋው ሕመም ሆነበት። ወደ እግዚአብሔር መጥቶ ንስሓ ከገባ በኋላ ግን የቀድሞ ቂሙና የበቀል ስሜቱ ርቆለት አየሁት። አንድ ቀንም፦ «ይህ ሰው ብዙ ነገሮችን አስተምሮኛል። አንድ ኮሌጅ ገብቼ ብማር እየከፈልኩ ነው የምማረው። ስለዚህ ይህን ትምህርት በዚህ ገንዘብ ስለተማርኩት ደስ ብሎኛል። አግኝቼ ግን ይቅርታዬን ብገልጽለት እረካለሁ» አለኝ።

አም ክፉዎችም ያስተምሩናል። የሚገጥሙን አስቸጋሪ ሰዎች በብዙ ይቀርፁናል። ቢሆንም ሮያጠላቶቻችን መብዛት፣ እኛን ለማጥፋት መሻረካቸው፣ የጉልበታቸው መጨመር ብዙ ጊዜ ያስጨንቀናል። የሰዎች ኃይለ ቃል አንኳ ከምድር ላይ የሚሰርዘን እየመሰለን እንንቀጠቀጣለን። ከእነዚህ ከፀጉር ከሚበዙ፣ ዘመን ከሰጣቸው ጠላቶች ማን ያድነኛል? እንላለን። እግዚአብሔር ለሚወረወርብን ፍላፃ ጋሻችን፣ ከሚያሳድዱን ጠላቶች መጠጊያችን ነው። እርሱ ያለው ብቻ ይሆናልና በብርቱ መጸለይ ያስፈልገናል። አጥራችንን በጸሎት ካላጠበቅን ፈተናውና ውጊያው ይበዛል። ስለዚህ በጸሎት መትጋት ይገባናል። የጸሎት አጥር አይታይም። ነገር ግን የሚታየውንም የማይታየውንም ጠላት ይመልሳል። ደግሞም የአገራችን ሰው «እግዚአብሔር እንኳን ከተዛተ ከተወረወረ ያድናል» የሚለውን ማሰብ ይገባናል።

ነቢዩ ዳዊት በዕድሜው መጨረሻ፦ «እንደ ጠላት ያኔ ነው የሞትኩት፣ ያለሁት እንደ አንተ ነው» ሳይል አልቀረም ይባላል። የጠላት ብዛት አይገድልም።

የጽሞና ጊዜ

ትልቁ ጠላትህ ስስትህ፣ የዝሙት ጠባይህ ነው። የውጭውን ጠላት ስትከላከል የውስጡ በልቶ እንዳይጨርስህ ተጠንቀቅ። በርና አጥርህን ከማጠባበቅ፣ በዓይነ ቊራኛ እያዩ፣ እየተገለማመጡ ከመኖር መጸለይ ይሻልሃል። አንድ ሰው በእግዚአብሔር ታምናለህን? ቢሉት «ተኝቼ የሚጠብቀኝ እርሱ አይደለምን?» ብሏል። ራስህን ጠብቀህ ማዳን አትችልም፣ እግዚአብሔር ግን ይጠብቅሃል።

ስለዚህ፦

- እኔ ብቻ ነኝ ያለሁት ብለህ አታስብ፣
- ሰዎች እንዲወዱህ ከፈለግህ ውደዳቸው፣
- ሁሉም ሰው ሲወድህ በጣም ደስ አይበልህ፣ ሁሉም ሰው አልወደደኝም ብለህም አትዘን።

- ለላም ቀንድ ላንተ ጸሎት መከላከያ ሆኖ ተሰጥቷችኋል።
- ሰዎች ከፉ የሚሆኑት ዝም ብሎ አይደለም። ከሰውነታቸው መታወክና ሲማሩት ካደጉት ከፉ ትምህርት የተነሣ ነውና እርዳቸው።
- እግዚአብሔርን መፍራት ሲበዛልህ ሰውን መፍራት ታቆማለህ።

ጸሎት

ይቅር ባይ፣ ሰውን የምትወድ ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ። ለተገፋኹት ድጋፍ፣ ለወደቅኹት ምርኩዝ፣ ለተጠላኹት ሞገስ፣ ለተባረርኩት መማፀኛ ሆነኸኛልና አመሰግንሃለሁ። ከጠላቶቼ ግፍ ያንተ ፍቅር በልጧልና ተመስገን። ዘመድ ገሸሽ ላለው ዘመዱ፣ ወዳጅ ለከዳው ወዳጁ አንተ ነህና አመሰግንሃለሁ። ሁሉን ሸኝቼ የቀረኸኝ አንተ ነህና ትብቃኛለህ አያልኩ እጽናናለሁ። አንተ ካልተውከኝ በሰው መቀየም ከንቱ ነውና ዓይኔን ከሰው ላይ አንሣልኝ። ራሴን በኃጢአት የጎዳኹትን ያህል ሰዎች አልጎዱኝምና ይቅር ባይ እንድሆን እርዳኝ። ሰሚጠሉኝ እንዲወዱኝ እርዳቸው። ለእኔም በፍቅር ማሸነፍን አስተምረኝ። አንተን ያገኘ ሁሉን አገኘ፣ አንተን ያጣ ሁሉን አጣ። ማትረፊያዬ ሆይ ተመስገን። ወዳጅነትህ መለወጥ የለበትምና ለዘላለሙ አሜን።

ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት
የመሪ ዋስትና

የእስራኤል ልጆች ወደ ከነዓን ድንበር እየተጠጉ ሲመጡ ብዙ ነገሮች ከዓይናቸው ፊት እየተነሡ ስለ ነበር መንፈሳዊው ሳይሆን ሥጋዊው ባሕርያቸው የሚያየውን ሲያጣ በፍርሃት መናጥ ጀምሮ ነበር። ከፍርሃታቸው አንዱ የሟሪያቸው የሙሴ መሞት ነበር። ስለዚህ የመሪ ዋስትና እየፈለጉ ይጨነቁ ነበር። እንኳን ሙሴን የመሰለ ደግ መሪ ክፉ መሪም ምቱ ያስጋል። በሩዋንዳ ከአንድ ሚሲየን በላይ ሕዝብ ያለ በደሉ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የተጨፈጨፈው መሪያቸው በአውሮፕላን ላይ ሳለ በመሞቱ ነበር። ሙሴ የተስፋይቱን ምድር እንደማይወርስ አስራኤል ሁሉ ስምተዋል። ያለ መሪያቸው ዮርዳኖስን መሻገር ግን ፍርሃት ሆኖባቸዋል። ሙሴም ለጥያቄዎቻቸው ሁሉ መልስ የሚሆን ቃል ተናገረ፦ *«መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው፥ የዘላለምም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው፤»* (ዘዳ.33፥27)። እንደዚህ ያሉ የተስፋና የእውነት ቃሎች ከመቀነት ይልቅ ወገብን ያጠብቃሉ።

መሪን መፈለግ የሰው ልጅ የተፈጥሮ ባሕርይ ነው። ሰው የሚመራው ይፈልጋል። መሪ ለብዙዎች አንድ ድምፅ የሚያስገኝ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ሲፈጥር መሪነትን በውስጡ አስቀምጠበታል። እንስሳትንና አራዊትን ሲገዛ እርሱን የሚመስለውን ሰው ግን ይመራል። መሪ መድረሻውን አውቆ ብዙዎችን አስከትሎ የሚቀድም ነው። መሪ ለመሆን የሚያስፈልገውም ቀድሞ ማየት ነው። ቀድሞ ያየ ሰው መሪ ይሆናል። መሪ ማለት ግዙፍ አይደለም። የመኪናም ሆነ የመርከብ መሪ ትንሽ ነው። ነገር ግን አቅጣጫውን የሚወስነው ትንሹ መሪ ነው። የመሪ ትንሽ የለውም።

በገሀዱ ዓለም ያሉ ሦስት ታላላቅ ተቋማት ቤተሰብ፣ ቤተ ክርስቲያንና አገር መሪ ይፈልጋሉ። እነዚህ ተቋማት እርስ በርሳቸው ተያያዥና ተለያይተው መቆም የማይችሉ ናቸው።

ቤተሰብ

የሰው ልጅ ጉዞ የጀመረው ከአዳምና ከሔዋን መሆኑን ሁሉም ሰው ይቀበለዋል። የታሪክና የቤተሰብ መነሻ እነዚህ ሰዎች ሲሆኑ የዓለም ሕዝብ መሠረቱም ቤተሰብ ነው። የሰው ልጅ በተፈጥሮው ማኅበራዊ ፍጡር በመሆኑ ብቸኝነት ይጎዳዋል፣ ያለ ሌላው ወገኑም

ሙሉ አይደለም። በዘፍ.2፥18 ላይ ያለው ቃል ትዳርን ከመግለጽ የሰውን ማኅበራዊ ተፈጥሮ ለመግለጽ ያደላል፦ *«ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት።»* ይህ ቃል በከፊል ትዳርን ይገልጻል። በሙሉነት ግን ማኅበራዊ ተፈጥሮን ይገልጻል። ምክንያቱም ትዳር ሰጥታ በመሆኑ ሁሉም ሰው ላያገባ ይችላልና ነው። ማንኛውም ሰው ግን እርሱን የሚመስል የአሳብ ረዳት ያስፈልገዋል። ቢሆንም ከማኅበራዊ ተቋማት አንዱ ትዳር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ትዳር በረከት መሆኑን ይናገራል እንጂ ትዳር ትእዛዝ እንደ ሆነ አይነግረንም። ትዳርም ሆነ የድንግልና ሕይወት ሁለቱም ስጦታ ሲሆኑ ሁለቱም ትእዛዝ አይደሉም። ስጦታ ከሆኑ ሁሉም ሰው አያገባም ሁሉም ሰው በድንግልናዊ ሕይወት አይኖርም ማለት ነው። ሁለቱም ትእዛዝ ካልሆኑ ፈቃድ ናቸው ማለት ነው። ስለዚህ ትዳር ፈቃድ ነውና ሰው ትዳሩን እንደ ስጦታና በረከት ተቀብሎ መኖር ይገባዋል። ለፈቀደው ነገር የሚከፍለውን ዋጋም መቍጠር የለበትም።

መልካም ትዳርን መመኘት ብዙ ጊዜ ውጤታማ አይደለም። የትዳርን ልብ መለመን ግን የመልካም ትዳር መሠረት ነው። *«ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ»* (ማቴ.19፥5) ስለሚል ባልና ሚስት አንድ ሥጋ ሆኑ ሳይሆን «ይሆናሉ» የሚል የጊዜ ቀጠሮ ያለው ነው። አንድነቱ በቃል ኪዳኑ ቀን ይጀምራል ትዳሩ ወደ አንድነት ፍጻሜ እያመራ ይሄዳል። ትዳር ትምህርት ቤት መሆኑን ያልተረዳ ሰው ትዳር ያደናብረዋል እንጂ ደስታ አይሆነውም። በትዳር ውስጥ ሰው የሚባለው ፍጡር እስክ ዕድሜ ልክ ተጠንቶ የማያልቅ መሆኑ ይገባናል። ከዚህ ሁሉ በላይ የራሳችንን የተሰወረ ባሕርይ የምናገኘውም በትዳር ውስጥ ነው። ለትዳር ያቀረብናቸው መስፈርቶች መልክ፣ ቍመና፣ ሀብት ከንቱ መሆኑ የሚገባን ዘግይቶ ነው። ከአካባቢው ተጽእኖ ለመላቀቅ ብቻ ወደ ትዳር መግባት ተገቢ አይደለም። ከአጉል ጎብረት ጥሩ ብቸኝነት እንደሚሻልም ማስብ ያስፈልጋል። ነገር ግን ይህን የምናስበው ከትዳር በፊት እንጂ የትዳር መስመር ውስጥ ገብተን አቅጣጫ ማስተካከል አይቻልም።

ትዳር ቤተሰብን ያፈራል። ትዳር የታሪክ ጉዞ እንዲቀጥል ትልቅ ባለ ውለታ ነው። በዓለም ላይ በመልካም ዝና ያለፉ ሰዎች የመልካም ትዳር ውጤቶች ሲሆኑ ዓለምን አስጨንቀው ያለፉ ሰዎችም ከተሰበረ የትዳር ጎብረት ውስጥ የወጡ ናቸው። የትዳር

ሕይወት ከተስተካከለ የአገር ሀልውና ጤናማ ይሆናል። ቤተሰብ ለቤተ ክርስቲያን አማኝ፣ ለአገር ዜጋ የሚወጣበት በመሆኑ ቤተ ክርስቲያንና አገር ከቤተሰብ ብዙ ይጠብቃሉ። ቤተሰብ የደከመበት አማኝ ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሚጠይቀው ጉልበት ትንሽ ብቻ ነው። ቤተሰብ ያላቀናውን ትውልድ ግን አገር የመለወጧ ነገር በጣም አጠራጣሪ ነው። አሥ የቤተሰብ ሕይወት ከተናጋ የአገር ሀልውና ይናጋልና ቤተሰብ እንደ ቀላል የሚታይ አይደለም።

መልካም ቤተሰብ መልካም መሪ ይፈልጋል። ለቤተ ክርስቲያንና ለአገር ኃላፊነት የተሰጠው ወንድ ልጅ በመሆኑ ለቤተሰብም የቤቱ መሪ ባል ነው። ባል ትክክለኛውን ስፍራ ሚስትም ተገቢ ስፍራቸውን ሲይዙ የኑሮ ጉድለት እየተሟላ ትእዛዝም ተፈጻሚ እየሆነ ይመጣል። ቦታ ሲቀያየር ግን ጫና እንጂ ቤተሰብ ጉዞ አይኖረውም። የመሪነት ሁሉ መነሻው ራስን መምራት ሲሆን ራሱን የሚመራ ሰው ቤተሰቡን በቅጡ መምራት ይችላል። ቤተሰቡንም በቅጡ የሚመራ ቤተ ክርስቲያንንና አገሩን መምራት ይችላል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች መስፈርት በተናገረበት አንቀጽ «... *ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፦ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?*» (1ጢሞ.3÷4-5) ብሏል። ቤተሰብን የማስተዳደር ብቃት የቤተ ክርስቲያንንና የአገርን ኃላፊነት ለመሸከም የሚረዳ ነው። የተለያዩ የኃላፊነት ስፍራዎች «ያገባ» የሚል መስፈርት ይጠይቃሉ። የአገር መሪዎችም ያገቡ እንዲሆኑ የሚያስገድዱ አገሮች አሉ።

የቤተሰቡ ራስ ወይም መሪ የሆነው ባል ሲያሟላቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ። የቤተሰቡ መሪ የሆነው አባት ወይም ባል ቤተሰቡን በፍቅር ሥልጣን መምራት የሚችል መሆን አለበት። ትእዛዙ የሚከበረው ስለሚወደድና ትእዛዙ ትክክለኛ ስለሆነ ብቻ መሆን አለበት። ፖፑ አይሳሳትም እንደሚባለው የቫቲካን ሕግ ባል አይሳሳትም ብሎ ማሰብ የለበትም። የቤተሰቡ መሪ እርምትን በደስታ የሚቀበል መሆን አለበት። ቤተሰብ የመሠረተው በዚህ ዓለም ላይ እንደፈለጋት የሚያደርጋት የፈጠራትን ሚስት ደግሞም አሳቡን ሁሉ የሚጠቀጥቅባቸው ልጆች ፈልጎ ከሆነ አጅግ ተሳስቷል። የሰውን ነፃ ተፈጥሮና ሰብአዊ ክብር የማያውቅ ገዥ እንጂ መሪ ሲሆን አይችልም። ባል እጅግ ልፍስፍስ እጅግም ደረቅ መሆን አይገባውም። ደግሞም የሚያዘውን፣ የሚናገረውንና የሚሠራውን

ማወቅ አለበት። የባልነት መገለጫው ኃይለኝነት፣ የአባት መገለጫው ማንቀጥቀጥ አድርጎ በትንሹ ማሰብ የለበትም። ወንዶች ልጆቹ ልክ እንደ አርሱ ያለ ባል ስለሚሆኑ ለትውልድ የሚያስተምረው ሲኖረው ይገባል።

የቤተሰቡ መሪ ለሚስቱ ባል፣ ለልጆቹ አባት መሆን ይገባዋል። ይህ ብቻ አይደለም ድርሻውን የሚወጣ መሆን አለበት። የእኔን ድርሻ ሚስቴ፣ ልጆቹ ይወጡልኝ ብሎ ማሰብ የለበትም። ሚስትና ልጆች ሁልጊዜ ዋስትና ይፈልጋሉ። ስለዚህ በእርሱ ደስ የሚላቸው ድርሻውን ሲወጣ ነው። ልጆቹን መንከባከብ፣ ጓዳውን ማደራጀት የሚስት ድርሻ ሲሆን የልጆቹን ባሕርይ መቆጣጠር፣ ለቤተሰቡ ጉድለት አንዳይመጣ ተግቶ መሥራት፣ ሚስቱን ማበረታታት የባል ድርሻ ነው። ባል በደጅ እርሱን የሚያህለው የለም፣ ሚስትም በቤቷ የሚያህላት የለም። ባል ማኅበራዊ ኑሮው የተጎዳ ከሆነ ሚስቲቱ ጫና ይወድቅባታል፣ እርሱን ሽፍና መኖር ስለምትጀምር ድካምና ህዘን ይገጥማታል። ያ እንዳይሆን ባል ማኅበራዊ ድርሻውን የሚወጣ መሆን አለበት። ስለ ቤቱ ሁልጊዜ ከሚስቱ ወይም ከደጅ ሰዎች የሚሰማ ሳይሆን ቤቱን የሚያውቅ መሆን ይገባዋል።

መልካም የቤተሰብ መሪ ሁልጊዜ ከቤተሰቡ ምክርን ይጠይቃል። አሳቡ መልካም ቢሆንም እንኳ ብቻውን አይወሰንም። ሚስቱን፣ አስፈላጊ ከሆነ ልጆቹን ያማክራል። ይህ አሳቡን የመግለጥ፣ የማሳመን፣ የንግግር ችሎታውን የሚያሳድግለት ሲሆን ውሳኔውንም አብሮት የሚሸከም ተባባሪ ያገኛል። ውሳኔው ትክክል ባይሆን እንኳ ቤተሰቡ የሚያበረታታው እንጂ የሚወቅሰው አይሆንም።

መልካም አባወራ ለቤተሰቡ ጊዜ በመስጠት ይታወቃል። ሚስቱ፣ ልጆቹ ከእርሱ ጋር የሚሆኑበት ጊዜ ይፈልጋሉ። ሚስት ጊዜ ካጣች የተረሳች ይመስላታል፣ ልጆችም ጊዜ ካጡ አባታቸው እንደሚወዳቸው ይጠራጠራሉ። ስለዚህ የቤተሰቡ መሪ ለቤተሰቡ ጊዜ መስጠት አለበት። በሚሰጠው ጊዜ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ፣ በጋራ መጸለይ ደስታ ያለውን ቤተሰብ ይፈጥራል። በዙሪያችን ብዙ ትዳሮች ጊዜ በማጣት በየዕለቱ ሲፈርሱ እንመለከታለን።

የቤተሰቡ መሪ አባወራው በጨዋቱ የሚደመጥ መሆን የለበትም። እርሱ ሳይሰወጥም ተሰወጡ በሚለው ምክሩ ቤተሰቤ ይከተለኛል ብሎ ማሰብ የለበትም። ሰዎች የሚለወጡት ከቃል

ይልቅ በሕይወት ነው። ስለዚህ ባል በሕይወቱ ሚስቱንና ልጆቹን የሚማርክ፣ አርአያ የሚሆን አባት ሲሆን ይገባዋል። ሳይለወጥ ተለወጡ የሚል ባል ግብዝ ነው። ስለዚህ ሱስን ሲያወግዝ እርሱ እየተወ፣ አንብቡ ሲል እያነበበ መሆን ይገባዋል።

የቤተሰቡ መሪ ባል ቤተሰቡ የማይፈራው ነገር ግን የሚያከብረው ሲሆን ይገባል። መልካም አከብሮትን የሚያተርፈው እከብሩኝ በሚል መመሪያ ሳይሆን የተከበረ ሰው ሆኖ በመገኘት ነው። በቤተሰብ ውስጥ አባወራ ካልተከበረ ቤተሰቡ ወደ ትክክለኛው ግብ እየተጓዘ አይደለም ማለት ነው። ስለዚህ አባወራው ተገቢውን ክብርና መሪነት እንዲያገኝ ከሚስቱ ጋር ጥሩ አንድነት ሊኖረው ይገባል።

የቤተሰቡ መሪ ባል የቤተሰቡ ራስ ነው። ራስ ራስ ያስፈልገዋል። ስለዚህ እግዚአብሔር የሕይወቱ ራስ ሊሆንለት ይገባል። የሚመራ ሰው የሚመራው ኃይል ክሌለ መሪነቱ የተሳካ አይሆንም።

ባለንበት ዘመን የትዳር ሕይወት እየተናጋ ትዳርም ዋስትና እያጣ መጥቷል። በዚህ ምክንያት ብዙዎች ጋብቻን እንደ ጦር ፈርተው ተቀምጠዋል። ወደ ትዳር የገቡትም የትዳርን ግብ መፋታት አድርገውታል። በጎዳና ላይ የወደቁ ልጆችም የዚህ የትዳር ክፍተት ውጤቶች ናቸው። ወደ ትዳር የገቡ ሰዎች በትዕግሥት፣ በጸሎት፣ በመመካከር አብረው ሲኖሩ ሲገባቸው የመምረጥና የመተው መብት ያላቸውን ገና ወደ ትዳር የሚገቡትን ሰዎች ግን ቀጥሎ ያለውን ጥያቄ ለራሳቸው እንዲጠይቁ አደራ እንላለን።

- ለትዳር ያሰብኳት ወይም ያሰብኩት እግዚአብሔር አላቸው ወይ?
- በእግዚአብሔር ቃል አርፏል ወይስ አርፋለች?
- ባሕርያችን ይጣጣማል ወይስ ይሁን ይሁን እያልን ነው የምንኖረው?
- እስከ ዕድሜ ልክ አብረን እንደምንኖር አስበንበታል?
- በመካከላችን በሚነሡ ግጭቶች ይቅር እንባባላለን?

እነዚህን ጥያቄዎች የትዳር ዋዜማ ላይ ቆመን ራሳችንን ብንጠይቅ መልካም ነው። ከዚህ ባሻገር መልካም ትዳር በንቃት ሳይሆን በጸሎት የሚገኝ ነው። ትዳር ከምንለው ባሻገር ያለ ሥዕል መሆኑን ኑሮም ተኝቶ መብላት ሳይሆን ትግል መሆኑን መገንዘብ ይገባናል። ወደ ትዳር የገቡ ሰዎች በትዳራቸው ዋስትና

እንደማይሰማቸው እናውቃለን። በፀባይ ለውጦች፣ በሱሶች፣ በትዳር ባለመታመን፣ በመሰለቻቸት ምክንያት ብዙዎች ትዳራቸው የቀን ጉዳይ እንጂ እንድ ቀን እንደሚፈርስ እርግጠኛ ናቸው። ወደ አገልጋዮችም በመምጣት ለፍቺ አሳባቸው ይሁንታ እንዲሰጡአቸው ይፈልጋሉ። እሺታም ሲያጡ ይቀየማሉ። በብዙ ልምድ እንዳየሁት ባለ ትዳሮቹ ራሳቸው ቁጭ ብለው ሲወያዩ ችግሩ በጣም ቀላል ይሆናል። አለመነጋገር እንዳንድ ጊዜ ትንንሽ ነገሮችን ያገዝፋቸዋል። ቢሆንም የትዳር ዋስትና እግዚአብሔር ነውና በትዳራችን እግዚአብሔር የበላይ እንዲሆን መጣር አለብን።

<u>ቤተ ክርስቲያን</u>

መሪ ከሚፈልጉ ተቋማት አንዷ ቤተ ክርስቲያን መሆኗን ቀደም ብለን እንሥተናል። የምንኖርበት ዓለምና ዘመን የመሪ ያለህ የሚል ጩኸት ያሰማሉ። የመሪዎች መፍለቂያ መሆን የሚገባት ቤተ ክርስቲያንም መሪ አጥታ ትጮኻለች። የዓለሙ ጩሰማ መጨለሙ ባይደንቅም የቤተ ክርስቲያን ብርሃን መጨለሙ ግን ያስተክላል። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክነትና ፍጹም እዳኝነት የሚያምኑ፣ በስመ ሥላሴ የተጠመቁ፣ እግዚአብሔርን ለማምለክ የቆረጡ፣ ሁለትና ሦስት ሆነው በስሙ የተሰበሰቡ ምእመናን ቤተ ክርስቲያን ተብለው ይጠራሉ። ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ከሕንጻ ይልቅ የነፍሳትን ስብስብ (መዋቅር- አንድነት) ይገልጻል (የሐዋ.ሥራ 20÷28)።

ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ያለች የእግዚአብሔር ተወካይ ናት። ኢየሱስ ክርስቶስም መልእክቱንና ጸጋውን ለቤተ ክርስቲያን ትቶላት ሄዷልና ከእግዚአብሔር መገናኘት የሚፈልግ ሰው በቤተ ክርስቲያን አማካይነት ይገናኛል። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ኤምባሲ ናት። ሠራተኞቿም እንደራሴዎች ወይም አምባሳደሮች (የክብር መልእክተኞች) ተብለው ይጠራሉ (2ቆሮ.5÷20)። ኤምባሲ ወደዚያኛው አገር ለሚሄዱ ቪዛ ይሰጣል። ቤተ ክርስቲያንም ወደ መንግሥተ ሰማያት የምንገባበትን የእምነት ማኅተም ትሰጠናለች። ኤምባሲ በግዛት ውስጥ ያለ ግዛት ነው። ቤተ ክርስቲያንም ነገሥታት በሚያስተዳድሩት ምድር ላይ ብትኖርም መመሪያዋ ሰማያዊ ነው። ኤምባሲ መማፀኛ ነው። ቤተ ክርስቲያንም ዓለም ላጎሳቆሉቻቸውና የበደለኞነት ስሜት ለሚያሰቃያቸው መጠለያ (መማፀኛ) ናት። ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ባትኖር ኖሮ የተስፋ መቅረዝ በምድር ላይ ባልታየና ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙት ሕዝቦች ሁሉ በሕይወት ባልኖሩ ነበር።

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ናት። ቤተ ክርስቲያን የነገሥታት ሞግዚት፣ የቀሳውስትም መፈንጫ አይደለችም። ቤተ ክርስቲያን የሞተላት የክርስቶስ ናት። የሚታዩ አለቆች ቢኖሯትም እነዚህ ባለ አደራዎች እንጂ ባለቤቶች አይደሉም። ባለቤቷና የሚቀናላት መንፈሳዊ አባወራዋ ክርስቶስ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ለሐዋርያት ከዚያም በእነርሱ እግር ለሚተኩ አረኞች አደራ ሰጥቷታል።

ቤተ ክርስቲያን ለቤተሰብኝ ለአገር ልዩ አስተዋጽኦ አላት። የትዳርን ሰላም በመጠበቅ፣ ምእመናንን በማማከር፣ የተረሱትን በማስታወስ፣ ልጆችን በፈሪሃ እግዚአብሔር በማሳደግ፣ የግብረ ገብ መስኪያዎችን በማስተማር፣ በተራራቁት መካከል ድልድይ በመሆን ተግባሯን መወጣት ይገባታል። የተለወጡ መሪዎች ስታገኝም በትውልድ ላይ ተጽእኖ ማምጣት ትችላለች። ነገሥታት ከተማን ሲሠሩ ትውልድን መሥራት የእናት ቤተ ክርስቲያን ልዩ ተሰጥኦ ነው። ቤተ ክርስቲያን ከእውነት ካፈነገጠች ደግሞ ምድር ትጨነቃለች። በእውነት በዓለም ላይ የምናየው ነገር የቤተ ክርስቲያን ጥላ ነው። ቤተ ክርስቲያን ዘረኛ ስትሆን ዓለም በዘረኝነት ይዋጣል።

ሐዋርያው ጳውሎስ፦ *«ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው»* (1ጢሞ. 3÷1) ብሏል። እግዚአብሔርን ማገልገል የሥራዎች ሥራ ከዚህ ሁሉ በላይ «መልካም ሥራ» ነው። ነቢዩ ዮናስ «ሥራህ ምንድር ነው?» በማለት ሲያዋክቡት እርሱ ግን *«እኔ ዕብራዊ ነኝ፤ ባሕሩንና የብሱን የፈጠረውን የሰማይን አምላክ እግዚአብሔርን አመልካለሁ አላቸው»* (ዮና.1÷8-9)። እግዚአብሔርን ማምለክ ትልቅ ሥራ ነው። የሰው አገልጋይ ከመባል የእግዚአብሔር አገልጋይ መባል ያስደስታል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መልእክት በሚጽፍበት ዘመን ኤጲስ ቆጶስ (ጳጳስ) ለመሆን የሚጠይቀው ፍላጎት ነበር። ዘመኑ ዘመነ ሰማዕታት ስለ ነበር መከራ ሲመጣ በመጀመሪያ የሚሞተው የቤተ ክርስቲያኑ መሪ ነው። ስለዚህ ጳጳስነትን መምረጥ አብሮ ሞትን መምረጥ ነበርና «ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ» አለ። ዛሬ ቢፈልግ ቢባል ማን ይቀራል? መከራ የለማ! እንደውም ማዕረጉ እንደ ምድራዊ ሥልጣን ሰው መጨቆኛ ሆኗል። በቀደመው ዘመን ጳጳስ ያፀናውን ግብር ንጉሥ ይቀንስ ነበር። ቀሳውስቱም የተማረኩ ባሮችን ከነገሥታት ገፀ በረከት ይቀበሉ ነበር።

ቤተ ክርስቲያን መሪ እየፈለገችበት ያለ ጊዜ ነው። የመሪዎች መስፈርት እንግሊዝኛ ቋንቋ ሳይሆን መንፈሳዊነት፣ የድምፅ ብልጫ

ሳይሆን ጸጋ ሊሆን ይገባዋል። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪ ጳውሎስ ከሰጠው መመዘኛ ጋር፦

- እግዚአብሔር የሚመራው፣
- ዓለምን የካደ፣
- ለመንጋው ፍቅር ያለው፣
- ቅዱስና እውነተኛ፣
- ለፍትሕ የሚሟገት፣
- ነፍሱን ለመንጋው አሳልፎ የሚሰጥ፣
- ትውልድን የሚንከባከብ፣
- ግፍን የሚያወግዝ፣
- ሕዝብን ከሕዝብና መንግሥትን ከመንግሥት የሚያስታርቅ፣
- የድሆች ወዳጅ መሆን ይገባዋል።

ምእመናን እንደዚህ ያለ መሪ ይፈልጋሉ። ይህን በማጣት ብዙዎች ወደ ዓለም ይሄዳሉ፣ ሌሎችም በራቸውን ዘግተው እቤታቸው ተቀምጠዋል። በግ ሊውልበት የሚገባው የእግዚአብሔር ቤትም የተኩላ መደነሻ ሆኗል። የመሪዎችም አለማፈር በርክቷል። ምእመናን የመሪ ዋስትና ይፈልጋሉ። ነገር ግን የሃይማኖት እውነተኛ መሪ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና እርሱን ብቻ መመልከት ይገባቸዋል። እርሱ ከዘመን ዘመን አይለወጥምና። *«ስለዚህ ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ፥ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ፤»* (ዕብ.3÷1)።

ደግሞም የነቢዩ የዕንባቆም ጸሎት ወገባችንን ያጠነክር ልናል፦

«ምንም እንኳን በለስም ባታፈራ፥
በወይንም ሐረግ ፍሬ ባይገኝ፥
የወይራ ሥራ ቢጐድል፥
እርሻችም መብልን ባይሰጠ፥
ላሞችም በጋጡ ውስጥ ባይገኙ፥
እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፤
በመድኃኒቴ አምላክ ሐሴት አደርጋለሁ።
ጌታ እግዚአብሔር ኃይሌ ነው፤
እግሮቼን እንደ ዋላ እግሮች ያደርጋል፤
በከፍታዎችም ላይ ያስሄደኛል»
(ዕንባ.3÷17-19)።

አገር

አገር የምንለው ተራራና ሸንተረሩ ዳርና ድንበሩ ብቻ ሳይሆን ሕዝብም ነው። ምድራችን ሕዝቧን የማይወዱ አፈሯን ግን የሚወዱ መሪዎችን ለዘመናት አስተናግዳለች። የአገር እውነተኛ ትርጉሙ ግን ሕዝብ ነው። ከዚያም እግዚአብሔር የከሰከልን ርስት ነው። አገር ሕዝቧን የሚመራላት፣ ግዛቷን የሚያስከብርላት፣ እንደ መልካም ባል የሚያስብላት፣ ዕዛሬ ብቻ ሳይሆን ስትውልድም የሚያስብ መሪ ትፈልጋለች። መሪ ሕዝብን ለመምራት ማስተማርና መቅጣት በድርብ የተሰጡት ነው። መሪ የተፈጥሮ ፍላጎት ነው። በመሆኑም ሕዝብ አንድ ድምፅ ሆኖ እንዲያለማ፣ አንድ ሆኖ ጠላቱን እንዲከላከል መሪ ያፈልጋል።

ምእመናን ሥልጣን ከእግዚአብሔር መሆኑን ተረድተው ድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል። ለአገር መሪዎች የምእመናን ድርሻ፦

1. <u>መጸለይ</u>፦ ነገሥታትና መኳንንት ጸሎት ያስፈልጋቸዋል (1ጢሞ.2÷1)። አሊያ ሲያጣን ሲያውካቸው ስላማችንን ያናጉታል። የጸሎት ድርሻችንን ሳንወጣ ልንወቅሳቸው አይገባም። ቤተ ክርስቲያን የሞቱትን ነገሥታት ስም እየጠራች ስትጸልይላቸው ላሉት ነገሥታት ግን ስም እየጠራች አለመጸለይዋ ያሳዝናል።

2. <u>ለትክክለኛ ሕጋቸው መገዛት</u>፦ እውነተኛ ሕጋቸውን ማክበር ይገባል። የሃይማኖትም አለቃው እኔ ነኝ ብለው ሃይማኖትን ካዱ ያሉ አንደ ሆነ ግን የሃይማኖት መሪው ክርስቶስ ነውና አንገዛላቸውም (ሮሜ.13÷1)።

3. <u>ግብርን በጊዜው መክፈል</u>፦ ነገሥታት ሕዝብን የሚያስተዳድሩት ከሕዝብ በሚሰበስቡት ግብር በመሆኑ ይህም ከእግዚአብሔር ተፈቅዶላቸዋልና ልንክፍል ይገባናል። መክፈል ብቻ ሳይሆን በጊዜው መክፈልም ይገባናል (ሮሜ.13÷6)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ገብሯል (ማቴ.17÷24-27)።

4. <u>የጋራ አገራችንን ማልማት</u>፦ አገሬ ለእኔ ምን አደረገችልኝ? ሳይሆን እኔ ለአገሬ ምን አደረግኹላት? ማለት ይገባናል። አገራችን ክእኛ የምትፈልገው አላት። ነገሥታትም ሆኑ እኛ ቋሚ አይደለንም። መሬቱና ትውልድ ግን ቋሚ ነውና የተባረከች አገር ለማቆየት መትጋት ያስፈልገናል። ከሰው ቆንጆ አገር የኛ ደካማ አገር ናት የእኛ አገር! ስለዚህ እንደ ባዕድ ስትጎዳ ጥለናት መሄድ

አይገባንም። ምድራዊት አገራችን ይህችው ኢትዮጵያ ናት። ዐፄ ዮሐንስ ጠላት በመጣ ጊዜ ያወጁት አዋጅ ልብ ይነካል፦

«የኢትዮጵያ ልጅ ሆይ ልብ አድርገህ ተመልከት! ኢትዮጵያ የተባሰችው አንደኛ እናትህ ናት፤ ሁለተኛ ዘውድህ ናት፤ ሦስተኛም ሚስትህ ናት፤ አራተኛም ልጅህ ናት፤ አምስተኛም መቃብርህ ናት፤ እንግዲህ የእናት ፍቅር። የዘውድ ክብር። የሚስት ደግነት። የልጅ ደስታ። የመቃብር ክባቲነት እንደዚህ መሆኑን አውቀኽው ተነሣ» የሚል ነበር።

አገራችን የሚገድል ሳይሆን የሚሞትላት፣ እግዚአብሔርን የሚያውቅና የሚፈራ መሪ ትፈልጋለች። በአገራችን መሪ ኖሮም ሞቶም ያስፈራል። ስለዚህ የመሪ ዋስትና እያጣን እንጨነቃለን። በንጉሡ ጊዜ ሰው ውጭ አገር ሄዶ ቸኩሎ ይመጣል። ተምሮም አገሩን ሊያገለግል ይመስላል። ክደርግ ዘመን በኋላ ግን ኢትዮጵያዊ አገሩን ጠላ። ጉልበቱም መታሰቢያ በሌለው በባዕድ አገር መፍሰስ ጀመረ። አሁንም ወደ አገር ላለመመለስ ራሱን በሚመስል ነገር አስሮ የቀረው ብዙ ነው። ምድሩ እንደ ብረት ምድጃ እያቃጠለችው አገሩ ለአርሱ እንደ ተፈጠረች የማያስብ በዚህ መኖር ምንም ዋስትና የማይሰማው ወገን ብዙ ነው። ነገር ግን የእኛስ ድርሻ ምንድነው? ብለን መጠየቅ ይገባናል። አገራችንን መኖሪያችን ባናደርጋት የምንቀበርባት ምድር ናትና ልናስብላት በተግባርም ልንወዳት ይገባል። ያስ አገር ክብር እንደ ሌለ፣ እንኳን ሠርጉ ልቅሶውም እንደማይደመቅ እናውቃለን። አናታችንን የምንወዳት ባሰጠጋ ስለሆነች ሳይሆን እናታችን ስለሆነች ነው። አገራችንንም የምንወዳት ባለጠጋ ስለሆነች ሳይሆን የእኛ ስለሆነች ነው።

እውነተኛው መሪ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በነገሥታትም ታምነን መኖር አይገባም። እነርሱ ተሰባሪዎችና ቀን ሲጐድል ራሳቸውን እንኳ ማዳን የማይችሉ ናቸው። የትዳር፣ የቤተ ክርስቲያንና የአገር እውነተኛ መሪ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በእርሱ ስናምን ዓለም የማትሰጠውን ሰላም፣ ከሰው የማይገኘውን ፍቅር እናገኛለን። ሰላምንና ፍቅርን ከሰው የምንጠብቅ ሳይሆን የምንሰጥ አድርጎ ይባርከናል። የበረታብንን ያስገዛልናል። በታሪክ የማይታመኑትን አገልጋይ ያደርግልናል። ሰሌልያስ ከቁራ አፍ ሥጋ እንደመገበ ማለት ነው። በእውነት የኑሮ መድኀኒ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

የጽሞና ጊዜ

መሪ ነህ ወይስ ገዥ? መሪ ብዙ ጊዜ ተመሪ ነው። ሰው ደስ የሚለውን እየመረጠ የሚያደርግ ነውና። ነገር ግን ሰው ደስ የሚለውን ብቻ እያደረግህ ከእውነት አትራቅ። ትዳርን በፍቅር ለመምራት አሳቡ ከሌለህ ባትገባበት ይሻላል። ወደ ትዳር ገብተህ ከሆነም ትዳርህን ለማቆም እንጂ ለማፍረስ ምክንያት አትፈልግ። የመለያየትን አሳብ በውስጥ እንኳ አታስተናግደው። ትዳርን ማፍረስ ብዙ ጉዳቶች አሉትና። የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ስትሆን በአጥቢያህ ቅድስና ጌጣችሁ ይሁን፥ አንተ መንጋውን ያለ አድልኦ የምትመራ ከሆነም አባላቱ ይፋቀራሉ።

ስለዚህ፦

- ትዳርህ ገና አንድ የምትሆንበት መሆኑን አስብ። «አንድ ይሆናሉ» ይላልና።
- ወንዶች ልጆችህ እንዳንተ ያለ አባት ይሆናሉ፣ ሴቶች ልጆችም እንደ እናታቸው ያሉ ሚስቶች ይሆናሉና ለትውልድ ስለምታስተምረው ነገር ተጠንቀቅ።
- ቤትን የማስተዳደር ብቃት ቤተ ክርስቲያንንና አገርን ለማስተዳደር ብቃት ይሆናልና ቤትህን በመልካም አስተዳድር።
- የቤተ ክርስቲያን አለቃ ከሆንህ ባለ አደራ እንጂ ባለቤት እንዳይደለህ አስብ።
- ዓለምን ካልናቅህ ትክክለኛ መሪ መሆን እንደ ማትችል አስብ።
- ለአገሬ ምን አደረኩላት? በል።
- የገዛ ሕሊናህ አይተውህምና በሥልጣን ላይ ስትሆን የምትፀፀትበትን ነገር አታድርግ።

ጸሎት

እቤቱ ተስፋዬ ሆነህ መርተኸኛልና እመሰግንሃለሁ። ትልቁ መሪ አንተ ነህ። እኛ ከሰማይ በታች እንደራሴዎችህ ነን። ጌታ ሆይ ባስቀመጥከን ኃላፊነት ስፍራ ሥራችንን እንድንፈጽም እርዳን። ዓለም የመሪ ረሀብ አለባትና መሪዎችን አብዛልን። የቤተሰብን፣ የቤተ ክርስቲያንን፣ የአገርን ሰላም አንተ ጠብቅልን። በሕያው ስምህ አሜን!

ምዕራፍ ዐሥራ አራት
የእንጀራ ዋስትና

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጸመው ጾም ዐቢይ /ትልቅ/ ጾም ሲባል ያስተማረውም «የአቡነ ዘበሰማያት» ጸሎት ትልቅ ጸሎት ይባላል። አባታችን ሆይ ብዙ የተጻፈለት ብዙ ተርጓሚዎች ያፍታቱት ቢሆንም የምሥጢሩ ጥልቀት፣ የፍቅሩ ትንታኔ ዛሬም የማይጠገብ ነው። አባታችን ሆይ ደጋግመን ከምንጸልየው ይልቅ እንደ ጸሎት ትምህርት ቤት ብንማርበት የተሻለ ነው። ጸሎቱ ብዙ ነገሮችን አካቷል። ምሥጋና፣ ጸሎት፣ ንስሓ፣ ምልጃን አጠቃሎ ይዟል። የጥንት አባቶች የልመናውን ይዘት እንዲህ ያቀርቡት ነበር። ለምሳሌ፦ «የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን» የሚለውን «በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ÷ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን መንግሥት ያንተ ናትና ለዘላለሙ አሜን» ይላሉ።

ከፊት ምስጋናውን እንደ አዝማች ማድረጋቸው ልመናን የምትቀበለውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማወደስ ሲሆን መዝጊያው መንግሥት ያንተ ናትና መሆኑ ደግሞ የዕለት እንጀራ የሚሰጠን በመንግሥቱ ሥልጣን መሆኑን ለመግለጥ ነው። የአባታችን ሆይ ጸሎት ነፍስን ብቻ ሳይሆን ሥጋንም ይመለከታል። እግዚአብሔር የነፍስና የሥጋ ፈጣሪ ነውና የነፍስና የሥጋ መሻታችንን የሚፈጽምልን እርሱ ነው። ለዚህ ነው በታላቁ ጸሎት «የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን» (ማቴ.6÷11) ብለን እንድንጸልይ የታዘዝነው።

የቋጠሩት ስንቅ ያልቃል፣ የሰሙ ስንቅ ግን አያልቅም። በጎተራ ያከማቹት በዘንጉለት ቀጥር ይቀንሳል። ከሰማይ ግምጃ ቤት የሚሰፍሩ ግን አያልቅባቸውም። ገንዘብ ያከማቹ ይደኸያሉ፣ እግዚአብሔር አለኝ የሚሉ ግን በረከታቸው ከዘመን ዘመን ይሻገራል። እግዚአብሔር እርሻ አየታየ ይመግባል፣ እርሻ ሳይታይም ያኖራል። ደመና አዙሮ ያዘንባል፣ በጠራራ ፀሐይም ማዝነብ ይችላል። 3 ዓመት ከ6 ወር የደረቀችውን የሰማርያን ምድር ያረካት እጅ በምታህል ደመና ነው። ለእኛ ትልቅ የሆነው ጉዳይ ለእርሱ እቅም ትንሽ ነው። እርሱ ለመንገዱ ፍለጋ የለውም። በታሪክ የተጠና፣ በሊቃውንት የተረጋገጠ የእግር ፈለግ የለውም። በየብስ ሲጠብቁት በባሕር መጥቶ ይረዳል። ሀላችንም ለተፈጥሮ ሕግ ተገዝተናል። እርሱ ግን ከተፈጥሮ ሕግ በላይ ይሠራል።

የእግዚአብሔርን የበረከት እጆች ከተለማመድን የስሌት ኑሮ መልመድ ያቅተናል። እም «የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን» መባሉ እውነት ነው።

የዓለማችን 81% የሚሆነው ሕዝብ ደሃ ነው። የዓለማችን ሀብትም ያለው 17% በሚያህሉ ሰዎች እጅ ነው። ከአንድ ቀን በላይ የማያውል በረከት ያላቸው ሕዝቦች እልፍ ናቸው። እንድ ቀን እቤታቸው ከዋሉ የሚራቡና የሚሞቱ ቁጥር የላቸውም። እነዚህ ሁሉ ድሆች በምንድነው የሚኖሩት? ስንል በተአምራት ነው። እግዚአብሔር ፍጥረትን ስለ ቃል ኪዳኑ ያኖራል። ከገቢያችን በላይ በሆነ ወጪ እግዚአብሔር ሲያኖረን አይተናል። እግዚአብሔርን በቃሉ ስንፈልገው፣ በእምነት ስንጠብቀው አናገኝዋለን። እርሱ እንዳወቅነው ሳይሆን እንዳመነው ነው። «የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን»

እንጀራን ሁሉም ሰው ይፈልጋል። የእንጀራውን አድራሻ ግን የሚያውቅ ጥቂት ነው። እንጀራ ተዘርቶ፣ ታጭዶ፣ ባለ ሙያ ሴት አሰናድታ የምታቀርበው የሚመስለው ሰው ብዙ ነው። እንጀራ ግን ከሰማይ ነው። በየዕለቱ እንጀራን የሚሰጠን እግዚአብሔር ነው። የፍላጎቶቻችን ሁሉ ሙሉ መልስ ያለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። እግዚአብሔር የፍላጎታችን ንጉሥ ነው። እርሱ ለነፍሳችን እንደሚያስብ ለሥጋችንም ያስባል። ይልቁንም የምንፈልገው ከእግዚአብሔር አቅም በላይ ስላልሆነ ደስ ሊለን ይገባል። እግዚአብሔር የእጁን ሳይሆን ልጁን ሰጥቶናል። የእጁን የዘገኑ ይጎድልባቸዋል፣ ጸጋውን የወሰዱ ያልቅባቸዋል። ባለጸጋውን የያዙ ግን ምንም አይጎድልባቸውም። እግዚአብሔር ጸጋውን ፍለጋ በደርሶ መልስ እንድንኖር ፈቃዱ አይደለም። ራሱን ሊሰጠንና ወደ በረከትነቱ ምንጭ ሊያስጠጋን ይፈልጋል። ያዕቆብ ሲሰደድ የበረከቱ አድራሻ ወደ ሆነው ጌታ ጸለየ፦ *«እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን÷ በምሄድባትም በዚች መንገድ ቢጠብቀኝ÷ የምበላውንም እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ÷ ወደ አባቴ ቤትም በጤና ብመለስ÷ እግዚአብሔር ለምላኬ ይሆንልኛል፤... ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከአሥር እጅ አንዱን እሰጥሃለሁ»* (ዘፍ.28÷20-22)።

«የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን» ስንል ግዙፉን እንጀራ ብቻ ሳይሆን የዕለት ቃልህንም ስጠን ማለታችን ነው። እግዚአብሔር የዕለት መና አለው። መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ወይም ቃሉን በመስማት የዕለት እንጀራችንን እንቀበላለን። በእንጀራ ብቻ መኖር የተሟላ አይሆንምና የዕለት ቃልህን ስጠን ማለት ያስፈልጋል።

የዕለት እንጀራችንን ስጠን ከማለት የዓመት ቀለባችንን ስጠን ማለት አይቀልም ወይ? ነገሥታት እንኳ በጀት የሚባጅቱት በዓመት ነው፣ በንጉሥነት የሚኖረው እግዚአብሔር ለምን በየዕለቱ ለምኑ አለ ብንል እርሱ ፈቃዱ ሕይወትን ዕለት በዕለት እንድንኖራት በመሆኑ ነው። ከዛሬ አልፈን ስለ ነገ እንድናስብ ፈቃዱ አይደለም። *መጀመሪያ ስለ መኖራችን* እናስብ። ከዚያ በኋላ ስለ መኖሪያው እናስብ። *መጀመሪያ ለመኖራችን* ዋጋ እንስጥ። ከዚያ በኋላ ፍላጎታችንን እግዚአብሔር ይሞላልናል።

የምንኖረው ኑሮ በትላንትናና በነገ መካከል እጣብቂኝ ውስጥ ነው። የትላንት ትዝታ የነገ ፍርሃት ዛሬን እንዳንኖር አድርጎናል። ሕጻናት ደስተኛ ከሚሆኑበት ነገር አንዱ ሕይወትን በሰዓቱ ስለሚኖሯት ነው። ትክክለኛ የሕይወት መልክ ያለንበትን ቀን መኖር ነው። ነገ በደኅንነት ሠራተኞች ጥልቅ ምርመራ፣ በፖለቲካ ተንታኞች ግምት፣ በእስተዋይነትም አትታወቅም። ነገ የእግዚአብሔር ምሥጢር ናት። እግዚአብሔር ስለ ነገ ያልገለጠልን የምንለውጠው ነገር ስለ ሌለ ነው። የጨቦጥናትን ዛሬን መኖር እያቃተን ስለ ነገ መጨነቅ ድካም ነው። የብዙዎቻችን ፍርሃት ራበኝ ሳይሆን ሊርበኝ ነው የሚል ነው። ነገ ምን እንደምንሆን አናውቅም። ዛሬን እንድንኖር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

«የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን» ብለን መጸለያችን የእንጀራችን አድራሻ እንተ ነህ፣ የእንጀራችን ባለቤቱ እንተ ነህ ማለታችን ነው። እንጀራ የሚሰጡን ተስፋ የሰጡን ወይም ስልኮቻቸውን የመዘገብናቸው ትልልቅ ሰዎች አይደሉም። እነዚህ ጌታን እንዳናይ እንቅፋቶች ናቸው። እግዚአብሔር ካልሰጠ እንኳን ሰው መልአክ አይሰጥም። ሰዎች ብዙ አድርገውልን ይሆናል። ስለ እኛ እንቅልፍ የነሣቸው ግን እግዚአብሔር ነው። ውለታ አንረሳም፣ ሰጪ ግን እግዚአብሔር ነው። ሰው ሰጠን ብለን አንናገርም። መስጠት የሰው ባሕርይ አይደለምና።

ከእግዚአብሔር *መንግሥት* ለእያንዳንዳችን የዕለት በጀት አለን። አንዱ የእንዱን በጀት አይበላም። የአንዱ በጀት ለአንዱ አይሆንም። የየራሳችንን ድርሻ እንቀበላለን። ይህ ቢገባን ኖሮ እግዚአብሔር ሰጥቶ የሚነሣን፣ እግዚአብሔር ነሥቶን የሚሰጠን እንደ ሌለ እንረዳ ነበር። ይህ ብቻ አይደለም ቅንዓትና ምቀኝነት በራቀልን ነበር። «ሰጠኝ» እግዚአብሔርን እንቀበለዋለን እንጂ አንነጥቀውም። «ሰጠኝ» እርሱ የሰጣ አምላክ ነውና አበድረኝ አንለውም።

«ዛሬ ስጠን» የእኛ የምንላት ቀን ዛሬ ናት። የእኛ በምንላት ቀን እግዚአብሔር ያስብልናል። የተፈጥሮ ተግባራችንን እንፈጽምባታለን። እንሮጥባታለን። የእኛ ቀን ዛሬ ናት። ነገ የእኛ አይደለችም።

«ስጠኝ» የስጦታ ባለቤት እግዚአብሔር ነው። *ያዕቆብ «በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ»* (ያዕ.1÷17) ይላል። «እንጀራ ስጠኝ» ሁሉም ሰው እንዲህ አይባልም። ምንም ቢርብ እንጀራ ስጡኝ ለማለት ክብር ይይዘናል። እንጀራ ስጪኝ ስንል የማናፍረው እናታችንን ነው። እግዚአብሔርም እናት ነውና እንጀራ ስጠኝ እንለዋለን። እንጀራ የበሰለ ነው። እግዚአብሔርም ያለቀለት በረከት አለው። ብዙ ዘመን አጉርሶናል። የእጁም ጠረን ይሸተናል።

ዳግማዊ ሚኒልክ ሁልጊዜ ሲያልፉባት በብዙ በረከት የምትቀበላቸውን አገር «ምን ልበልሽ ማጀቴ ብዬሻለሁ» ብለዋል። በዚህ ምክንያት በሸዋ ውስጥ ማጀቴ የምትባል ከተማ አለች። እግዚአብሔር ማጀታችን ነው። ማጀት ምግብ የሚሠናዳበት ማእድ ቤት ነው። ማጀት በድብቅ ነው፣ በአደባባይ የቁንጅና ውድድር የሚወዳደሩት ግን በእርሱ ነው። ማጀት ሲያዩት አያምርም። የብዙ ሽቅርቅሮች ምሰሶ ግን እርሱ ነው። በድብቅ የሰመኑትን በአደባባይ የሚመልስ እግዚአብሔር ማጀታችን ነው። በማጀት አንድ ነገር አይታጣም። ከእግዚአብሔርም አይታጣም። የጸሎታችን መልሱ ገና ቢሆን እንኳ ሌላ በረከት አስታቅፎ ይሸኘናል።

የእንጀራውን አድራሻ የማያውቅ በልቶ ካጅ፣ የሰውነት ክብር የተሰየው፣ ምስጋና የማያውቅ ነው። አይሁዶች «ተቀብሎ የማያመሰግን ከቀማኛ ይቆጠራል» ይላሉ። ሃያ ሠላሳ ዓመት እድሜ ሰእገሌ እርሱ እዚህ ቦታ ባይተክሰኝ ኖሮ እያሉ የሚናገሩ ሰዎች አሉ። ሰዎች ምክንያት ሆነው በዚያ ቦታ ላይ እንድንቀመጥ አስተዋጽኦ አድርገው ይሆናል። እነርሱ ግን ሎሌ ናቸው፣ ያስቀመጠን እግዚአብሔር ነው። ሰው ይነቅለኛል ብሎን የምንፈራው ሰው ያስቀመጠን ስለሚመስለን ነው። እግዚአብሔር እንደ ሰጠን ብናምን ግን የእርሱን ስጦታ ነገሥታት እንኳ በጉልበታቸው እንደማይነጥቁን ይገባናል።

«የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን» ልመናው የኅብረት ነው። የዕለት እንጀራዬን አይልም። እኛ ስንበላ ጎረቤታችንም መብላት አለበት። እኛ እንጀራ ስናገኝ ጎረቤታችንም ማግኘት አለበት። እኛ

እየበላን ጎረቤታችን ካልበላ ደስታችን ሙሉ አይሆንም። ከበላነው በኋላ አይጣፍጠንም። በሽታ ሆኖ ያስቃየናል። ከላይ የሚያየው እግዚአብሔር እኛ ቤት ያለውን ጥጋብ፣ ጎረቤታችን ቤት ያለውን ረሀብ በእኩል ዓይን ሲያይ ያዝንብናል። እግዚአብሔር በትሮአችን ሲያዝንብን ደግሞ ደስታና ኃይል እናጣለን። ሰላምን መለመን ብቻ ሳይሆን ማካፈልም ያስፈልጋል። 10 እንጀራ ስንጋገር አንዱን አጥፈን ለጎረቤታችን መስጠን አለብን።

በዚህች ከተማ ላይ ብዙ ድሆች በባለጠጎች ግርማዊ አጥር ተሸፍነው ያቃስታሉ። አንድ ቀን ከቤት ካልወጡ የሚሞቱ፣ እስክ ማታ የማይቆዩ ብዙ ጎስቋሎች አሉ። የክረምቱን ዝናብ የሚከላከሉበት የሌላቸው ልጆቻቸውን የብረት ምጣድ አልብሰው የሚያሳድሩ ብዙ ወላጆች አሉ። በዚህች በአዲስ አበባ ውስጥ ገላቸውን ሽንት ቤት በሚሰቀቅባቸው ወንዞች የሚታጠቡ ብዙ ጎልማሶች ይታያሉ። የዚያን ያህል ደግሞ ውሾች በሻንፖ ይታጠባሉ። ታዲያ እነዚህ እያሉ እንዴት ደስ ይሰናል? እንዴት በልተን እንጠግባለን? እንዴት ሰብሰን እንደምቃሰን? እነዚህ ድሆች በእግዚአብሔር ፊት ይከሱናል። የድሆች ድርሻ ነገሥታት ጋ ብቻ ሳይሆን እኛም ጋ አለ።

ጎረቤቶቻችን ካልበሉ ክፉ ያስቡብናል። በጎዳና ላይ የፈሰሱ ልጆች ያሳስባሉ። እኛ ልጆቻችንን በልዩ ማባበያ ወደ ትምህርት ቤት ስንሸኝ፣ ስንንከባከብ ያዩናል። ከልጆቻችን ጋር እየተያዩ ያድጋሉ። ነገ እነዚህ ትውልዶች እንደ ይስሐቅና እስማኤል ባላጋራዎች መሆናቸው የማይቀር ነው። በእውነት መማር የሚገባቸው ሕጻናት እንጀራ ለማግኘት ከመኪና መኪና ሲሯሯጡ ማየት ያሳዝናል። እነዚህን ድሆች አስብ እያሉ መጸለይ ብቻ አይበቃም። የድርሻችንን መወጣት ያስፈልገናል። ጸሎት ከተግባር ጋር ነውና።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ አምስት ሺህ ሕዝብ መግቦ አሥራ ሁለት መሶብ እንደ ተረፈ እናነባለን (ማቴ.14÷13-21)። በትንሽ ነገር ብዙ ረሀብተኞችን ሸኘ። ይህ የበረከት እጅ በታሪክ የቀረ ሳይሆን ዛሬም የሚሠራና ብዙዎችን የሚያኖር ነው። ወላጆቻችን ይህን እጅ በትንሽ ገቢያቸው ብዙ ቤተሰብ ሲያስተዳድሩበት አይተዋል። እንደ እኛ በስሌት ሳይሆን በእምነት መኖርን ያውቁታል። የእግዚአብሔር እጅ ዛሬም አለ። እኛ በስፍራችን የለንም እንጂ።

አንድ አገልጋይ ደሞዙ በጣም ዝቅተኛ ነው። የሚከፍለው የቤት ኪራይ ግን ከደሞዙ ሠላሳ ብር የሚጨምር ነው። በዚህ

ኑሮው ተሰማምቶት ሲኖር የልጅነት ጓደኛው የነበረችውን እህት በቶሎ እንዲያገባ አሲያ እንዲተዋት የልጅቱ አባት ጠርተው ነገሩት። እንደውም ቀን ቆርጠው በዚህ ቀን ካላገባህ ሰሌላ እድራታለሁ ብለው በሀብታቸው ተማምነው ተናገሩት። እርሱም አንድ አባት ጋ መጥቶ እማከራቸው። ታዲያ አግባታ አሉት። አገልጋዩም ጮኸ «ደሞዜ እኮ ትንሽ ነው» አላቸው። እርሳቸውም «ሁለት ዓሣና አምስት እንጀራ አበርክቶ እምስት ሺህ ሰው በመገበ ጌታ ታምናለህ?» አሉት። እርሱም «አምናለሁ» አላቸው። «ካመንህ ይዘሃት ግባ» አሉት። አገልጋዩም «የምግቢንስ ይገርለሁ፤ የት እኖራታለሁ? ቤት የለኝም» አላቸው። እርሳቸውም «ሣጠራ ክልልና አስገባት፣ የምታምነው እግዚአብሔር ምን እንደሚሠራ ያኔ ታያለህ» አሉት። በቅርብ እንደማውቀው ባገባ በሁለት ወሩ የማይጠብቃቸው ሰዎች ቤት ገዝተው ሰጡት። ካገባ ጀምሮም የጎደለበትን አላየሁም።

የሕፃናት እምነት ያስፈልገናል። ሕፃናት በወላጆቻቸው ያላቸው እምነት ከፍተኛ ነው። ምን እበላለሁ? ምን እጠጣለሁ? ምን እሰብሳለሁ? ብለው አይጨነቁም። ባለመጨነቃቸውም ምንም አልጎደለባቸውም። እኛም እንደ ሕፃናት ያለ እምነት ሲኖረን ይገባል። ሕፃናት የተሰጣቸውን ተስፋ ያምናሉ። እኛም እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ የሰጠንን ተስፋ ማመን አለብን። እግዚአብሔር ይሆናል ያለንን ይሆናል ብለን ማመን ያስፈልገናል። ሕፃናት ወላጆቻቸውን ብቻ ሳይሆን ስለ እግዚአብሔር ሲነገራቸውም ያምናሉ። እግዚአብሔርን ይቀርቡታል፣ ያምኑታል፣ ይወዱታል። ስለዚህ ነው *«እውነት እላችኋለሁ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ፦ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም»* (ማቴ.18÷3) የተባለው።

ታዲያ መሥራት እያስፈልግም ማለት ነው? *ሥራ* ርግማን ነው? *ሥራ* ሰው ከተፈጠረበት ዓላማ አንዱ ነው። በርግጥ ከበደል በኋላ «በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ» (ዘፍ.3÷19) የሚል ርግማን ቢሰጥም ቀድሞ *ሥራ* አልነበረም ማለት አይደለም። ከበደል በኋላ ግን የ*ሥራ* ጫናው ጨመረ፣ እርካታው ቀነሰ። ከዚያ በፊት ግን *ሥራ* በረከት ሆኖ ተሰጥቷል (ዘፍ.2÷15)። ስለዚህ *ሥራ* ያስፈልጋል። *ሥራ* በረከት ነው። እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች ዐርባ ዓመት መና አወረደላቸው ብለን ተምረን የሰም ወይ? ብንል አዎ መዝራት በማይቻልበት በረሃ ላይ መናን አውርዷል። ወደ ከነዓን ምድር ከገቡ በኋላ ግን መና ማውረድ አቁሟል። መዝራትና ማጨድ በሚቻልበት ምድር መናን ማውረድ ስንፍናን በሰማይ ሽንጎ ማጽደቅ ነው። ደግሞም የሰማይ ወፎች አይዘሩም፣ አያጭዱም

ጎተራም የላቸውም ተብሎ የሰም ወይ? ብንል አዎ አይዘሩም አያጭዱም ምግባቸውን ሰማግኘት ግን ይሯሯጣሉ።

ሥራችን አገልግሎታችን ነው። አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን እደባባይ ቆሞ ማገልገል ብቻ አይደለም። ባሉበት ቦታ *ሥራችንን* በታማኝነትና በትጋት *መፈጸም*ም አገልግሎት ነው። ወረቀት ላይ በታማኝነት *መፈረም*፣ እንግዳን በር ላይ መቀበል ለእግዚአብሔር ክብር የሚውል አገልግሎት ነው? አዎ ለእግዚአብሔር ክብር የሚውል አገልግሎት ነው። በእኛ *መልካምነት* ሰዎች እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑና ችግራቸው ሲቃለል አገልግሎት ነው። የአገልግሎት ጥሪ ካለንና በሙሉ ጊዜያችን እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚሰማን ድምፅ ካለ ቆርጠን መውጣት ነው። እግዚአብሔር ያኖራል። እንኳን ለቤቱ ለቤታችንም በጀት አለው።

በርግጥ የምንኖረው ስለ ሮጥን አይደለም። እንጀራ የምንቆርሰው አለቃችን ደስ ስላለውም አይደለም። እየጠሱን፣ እየተፈራረሙብንም እግዚአብሔር ያኖረናል። የእንጀራችን ጌታ እርሱ ነውና። ሰው ወዶ የሚሰጠን፣ ጠልቶ የሚያሳጣን ምንም ነገር የለም። የእኛ ዕጣችን ያለው በእግዚአብሔር እጅ ነው። አለቆቻችንን *መውደድ*፣ *ማክበር*፣ ምክር *መጠየቅ* ይገባናል። ከዚያ ባሻገር ግን እንደ ትንፋሻችን ጌታ አናያቸውም። እንኳን አለቃችን *መሥሪያ* ቤቱም ፈርሶ ያኖረናል። ሠርተን ከኖርነው በስጦታው የኖርነው ይበልጣል። ተግተን *መሥራት*፣ ተግተን *መማር*፣ ባለንበት ቦታ ብቁ ሆኖ *መገኘት* ያስፈልገናል። ከዚያ ባሻገር ግን እየበላን የሚርበን ሰዎች መሆን የለብንም። የእንጀራችን ዋስትና እግዚአብሔር ነው።

<u>የጽሞና ጊዜ</u>

እግዚአብሔር ስለ ፈጠራቸው ብቻ የሚያኖራቸው ብዙ የማያምኑት ሕዝቦችን ስናይ ለምናምነውማ እንዴት ቸር ነው! ኑሮን በስሌት ስታስበው ከባድ ነው። በእምነት ሁሉን ለእግዚአብሔር ስትተውለት ግን ደስታህ የማያቋርጥ ይሆናል። ላልፈጠርከው ራስህ ያን ያህል እትጨነቅ። *ሥራተኞችህ* ያንተን ደሞዝ ተማምነው እንቅልፍ ሲተኙ፣ ዕቁብ ሲገቡ እንተ ለምን ትናወጣለህ? ስለዚህ፦

- የምትኖረው *መንግሥት* የእግዚአብሔር ስለሆነ መሆኑን አስብ።

- ለትልቁ ጥያቄህ እግዚአብሔር አጅ በምታህል ደመና መልስ እንደሚለጥ አስብ።
- የእንጀራህ አድራሻ ከሰማይ እንደሆነ እመን።
- ሕይወትን ዕለት በዕለት መኖር ተለማመድ።
- በቤትህ ጥጋብ ሲሆን የጎረቤትህን ረሀብ አስብ።
- ክርስቲያን በሁሉም ነገር ብቁ ሲሆን መልካም ነውና ተግተህ ሥራ፣ ተግተህ ተማር። ያንተ አእምሮ ስለ ሰማይ ያውቃልና የምድሩን ማወቅ አያቅትህም።

ጸሎት

አቤቱ ጉልበቴ ሆይ አመሰግንሃለሁ። ወገን በወገን፣ ሰው በሰው ሲጠቃቀም እኔ ግን አንተን ከመጥራት በቀር የማውቀው የለኝምና ትበቃኛለህ እያልኩ አመሰግንሃለሁ። ሁሉ ሲለወጥ መለወጥ በማይደርስበት ከፍታ የምትኖር ጌታዬ ሆይ, አመሰግንሃለሁ። ከእኔ ምን የሚያሰወድድ ነገር አግኝተህ ነው ክረምት ከበጋ የምታባብለኝ? እኔ የጠላኹትን ይህን አዳፋ ሰውነቴን ሳይከብድህ መውደድህ ይገርመኛል። እንደ ጴጥሮስ ኃጢአተኛ ነኝና ከእኔ ራቅ አልልህም። አንተ ከራቅኸኝ የሚቀርበኝ የለምና እኔስ ኃጢአተኛ ነኝና ከእኔ አትራቅ እልሃለሁ። በረከቴ አንተ ነህ። የኖርኩት በአንተ አንጂ በሥራዬ አይደለም። አሁንም በተስፋህ አኑረኝ። ሰይጣን በኑሮ ፍርሃት ሲንጠኝ አንተ በእምነት ዓለት ላይ አቁመኝ። ሲርበኝ ሁሉም ሰው የራበው ይመስለኛል፣ ስጠግብም ሁሉም ሰው የጠገበ ይመስለኛል። አባክህ ይህ ራስ ወዳድነቴ ነውና የፍቅር ሰው አድርገኝ። የእኔና የሕዝብህ የእንጀራችን አድራሻ አንተ ነህና እናመሰግንሃለን። በማያልቀው ቸርነትህ ለዘላለሙ አሜን።

ማጠቃለያ

ኑሮና ሕይወት እንደ ተከፈተ መጽሐፍ ጎንና ጎን ተቀምጠው ፊት ለፊት ይታዩናል። ኑሮ እስኪያልፍ የሚያለፋ ነው። ሕይወት ግን ማንም የማይገድለው በክርስቶስ ላመኑት ሁሉ የተሰጠ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። የማያልፈው ከሚያልፈው ይወለዳል። የማያልፈው የዘላለም ሕይወት በሚያልፈው ዕድሜ ውስጥ የተቀመጠ ዕድል ነው። ዕድል ግን በምርጫ የሚገኝ እንጂ እንደሚመስለን ራሱ ፈልጎን የሚመጣ አይደለም። *«ማርያምም መልካም ዕድልን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም»* (ሉቃ.10÷42)። ሁሉም ሰው የሚስማማበትና የማይቀር ነገር አለ። እርሱም መሞታችን ነው። ስለዚህ መጀመሪያ ለማይቀረው ቀጥሎ ሊሆንም ላይሆንም ለሚችለው ነገር ማሰብ አለብን።

ሁለት በሬዎችን ጠምዶ የሚያርሰው ገበሬ ለማንኛው በሬ ያደላል? ሁለቱንም በእኩል ይመለከት የለምን? እንዲሁም ሰው በዚህ ዓለም ላይ ነፍስና ሥጋ የተባሉ ሁለት ማንነቶችን ጠምዶ የሚኖር ፍጡር ነው። ስለዚህ ለነፍሱም ለሥጋውም እኩል ማሰብ ይገባዋል። ብዙ ሰዎች «የምንኖረው እኩል ለሥጋ፣ እኩል ለነፍስ ነው» ይላሉ። ንግግራቸውን ደግመው ቢያዳምጡት ግን እንዳልሆነ ይገባቸዋል። ነፍስና ሥጋችንን እኩል ብናያቸውማ መልካም ነበር።

የእንጀራን ያህል ቃሉ ያስፈልገናል። ቃሉን የማይመገብ መንፈስ የሬሳ ሽክም ነው። ብርቱ ሥጋ የሞተን መንፈስ መሸከም አይችልም። የበረታ መንፈስ ግን የደከመውን ሥጋ ይሸከመዋል።

የሰው ልጅ ዘላለማዊ ሕይወቱ ጥያቄ ውስጥ ሆኖ ዓለምንና ሞላዋን ቢገዛ ደስተኛ ሊሆን አይችልም። በምድራዊው ኑሮአችን እውነተኛ ደስታ የምንጎናጸፈው የለማዩን ዋስትና ስንጨብጥ ነው። ለነገ ስንቅ የሚቋጠረው ዛሬ ነው። ለነገ ነገ ለንቅ የሚቋጥር መንገደኛ የለም። እንዲሁም ለወዲያኛው ዓለም የሃይማኖትና የምግባር ስንቅ የምንቋጥረው ዛሬ ነው። ከዘላለም አንጻር ሲታይ የዚህ ዓለም ኑሮ አጭር ቆይታና አስደሳች ነው። ሁሉም ነገር የሚታየን ከቆምንበት አቅጣጫ ነው። በምድር ላይ ትልቅ ሆነው የሚታዩን ነገሮች ከሰማይ ሆነን ስናያቸው ትንሽ ናቸውና በስፍራችን መቀመጥ አለብን። *«በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን»* (ኤፌ.2÷6)።

በክርስቶስ አምነን እንደ ፈቃዱ ብንኖር ከዚህ ዓለም ስንሄድ ትግሉን ወደ ኋላ ጥለን ነው የምንሄደው። ለዚህ ነው «የጻድቃን ሞታቸው ሕይወታቸው ነው» የሚባለው። ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ሲሞቱ ሠርጋቸው ነው ይባላል። ከሙሽራቸው ጋር ሊገናኙ እየሄዱ ነውና። በዚህ ዓለም ላይ የደረሰብን ስድብ፣ ንቀት፣ ድካምና ዝለት አይከተሰንም። ለዘላለም አይዘንም። ይህ የሚሆነው ግን በክርስቶስ አምነን በፍቅሩ የፀናን እንደ ሆነ ብቻ ነው። አሊያ «የኃጥአን ሞታቸው ሞት ነው» የተባለው ይደርስብናል።

ዋናው ጥያቄ እንዴት እኖራለሁ? ሳይሆን ለምን እኖራለሁ? የሚለው ነው። ብዙ ሰዎች የሚጨነቁት ስለሚኖሩበት አገርና ቤት ስለሚኖራቸው የህብት ዓይነት ነው። ለምን እንደሚኖሩ ግን አያውቁም። ማወቅም አይፈልጉም። ስለዚህ እውነተኛ ደስታ የላቸውም። ወደ ክርስቶስ ስንመጣ ብቻ የመኖራችንን ዓላማ እናውቃለን። አኗኗር ኑሮን አይለውጠውም። ክርስቶስ ግን የሕይወት ጣዕም ነው።

የፀሐይ ዕድሜ አጭር እንደ ሆነ ሁሉ በዚህ ዓለም ላይም የምናሳልፈው ቆይታ በጣም አጭር ነው። ስለዚህ መጨነቅ የለብንም። በመጨነቅ አይገኝም እንጂ ለሰማዩ ብንጨነቅ ይሻል ነበር። የዚህ ዓለም ኑሮ እንደ ምንም ያልፋል። የማያልፈው የወዲያኛው ዓለም ነውና ስለ ሰማዩ ማሰብ ይገባናል። እግዚአብሔር የማይፈርስ ሰማያዊ ቤትን አዘጋጅቶልናል። ወደ እርሱም በርረን የምንገባበት ሁለት ክንፍ ሃይማኖትና ምግባር ነው። ይህን ያህል ክብር ተዘጋጅቶልን ሳለ በምድራዊ ነገር መታከት አይገባንም። ዐይጥ ለሰውዬው ብዙ ውለታ ዋለችለትና ጎተራው አስገብቶ ምን ልስጥሽ? ቢላት አንድ ጥሬ አተር ወድቃ አይታ ይህን ስጠኝ አለችው ይባላል። እኛም እግዚአብሔርን እንዲህ እያልነው ይመስላል። በዘላለማዊ ስጦታ ፊት እንቅልፍ የሚነሣን ጊዜያዊው ነውና። 9 ቁጥር ከምድር ሲያዩት ትልቅ ነው። ከላይ ሲመለከቱት ግን 6 ቁጥር ነው። ትንሽ ነው!

በዛሬው ዘመን ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚመጡት ሰምድራዊ ኑሮአቸው ዋስትና ለማግኘት፣ ለአስቤዛ ኑሮአቸው መሟላት ነው። በአጠቃላይ የኑሮን ስቃይ ለመርሳት ነው። ለብዙ ሰዎች የዘላለም ሕይወት ዋጋ አይታያቸውም። ቃለ እግዚአብሔርን ግን ዛሬን ለመርሳት እንደ ሕመም ማስታገሻ ኪኒን ይፈልጉታል። ጳውሎስ፡- *«ለዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆኑ፡ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን»* (1ቆሮ.15÷19) ያለውን ማስተዋል

ይገባል። እግዚአብሔር የተመኘልን የምድሩን ሳይሆን የሰማዩን ነው። እኛስ የሰማዩ ሕይወት ዋጋ ገብቶናል?

ለዚህ ዓለም ኑሮአችን ያስንን እንዲያስበላን እንለምነው። ልከኛ ኑሮም በቂ መሆኑን እንመንበት (ምሳ.30÷7-9)። እርኩም የተባለው እንስሳ ትንሽ ነገር ፀአፉ ሲያስገባ ወደ ሰማይ ቀና ይላል። ሽማግሌዎቹም ሲተረጉሙ «ይህን እስክውጥ ዕድሜ ስጥ» ማለቱ ነው ይላሉ። የጎረሱትንም ለመዋጥ ዕድሜ ያስፈልጋል። እኛ ለመሰብሰቡ እንጂ ለዕድሜ አስበን አናውቅም። የምንኖረው መኖር መብታችን ስለሆነ ይመስለናል። መኖር ግን የእግዚአብሔር ትልቅ ስጦታ ነው። ቢርበን ለምነን እንበላለን። ዕድሜ ግን እናት ሰውድ ልጇ ቀንሳ የማትሰጠው ነው። ዕድሜ ካለ ትንሹ ብዙ ነው። የአገራችን ሰው «የጤና ቀስቡ ትንሽ ነው» ይላልና። እኛስ በያዝነው በምስጋና ተሞልተናል ወይስ እንደ ሕጻን ልጅ በሰው እጅ ያለውን እያየን እናለቅሳለን?

በሕይወታችን ቁጥር አንድ ያደረግነው ማንን ነው? እግዚአብሔርን ከሆነ ነገሮችን የምናየው ከእርሱ አንጻር ነው። አሥ የሚጠቅሙ ነገሮች ሁሉ የሚጠቅሙት እግዚአብሔር ሲቀድም ብቻ ነው። ሌሎች ነገሮችን ብንከስር በእግዚአብሔር ይካሳል። እግዚአብሔርን ብንከስር ግን መካሻ የሌለው ጥፋት ውስጥ እንወድቃለን። ሰው ስራሱ ዋስ መሆን አይችልም። በዚህ ዓለምና በሚመጣው ዓለም ዋላችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዕብ.7÷22)።

በማዕበል የምትንገላታ መርከብ መልሕቋን የምትጥልበት ዓለት ማግኘት ዕረፍቷ ነው። ከዚያ ሁሉ በላይ ወደ ወደቧ መድረስ አስደሳች ነው። በዚህ የትግል ዓለም ላይ አቅጣጫ የሚያስቀይር፣ አቋምን የሚጋፋ፣ የሚያናውጥ፣ ሊያዳፍነን የሚቃረብ ብዙ ፈተናና መከራ ቢኖርም ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሕይወት መልሕቃችንን የምንጥልበት ዓለት ነው። ቃሉ፡- *«እነሆ፡ የተመረጠና የከበረን የማዕዘን ራስ ድንጋይ በጽዮን አኖራለሁ በእርሱም የሚያምን አያፍርም»* (1ጴጥ.2÷6) ይላልና። ከዚህ ሁሉ በላይ በሰማይ ባለው ቤት ስፍራን አዘጋጅቶ እየጠበቀን ነው (ዮሐ.14÷1-3)። የምድር ጉዞአችንን ፈጽመን ወደ ሰማይ ስንሄድ በሰማዩ ወደብ ላይ ተቀብሎ ወደ ዘላለም ዕረፍት ያስገባናል። ይህ እንዲሆን ግን ልናምንበት ግድ ነው። *«ልባችሁ አይታወክ በእግዚአብሔር አመኑ በእኔም ደግሞ አመኑ»* (ዮሐ.14÷1) ይላልና። /መታወክ በእግዚአብሔር አለማመን ነው።/

እንግዲህ በዚህ የፈንጂ ወረዳ በሆነው ዓለም ውስጥ መድኀናችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው! እርሱን አባት ብለን ስንወደው፣ አዳኝ ብለን ስናምንበት፣ ጌታ ብለን ስንገዛለት፣ እረኛ ብለን ስንከተለው የኑሮአችን መድኀን ይሆንልናል። መድኃኒት የሚፈውሰው ሐኪሙ ሲያዝልን ሳይሆን ስንወስደው ነው። እንዲሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት የሚሆነን ስናምንበት ነው። በእውነት አምነንበታል?